፫ በዚያን፡ ጊዜ፡ የካህናት፡ አለቆችና፡ ጻፎች፡ የሕዝቡም፡ ሽማግሎች፡ ቀያፋ፡ በሚባለው፡ በሊቀ፡ ካህናቱ፡ ቤት፡ ተሰበሰቡ።

፬ ኢየሱስንም፡ በተንኰል፡ ሊይዙትና፡ ሊገድሉት፡ ባንድነት፡ ተማከሩ።

፭ ነገር፡ ግን፡ በሕዝቡ፡ ሁከት፡ እንዳይሆን፡ በበዓል፡ አይሆንም፡ አሉ።

፮ ኢየሱስም፡ በቢታንያ፡ በለምጻሙ፡ ስምዖን፡ ቤት፡ ሳለ። ዮሐ፡ ፲፪

፯ ፮ አንዲት፡ ሴት፡ ዋጋው፡ የበዛ፡ የሽቱ፡ ብርሌ፡ ይዛ፡ ወደ፡ እርሱ፡ መጣች፡ እርሱም፡ ተቀምጦ፡ ሳለ፡ በራሱ፡ ላይ፡ አፈሰሰችው። ሉቃ፡ ፯፡ ፴፯

፰ ደቀ፡ መዛሙርቱም፡ ያንን፡ ባዩ፡ ጊዜ፡ ይህን፡ ያህል፡ ጥፋት፡ ለምንድር፡ ነው።

፱ በብዙ፡ ዋጋ፡ ተሸጦ፡ ለድኆች፡ ይሰጥ፡ ነበር፡ ብለው፡ ተቈጡ።

፲ ኢየሱስም፡ ይህን፡ ባወቀ፡ ጊዜ፡ ይህች፡ ሴት፡ ለእኔ፡ መልካም፡ ሥራ፡ አደረገችልኝ፡ ለምን፡ ታሳዝንዋታላችሁ፡ አላቸው።

፲፩ ወለነዳያንሰ፡ ዘልፈ፡ ትረክብዎሙ፡ ወኪያየሰ፡ አኮ፡ ዘልፈ፡ ዘትረክቡኒ።

፲፪ ወዘንተሰ፡ ዕፍረተ፡ ዘሦጠት፡ ዲበ፡ ርእስየ፡ ለቀበርየ፡ ገብረት።

፲፫ አማን፡ እብለክሙ፡ በኀበ፡ ቱሰብከ፡ ዝወንጌል፡ በውስተ፡ ኵሉ፡ ዓለም፡ ያነብቡ፡ ዘገብረት፡ ዛቲ፡ ብእሲት፡ ወይዝክርዋ።

፲፬ ወእምዝ፡ ሖረ፡ አሐዱ፡ እም ዐሥርቱ፡ ወክልኤቱ፡ አርዳኢሁ፡ ዘስሙ፡ ይሁዳ፡ አስቆሮታዊ፡ ኀበ፡ ሊቃነ፡ ካህናት።

፲፭ ወይቤሎሙ፡ ሚመጠነ፡ ትሁቡኒ፡ ወአነ፡ አገብኦ፡ ለክሙ፡ ወተሰነዓዉ፡ ምስሌሁ፡ ከመ፡ የሀብዎ፡ ሠላሳ፡ ብሩረ።

፲፮ ወእምአሚሁ፡ ኮነ፡ የኀሥሥ ሳሓተ፡ ከመ፡ ይመጥዎሙ።

፲፯ ወበቀዳሚት፡ ዕለት፡ እምነ፡ ፍሥሕ፡ ቀርቡ፡ አርዳኢሁ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወይቤልዎ፡ በአይቴ፡ ትፈቅድ፡ ናስተዳሉ፡ ለከ፡ ትብላዕ፡ ፍሥሐ።

፲፰ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱ

፲፩ ድሆች፥ ሁል፡ ጊዜ፡ ከእናንተ፡ ጋራ፡ ናቸው፡ እኔ፡ ግን፡ ከእናንተ፡ ጋራ፥ ሁል፡ ጊዜ፡ አልኖርም። ዘዳግ፡፲፭

፲፪ ፲፩። ይህንም፡ በራሴ፡ ላይ፡ ያፈሰሰችው፡ ሽቱ፡ ለመቃብሬ፡ አደረገችው።

፲፫ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ ይህ፡ ወንጌል፡ በሚሰበክበት፡ ስፍራ፥ በዓለሙ፥ ሁሉ፥ ይህች፡ ሴት፡ ያደረገችው፡ ለእርስዋ፡ መታሰቢያ፡ ሆኖ፡ ይነገራል።

፲፬ በዚያ፡ ጊዜ፡ ከዓሥራ፡ ሁለቱ፡ አንዱ፡ ስሙ፡ ይሁዳ፡ የሚሉት፡ የአስቆሮቱ፡ ወደ፡ ካህናቱ፡ አለቆች፡ ሔደ።

፲፭ እኔ፡ ባሰይዛችሁ፡ ምን፡ ትሰጡ?ላችሁም፡ አላቸው፤ እርሳቸውም፡ በሠላሳ፡ ብር፡ ከእርሱ፡ ጋራ፡ ተስማሙ። ዮሐ፡፲፩፡፴፫፡፡ ዘካ፡፲፩፡፲፪።

፲፮ ከዚያችም፡ ሰዓት፡ ጀምሮ፡ አሳልፎ፡ ሊሰጣቸው፡ ምቹ፡ ጊዜ፡ ይሾ፡ ነበር። ፩ጢሞ፡፮፡፱፡፲።

፲፯ ከፋሲካም፡ አስቀድሞ፡ በነበረው፡ የቂጣ፡ በዓል (በዓለ፡ ናዕት፡) ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ወደ፡ ኢየሱስ፡ መጥተው፡ ፋሲካውን፡ ትበላ፡ ዘንድ፡ ወዴት፡ ልናዘጋጅልህ፡ ትወዳለህ፡ አሉት። ዘፀአ፡፲፪፡፲፰፡፩።

፲፰ እርሱም፡ በከተማ፡ ወደ፡ እገሌ፡

ስ፡ሑሩ፡ውስተ፡ሀገረ፡ኀበ፡እ
ገሌ፡ወበልዎ፡ይቤለከ፡ሊቅ፡ጊ
ዜየ፡ቀርበ፡ወበኀቤከ፡እገብር፡
ፋሲካ፡ምስለ፡አርዳእየ።

፲፱ ወገብሩ፡አርዳኢሁ፡በከመ፡
አዘዞሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወ
አስተዳለዉ፡ፍሥሐ።

፳ ወምሴተ፡ከዊኖ፡ረፈቀ፡ምስለ፡
ዐሠርቱ፡ወክልኤቱ፡አርዳኢ
፳፩ ሁ። ወእንዘ፡ይበልዑ፡ይቤ፡አማ
ን፡እብለክሙ፡ከመ፡አሐዱ፡እ
ምኔክሙ፡ያገብአኒ።

፳፪ ወተከዙ፡ጥቀ፡ወአኀዙ፡ይበ
ልዎ፡በበአሐዱ፡አነኑ፡እኄ፡እ
ግዚእ።

፳፫ ወአውሥአ፡ወይቤ፡ዘያወር
ድ፡እዴሁ፡ምስሌየ፡ውስተ፡መ
ጽኅብሐ፡ውእቱ፡ያገብአኒ።

፳፬ ወወልደ፡እጓለ፡እመሕያው፡ሰ
የሐውር፡በከመ፡ጽሑፍ፡በእንቲአሁ፡
ወባሕቱ፡አሌ፡ሎቱ፡ለውእቱብእሲ፡
ዘበላዕሌሁ፡ይትሜጠውዎ፡ለ
ወልደ፡እጓለ፡እመሕያው፡እር
ምኀየሰ፡ለውእቱ፡ብእሲ፡ሰበ፡
ኢተወልደ።

፳፭ ወአውሥአ፡ይሁዳ፡ዘያገብኦ፡
ወይቤ፡አነኑ፡እኄ፡ረቢ፡ወይ

ዘንድ፡ሒዱቹሁ፡መምህር፡ጊዜ፡
ዬ፡ደርሶአል፡በእንተ፡ቤት፡ከደ
ቀ፡መዛሙርቴ፡ጋራ፡ፋሲካን፡
አከብራለሁ፡ይልሃል፡በሉት፡
አላቸው። ም፡፳፩፡፫።

፲፱ ደቀ፡መዛሙርቱም ኢየሱስ፡እ
ንደ፡አዘዛቸው፡አደረጉ፡ፋሲ
ካውንም፡አዘጋጁ።

፳ በመሸም፡ጊዜ፡ከዓሥራ፡ሁለ
ቱ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡ጋራ፡ለመ
ብላ፡ተቀመጠ። ሲበሉም፡እው
ነት፡እላችኋለሁ፡ከእናንተ፡አን
ዱ፡አሳልፎ፡ይሰጠኛል፡አላቸ
፳፪ ው። ዮሐ፡፲፫፡፳፩፡፳፪። እጅግም፡አዘ
ኑ። ከእርሳቸውም፡እያንዳን
ዱ፡አቤቱ፡ከቶ፡እኔ፡እሆንን፡ይ
፳፫ ሉ፡ጀመር። እርሱም፡መለሰ፡
ከእኔ፡ጋራ፡እጁን፡ወዴ፡ወጡ፡
ወጭት፡የሚጠልቅ፡እርሱ፡አሳ
፳፬ ልፎ፡ይሰጠኛል፡አለ። ዮሐ፡፲፫፡፲፰። የሰ
ው፡ልጅ፡ግን፡ስለ፡እርሱ፡እንደ፡
ተጻፈ፡ይሔዳል፤ነገር፡ግን፡በእ
ርሱ፡ምክንያት፡የሰው፡ልጅ፡አ
ልፎ፡ለሚሰጥበት፡ለዚያ፡ሰው፡
ወዮለት፡ያ፡ሰው፡ባይወለድ፡
ይሻለው፡ነበር።

፳፭ አሳልፎ፡የሚሰጠው፡ይሁዳም፡
መልሶ፡መምህር፡ሆይ፡ከቶ፡እ

ቢሶ፡ ለሊከ፡ ቱብል፨

፳፮ ወእንዘ፡ ይበልዑ፡ ነሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ኅብስተ፡ ወባረከ፡ ወፈተተ፡ ወወሀበ፡ ለአርዳኢሁ፡ ወይቤ፡ እንከሙ፡ ብልዑ፡ ዝውእቱ፡ ሥጋየ፨

፳፯ ወነሥአ፡ ጽዋዐ፡ ወአእኰተ፡ ወወሀቦሙ፡ እንዘ፡ ይብል፡ ስትዩ፡ እምውስቴቱ፡ ኵልክሙ፨

፳፰ ዝውእቱ፡ ደምየ፡ ዘሐዲስ፡ ሥርዓት፡ ዘይትከዓው፡ ለቤዛ፡ ብዙኃን፡ ወለኀድገተ፡ ኃጢአት፨

፳፱ ወእብለክሙ፡ ኢይሰቲ፡ እነ፡ እምይእዜ፡ እምዝንቱ፡ ፍሬ፡ ወይን፡ እስከ፡ እንታክቲ፡ ዕለት፡ አመ፡ እሰትዮ፡ ሐዲሰ፡ ምስሌክሙ፡ በመንግሥቱ፡ ለአቡየ፨

፴ ወሰቢሖሙ፡ ወፅኡ፡ ውስተ፡ ደብረ፡ ዘይት፨

፴፩ ወእምዝ፡ ይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ኵልክሙ፡ ተዐልዉኒ፡ በዛቲ፡ ሌሊት፨ እስመ፡ ይቤ፡ መጽሐፍ፡ እቀትሎ፡ ለኖላዊ፡ ወይዘረዉ፡ አባግዐ፡ መርዔቱ፨

፴፪ ወእምከመ፡ ተንሣእኩ፡ እቀድመክሙ፡ ገሊላ፨

ኔ፡ እሆኝን፡ አለ፡፡ አንተ፡ ትላለህ፡ አለው፨

፳፮ እነ እርሳቸውም፡ ሲበሉ፡ ኢየሱስ፡ ኅብስቱን፡ አንሥቶ፡ ያዘ፡ ባረከውም፡ ቈርሶም፡ ለደቀ፡ መዛሙርቱ፡ እንኩ፡ ብሉ፡ ይህ፡ ሥጋዬ፡ ነው፡ ብሎ፡ ሰጠ፨ ፩ቆሮ፡ ፲፩፡ ፳፫—፳፱፨

፳፯ ጽዋንም፡ ተቀብሎ፡ አመሰገነ፡ ሁላችሁ፡ ከዚህ፡ ጠጡ፡ ብሎም፡ ሰጣቸው፨

፳፰ ይህ፡ የሐዲስ፡ ሥርዓት፡ ኃጢአትን፡ ለማስተሥረይ፡ ስለ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ የሚፈስ፡ ደሜ፡ ነውና፨

ዘፀአ፡ ፳፬፡ ፰። ኤር፡ ፴፩ ፴፩፡፡ ዘካ፡ ፱፡ ፲፩፨

፳፱ በአባቴ፡ መንግሥት፡ ከእናንተ፡ ጋራ፡ አዲሱን፡ እስከ፡ እምጠጣበት፡ እስከዚያ፡ ቀን፡ ድረስ፡ ከዛሬ፡ ጀምሬ፡ ከዚህ፡ ከወይን፡ ፍሬ፡ አልጠጣም፡ እላችኋለሁ፨

፴ የምስጋናም፡ መዝሙር፡ ከዘመሩ፡ በኋላ፡ ወደ፡ ደብረ፡ ዘይት፡ ወጡ፨ መዝ፡ ፻፲፫

፴፩ ፻፲፰ ከዚህ፡ በኋላ፡ ኢየሱስ፡ በዚች፡ ሌሊት፡ ሁላችሁ፡ ትክዱኛላችሁ፡ አላቸው፡ ጠባቂውን፡ እገድላለሁ፡ የመንጋውም፡ በጎች፡ ይበተናሉ፡ ተብሎ፡ ተጽፎአልና፨ ዘካ፡ ፲፫፡ ፯። ዮሐ፡ ፲፯፡ ፴፪፨

፴፪ ነገር፡ ግን፡ በተነሣሁ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ገሊላ፡ እቀድማችኋለሁ፤ ም፡ ፳፰

፴፫ ወአውሥአ፡ ጴጥሮስ፡ ወይቤሎ፡ እመሂ፡ ኵሎሙ፡ ዐለውከ፡ አንሰ፡ ኢየዐልወከ፡ ግሙራ።

፴፬ ወይቤሎ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ አማን፡ እብለከ፡ ከመ፡ በዛቲ፡ ሌሊት፡ ሥልሰ፡ ትክሕደኒ፡ ዘእንበለ፡ ይንቁ፡ ዶርሆ።

፴፭ ወይቤሎ፡ ጴጥሮስ፡ እመውቴ፡ ሂ፡ ምስሌከ፡ ወኢይክሕደከ፤ ወከማሁ፡ ይቤሉ፡ ኵሎሙ፡ አርዳኢሁ።

፴፮ ወእምዝ፡ ሖረ፡ ምስሌሆሙ፡ ኀበ፡ ዓፀደ፡ ወይን፡ ዘስሙ፡ ጌቴሴማኒ፤ ወይቤሎሙ፡ ለአርዳኢሁ፡ ንበሩ፡ ዝየ፡ እስከ፡ ሶበ፡ አሐውር፡ ከሐ፡ ወእጼሊ።

፴፯ ወነሥኦሙ፡ ለጴጥሮስ፡ ወለክልኤቲ፡ ደቂቀ፡ ዘብዴዎስ፡ ወአኀዘ፡ ይተክዝ፡ ወይፋዝዝ።

፴፰ ወእምዝ፡ ይቤሎሙ፡ ተከዘት፡ ነፍስየ፡ እስከ፡ ለሞት፡ ንበሩ፡ ዝየ፡ ወትግሁ፡ ምስሌየ።

፴፱ ወተአተተ፡ ሕቀ፡ እምህየ፡ ወሰገደ፡ በገጹ፡ ወጸለየ፡ ወይቤ፡ አቡየ፡ እመሰ፡ ይትከሀል፡ ይኅልፍ፡ እምኔየ፡ ዝጽዋዕ፡ ወባሕቱ፡ ፈቃድከ፡ ይኩን፡ ወአኮ፡ ፈቃድ

፴፫ ፫፥ ጴጥሮስም፡ መለሰ፡ ሁሉ፡ ቢክዱህ፡ እኔ፡ ከቶ፡ አልክድህም፡ አለው።

፴፬ ኢየሱስም፡ መለሰ፡ በዚች፡ ሌሊት፡ ዶሮ፡ ሳይጮህ፡ አስቀድመህ፡ ሦስት፡ ጊዜ፡ እንድትክደኝ፡ እውነት፡ እልሃለሁ፡ አለው። ዮሐ፡ ፲፫፡

፴፭ ፴፭ ጴጥሮስም፡ ከአንተ፡ ጋራ፡ እሞታለሁ፡ እንጂ፡ አልክድህም፡ አለው፡ ደቀ፡ መዛሙርቱም፡ ሁሉ፡ እንዲሁ፡ አሉ። ቀ፡ ፶፯።

፴፮ ከዚህ፡ በኋላ፡ ኢየሱስ፡ ከእርሳቸው፡ ጋራ፡ ጌቴሴማኒ፡ ወደምትባል፡ ስፍራ፡ መጣ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱንም፡ ወደዚያ፡ ሒጄ፡ እስክጸልይ፡ ድረስ፡ ከዚህ፡ ቆዩ፡ አላቸው። ከእርሱም፡ ጋራ፡ ጴጥሮስን፡ ሁለቱን፡ የዘብዴዎስን፡ ልጆች፡ ወስዶ። ያዝንም፡ ይተክዝም፡ ጀመር። ዕብ፡ ፭፡ ፯።

፴፰ በዚያን፡ ጊዜ፡ ነፍሴ፡ እስከ፡ ሞት፡ ድረስ፡ አዘነች፡ በዚህ፡ ተቀመጡ፡ ከእኔ፡ ጋራም፡ ትጉ፡ አላቸው። ዮሐ፡ ፲፪፡ ፳፯።

፴፱ ከዚያ፡ ጥቂት፡ ፈቀቅ፡ ብሎ፡ እየጸለየ፡ በግምባሩ፡ ሰገደ፡ እንዲህም፡ እያለ፡ አባቴ፡ ሆይ፡ ይቻል፡ እንደ ሆነስ፡ ይህች፡ ጽዋ፡ ከእኔ፡ ትለፍ፤ ነገር፡ ግን፡ ያንተ፡ ፈቃድ፡ ይ

የ።

፵ ወሐረ፡ኀበ፡አርዳኢሁ፡ወረከቦሙ፡እንዘ፡ይነውሙ፡ወይቤሎ፡ለጴጥሮስ፡ከመዝኑ፡ስእንክሙ፡ተጊሀ፡ምስሌየ፡አሐተ፡ሰዓተ።

፵፩ ተጋሁ፡ወጸልዩ፡ከመ፡ኢትባኡ፡ውስተ፡መንሱት፡እስመ፡መንፈስ፡ይፈቱ፡ወሥጋ፡ይደክም።

፵፪ ወካዕበ፡ሖረ፡ወዳግመ፡ጸለየ፡ወይቤ፡አአቡየ፡እመ፡ይትከሀል፡ይኅልፍ፡ዝጽዋዕ፡ዘእንበለ፡እስትዮ፡ይኩን፡ፈቃድከ።

፵፫ ወመጽአ፡ካዕበ፡ኀበ፡አርዳኢሁ፡ወረከቦሙ፡እንዘ፡ይነውሙ፡እስመ፡አዕይንቲሆሙ፡ክቡዳት።

፵፬ ወኀደጎሙ፡ወሖረ፡ካዕበ፡በሣልስ፡ወጸለየ፡ኪያሃ፡ክመ፡ቃለ፡እንዘ፡ይብል።

፵፭ ወገብአ፡ካዕበ፡ኀበ፡አርዳኢሁ፡ወይቤሎሙ፡ኑሙ፡እንከሰ፡ወአዕርፉ፡ናሁ፡በጽሐ፡ጊዜሁ፡ወየገብእዎ፡ለወልደ፡እጓለ፡እመሕያው፡ውስተ፡እደ፡ኃጥአን።

፵፮ ተንሥኡ፡ንሖር፡ናሁ፡ቀርበ፡ዘየገብአኒ።

፵፯ ወእንዘ፡ዘንተ፡ይትናገር፡ናሁ፡መጽአ፡ይሁዳ፡አሐዱ፡እምዓ

ሁን፡እንጂ፡የኔ፡ፈቃድ፡አይደለም።

፵ ወደ፡ደቀ፡መዛሙርቱም፡መጣ፡ተኝተውም፡አገኛቸው፡ጴጥሮስንም፡ከእኔ፡ጋራ፡አንዲት፡ሰዓት፡ትተጉ፡ዘንድ፡እንዴት፡አልቻላችሁም፡አለው።

፵፩ ወደ፡ፈተናም፡እንዳትገቡ፡ትጉ፡ጸልዩም፡መንፈስ፡ይወዳልና፡ሥጋ፡ግን፡ደካማ፡ነው።

፵፪ ደግሞ፡ሁለተኛ፡ሔደና፡አባቴ፡ሆይ፡ይህችን፡ጽዋ፡ሳልጠጣት፡ከኔ፡ታልፍ፡ዘንድ፡የማይቻል፡እንደሆነ፡ፈቃድህ፡ትሁን፡ብሎ፡ጸለየ።

፵፫ ሁለተኛም፡በተመለሰ፡ጊዜ፡ዓይኖቻቸው፡በእንቅልፍ፡ከብደው፡ነበሩና፡ተኝተው፡አገኛቸው።

፵፬ ደግሞም፡ትተዋቸው፡ሔደ፡ሦስተኛም፡ያንኑ፡የፊተኛውን፡ቃል፡ጸለየ።

፵፭ ከዚያ፡ወደ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡መጥቶ፡አላቸው፡እንግዲህ፡ተኙ፡እረፉም። እነሆ፡ሰዓቱ፡ደረሰ፡የሰው፡ልጅም፡በኃጢአተኞች፡እጅ፡ይሰጣል።

፵፮ ተነሡ፡እንሒድ፡እነሆ፡አሳልፎ፡የሚሰጠኝ፡አሁን፡ደረሰ።

፵፯ እርሱም፡ይህን፡ሲናገር፡እነሆ ከአሥራ፡ሁለቱ፡አንዱ፡ይሁዳ፡

ሠርቱ፡ ወክልኤቱ፡ ወምስሌ
ሁ፡ ኅብዙኃ፡ ሰብእ፡ ምስለ፡ መ
ጣብሕ፡ ወዕፀው፡ እምኀበ፡
ሊቃነ፡ ካህናት፡ ወረበናቱ፡ ሕ
ዝብ።

፵፰ ወዘ ያገብኦ፡ ወሀበሙ፡ ትእ
ምርተ፡ እኄዝ፡ ይብል፡ ዘሰዐም
ኩ፡ ውእቱ፡ ኪያሁ፡ አኃዙ።

፵፱ ወቀርበ፡ ኀበ፡ እግዚእ፡ ኢየሱ
ስ፡ ወሰዐሞ፡ ወይቤሎ፡ በሐ፡ ረ
ቢ።

፶ ወይቤሎ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡
በእንተ፡ ዝኑ፡ መጻእከ፡ ካልእ
የ፡ ወንሥኡ፡ እደዊሆሙ፡ ወ
አኃዝዎ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ።

፶፩ ወናሁ፡ አሐዱ፡ እምእለ፡ ምስ
ሌሁ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ሰፍ
ሐ፡ እዴሁ፡ ወመልሐ፡ መጥባሕ
ቶ፡ ወዘበጠ፡ ለገብረ፡ ሊቀ፡ ካህ
ናት፡ ወመተረ፡ ዕዝኖ።

፶፪ ወይቤሎ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ አ
ግብእ፡ ለመጥባሕትከ፡ ውስተ፡
ቤታ፡ እስመ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ መ
ጥባሕተ፡ ያነሥኡ፡ በመጥባሕ
ት፡ ይመውቱ።

፶፫ ይመ ስለከሙኑ፡ ዘኢይክል፡ አ
ስተብቍዖ፡ ለአቡየ፡ ይፌኑ፡
ሊተ፡ ፈድፋደ፡ እምዓሠርቱ።

መጣ፡ ከእርሱም፡ ጋራ፡ ከካህ
ናቱ፡ አለቆችና፡ ከሕዝብ፡ ሽ
ማግሌዎች፡ ዘንድ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡
ሰይፍና፡ ጎመድ፡ ይዘው፡ መጡ።

፵፰ አሳልፎ፡ የሚሰጠውም፡ የም
ስመው፡ እርሱ፡ ነው፡ ያዙት፡
ብሎ፡ ምልክት፡ ሰጣቸው።

፵፱ ወዲያውም፡ ወደ፡ ኢየሱስ፡ ቀረ
በ፡ መምህር፡ ሆይ፡ ደኅና፡ ነህን፡
ብሎ፡ ሳመው።

፶ ኢየሱስም፡ ወዳጄ፡ ሆይ፡ መጣ
ህን፡ አለው፡ በዚያን፡ ጊዜ፡ ቀረ
ቡ፡ እጃቸውንም፡ በኢየሱስ፡ ላ
ይ፡ ጫኑ፡ ያዙትም። መዝ፡ ፵፫፡ ፲፬፡

፶፩ እነሆም፡ ከኢየሱስ፡ ጋራ፡ ከነ
በሩት፡ አንዱ፡ እጁን፡ ዘርግቶ፡
ሰይፉን፡ መዘዘ፡ የካህናቱንም፡
አለቃ፡ አገልጋይ፡ መታው፡ ጆሮ
ውንም፡ ቆረጠው። ዘፍ፡ ፱፡ ፮፡ ራእ፡ ፲፫፡ ፲፡

፶፪ በዚያን፡ ጊዜ፡ ኢየሱስ፡ አለው፡
ሰይፍ፡ የሚያነሡ፡ ሁሉ፡ በሰይ
ፍ፡ ይጠፋሉና፡ ሰይፍህን፡ ወደ
አፎቱ፡ መልስ።

፶፫ ወይስ፡ ከመላእክት፡ ወገን፡ ከሥ
ራ፡ ሁለቱ፡ አለቆች፡ የሚበልጡ፡
ይሰዱልኝ፡ ዘንድ፡ አሁን፡ ወደ፡

ወክልኢቱ፡ ሠራዊተ፡ መላእ
ክት ።
፶፬ አፎ፡ እንከ፡ ይትፌጸም፡ ቃለ፡
መጽሐፍ፡ ዘይቤ፡ እስመ፡ ከመ
ዝ፡ ሀለዎ፡ ይኩን ።
፶፭ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡
ለሕዝብ፡ ሰቤሃ፡ ከመ፡ ሰራቂኑ፡
ትዴግኑኒ፡ መጻእክሙ፡ በአስፍ
ት፡ ወበአብትር፡ ትእኅዙኒ፡ ወ
ዘልፈ፡ እነብር፡ ምስሌክሙ፡ በምኵ
ራብ፡ እሜህር፡ ወኢአኀዝክሙ
ኒ ። ፶፮ ወዝ፡ ኵሉ፡ ዘኮነ፡ ከመ፡ ይብ
ጻሕ፡ ቃለ፡ ነቢያት ። ወእምዝ፡
ኀደግዎ፡ ኵሎሙ፡ አርዳኢሁ፡
ወጐዩ ።
፶፯ ወእለ፡ አኀዝዎ፡ ለእግዚእ፡ ኢ
የሱስ፡ ወሰድዎ፡ ኀበ፡ ቀያፋ፡ ሊ
ቀ፡ ካህናት፡ ኀበ፡ ተጋብኡ፡ ጸሐ
ፍት፡ ወረበናት ።
፶፰ ወተለዎ፡ ጴጥሮስ፡ እምርኁቅ፡
እስከ፡ ዓፀደ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ ወ
በአ፡ ውስተ፡ ወነበረ፡ ምስለ፡ ወ
ዓልት፡ ይርአይ፡ መኣለቅቶ፡ ለ
ነገር ።
፶፱ ወሊቃነ፡ ካህናትሰ፡ ወጸሐፍ
ት፡ ወረበናት፡ ወኵሉ፡ ዓውድ፡
የኀሥሡ፡ ሰማዕተ፡ ሐሰት፡ ላ
ዕለ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ከመ፡

አባቴ፡ ለመለመን፡ የማልች
ል፡ ይመስልሃልን ። ዳን፡፯፡፲፡
፶፬ ነገ ር፡ ግን፡ እንዲህ፡ ይሆን፡ ዘ
ንድ፡ እንዲገባ፡ መጻሕፍት፡ እ
ንዴት፡ ይፈጸማል ።
፶፭ በዚ ያን፡ ጊዜ፡ ኢየሱስ፡ ሕዝቡ
ን፡ አላቸው፡ እንደ፡ ሌባ፡ በሰይ
ፍና፡ በጎመድ፡ ልትይዙኝ፡ መ
ጥታችኋልን፡ በቤት፡ መቅደስ፡
ተቀምጬ፡ እያስተማርሁ፡ ሁ
ልጊዜ፡ ከእናንተ፡ ጋራ፡ እኖር፡ ነበር
ሁ፣ ለምን፡ አልያዘችሁም ። የሉ፡፳፪፡፶፫፡
፶፮ ነገ ር፡ ግን፡ ይህ፡ ሁሉ፡ የሆነ፡ የነቢ
ያት፡ መጻሕፍት፡ ይፈጸሙ፡ ዘን
ድ፡ ነው፡ ከዚህ፡ በኋላ፡ ደቀ፡ መዛ
ሙርቱ፡ ሁሉ፡ ጥለውት፡ ሸሹ፡ የሐዋ፡፲፫፡፳፯፡
፶፯ ኢየሱስን፡ የያዙት፡ ግን፡ ጻፎችና፡ ሽ
ማግሌች፡ ወደተሰበሰቡበት፡ ወደ፡
ሊቀ፡ ካህናቱ፡ ወደ፡ ቀያፋ፡ ቤት፡ ወሰ
ዱት ። የሐ፡፲፰፡፲፫፡፳፬፡ ፶፰ ጴጥ ሮስ፡ ግን፡ የነ
ገሩን፡ ፍጻሜ፡ ያይ፡ ዘንድ፡ በሩቅ፡
ሁኖ፡ እስከ፡ ሊቀ፡ ካህናቱ፡ ቤት፡ ደ
ረስ፡ ተከተለው፡ ወደ፡ ውስጥም፡
ገብቶ፡ ከሎሌሎች፡ ጋራ፡ ተቀመጠ ።
፶፱ የካ ህናት፡ አለቆችና፡ ሽማግሌ
ችና ጻፎችም፡ በሸንጎም፡ ያሉት፡
ሁሉ፡ ይገድሉት፡ ዘንድ፡ በኢየሱ
ስ፡ ላይ፡ የሐሰት፡ ምስክር፡ ይሹ፡

ይቀትልዎ፡ ወኢረከቡ።
፷ ወመጽኡ፡ ብዙኃን፡ ሰማዕ
ት፡ ሐሰት፡ ወሰእኑ፡ ወድኅረ፡
መጽኡ፡ ክልኤቱ፡ ወይቤሉ።
፷፩ ይቤ፡ ዝንቱ፡ እክል፡ ነሢቶቶ፡
ለቤት፡ እግዚአብሔር፡ ወበ
ሣልስት፡ ዕለት፡ አሐንፆ።
፷፪ ወተንሥአ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ ወ
ይቤሎ፡ ኢትሰምዖኑ፡ እንዘ፡
መጠነዝ፡ ያስተዋድዩከ።
፷፫ ወአርመመ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ
ወይቤሎ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ አም
ሐልኩከ፡ በእግዚአብሔር፡ ሕ
ሕያው፡ ከመ፡ ትንግረኒ፡ እመ
አንተሁ፡ ክርስቶስ፡ ወልዱ፡ ለ
እግዚአብሔር።
፷፬ ወይቤሎ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡
አንተ፡ ትቤ፡ ወባሕቱ፡ እብለ
ክሙ፡ እምይእዜሰ፡ ትሬእይ
ዎ፡ ለወልደ፡ እጓለ፡ እመሕያው
እንዘ፡ ይነብር፡ በየማነ፡ ኃይል፡
ወእንዘ፡ ይመጽእ፡ በደመና፡
ሰማይ።
፷፭ ወሶቤሃ፡ ሰጠጠ፡ አልባሲሁ፡
ሊቀ፡ ካህናት፡ እንዘ፡ ይብል፡ ም
ናተ፡ እንከ፡ ትፈቅዱ፡ ሎቱ፡ ሰ
ማዕተ፤ ናሁ፡ ፀረፈ፡ ወሰማዕ

ነገር፡ ግን፡ አላገኙበትም።
፷ ብዙም፡ የሐሰት፡ ምስክሮች
መጡና፡ አላገኙበትም፡ በኋላ
ም፡ ሁለት፡ የሐሰት፡ ምስክሮ
ች፡ መጥተው፡ እንዲህ፡ አሉ።
፷፩ ይህ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔርን፡ አ
ፍርሼ፡ በሦስት፡ ቀን፡ እሠራው፡
ዘንድ፡ እችላለሁ፡ አለ። የሐ፡ ፪፡ ፲፱ ፳፬።
፷፪ የካህናት፡ አለቃም፡ ተነሥቶ፡
እነዚህ፡ የሚመሰክሩብህን፡ አ
ትሰማምን፡ አለው።
፷፫ ኢየሱስም፡ ዝም፡ አለ፡ የካህና
ት፡ አለቃም፡ አንተ፡ የእግዚአ
ብሔር፡ ልጅ፡ ክርስቶስ፡ እንደ፡
ሆንህ፡ እንድትነግረኝ፡ በሕያው፡
እግዚአብሔር፡ አምልሃለሁ፡
አለው። ም፡ ፳፯፡ ፲፪።
፷፬ ኢየሱስም፡ አንተ፡ አልህ፡ አለ
ው፡ ከእንግዲህ፡ ወዲህ፡ ግን፡ እ
ላችኋለሁ፡ የሰው፡ ልጅ፡ በኃይ
ል፡ ቀኝ፡ ሲቀመጥ፡ በሰማይ፡ ም፡
ደመና፡ ሲመጣ፡ እንድታዩ።
ም፡ ፲፮፡ ፳፯። መዝ፡ ፻፲። ፮ ዳን፡ ፯ ፲፫ ፲፬።
፷፭ በዚያን፡ ጊዜ፡ የካህናት፡ አለቃ፡
ልብሱን፡ ቀደደ፡ እንዲህ፡ ብሎ፡
እነሆ፡ እርሱ፡ እግዚአብሔርን፡
ተሳደበ፡ ሰድቡንም፡ ሰማችሁ፡

ከሙ፡ ፅርፈቶ።
፷፮ ምንተ፡ እንከ፡ ትብሉ፡ ወአ
ውሥኡ፡ ወይቤሉ፡ ዝንቱ፡ ድ
ልው፡ ለሞት።
፷፯ ወእምዝ፡ ተፍኡ፡ ውስተ፡ ገ
ጹ፡ ወኰርዕዎ፡ ወጸፍዕዎ፡ እ
ንዘ፡ ይብሉ።
፷፰ ተነበይ፡ ለነ፡ ክርስቶስ፡ መኑ፡
ውእቱ፡ ዘጸፍዐከ።
፷፱ ወጴጥሮስሰ፡ ይነብር፡ አፍኣ፡
ውስተ፡ ዓፀድ፡ ወመጽአት፡ ወ
ለት፡ ወትቤሎ፡ አንተኒ፡ ምስ
ለ፡ ኢየሱስ፡ ገሊላዊ፡ ሀለውከ።
፸ ወክሕደ፡ በቅድመ፡ ኵሉ፡ እንዘ፡
ይብል፡ ኢየአምር፡ ዘትብሊ።
፸፩ ወወፂኦ፡ ኆኅተ፡ ርእየቶ፡ ካል
እት፡ ወትቤሎሙ፡ ለእለ፡ ይቀ
ውሙ፡ ህየ፡ ዝኒ፡ ሀሎ፡ ምስለ፡ ኢ
የሱስ፡ ናዝራዊ።
፸፪ ወክሕደ፡ ካዕበ፡ ወመሐለ፡ ከመ
ኢየአምሮ፡ ለውእቱ፡ ብእሲ።
፸፫ ወጎንደዮ፡ ሕቀ፡ መጽኡ፡ እለ፡
ይቀውሙ፡ ወይቤልዎ፡ ለጴጥ
ሮስ፡ አማን፡ አንተኒ፡ እምኔሆ
ሙ፡ አንተ፡ ወነገርከ፡ ያዓውቀ
ከ።
፸፬ ወእምዝ፡ መሐለ፡ ወተረግመ፡

እንግዲህ፡ ወዲህ፡ ምስክር፡
፷፮ ምን፡ ያስፈልገናል፤ (ዮሐ፡፲፡፴፫) እን
ግዲህ፡ ምን፡ ይመስላችኋል፡
እርሳቸው፡ ግን፡ መልሰው፡
ይህ፡ ሞት፡ ይገባዋል፡ አሉ፤ (ዮሐ፡፲፱፡፯)
፷፯ በዚያን፡ ጊዜ፡ በፊቱ፡ ተፉበት፡ ራሱ
ንም፡ መቱት፡ ሌሎችም፡ በጥፊ፡
፷፰ መቱት። (ኢሳ፡፶፡፮) ክርስቶስ፡ ሆይ፡
ትንቢት፡ ንገረን፡ ማነው፡ በ
፷፱ ጥፊ፡ የመታህ፡ አያሉ። ጴጥሮስ፡
ግን፡ ከቤት፡ በስተውጭ፡ ተቀ
ምጦ፡ ነበር፡ አንዲቱ፡ ገረድ፡ መ
ጣችና፡ አንተ፡ ደግሞ፡ ከገሊላ፡ ከ
ኢየሱስ፡ ጋራ፡ ነበርህ፡ አለችው።
፸ (ዮሐ፡፲፰፡፲፯፡፳፭) እርሱ፡ ግን፡ የምት
ዪውን፡ አላውቅም፡ ብሎ፡ በሁ
፸፩ ሉ፡ ፊት፡ ካደ። ወደ፡ ውጭም፡ በወ
ጣ፡ ጊዜ፡ ሌላዪቱ፡ አየችው፡ በዚ
ያም፡ ለነበሩት፡ ይህም፡ ደግሞ፡ ከና
ዝሬቱ፡ ከኢየሱስ፡ ጋራ፡ ነበረ፡ አለ
፸፪ ቻቸው። (ዮሐ፡፲፰፡፳፭) ዳግመኛም፡ ያን
ን፡ ሰው፡ እንዳያውቀው፡ በመሐላ፡
፸፫ ካደ። ጥቂትም፡ ቆይተው፡ ቁመ
ው፡ የነበሩት፡ ቀርበው፡ ጴጥሮ
ስን፡ አነጋገርህ፡ ያስታውቅብ
ሃልና፡ በእውነት፡ አንተም፡ ደ
ግሞ፡ ከእርሳቸው፡ ወገን፡ ነህ፡
፸፬ አሉት። ከዚያ፡ በኋላ፡ ይህን፡ ሰ

ከመ፡ኢየአምሮ፡ለውእቱ፡ብ
እሲ፨ወበጊዜሃ፡ነቀወ፡ዶርሆ።

፸፬ ወተዘከረ፡ጴጥሮስ፡ቃሎ፡ለእ
ግዚእ፡ኢየሱስ፡ዘይቤሎ፡ሥ
ልሰ፡ትክሕደኒ፡ዘእንበለ፡ይን
ቁ፡ዶርሆ፡ወወፅአ፡አፍአ፡ወ
በከየ፡ብከየ፡መሪረ፨

ምዕራፍ፡፳፯።

ኢየሱስን፡ሊገድሉት፡እንደ፡መከሩ። ይሁዳ፡ታን
ቆ፡እንደሞተ። በተቀበለው፡ብር፡የመቃብር፡ቦታ፡
እንደተገዘበት። በጲላጦስ፡ፊት፡እንደቆመ። ጲላጦ
ስ፡እጁን፡እንደታጠበ። እንደ፡ተገረፈ፡እንደ፡ተሰቀለ።

፩ ወጸቢሐ፡ተማከሩ፡ኵሎሙ፡
ሊቃነ፡ካህናት፡ወሊቃናተ፡ሕዝ
ብ፡ይቅትልዎ፡ለእግዚእ፡ኢ
የሱስ፨

፪ ወአሠርዎ፡ወሰድዎ፡ወመ
ጠውዎ፡ለጲላጦስ፡ጳንጤናዊ፡
መስፍን፨ወእምዝ፡ሶበ፡ርእየ፡ይ

፫ ሁዳ፡ዘአግብኦ፡ከመ፡ተኰነነ፡ነስሐ፡
ወአግብአ፡ውእተ፡ሠላሳ፡ብሩረ፡
ለሊቃነ፡ካህናት፡ወለሊቃውን
ተ፡ሕዝብ፨

፬ እንዘ፡ይብል፡አበስኩ፡ዘአግ
ባእኩ፡ደመ፡ንጹሐ፨ወይቤልዎ፡
ሚ፡ላዕሌነ፡አንተ፡አእምር፨

፭ ወገደፈ፡ውእተ፡ብሩረ፡ውስ

ው፡አላውቀውም፡እያለ፡ደ
ረጋምና፡ይምል፡ጀመረ፡በዚ

፸፬ ያን፡ጊዜም፡ዶሮ፡ጮኸ፨ጴጥሮስም፡
ዶሮ፡ሳይጮህ፡ሶስት፡ጊዜ፡ትክ
ዳኛለህ፡ያለውን፡የኢየሱስን፡
ቃል፡አሰበ፡ወደ፡ውጭም፡ው
ጥቶ፡መራራ፡ልቅሶ፡አለቀሰ። ሉቃ፡፷፪

ሀያ፡ሰባት፡ምዕራፍ።

ሁለት፡ወንበዴች፡ከርሱ፡ጋራ፡እንደ፡ተሰቀሉ። የቤተ፡
መቅደስ፡መጋረጃ፡እንደ፡ተቀደደ። የአርማትያሱ፡
ዮሴፍ፡ሥጋውን፡ከመስቀል፡አውርዶ፡እንደ፡ቀበረ
ው። የካህናት፡አለቆች፡መቃብሩን፡በዘበኛ፡እንዳስጠበቁት።

፩ በጧትም፡ጊዜ፡የካህናት፡አለቆ
ች፡ሁሉ፡የሕዝቡም፡ሽማግሌ
ዎች፡ይገድሉት፡ዘንድ፡በኢየሱ
ስ፡ላይ፡ተማከሩ፨ማር፡፲፭፡፩፡ሉቃ፡፳፪
፷፮። ዮሐ፡፲፰፡፳፰፨

፪ አሰረውም፡ይዘው
ት፡ሔዱ፡ለሹሙም፡ለጳንጤናዊ፡
ለጲላጦስ፡አሳልፈው፡ሰጡት፨

፫ በዚያን፡ጊዜ፡አሳልፎ፡የሰጠው፡
ይሁዳ፡እንዲተፈረደበት፡ባየ፡
ጊዜ፡ተጠጠተ፨ሠላሳውንም፡
ብር፡ወደ፡ካህናቱ፡አለቆችና፡ወደ፡ሽማ
ግሌዎች፡መለሰው፡እንዲህ፡ሲል፨ምሳ፡፳፰፡፲፯ ን

፬ ጹሕ፡ደም፡አሳልፌ፡በመስጠቴ፡በ
ደልሁ፡እርሳቸው፡ግን፡እኛን፡ምን፡
አግደን፡ለራስህ፡አንተ፡እወቅ፡አ
ሉት፨

፭ ያን ንም፡ብር፡በቤተ፡መ

ተ፡ ምኵራብ፡ ወሐረ፡ ወተ
ኀኘቀ ✤

፮ ወነሥኡ፡ ሊቃነ፡ ካህናት፡
ውእተ፡ ብሩረ፡ ወይቤሉ፡ ኢ
ይከውነነ፡ ንደዮ፡ ውስተ፡ ቤ
ተ፡ ቍርባን፡ እስመ፡ ሤጠ፡ ደ
ም፡ ውእቱ ✤

፯ ወተማኪሮሙ፡ ተሣየጡ፡ በ
ቱ፡ ገራህተ፡ ለብሐዊ፡ ለመቃ
ብረ፡ እንግዳ ✤

፰ ወበእንተ ዝ፡ ተሰምየ፡ ውእ
ቱ፡ ገራህት፡ ገራህተ፡ ደም፡ እ
ስከ፡ ዮም ✤

፱ ወይእቲ፡ አሚረ፡ በጽሐ፡ ቃ
ለ፡ ኤርምያስ፡ ነቢይ፡ ዘይቤ፡
ነሥኡ፡ ሠላሳ፡ ብሩረ፡ ሤጠ፡
ለክቡር፡ ዘአክበርዎ፡ እምደ
ቂቀ፡ እስራኤል ✤

፲ ወወሀብዎ፡ ለገራህተ፡ ለብሐ
ዊ፡ በከመ፡ አዘዘኒ፡ እግዚአ
ብሔር ✤

፲፩ ወቆመ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡
ቅድሜሁ፡ ለመልአክ፡ አሕዛብ፡
ወተስእሎ፡ መልአክ፡ አሕዛብ፡
ወይቤሎ፡ አንተኑ፡ ንጉሦሙ፡
ለአይሁድ፡ ወይቤ፡ እግዚእ፡ ኢ
የሱስ፡ አንተ፡ ትቤ ✤

፲፪ ወእንዘ፡ ያስተዋድይዎ፡ ሊቃ

ቀደሰ፡ በተኑና፡ ሔደ፡ ታንቆ
ሞ፡ ሞተ ✤ የሐዋ፡ ፩፡ ፲፰፡ ፪ ሳሙ፡ ፲፯ ፳፫ ✤

፮ የካህናትም፡ አለቆች፡ ብሩ
ን፡ ወሰደው፡ የደም፡ ዋጋ፡ ነው
ና፡ በእግዚአብሔር፡ ቍርባ
ን፡ ሣጥን፡ እንጨምረው፡ ዘን
ድ፡ አይገባንም፡ አሉ ✤ ማር፡ ፲፪ ፵፩፡

፯ ተማክረውም፡ ለእንግዶች፡
መቃብር፡ የሸክላ፡ ሠሪ፡ መሬ
ት፡ ገዙበት ✤ የሐዋ፡ ፩፡ ፲፱ ✤

፰ ስለዚህም፡ ያ፡ መሬት፡ እስከ፡
ዛሬ፡ ድረስ፡ የደም፡ ምድር፡
ተብሎ፡ ተጸራ ✤

፱ በዚያን፡ ጊዜ፡ በነቢዩ፡ በኤር
ምያስ፡ የተባለው፡ ተፈጸመ፡
የእስራኤል፡ ልጆች፡ የገመገ
ሙትን፡ የክቡሩን፡ ዋጋ፡ ሠላሳ
ውን፡ ብር፡ ወሰዱ ✤ ዘካ፡ ፲፩፡ ፲፪፡ ፲፫ ✤

፲ ኤር፡ ፴፫፡ ፯፡፡ ለሸክላ፡ ሠሪም፡ መ
ሬት፡ ሰጡት፡ እግዚአብሔር፡ እ
ንዳዘዘኝ ✤

፲፩ ኢየሱስም፡ በሹሙ፡ ፊት፡ ቆ
መ፡ ሹሙም፡ የአይሁድ፡ ንጉ
ሥ፡ አንተ፡ ነህን፡ ብሎ፡ ጠየቀ
ው፡፡ ኢየሱስም፡ አንተ፡ ትላለ
ህ፡ አለው ✤ ማር፡ ፲፭፡ ፪፡፡ ሉቃ፡ ፳፫ ✤ ዮሐ፡ ፲፰
፴፫፡ ፴፯ ✤

፲፪ የካህናት፡ አለቆችና፡ ሽማግ

ኒ፡ ካህናት፡ ወሊቃውንተ፡
ሕዝብ፡ አልቦ፡ ዘያወሥአ
ሙ፡ ወኢምንተኒ።
፲፫ ወእምዝ፡ ይቤሎ፡ ጲላጦስ፡
ኢትሰምዖኑ፡ መጠነ፡ ያስተ
ዋድዩከ።
፲፬ ወኢያውሥኦ፡ ቃለ፡ ወኢአ
ሐተኒ፡ እስከ፡ ያነክር፡ መል
ክ፡ ዋቀ።
፲፭ ወበበ፡ በዓል፡ ያለምድ፡ ረ
መልአክ፡ አሕዛብ፡ ያሕዩ፡ ሎ
ሙ፡ ለሕዝብ፡ አሐዱ፡ እምውዑ
ስተ፡ ሙቁሐን፡ ዘፈቀዱ።
፲፮ ወቦ፡ አሜሃ፡ ሙቁሕ፡ ዘስሙ፡
በርባን፡ ሰሙዕ፡ ወየአምሮ፡
፲፯ ኵሉ። ወእንዘ፡ ጉቡአን፡ እ
ሙንቱ፡ ይቤሎሙ፡ ጲላጦ
ስ፡ ለሕዝብ፡ መኑ፡ ትፈቅዱ፡
አሕዩ፡ ለክሙ፡ በርባንሃኑ፡
ወሚመ፡ ኢየሱስሃኑ፡ ዘይብ
ሎዎ፡ ክርስቶስ።
፲፰ እስመ፡ የአምር፡ ከመ፡ በቅ
ንአቶሙ፡ አግብእዎ።
፲፱ ወእንዘ፡ ይነብር፡ ዓውደ፡ ለ
አከተ፡ ኀቤሁ፡ ብእሲቱ፡ እንዘ፡
ትብል፡ ዑቅአ፡ ኢትእብስ፡ ለ
ዕለ፡ ውእቱ፡ ጻድቅ። እስመ፡
ብዙኀ፡ ሐመምኩ፡ ዮም፡ በሕ

ሎችም፡ ሲያሳጡት፡ ምንም፡
አልመልሰላቸውም። ኢሳ፡፶፫፡፯
፲፫ በዚያን፡ ጊዜ፡ ጲላጦስ፡ ይህን፡
ያህል፡ ሲያሳጡህ፡ አትሰማ
ምን፡ አለው።
፲፬ እርሱም፡ አንዲት፡ ቃል፡ ስን
ኳ፡ አልመለሰለትም፡ ሹሙ፡
እጅግ፡ እስኪያደንቅ፡ ድረስ።
፲፭ በየበዓሉም፡ ለሕዝቡ፡ ከእ
ሥረኞቹ፡ ውሥዋ፡ የወደዱ
ት፡ አንድ፡ እሥር፡ ይፈታላቸ
ው፡ ዘንድ፡ ለሹሙ፡ ልማድ፡ ነ
፲፮ በረው። በዚያን፡ ጊዜም፡ በርባ
ን፡ የሚባል፡ የታወቀ፡ አንድ፡
፲፯ እሥር፡ ነበረ። እርሳቸውም፡
ተሰብስበው፡ ሳሉ፡ ጲላጦስ፡
ማንን፡ እፈታላችሁ፡ ዘንድ፡ ት
ወዳላችሁ፡ በርባንን፡ ወይስ፡
ክርስቶስ፡ የሚባለው፡ ኢየ
ሱስን፡ አላቸው።
፲፰ በቅናት፡ አሳልፈው፡ እንደ፡ ሰ
ጡት፡ ያውቅ፡ ነበርና።
፲፱ እርሱም፡ በፍርድ፡ ወንበር፡
ተቀምጦ፡ ሳለ፡ ሚስቱ፡ በዚያ፡
ጻድቅ፡ ሰው፡ በዴል፡ እንዳት
ውል፡ ተጠንቀቅ፡ ስለ፡ እርሱ፡
ዛሬ፡ በሕልም፡ እጅግ፡ መከራ፡

ልምየ፡ በእንቲአሁ።

፳ ወሊቃነ፡ ካህናትሰ፡ ወሊቃውንት፡ ሄጥዎሙ፡ ለሕዝብ፡ ወአሆ፡ አብልዎሙ፡ ከመ፡ በርባንሃ፡ ያሕዩ፡ ሎሙ፡ ይሰአሉ፡ ወኢየሱስሃ፡ ይቅትሉ፨

፳፩ ወአውሥአ፡ መስፍን፡ ወይቤሎሙ፡ መኑ፡ ትፈቅዱ፡ እምክልኤሆሙ፡ አሕዩ፡ ለክሙ፡ ወይቤሉ፡ በርባንሃ።

፳፪ ወይቤሎሙ፡ ጲላጦስ፡ ምንተ፡ እሬሲ፡ ለኢየሱስ፡ ዘተብህለ፡ ክርስቶስ፡ ወይቤሉ፡ ኵሎሙ፡ ስቀሎ፨

፳፫ ወይቤሎሙ፡ መስፍን፡ ምንተ፡ እኩየ፡ ገብረ፡ ወአፈድፈዱ፡ ጸርኆ፡ እንዘ፡ ይብሉ፡ ስቀሎ ስቀሎ።

፳፬ ወእምዝ፡ ሶበ፡ ርእየ፡ ጲላጦስ፡ ከመ፡ አልቦ፡ ዘይበቍዕ፡ ዘእንበለ፡ ዳዕሙ፡ ዘይበዝኅ፡ ሀከክ፡ ነሥአ፡ ማየ፡ ወተኃፅበ፡ እዴሁ፡ በቅድሜሆሙ፡ ለሕዝብ፡ እንዘ፡ ይብል፡ ንጹሕ፡ አነ፡ እምደሙ፡ ለዝ፡ ጻድቅ፡ አንትሙ፡ ለሊክሙ፡ አእምሩ፨

፳፭ ወይቤሉ፡ ኵሉ፡ ሕዝብ፡ ደሙ፡ ላዕሌነ፡ ወላዕለ፡ ውሉድ

ተቀብያለሁና፡ ብላ፡ ላከችበት፨

፳ የካህናት፡ አለቆችና፡ ሽማግሎች፡ ግን፡ በርባንን፡ ለማዳን፡ ኢየሱስንም፡ ለመግደል፡ ይለምኑት፡ ዘንድ፡ ሕዝቡን፡ አባብለው፡ አሹ፡ አሰኛዋቸው፨

፳፩ ሹሙ፡ ግን፡ መልሶ፡ ከሁለቱ፡ ማናቸውን፡ እፈታላችሁ፡ ዘንድ፡ ትወዳላችሁ፡ አላቸው፡ እርሳቸውም፡ በርባንን፡ አሉ።

፳፪ ጲላጦስም፡ ክርስቶስ፡ በሚባለው፡ በኢየሱስ፡ ምን፡ ላድርግበት፡ አላቸው፡ ሁሉም፡ ይሰቀል፡ አሉ፨

፳፫ ሹሙም፡ ምን፡ ክፉ፡ አደረገ፡ አላቸው። እርሳቸው፡ ግን፡ ይሰቀል፡ እያሉ፡ ጩኸት፡ አበዙ።

፳፬ ጲላጦስም፡ ሁከት፡ ከመብዛት፡ በቀር፡ እንዳች፡ እንዳይረባ፡ ባየ፡ ጊዜ፡ ውሀ፡ አስመጥቶ፡ እኔ፡ ከዚህ፡ ጻድቅ፡ ደም፡ ንጹሕ፡ ነኝ፡ እናንተ፡ እወቁ፡ ብሎ፡ በሕዝቡም፡ ፊት፡ እጁን፡ ታጠበ፨ ዘዳግ፡ ፳፩፡ ፯፨

፳፭ ሕዝቡም፡ ሁሉ፡ ደሙ፡ በእኛ፡ በልጆቻችንም፡ ላይ፡ ይሁን፡ ብለ

ኔ።

፳፮ ወእምዝ፡ፈትሐ፡ሎሙ፡በ
ርባንሃ፡ወቀሠሮ፡ለእግዚ
እ፡ኢየሱስ፡ወመጠዎሙ፡ይ
ስቅልዎ።

፳፯ ወእምዝ፡መስተራትዒተ፡
ሐራ፡ነሥእዎ፡ለእግዚእ፡
ኢየሱስ፡እምውስተ፡ምኵ
ናን፡ወአስተጋብኡ፡ላዕሌ
ሁ፡ማኅበሮሙ።

፳፰ ወአእተቱ፡አልባሲሁ፡ወአ
ልበስዎ፡ክላሚደ፡ዘለይ።

፳፱ ወፀፈሩ፡አክሊለ፡ዘሦክ፡ወ
አስተቀጸልዎ፡ዲበ፡ርእሱ፡
ወአስተአኅዝዎ፡ኅለተ፡ው
ስተ፡የማኑ። ወአስተብረ
ኩ፡ቅድሜሁ፡ወይሣለቁ፡
ላዕሌሁ፡ወይቤልዎ፡በሐ፡
ንጉሠ፡አይሁድ።

፴ ወይወርቁ፡ላዕሌሁ፡ወነሥኡ፡
ኅለተ፡ወኰርዕዎ፡ርእሶ።

፴፩ ወተሣለቁ፡ላዕሌሁ፡ሰ
ለብዎ፡ውእተ፡ልብሰ፡ክሌ
ሚደ፡ወአልበስዎ፡አልባሲ
ሁ፡ወወሰድዎ፡ይስቅልዎ።

፴፪ ወእንዘ፡ይወፅኡ፡ረከቡ፡ብ
እሴ፡ቀሬናዌ፡ዘስሙ፡ስምዖ
ን፡ወዐበጥዎ፡ይፁር፡መስቀ

ው፡መስሉ። የሐዋ፡፫፡፳፰፡ዘዳግም፡፳፩፡፳፫።

፳፮ በዚያን፡ጊዜ፡በርባንን፡ፈታ
ላቸው። ኢየሱስንም፡ግርፎ
እንዲሰቀል፡አሳልፎ፡ሰጣ
ቸው።

፳፯ ከዚያ፡ወዲያም፡የሹሙ፡ጭ
ፍሮች፡ኢየሱስን፡ወደ፡ፍር
ድ፡ሸንጎ፡ወሰዱት። ጭፍራው
ንም፡ሁሉ፡ሰበሰቡበት።
ዮሐ፡፲፱፡፩።

፳፰ ልብሱንም፡ገፈፈው፡ቀይ፡
ልብስ፡አለበሱት።

፳፱ የሾህ፡አክሊልም፡ጐንጕነ
ው፡በራሱ፡ላይ፡ጫኑበት፤ በ
ቀኙ፡እጁም፡ዘንግ፡አስያዙ
ት፡በፊቱም፡በጕልበታቸው፡
ተንበርክከው፡ሰላም፡ይድ
ረስህ፡የአይሁድ፡ንጉሥ፡ሆ
ይ፡እያሉ፡ተሣለቁበት።

፴ ይተፉበትም፡ነበር፡ዘንጉን
ም፡ነጥቀው፡ራሱን፡መቱት፡

፴፩ ኢሳ፡፶፫፡፯። ካፌዙበትም፡በኋላ፡
ቀዩን፡ልብሱ፡ገፈፉና፡ልብ
ሱን፡አልብሰው፡ሊሰቅሉት፡
ወሰዱት።

፴፪ ሲወጡም፡ስሙን፡ስምዖን፡የ
ሚሉት፡የቀሬና፡ሰው፡አገኙ፡
እርሱንም፡መስቀሉን፡ይሸ

ሎ፨

፴፫ ወበጺሖሙ፡ መካነ፡ ዘስሙ፡ ጎልጎታ፡ ዘበትርጓሜሁ፡ ቀራንዮ፡፡

፴፬ ወሀብዎ፡ ይስተዩ፡ ብሒአ፡ ወይነ፡ ድሙረ፡ ምስለ፡ ሐሞት፡ ወጥዒሞ፡ አበየ፡ ሰትዮ፨

፴፭ ወእምዝ፡ ሰቀልዎ፡ ወተካፈሉ፡ አልባሲሁ፡ ወተዓፀውዎ፡ ላዕሌሁ፡ ከመ፡ ይትፈጸም፡ ቃለ፡ ነቢይ፡ ዘይቤ፡ ተካፈሉ፡ አልባስየ፡ ለርእሶሙ፡

፴፮ ወነበሩ፡ የዐቅብዎ፡ ህየ፡፡

፴፯ ወአንበሩ፡ መልዕልተ፡ ርእሱ፡ ጽሒፎሙ፡ መጽሐፈ፡ ጌጋዩ፡ ዘይብል፡ ዝውእቱ፡ ኢየሱስ፡ ንጉሦሙ፡ ለአይሁድ፡

፴፰ ወእምዝ፡ ሰቀሉ፡ ምስሌሁ፡ ክልኤተ፡ ፈያተ፡ አሐዱ፡ በየማኑ፡ ወአሐዱ፡ በፀጋሙ፨

፴፱ ወእለ፡ የኀልፉ፡ ይፀርፉ፡ ላዕሌሁ፡ እንዘ፡ የሐውሱ፡ ርእሶሙ፨

፵ ወይብሉ፡ አዘይነሥቶ፡ ለቤተ፡ መቅደስ፡ ወየሐንፆ፡ በሣልስት፡ ዕለት፡ አመሰ፡ ወ

ኢምን፡ ዘኝድ፡ ጉተቱት፤ ዕብ፡፲፫

፴፫ ፲፱ ፲፫ ፨ትርጓሜው፡ የራስ፡ አጽንት፡ ቦታ፡ የተባለ፡ ጎልጎታ፡ ወደሚሉት፡ ስፍራም፡ በደረሱ፡ ጊዜ፨

፴፬ በሐሞት፡ የተደባለቀ፡ መጸጸ (ከምጣጣ) ሰጡት፡ ቀምሶም፡ ሊጠጣው፡ አልወደደም፡፡ መዝ፡፷፰፡፳፩፨

፴፭ በሰቀሉትም፡ ጊዜ፡ ዕፃ፡ ተጣጣሉው፡ ልብሱን፡ ተካፈሉ፡ በነቢዩ፡ ልብሶቼን፡ እርስ፡ በርሳቸው፡ ተካፈሉ፡ በቀሚሴም፡ ዕፃ፡ ተጣጣሉ፡ የተባለው፡ ይፈጸም፡ ዘንድ፡ መዝ፡፳፩፡፲፰

፴፮ ፨በዚያም፡ ተቀምጠው፡ ይጠብቁት፡ ነበር፨

፴፯ ከራሱም፡ በላይ፡ ይህ፡ ኢየሱስ፡ የአይሁድ፡ ንጉሥ፡ ነው፡ ተብሎ፡ የተጻፈውን፡ ወንጀሉን፡ ለጠፉ (አጣበቁ፨

፴፰ በዚያን፡ ጊዜ፡ ሁለት፡ ወንበዶች፡ አንዱን፡ በቀኙ፡ አንዱንም፡ በግራው፡ ከእርሱ፡ ጋራ፡ ሰቀሉ፡፡ ኢሳ፡፶፫፡፲፪

፴፱ የሚያልፉትም፡ ራሳቸውን፡ እየነቀነቁ፡ እንደዚህ፡ እያሉ፡

፵ ይሰድቡት፡ ነበር፨ቤተ፡ መቅደስን፡ አፍርሰህ፡ በሶስት፡ ቀን፡ የምትሠራ፡ ሆይ፡ ራስህን፡ አ

ልዱ፡ እግዚአብሔር፡ አ
ንተ፡ አድኅን፡ ርእሰከ፡ ወ
ረድ፡ እመስቀልከ።

፵፩ ወከማሁ፡ ሊቃነ፡ ካህናት፡
ሂ፡ ይሣለቁ፡ ምስለ፡ ጸሐፍ
ት፡ ወሊቃናት፡ እንዘ፡ ይብ
ሉ።

፵፪ ባዕደ፡ ያድኅን፡ ወርእሶ፡
ኢይክል፡ አድኅኖ፡ እመሰ፡
ንጉሠ፡ እስራኤል፡ ውእቱ፡
ለይረድ፡ ይእዜ፡ እመስቀል፡
ወንእመን፡ ቦቱ።

፵፫ እመሂ፡ ተአመነ፡ በእግዚአ
ብሔር፡ ናሁ፡ ይእዜ፡ ያድኅ
ኖ፡ እመ፡ ይፈቅዶ፡ እስመ፡
ይብል፡ ወልዱ፡ እግዚአብ
ሔር፡ አነ።

፵፬ ወከማሁ፡ ፈያትኒ፡ እለ፡ ተ
ሰቅሉ፡ ምስሌሁ፡ ይዘነጕጕ
ዎ።

፵፭ ወእምሰሱ፡ ሰዓት፡ ጸልመ፡
ኵሉ፡ ዓለም፡ እስከ፡ ተሱዑ፡
ሰዓት።

፵፮ ወጊዜ፡ ተሱዓት፡ ሰዓት፡ ጸር
ሐ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ በቃል፡
ዓቢይ እንዘ፡ ይብል፡ ኤሎሂ ኤሎሂ፡ ለ
ማ፡ ሰበቅታኒ፡፡ ዝውእቱ፡ ብ
ሂል፡ አምላኪየ፡ አምላኪየ፡

ድን፡ የእግዚአር፡ ልጅም፡
እንደሆንህ፡ ከመስቀል፡ ው
ረድ። ዮሐ፡ ፱፣ ፲፱ ።

፵፩ እንዲሁም፡ ደግሞ፡ የካህ
ናት፡ አለቆች፡ ከጸፎችና፡ ከ
ሽማግሎች፡ ጋራ፡ ያፌዘበ
ት፡ ነበር፡ እንዲህ፡ እያሉ።

፵፪ ሌሎችን፡ ያድናል፡ ራሱን፡
ግን፡ ማዳን፡ አልቻለም፡ እ
ርሱ፡ የእስራኤል፡ ንጉሥ፡
ከሆነስ፡ አሁን፡ ከመስቀል፡
ይውረድ፡ እኛም፡ አይተን፡ እ
ንመንበት።

፵፫ በእግዚአብሔ
ር፡ ከታመነ፡ ከወደደውም፡
አሁን፡ ያድነው፡ እኔ፡ የእግ
ዚአብሔር፡ ልጅ፡ ነኝ፡ ብሏ
ልና። መዝ፡ ፳፩፡ ፱ ።

፵፬ እንዲሁም፡ ደግሞ፡ ከእርሱ፡
ጋራ፡ የተሰቀሉት፡ ወንበዴ
ች፡ ይሰድቡት፡ ነበር።

፵፭ ከስድስት፡ ሰዓትም፡ ጀምሮ፡
እስከ፡ ዘጠኝ፡ ሰዓት፡ በምድር፡
ላይ፡ ሁሉ፡ ጨለማ፡ ሆነ።

፵፮ በዘጠኝ፡ ሰዓት፡ ጊዜም፡ ኢየ
ሱስ፡ ኤሎሂ፡ ኤሎሂ፡ ላማ፡
ሰበቅታኒ፡ ብሎ፡ በታላቅ፡ ቃ
ል፡ ጮኸ፡ ይህም፡ አምላኪየ፡
አምላኪየ፡ ለምን፡ ተውኸኝ፡

ለምንት፡ ኀደገኒ ✚

፵፯ ወሰሚዖሙ፡ እለ፡ ይቀውሙ፡ ህየ፡ ይቤሉ፡ ኤልያስሃ፡ ይጼውዕ፡ ዝሰ።

፵፰ ወውእተ፡ ጊዜ፡ ሮጸ፡ አሐዱ፡ እምኔሆሙ፡ ወነሥአ፡ ሰፍነገ፡ ወመልዖ፡ ብሒአ፡ ወአሠረ፡ ውስተ፡ ሐለት፡ ወአሣዘዘ፤

፵፱ ወቦ፡ እለ፡ ይቤሉ፡ ኅድጉ፡ ንርአይ፡ እመ፡ ይመጽእ፡ ኤልያስ፡ ያድኅኖ ✚

፶ ወጸርሐ፡ ካዕበ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ በዐቢይ፡ ቃል፡ ወወፅአት፡ መንፈሱ ✚

፶፩ ወተሰጠ፡ መንጦላዕተ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ እምላዕሉ፡ እስከ፡ ታሕቱ፡ ወኮነ፡ ክልኤተ፤ ወአድለቅለቀት፡ ምድር፡ ወነቀዐ፡ ኰኵሐ ✚

፶፪ ወተከሥቱ፡ መቃብራት፡ ወተንሥኡ፡ ብዙኃን፡ አብድንቲሆሙ፡ ለጻድቃን ✚

፶፫ ወወፅኡ፡ እመቃብሪሆሙ፡ ወቦኡ፡ ውስተ፡ ሀገር፡ ቅድስት፡ እምድኅረ፡ ተንሥኡ፡ ወአስተርአይዎሙ፡ ለብዙኃን ✚

፶፬ ወመኰንንሰ፡ ምዕትሰ፡ ወእለ፡ ምስሌሁ፡ የዐቅብ

ማለት፡ ነው ✚ መዝ፡ ፳፩፡ ፩፡

፵፯ ከዚያ፡ የቆሙትም፡ ሕዝብ፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ ይህስ፡ ኤልያስን፡ ይጠራል፡ አሉ።

፵፰ ከእርሳቸው፡ አንዱ፡ ሩጦ፡ ሰፍነግ፡ ወሰዶ፡ መጻጻም፡ መላበትና፡ በዘንግ፡ ላይ፡ አሥሮ፡ አጠጣው ✚ ዮሐ፡ ፲፱፡ ፳፱፡ መዝ፡ ፷፰፡ ፳፩፡

፵፱ ሌሎቹ፡ ግን፡ ተወው፡ ኤልያስ፡ መጥቶ፡ ያድነው፡ እንደ፡ ሆነ፡ እንይ፡ አሉ ✚

፶ ኢየሱስም፡ ደግሞ፡ በታላቅ፡ ቃል፡ ጮኾ፡ ነፍሱንም፡ ሰጠ፡

፶፩ እነሆም፡ የቤተ፡ መቅደስ፡ መጋረጃ፡ ከላይ፡ እስከ፡ ታች፡ ከሁለት፡ ተቀደደ፡ ምድርም፡ ተናወጠች፡ ደንጎቹም፡ ተሰነጠቁ ✚ ዘፀአ፡ ፳፮፡ ፴፩ ።። ዕብ፡ ፲፡ ፲፱፡ ፳ ።።

፶፪ መቃብሮችም፡ ተከፈቱ፡ ከተኙትም፡ የቅዱሳን፡ በድኖች፡ ብዙዎች፡ ተነሡ ✚

፶፫ ከመቃብራቸውም፡ ወጡ፡ ከትንሣኤውም፡ በኋላ፡ ወደ፡ ቅድስት፡ ከተማ፡ ገብተው፡ ለብዙዎች፡ ታዩ ✚ የሐዋ፡ ፳፫፡ ፳፯ ✚

፶፬ የመቶው፡ አለቃ፡ ግን፡ ከእርሱም፡ ጋራ፡ ኢየሱስን፡ ሲጠብ

ዎ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ርእ
ዮሙ፡ ውእተ፡ ድልቅልቀ፡
ወዘከመ፡ ይከውን፡ ፍርሁ፡
ጥቀ፡ ወይቤሉ፡ አማን፡ ወል
ዱ፡ እግዚአብሔር፡ ውእቱዝ፡
፶፭ ወሀ ለዋ፡ ህየ፡ ብዙኃት፡ አን
ስት፡ እለ፡ ይሬእያ፡ እምርኁ
ቅ፡ ኮሉ፡ ዘኮነ፡ እለ፡ ተለዋሁ፡
ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ እምገ
ሊላ፡ እለ፡ ይትለአካሁ፡፡
፶፮ ወእ ማንቱ፡ ማርያም፡ መግ
ደላዊት፡ ወማርያም፡ እንተ፡
ያዕቆብ፡ ወእሙ፡ ለዮሳ፡ ወ
እሞሙ፡ ለደቂቀ፡ ዘብዴዎ
፶፯ ስ ፨ ወ መስዮ፡ መጽአ፡ ብእሲ፡
ባዕል፡ እምአርማትያስ፡ ዘ
ስሙ፡ ዮሴፍ፡ ወውእቱኒ፡ ተ
ፀምዶ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡፡

፶፰ ወሖ ረ፡ ኀበ፡ ጲላጦስ፡ ወሰአ
ሎ፡ በድኖ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱ
ስ፡ ወአዘዘ፡ ጲላጦስ፡ የሀብዎ፡

፶፱ ወ ነሥአ፡ በድኖ፡ ዮሴፍ፡ ገ
ነዞ፡ በሰንዱን፡ ንጹሕ ፨
፷ ወቀ በሮ፡ ውስተ፡ መቃብር፡
ሐዲስ፡ ዘአውቀረ፡ ውስተ፡
ኰኵሕ፡ ለርእሱ፡ ወአንኰር

ቁ፡ የነበሩ፡ መናወጡን፡ የሆ
ነውንም፡ ሁሉ፡ ባዩ፡ ጊዜ፡ እጅ
ግ፡ ፈሩ፡ በእውነትም፡ ይህ፡ የ
እግዚአብሔር፡ ልጅ፡ ነው፡
አሉ፡፡
፶፭ በዚ ያም፡ ብዙ፡ ሴቶች፡ በሩቁ፡
ያዩ፡ ነበር፡ እርሳቸውም፡ ኢ
የሱስን፡ ከገሊላ፡ የተከተሉ
ትና፡ ያገለግሉትም፡ ናቸው፡፡
ሉቃ ፳፫፡ ፬፱፡ ፫፫ ፨
፶፮ እነ ዚያውም፡ ማርያም፡ መ
ግደላዊት፡ ማርያምም፡ የ
ያዕቆብና፡ የዮሳ፡ እናት፡ የዘ
ብዴዎስም፡ የልጆቹ፡ እናት፡
፶፯ ናቸው ፨ በመ ሸም፡ ጊዜ፡ ስሙ
ን፡ ዮሴፍ፡ የሚሉት፡ ባለ፡ ጸ
ጋ፡ ሰው፡ ከአርማትያስ፡ መጣ፡
እርሱም፡ ደግሞ፡ የኢየሱስ፡
ደቀ፡ መዝሙር፡ ነበር ፨ ዮሐ፡ ፲፱
፶፰ ፴፰—፵፪፡ ዘፀአ፡ ፴፬፡ ፳፫፡፡ እር ሱም፡ ወ
ደ፡ ጲላጦስ፡ ሔዶ፡ የኢየሱስ
ን፡ ሬሳ፡ ለመነ፡ ጲላጦስም፡ ሬ
ሳውን፡ ይሰጡት፡ ዘንድ፡ አዘዘ፡፡
፶፱ ዮ ሴፍም፡ ሬሳውን፡ ወስዶ፡ በ
ንጹሕ፡ በፍታ፡ ከፈነው ፨
፷ ለራ ሱም፡ በዱንጊያ፡ ባሰነፀው፡
በአዲሱ፡ መቃብር፡ ቀበረው፡
የመቃብሩንም፡ ደጃፍ፡ ታላ

ኰረ፡ ዕብነ፡ ዓቢየ፡ ዲበ፡ ኆኅ
ተ፡ መቃብር፡ ወኀለፈ።

፷፩ ወሀለዋ፡ ህየ፡ ማርያም፡ መ
ግደላዊት፡ ወካልዕታሂ፡ ማ
ርያም፡ ይነብራ፡ ቅድመ፡ መቃ
ብር፨

፷፪ ወበሳኒታ፡ እንተ፡ ይእቲ፡ እም
ድኅረ፡ ዓርብ፡ ተጋብኡ፡ ሊቃነ፡ ካህ
ናት፡ ወፈሪሳውያን፡ ኀበ፡ ጲ
ላጦስ፨

፷፫ ወይቤልዎ፡ ተዘከርነ፡ እግዚ
እ፡ ዘይቤ፡ ዝኩ፡ መስሐቲ፡ እ
መ፡ ሕያው፡ ውእቱ፡ እመ፡ ሣል
ስት፡ ዕለት፡ እትነሣእ፨

፷፬ አዝ ዝ፡ እንከ፡ ይዕቀቡ፡ መቃ
ብረሁ፡ እስከ፡ ሠሉስ፡ መዋዕል
ከመ፡ ኢይምጽኡ፡ አርዳኢሁ፡
ወኢይስርቅዎ፡ ሌሊተ፡ ወኢ
ይበሉ፡ ለሕዝብ፡ ተንሥአ፡ እ
ምውታን፡ ወትከውን፡ ደኃሪ
ት፡ ጌጋይ፡ እንተ፡ ተአኪ፡ እም
ቀዳሚት፨

፷፭ ወይቤሎሙ፡ ጲላጦስ፡ ንሥኡ፡
ሠገራተ፡ ወሑሩ፡ ወአጽንዑ፡
በከመ፡ ተአምሩ፨

፷፮ ወሖሩ፡ ወቀተሩ፡ መቃብሮ፡
ወአጽንዕዎ፡ ወኀተምዎ፡ ለይ
እቲ፡ ዕብን፡ ምስለ፡ ሠገራት፤

ቁ፡ ደንጊያ፡ አገላብጦ፡ ገጥሞ
ት፡ ሔደ፨ [illegible]

፷፩ በዚያም፡ ማርያም፡ መግደላዊ
ት፡ ሁለተኛዪቱም፡ ማርያም፡
በመቃብሩ፡ አንጻር፡ ተቀምጠ
ው፡ ነበሩ፨

፷፪ በነገውም፡ ከዓርብ፡ በኋላ፡ በ
ሚሆን፡ ቀን፡ የካህናት፡ አለቆ
ችና፡ ፈሪሳውያን፡ ወደ፡ ጲላ
ጦስ፡ ተሰበሰቡ፨

፷፫ አሉትም፡ ጌታ፡ ሆይ፡ ያ፡ መስ
ሐቲ፡ በሕይወቱ፡ ሳለ፡ ከሦስት፡
ቀን፡ በኋላ፡ እነሣለሁ፡ ያለው
ን፡ እሰብን፨ [illegible]

፷፬ ስለ ዚህም፡ ደቀ፡ መዛሙር
ቱ፡ በሌሊት፡ መጥተው፡ እንዳ
ይሰርቁት፡ ለሕዝቡም፡ ከሙ
ታን፡ ተነሣ፡ እንዳይሉ፡ መቃብ
ሩ፡ እስከ፡ ሦስት፡ ቀን፡ እንዲጠ
በቅ፡ እዘዝ፡ የኋለኛዪቱም፡
ስሐተቱ፡ ከፊተኛይቱ፡ የከፋች
ት ሆናለች፨

፷፭ ጲላጦስም፡ ጠባቆች፡ አሏች
ሁ፡ ሒዱችሁ፡ እንደምታውቁ
መቃብሩን፡ አጽኑ፡ አላቸው።

፷፮ እርሳቸውም፡ ሒደው፡ መቃብ
ሩን፡ አጸኑ፡ ደንጊያውንም፡ አት
መው፡ ጠባቆችን፡ አስቀመጡ፨

ምዕራፍ፡ ፳፰።

ለእሑድ፡ አጥቢያ፡ ሴቶች፡ ወደ፡ መቃብሩ፡ እንደ፡ መጡ። ጌታችን፡ ከሙታን፡ እንደ፡ ተነሣ። የክህናት፡ አለቆች፡ ለዘበኞች፡ ገንዘብ፡

፩ ወሠርክ፡ ሰንበት፡ ለጸቢሐ፡ እሑድ፡ መጽአት፡ ማርያም፡ መግደላዊት፡ ወካልዕታ፡ ማርያም፡ ይርአያ፡ መቃብረ።

፪ ወናሁ፡ ኮነ፡ ድልቅልቅ፡ ዓቢይ፡ እስመ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ወረደ፡ እምሰማይ፡ ወቀርበ፡ ወአንኰርኰራ፡ ለይእቲ፡ ዕብን፡ እምአፈ፡ መቃብር፡ ወነበረ፡ ዲቤሃ።

፫ ወርእየቱ፡ ከመ፡ ዘመብረቅ፡ ወልብሱ፡ ፀዓዳ፡ ከመ፡ በረድ፡

፬ ወእምግርማሁ፡ ተሐውኩ፡ ወኮኑ፡ ከመ፡ አብድንት፡ እለ፡ የዓቅቡ፡ መቃብረ።

፭ ወአውሥአ፡ ውእቱ፡ መልአክ፡ ወይቤሎን፡ ለአንስት፡ ኢትፍርሃ፡ እንትንሰ፡ እስመ፡ አአምር፡ ከመ፡ ኢየሱስሃ፡ ዘተሰቀለ፡ ተኀሥሣ።

፮ ኢሀሎ፡ ዝየ፡ ተንሥአ፡ በከመ፡ ይቤ፡ ናዓ፡ ትርአያ፡ መካኖ፡ ኀበ፡ ተቀብረ።

ሀያ፡ ስምንት፡ ምዕራፍ።

እንደ፡ ሰጡ። የጥምቀትን፡ ሥርዓት፡ እንደ፡ አስተማረ። እስከ፡ ዓለም፡ ፍጻሜ፡ ከእናንተ፡ ጋራ፡ ነኝ፡ እንደ፡ አላቸው።

፩ በሰንበት፡ ማታ፡ ለእሑድ፡ አጥቢያ፡ ማርያም፡ መግደላዊት፡ ሁለተኛዪቱም፡ ማርያም፡ መቃብሩን፡ ሊያዩ፡ መጡ። ማር፡ ፲፮። ሉቃ፡ ፳፬። ዮሐ፡ ፳፡ ፩። ቆሮ፡ ፲፭፡ ፩፡ ፮።

፪ እነሆም፡ ታላቅ፡ መናወጥ፡ ሆኖ፡ ነበረ፡ የእግዚአብሔር፡ መልአክ፡ ከሰማይ፡ ወርዷልና፡ መጥቶም፡ ደጊያውን፡ ከመቃብሩ፡ ደጃፍ፡ ፈንቀለው፡ በላዩም፡ ተቀመጠ።

፫ መልኩም፡ እንደ፡ መብረቅ፡ ልብሱም፡ እንደ፡ በረድ፡ ነጭ፡ ነበረ።

፬ ም፡ ፲፯፡ ፪። የሐዋ፡ ፩፡ ፲። ከግርማውም፡ የተነሣ፡ ጠባቆች፡ ደንግጠው፡ እንደ፡ በድን፡ ሆኑ።

፭ መልአኩም፡ መለሰ፡ ሴቶቹንም፡ አላቸው፡ እናንተስ፡ አትፍሩ፡ የተሰቀለውን፡ ኢየሱስን፡ እንድትሹ፡ አውቃለሁና።

፮ እርሱም፡ እንደ፡ ተናገረ፡ ተነሥቶዋል፡ ከዚህ፡ ተቀብሮበት፡ የነበረውንም፡ ስፍራ፡ ታዩ፡ ዘንድ፡ ኑ፤

፯ ወፍጡነ፡ሑሩ፡ወንግራሆ
ሙ፡ለአርዳኢሁ፡ከመ፡ተን
ሥአ፡እምነ፡ምውታን፡ወና
ሁ፡ይቀድመክሙ፡ገሊላ፡ወ
በህየ፡ትሬእይዎ፡ናሁ፡አይ
ዳዕኩክን፡፡

፰ ወኅለፋ፡ፍጡነ፡እምኅ
በ፡መቃብር፡በፍርሃት፡ወ
በፍሥሐ፡ዓቢይ፡ወሮፃ፡ከ
መ፡ይንግራሆሙ፡ለአርዳኢሁ፡

፱ ወእንዘ፡የሐውራ፡ይንግራሆሙ፡
ለአርዳኢሁ፡ናሁ፡እግዚእ፡ኢ
የሱስ፡ተራከቦን፡ወይቤ፡በሀ
ክን፡ወቀርባ፡ወአኀዛ፡እገሪሁ፡
ወሰገዳ፡ሎቱ ፨

፲ ወእምዝ፡ይቤሎን፡እግዚእ፡
ኢየሱስ፡ኢትፍርሃ፡ሑራ፡ወ
ንግራሆሙ፡ለአኀውየ፡ከመ፡
ይሑሩ፡ገሊላ፡ወበህየ፡ይሬ
እዩኒ ፨

፲፩ ወኃሊፎን፡እማንቱ፡አትዉ
ሠገራት፡ሀገረ፡ወነገሩ፡ለሊ
ቃነ፡ካህናት፡ኵሎ፡ዘከመ፡ኮ
ነ፡፡

፲፪ ወተጋብኡ፡ረበናት፡ወተማ
ከሩ፡ምስለ፡ሊቃውንት፡ወወ
ሀብዎሙ፡ብዙኃ፡ወርቀ፡ለ
ሠገራት ፨

፲፫ ወይቤልዎሙ፡በ

፯ ም፡፲፪፡፵፡የሐዋ፡፪፡፴፫ ፨ ፈጥናችሁም፡
ሒዱ፡ለደቀ፡መዛሙርቱም፡
ከሙታን፡እንዲተነሣ፡ንገሯ
ቸው፡እነሆም፡ወደ፡ገሊላ፡ይ
ቀድማችኋል፡በዚያም፡ታዩታ
ላችሁ፡እነሆም፡ነገርኋችሁ፡፡

፰ ም፡፩፯፡ወ፡፱፡፡ ፈጥነውም፡ከመቃብ
ሩ፡ወጡ፡በፍርሃት፡በታላቅ፡ደ
ስታም፡ለደቀ፡መዛሙርቱ፡ይ
ነግሩ፡ዘንድ፡ሔዱ፡፡

፱ እነሆ፡ኢየሱስ፡አገኛቸውና፡
ደስ፡ይበላችሁ፡አላቸው፡እር
ሳቸውም፡ቀርበው፡እግሩን
ም፡ይዘው፡ሰገዱለት፡፡

፲ በዚያም፡ጊዜ፡ኢየሱስ፡አት
ፍሩ፡ሒዱ፡ወደ፡ገሊላ፡፡
እንዲሔዱ፡ለወንድሞቼ፡ን
ግሩ፡በዚያም፡ያዩኛል፡አላቸ
ው፡፡ ዕብ፡፪፡፲፩ ፨ ሲሔዱም፡ጊዜ፡

፲፩ ከጠባቆች፡ወገን፡ሰዎች፡ወደ፡
ከተማ፡መጥተው፡የሆነውን፡
ሁሉ፡ለካህናት፡አለቆች፡ነ
ገሩ፡፡

፲፪ እርሳቸውም፡ሽማግሌዎችን፡
ሰብስበው፡ተማክረው፡ለጭ
ሮችም፡ብዙ፡ገንዘብ፡ሰጧቸ
ው ፨

፲፫ እንዲህ፡ሲሉ፡እኛ፡ተኛ

ሉ፡አርዳኢሁ፡ሌሊተ፡መጽ
ኡ፡ወሠረቅዎ፡እንዘ፡ንነውም፡ንሕነ።

፲፬ ወእምከመ፡ተሰምዓ፡ዝንቱ፡ነገር፡በኀበ፡መልአክ፡አሐዝብ፡ንሕነ፡ናአምኖ፡ወኪያክሙኒ፡እለ፡ዘእንበለ፡ኀዘን፡ንሬስየክሙ፨

፲፭ ወነሢኦሙ፡ውእተ፡ብሩረ፡ኀለፉ፡ወገብሩ፡በከመ፡መሀርዎሙ፡ወወፅአ፡ዝነገር፡በኀበ፡አይሁድ፡እስከ፡ዮም።

፲፮ ወአርዳኢሁሰ፡ዓሠርቱ፡ወአሐዱ፡ሖሩ፡ውስተ፡ገሊላ፡ኀበ፡ደብር፡ዘአሰፈዎሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ።

፲፯ ወርእይዎ፡ወሰገዱ፡ሎቱ፡ወመንፈቆሙ፡ናፈቁ።

፲፰ ወቀርበ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወተናገሮሙ፡እንዘ፡ይብል፡ተውህበ፡ሊተ፡ኵሉ፡ሥልጣን፡ሰማይ፡ወምድር፨

፲፱ ሑሩኬ፡ወመሀሩ፡ኵሎ፡አሕዛበ፡ወእንዘ፡ታጠምቅዎሙ፡በሉ፡በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፨

፳ ወመሀርዎሙ፡ይዕቀቡ፡ኵሎ፡ዘአዘዝኩክሙ፡ወናሁ፡

ተኝ፡ሳለን፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡በሌሊት፡መጥተው፡ሠረቁት፡በሉ። ም፡፳፯፡፷፬።

፲፬ ይህም፡ወሬ፡በሹሙ፡ዘንድ፡የተሰማ፡እንደሆነ፡እንዲያምን፡እናደርገዋለን፡እናንተም፡ያለ፡ሥጋት፡እንድትሆኑ፡እናደርገዋለን።

፲፭ እነርሳቸውም፡ገንዘቡን፡ተቀብለው፡እንዳስተማርዋቸው፡አደረጉ፡ይህም፡ነገር፡እስከ፡ዛሬ፡በአይሁድ፡ዘንድ፡ሲነገር፡ይኖራል፨

፲፮ አሥራ፡አንዱ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡ግን፡ኢየሱስ፡እንዳዘዛቸው፡ወደ፡ገሊላ፡ተራራ፡ሔዱ፨

፲፯ ባዩትም፡ጊዜ፡ሰገዱለት፡እኵሌቶቹ፡ግን፡ተጠራጠሩ።

፲፰ ኢየሱስም፡ቀረበና፡የሰማይና፡የምድር፡ሥልጣን፡ተሰጠኝ፡ብሎ፡ነገራቸው፨
ም፡፲፩፡፳፯። ኤፌ፡፩፡፳፨

፲፱ እንግዲህ፡ሒዱና፡አሕዛብን፡ሁሉ፡አስተምሩ፡በአብና፡በወልድ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡እያጠመቃችሁ፨ ማር፡፲፮፡፲፭፡፲፮፨

፳ ያዘዝኋችሁንም፡ሁሉ፡እንዲጠብቁ፡አስተምሯቸው፡እነሆ

አነ፡ እሄሉ፡ ምስሌክሙ፡ በ
ኵሉ፡ መዋዕሊ፡ እስከ፡ ኅልቀ
ተ፡ ዓለም ፨ አሜን ፨

ተፈጸመ፡ ወንጌለ፡ ማቴዎስ፡

፨ ፨ ፨ ፨

ም፡ እኔ፡ እስከ፡ ዓለም፡ ፍጻ
ሜ፡ በዘመኑ፡ ሁሉ፡ ከእናን
ተ፡ ጋራ፡ ነኝ ፨ አሜን ፨ ም፳፰፡ ፳።
ዘፊቁ፡ ፲.፲፮ ፨

የማቴዎስ፡ ወንጌል፡ ተፈጸመ።

፨ ፨ ፨ ፨

ብስራቲ፡ ማርቆስ፡ ወንጌላዊ፡
አሐዱ፡ እምስብዓ፡ ወ፪ቱ፡ አርድ

፨ ፨ ፨ ፨ ፨ ፨

ስለ፡ መጥምቁ፡ ዮሐንስ፡ ስብከት፨ ስለ፡ ጊታችን፡
እንዳስተማረ፨ ምዕራፍ፡ ፩፡

፩ ቀዳሚሁ፡ ለወንጌለ፡ እግዚእን
ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ወልደ፡ እግ
ዚአብሔር፨

፪ በከመ፡ ጽሑፍ፡ ውስተ፡ ነቢያት፡ ና
ሁ፡ አነ፡ እፌኑ፡ መልአኪየ፡ ቅድመ
ገጽከ፡ ዘየጸይሕ፡ ፍኖተከ፡ በቅድ
፫ ሚከ፨ ቃለ፡ ዓዋዲ፡ ዘየሰብክ፡
በገዳም፡ ወይብል፡ ጺሕዉ፡ ፍኖ
ቶ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወዓርዩ፡

፬ መጽያሕቶ፨ ወሀሎ፡ ዮሐን
ስ፡ ያጠምቅ፡ በገዳም፡ ወይሰ
ብክ፡ ጥምቀተ፡ ለንስሐ፡ ወለ
ኅድገተ፡ ኃጢአት፨

፭ ወየሐውሩ፡ ኀቤሁ፡ ኵሉ፡ ሰብ
አ፡ ይሁዳ፡ ወኢየሩሳሌም፡ ወያ
ጠምቆሙ፡ ለኵሎሙ፡ በፈለ
ገ፡ ዮርዳኖስ፡ እንዘ፡ ይትአመኑ
ኃጢአቶሙ፨

፮ ወለብሱ፡ ለዮሐንስ፡ ፀጕረ፡ ገ

እት፡ ጸሎቱ፡ ወበረከቱ፡ የሃሉ፡ ምስ
ለ፡ ንጉሥነ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ ወምስለ፡ ን
ግሥትነ፡ ወለተ፡ ጊዮር ስ፨ ለዓ፡ አ
መጠመቁ፨ ከዲያብሎስ፡ እንዴ፡ ተፈተነ፨ በገሊላ

ምዕራፍ፡ ፩፡

የእግዚአብሔር፡ ልጅ፡ የኢየ
ሱስ፡ ክርስቶስ፡ ወንጌል፡ መ
ጀመሪያ፡ ይህ፡ ነው፨ ማቴ፡ ፫፡ ሉቃ፡ ፫፡ ዮሐ፡ ፩፡፲፱

፪ እነሆ፡ መንገድህን፡ የሚጠ
ርግ፡ መልክተኛዬን፡ በፊት
ህ፡ እልካለሁ፡ የጌታን፡ መንገ
፫ ድ፡ አዘጋጁ፡ ጥርጊያውንም
አቅኑ፡ እያለ፡ በምድረ፡ በዳ፡
የሚጮኽ፡ ድምፅ፨ ኢሳ፡ ፵፡ ፫፨

፬ ተብሎ፡ በነቢዩ፡ በኢሳይያስ፡
እንደ፡ ተጻፈ፡ ዮሐንስ፡ በምድ
ረ፡ በዳ፡ እያጠመቀ፡ የንስሐም፡
ጥምቀት፡ ለኃጢአት፡ ሥርየት፡
እየሰበከ፡ ኖረ፨

፭ የይሁዳም፡ አገር፡ ሁሉ፡ የኢ
የሩሳሌምም፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ወ
ደርሱ፡ ይወጡ፡ ነበር፡ በኃጢአ
ታቸውም፡ እየተናዘዙ፡ በዮር
ርዳኖስ፡ ወንዝ፡ በርሱ፡ ይጠመ
፮ ቁ፡ ነበር፨ ዮሐንስም፡ የግመል፡

ወሌ፡ ወቅናቱ፡ ዘዓዲም፡ ውስ
ተ፡ ሐቌሁ፡ ወሢሳዩ፡ አንበጣ፡ ወ
መዓረ፡ ፀደና፨

፯ **ወሰ**በከ፡ ወይቤ፡ ይመጽእ፡ እ
ምድኅሬየ፡ ዘይጸንእ፡ እምኔየ፡
ዘኢይደልወኒ፡ እድንን፡ ወእፍታ
፰ ሐ፡ ቶታነ፡ አሣዕኒሁ፡ እምአገሪሁ፨ **ወ**
አንሰ፡ አጠምቀክሙ፡ በማይ፡ ወ
ውእቱሰ፡ ያጠምቀክሙ፡ በመ
፱ ንፈስ፡ ቅዱስ፨ **ወይ**እተ፡ አሚረ፡
መጽአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ እም
ናዝሬት፡ ዘገሊላ፡ ወአጥመቆ፡
ዮሐንስ፡ በፈለገ፡ ዮርዳኖስ።

፲ **ወወ**ፂአ፡ እማይ፡ ርእየ፡ ተሠጥቀ፡
ሰማይ፡ ወወረደ፡ መንፈስ፡ ቅዱ
ስ፡ ከመ፡ ርግብ፡ ወነበረ፡ ዲቤ
፲፩ ሁ፨ **ወመ**ጽአ፡ ቃል፡ እምሰማይ፡
ዘይብል፡ አንተ፡ ውእቱ፡ ወልድ
የ፡ ዘአፈቅር፡ ወኪያከ፡ ሠመር
ኩ፨

፲፪ **ወአ**ውፅኦ፡ መንፈስ፡ ሶቤሃ፡ ገ
ዳመ፨

፲፫ **ወነ**በረ፡ ሐቅለ፡ ፵መዓልተ፡ ወ
፵ሌሊተ፡ ወያሜክሮ፡ ሰይጣን፡
ወነበረ፡ ምስለ፡ አራዊት፡ ወይ
ተለአክዎ፡ መላእክት፨

፲፬ **ወእ**ምድኅረ፡ እኅዝዎ፡ ወሞቅ
ሖ፡ ለዮሐንስ፡ መጽአ፡ እግ

ጠጉር፡ ለብሶ፡ በወገቡ፡ ጠፍር፡
ይታጠቅ፡ አንበጣና፡ የበረሃ፡ ማ
ርም፡ ይበላ፡ ነበር፨

፯ **ተጐ**ንብሼ፡ የጫማውን፡ ጠፍር፡
መፍታት፡ ከማይገባኝ፡ ከኔ፡ የ
ሚበረታ፡ በኋላዬ፡ ይመጣል፨

፰ **እኔ**፡ በውሀ፡ አጠመቅኋችሁ፡ እ
ርሱ፡ ግን፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ያ
ጠምቃችኋል፡ እያለ፡ ይሰብክ፡
፱ ነበር፨ **በዚ**ያ፡ ወራትም፡ ኢየሱ
ስ፡ ከገሊላ፡ ናዝሬት፡ መጥቶ፡ በ
ዮሐንስ፡ በዮርዳኖስ፡ ተጠመ
ቀ፨ ዮሐ፡ ፩፡ ፴፩፡ ፴፬። ሉቃ፡ ፫፡ ፳፩።

፲ **ወዲ**ያውም፡ ከውሀው፡ በወጣ፡
ጊዜ፡ ሰማያት፡ ሲሰነጠቁ፡ መን
ፈስም፡ እንደ፡ ርግብ፡ ሲወርድ
፲፩ በት፡ አየና፡ የምወድህ፡ ልጄ፡ እ
ንተ፡ ነህ፡ በአንተ፡ ደስ፡ ይለኛል፡
የሚል፡ ድምፅ፡ ከሰማያት፡ መ
ጣ፨ ም፡ ፱፡ ፯።

፲፪ **ወዲ**ያውም፡ መንፈስ፡ ወደ፡ ም
ድረ፡ በዳ፡ አወጣው፨

፲፫ **በም**ድረ፡ በዳም፡ ከሰይጣን፡ እየ
ተፈተነ፡ አርባ፡ ቀን፡ ኖረ፡ ከአራ
ዊትም፡ ጋር፡ ነበር፡ መላእክት
ም፡ አገለገሉት፨

፲፬ **ዮሐ**ንስም፡ አልፎ፡ ከተሰጠ፡ በኋ
ላ፡ ኢየሱስ፡ የእግዚአብሔር

ዚአ፡ ኢየሱስ፡ ገሊላ፡ ወሰበከ፡
፲፭ ወንጌለ፡ መንግሥተ፡ እግዚአ
ብሔር፨ ወይቤ፡ በጽሐ፡ ጊዜሁ፡ ወ
ቀርበት፡ መንግሥተ፡ ሰማያት፡
ነስሑ፡ ወእመኑ፡ በወንጌል፨
፲፮ ወእንዘ፡ የኀልፍ፡ መንገለ፡ ባ
ሕረ፡ ገሊላ፡ ረከቦሙ፡ ለስምዖ
ን፡ ወለእንድርያስ፡ እኁሁ፡ እ
ንዘ፡ ያሠግሩ፡ ውስተ፡ ባሕር፡
እስመ፡ መሠግራነ፡ ዓሣ፡ እሙ
፲፯ ንቱ፨ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢ
የሱስ፡ ንዑ፡ ትልዉኒ፡ ወእረስ
የክሙ፡ መሠግራነ፡ ሰብእ።
፲፰ ወኀደጉ፡ መሣግሪሆሙ፡ ወተ
ለውዎ፡ ሶቤሃ።
፲፱ ወኀሊፎ፡ ሕቀ፡ እምህየ፡ ረከቦ
ሙ፡ ለያዕቆብ፡ ወለዮሐንስ፡
እኁሁ፡ ደቂቀ፡ ዘብዴዎስ፡ ወለ
ሊሁኒ፡ ምስሌሆሙ፡ ውስተ፡ ሐ
፳ መር፡ እንዘ፡ ያስተሠንዩ፡ መሣ
ግሪሆሙ፨ ወጸውዖሙ፡ በጊዜሃ፡
ወኀደጉ፡ ዘብዴዎስሃ፡ አባሆሙ፡
ምስለ፡ አሳቡ፡ ውስተ፡ ሐመር፡
ወሖሩ፡ ወተለውዎ፨
፳፩ ወሖሩ፡ ቅፍርናሆም፡ ወቦአ፡ በ
ሰንበት፡ ምኵራበ፡ ወእኂዘ፡ ይ
ምህሮሙ፨
፳፪ ወአንከርዎ፡ ምህሮቶ፡ እስመ፡

ን፡ መንግሥት፡ ወንጌል፡ እየሰ
፲፭ በከና፨ ዘመን፡ ተፈጸመ፡ የእግዚ
አብሔርም፡ መንግሥት፡ ቀር
ባለች፡ ንስሐ፡ ግቡ፡ በወንጌል
ም፡ እመኑ፡ እያለ፡ ወደ፡ ገሊላ፡
፲፮ መጣ፨ በገሊላ ፡ ባሕር፡ አጠገ
ብም፡ ሲያልፍ፡ ስምዖንን፡ ወን
ድሙንም፡ እንድርያስን፡ አሣ፡
አጥማጆች፡ ነበሩና፡ መረባቸ
ውን፡ ወደ፡ ባሕር፡ ሲጥሉ፡ አየ፨
፲፯ ኢየሱስም፡ በኋላዬ፡ ኑና፡ ሰዎ
ችን፡ አጥማጆች፡ እንድትሆኑ፡
አደርጋችኋለሁ፡ አላቸው።
፲፰ ወዲያውም፡ መረባቸውን፡ ት
ተው፡ ተከተሉት፨
፲፱ ከዚያም፡ ጥቂት፡ እልፍ፡ ብሎ፡ የ
ዘብዴዎስን፡ ልጅ፡ ያዕቆብን፡
ወንድሙን፡ ዮሐንስን፡ እርሳ
ቸው፡ በታንኳ፡ ሳይ፡ መረባቸው
፳ ን፡ ሲያበጁ፡ አየ፨ ወዲያውም፡
ጠራቸው፡ አባታቸውንም፡ ዘብ
ዴዎስን፡ ከሞያተኞቹ፡ ጋር፡ በ
ታንኳ፡ ሳይ፡ ትተው፡ ተከተለው፡
ሔዱ፨
፳፩ ወደ፡ ቅፍርናሆምም፡ ገቡ፡ ወዲ
ያውም፡ በሰንበት፡ ወደ፡ ምኵ
ራብ፡ ገብቶ፡ አስተማረ፨ ሉቃ፡ ፬፡ ፴፩፡
፳፪ ሥልጣን፡ እንዳለው፡ ያስተምራ

ከመ፡ መኰንን፡ ይሜህሮሙ፡
ወአኮ፡ ከመ፡ ጸሐፍቶሙ።

፳፫ ወሀሎ፡ ብእሲ፡ ዘቦቱ፡ ጋኔን፡ ው
ስተ፡ ምኵራብ፡ ወአውየወ።

፳፬ ወይቤ፡ ምንትኔ፡ ብነ፡ ምስሌከ፡
ኢየሱስ፡ ናዝራዊ፡ መጻእከኑ፡
ታጥፍአነ፡ አአምረከ፡ መኑ፡ አ
ንተ፡ ኦቅዱሱ፡ ለእግዚአብሔ
ር።

፳፭ ወገሠጾ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወ
ይቤሎ፡ ተፈጸም፡ ወፃእ፡ እም
ኔሁ። ፳፮ ወአስተራገፆ፡ ውእቱ፡ ጋ
ኔን፡ እኩይ፡ ወአውየወ፡ በዓ
ቢይ፡ ቃል፡ ወወፅአ፡ እምኔሁ።

፳፯ ወደንገፁ፡ ኵሎሙ፡ ወይቤሉ፡
በበይናቲሆሙ፡ ምንትኑ፡ ዝ
ንቱ፡ ትምህርት፡ ሐዲስ፡ ዘበሥ
ልጣኑ፡ ይኤዝዞሙ፡ ለአጋን
ንት፡ ርኩሳን፡ ወይትኤዘዙ፡ ሎ
ቱ።

፳፰ ወተሰምዓ፡ ነገሩ፡ ሶቤሃ፡ በኵ
ሉ፡ በሐውርተ፡ ገሊላ።

፳፱ ወወፂኦ፡ እምኵራብ፡ ቦአ፡ ቤተ፡
ስምዖን፡ ወምስሌሁ፡ እንድር
ያስ፡ ወያዕቆብ፡ ወዮሐንስ።

፴ ወሐማቱ፡ ለስምዖን፡ ተፈጽን፡

ቸው፡ ነበር፡ እንደ፡ አንዱ፡ ጻፎች፡
አይደለምና፡ በትምህርቱ፡ ተገ
ረሙ። ፳፫ ወዲያውም፡ በምኵራብ
ርኩስ፡ መንፈስ፡ ያለው፡ ሰው፡
ሰው፡ ነበርና።

፳፬ የናዝሬቱ፡ ኢየሱስ፡ ሆይ፡ ከእ
ንተ፡ ጋር፡ ምን፡ አለን፡ ልታጠፋን፡
መጣህን፡ ማን፡ እንደ፡ ሆንህ፡ አ
ውቃለሁ፡ አንተ፡ የእግዚአብሔ
ር፡ ቅዱስ፡ ብሎ፡ ጮኸ።

፳፭ ኢየሱስም፡ ዝም፡ በል፡ ከርሱም፡
ውጣ፡ ብሎ፡ ገሠጸው።

፳፮ ርኩስ፡ መንፈስም፡ አንፈራፈረ
ውና፡ በታላቅ፡ ድምፅ፡ ጮሆ፡ ከ
ርሱ፡ ወጣ። ም፡ ፱፡ ፳፯ ።

፳፯ ሁሉም፡ ይህ፡ ምንድር፡ ነው፡ በሥ
ልጣን፡ ርኩሳን፡ መናፍስትን፡ ያ
ዝዛል፡ እርሳቸውም፡ ይታዘዙ
ለታል፡ ይህ፡ አዲስ፡ ትአምር
ት፡ ምንድነው፡ ብለው፡ እስኪ
ጠያየቁ፡ ድረስ፡ አደነቁ።

፳፰ ዝናውም፡ ወዲያው፡ በየሥፍ
ራው፡ ወደ፡ ገሊላ፡ ዙሪያ፡ ሁሉ፡ ወ
ጣ። ፳፱ ወዲያውም፡ ከምኵራብ፡ ወ
ጥቶ፡ ያዕቆብና፡ ከዮሐንስ፡ ጋር፡
ወደ፡ ስምዖንና፡ ወደ፡ እንድርያ
ስ፡ ቤት፡ ገባ። ማቴ፡ ፰፡ ፲፬፡ ፲፯ ። ሉቃ፡ ፬፡ ፴፰፡ ፵፩ ።

፴ የስምዖንም፡ አማት፡ በንዳድ፡ መ

ወነገርዎ፡ በእንቲአሃ።

፴፩ ወቀርበ፡ ኀቤሃ፡ ወአኀዛ፡ እዴሃ፡ ወአንሥኣ፡ ወኃደጋ፡ ፈፀንታ፡ ሶቤሃ፡ ወተንሥአት፡ ወተልእከቶሙ።

፴፪ ወመሰዩ፡ ጊዜ፡ የዐርብ፡ ፀሐይ፡ አምጽኡ፡ ኀቤሁ፡ ኵሎ፡ ድውያነ፡ ወእለሂ፡ አጋንንት።

፴፫ ወተጋብኡ፡ ኀቤሁ፡ ኵሉ፡ ሀገር፡ ኀበ፡ አንቀጽ።

፴፬ ወፈወሶሙ፡ ለብዙኃን፡ ድውያን፡ ወሕሙማን፡ ወአውፅኦሙ፡ ለብዙኃን፡ አጋንንት፡ ወኢያብሖሙ፡ ይንብቡ፡ እስመ፡ የአምርዎ፡ ከመ፡ ውእቱ፡ ክርስቶስ።

፴፭ ወለጽባሕ፡ ተንሥአ፡ ወአሊለየ፡ ጥቀ፡ ወወፅአ፡ ሐረ፡ ሐቅለ፡ ወጸለየ፡ በህየ።

፴፮ ወዴገንዎ፡ ስምዖን፡ ወእለ፡ ምስሌሁ።

፴፯ ወሶበ፡ ረከብዎ፡ ወይቤልዎ፡ ኵሉ፡ እንጋ፡ የኃሥሡከ።

፴፰ ወይቤሎሙ፡ ተንሥኡ፡ ንሑር፡ ካልአተኒ፡ አህጉረ፡ ከመ፡ በህየኒ፡ እስብክ፡ እስመ፡ እንበይነ፡ ዝንቱ፡ ግብር፡ መጻእኩ።

፴፱ ወሖረ፡ ወሰበከ፡ በምኵራባቲሆሙ፡ በኵሉ፡ ገሊላ፡ ወያወፅእ፡ አጋንንተ።

ንሾ፡ ቋማ፡ ተኝታ፡ ነበር፡ ስለ፡ርስዋ፡ም፡ ወዲያው፡ ነገሩት።

፴፩ ቀርቦም፡ እጅዋን፡ ይዞ፡ አነሣት፡ ንዳዱም፡ ወዲያው፡ ለቀቃትና፡ አገለገለቻቸው።

፴፪ ፀሐይም፡ ገብታ፡ በመሸ፡ ጊዜ፡ የታመሙትንና፡ አጋንንት፡ ያደረባቸውን፡ ሁሉ፡ ወደርሱ፡ አመጡ።

፴፫ ከተማይቱም፡ ሁሉ፡ በደጁ፡ ተሰብስባ፡ ነበር።

፴፬ በልዩ፡ ልዩ፡ ደዌም፡ የታመሙትን፡ ብዙዎችን፡ ፈወሰ፡ ብዙም፡ አጋንንት፡ አወጣ፡ አጋንንትም፡ አውቀውት፡ ነበረና፡ ሊናገሩ፡ አልፈቀደላቸውም። ሉቃ፡ ፬፡ ፵፩፡ ቍ፡ ፲፯፡

፴፭ ማለዳም፡ ተነሥቶ፡ ገና፡ ሌሊት፡ ሳለ፡ ወጣ፡ ወደ፡ ምድረ፡ በዳም፡ ሔዶ፡ በዚያ፡ ጸለየ።

፴፮ ስምዖንና፡ ከርሱ፡ ጋር፡ የነበሩት፡

፴፯ ገሥግሠው፡ ተከተሉት። በአገኙትም፡ ጊዜ፡ ሁሉ፡ ይፈልጉሃል፡ አሉት።

፴፰ ስለዚህም፡ ወጥቻለሁና፡ በዚያም፡ ደግሞ፡ ሊሰብክ፡ ወደ፡ ሌላ፡ ሥፍራ፡ በቅርብ፡ ወዳሉ፡ መንደሮች፡ እንሂድ፡ አላቸው።

፴፱ በምኵራባቸውም፡ እየሰበከ፡ አጋንንትንም፡ እያወጣ፡ ወደ፡ ገሊላ፡ ሁሉ፡ መጣ።

፵ ወመጽአ፡ ኀቤሁ፡ ዘለምጽ፡ ወአ
ስተብረከ፡ ወአስተብቍዖ፡
ወይቤሎ፡ እግዚኦ፡ አመሰ፡ ፡
፵፩ ፈቀድከ፡ ትክል፡ አንጽሖትየ። ወ
ምሕሮ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወ
ሰፍሐ፡ እዴሁ፡ ወገሠሦ፡ ወይቤ
፵፪ ሎ፡ እፈቅድ፡ ንጻሕ። ወዘንተ፡ ብ
ሂሎ፡ ሐደወ፡ ለምጹ፡ ሶቤሃ።
፵፫ ወገሠጾ፡ ወፈነዎ።
፵፬ ወይቤሎ፡ ዑቅ፡ ኢትንግር፡ ወ
ኢለመኑሂ፡ ዳዕሙ፡ ሑር፡ ወአ
ፍትን፡ ርእሰከ፡ ለካህን፡ ወአብ
እ፡ መባአከ፡ በእንተ፡ ዘነጻሕ
ከ፡ በከመ፡ አዘዘ፡ ሙሴ፡ ከመ፡
ይኩን፡ ስምዐ፡ ላዕሌሆሙ።
፵፭ ወወፂኦ፡ አኀዘ፡ ይስብክ፡ ወይ
ንግር፡ ብዙኀ፡ እስከ፡ ያንክሩ፡ ኵ
ሉ፡ ሀገር፡ ወስእነ፡ በዊአ፡ ሀገር፡
ክሡተ፡ አላ፡ አፍአ፡ ገዳመ፡ ይ
ብር፡ ወይመጽኡ፡ ኀቤሁ፡ እም
ከለሄ።

✤ ✤ ✤ ✤ ✤ ✤ ✤

ምዕራፍ ፡፡ ፪ ፡፡

፩ ወቦአ፡ ካዕበ፡ ሀገረ፡ ቅፍርናሆ
ም፡ እምድኅረ፡ ኍኅዳደ፡ መዋ
ዕል፡ ወሶበ፡ ተሰምዐ፡ ከመ፡ ሀ
፪ ሎ፡ ውስተ፡ ቤት። ወተጋብኡ፡ ብ
ዙኃን፡ እስከ፡ ኢያገምሮሙ፡ መ

፵ ለምጣምም፡ ወደርሱ፡ መጣ፡ ተ
ንበረከከም፡ ብትወድስ፡ ልታነ
ጻኝ፡ ትችላለህ፡ ብሎም፡ ለመነ
፵፩ ው። ኢየሱስም፡ አዘነለት፡ እጁ
ንም፡ ዘርግቶ፡ ዳሰሰውና፡ እወ
ድዳለሁ፡ ንጻ፡ አለው።
፵፪ በተናገረም፡ ጊዜ፡ ለምጡ፡ ወዲ
ያው፡ ለቀቀውና፡ ነጻ።
፵፫ ገሥጾም፡ ወዲያው፡ አወጣውና።
፵፬ ለማንም፡ አንዳች፡ እንዳትናገ
ር፡ ተጠንቀቅ፡ ነገር፡ ግን፡ ሒደህ፡
ራስህን፡ ለካህን፡ አሳይ፡ ለርሳ
ቸውም፡ ምስክር፡ እንዲሆን፡
ስለ፡ መንጻትህ፡ ሙሴ፡ ያዘዘ
ውን፡ አቅርብ፡ አለው። ዘሌዋ፡ ፲፬ ፡፡
፵፭ እርሱ፡ ግን፡ ሲወጣ፡ ብዙ፡ ሊሰ
ብክና፡ ነገሩን፡ ሊያወራ፡ ጀመ
ረና፡ ተገልጦ፡ ወደ፡ ከተማ፡ መ
ግባት፡ ወደ፡ ፊት፡ ተሳነው፡ ነገ
ር፡ ግን፡ በውጭ፡ በምድረ፡ በዳ፡
ደኖር፡ ነበር፡ ከየሥፍራውም፡
ወደርሱ፡ ይመጡ፡ ነበር። ።

ምዕራፍ ፡፡ ፪ ፡፡

፩ ከጥቂት፡ ቀን፡ በኋላ፡ ወደቅፍ
ርናሆም፡ ደግሞ፡ ገብቶ፡ በቤ
ት፡ እንዳ፡ ሆነ፡ ተሰማ።
፪ በደጅ፡ ያለው፡ ሥፍራም፡ እስ
ኪጠባቸው፡ ድረስ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡

ካን፡ ወኢኀበ፡ ኆኅት፡ ወይነግ
፫ ሮሙ፡ ቃሎ፡ ለእሉ፡ መጽኡ፡ ኀ
ቤሁ። ወአምጽኡ፡ ኀቤሁ፡ ድውየ፡
፬ መፃጕዕ፡ እንዘ፡ ይፀውርዎ፡ በዓ
ራት፡ ፬ቱ፡ ዕደው። ወሶ አኑ፡ አብ
ኦቶ፡ ኀቤሁ፡ እስመ፡ ጽፉቅ፡ ሰብ
እ፡ ነበ፡ ሀሎ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወነ
ሠቱ፡ ጠፈረ፡ ወአውረድዎ፡ ምስለ፡
፭ ዓራቱ፡ ዘዲቤሁ፡ ይሰክብ፡ ውእቱ፡ መፃጕዕ። ወ
ርእዮ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ሃይማኖቶ
ሙ፡ ይቤሎ፡ ለውእቱ፡ መፃጕዕ፡ ወ
፮ ልድየ፡ ተኃድገ፡ ለከ፡ ኃጢአትከ። ወ
ሀለዉ፡ ህየ፡ ጸሐፍት፡ ይነብሩ፡
፯ ወሀለዩ፡ በልቦሙ። ወይቤሉ፡ ም
ንትኑ፡ ዘከመዝ፡ ይነብብ፡ ፅ
ርፈተ፡ ወመኑ፡ ይክል፡ ኃዲገ፡ ኃጢ
አት፡ ዘእንበለ፡ አሐዱ፡ እግዚአ
፰ ብሔር። ወአእመሮሙ፡ እግዚ
እ፡ ኢየሱስ፡ በመንፈሱ፡ ከመ፡
ከመዝ፡ ይሔልዩ፡ ወይቤሎሙ፡
ለምንት፡ ከመዝ፡ ትሔልዩ፡ በአ
ልባቢክሙ።
፱ ምንት ትኑ፡ ይቀልል፡ አምብሂሎ
ቱ፡ ለዝመፃጕዕ፡ ተኃድገ፡ ለከ፡ ኃ
ጢአትከ፡ ወእምብሂሎቱ፡ ተንሥእ፡
፲ ወንሣእ፡ ዓራተከ፡ ወሑር፡ በእግሪከ። ወ
ከመ፡ ታእምሩ፡ ከመ፡ ብውሕ፡ ሎ
ቱ፡ ለወልደ፡ እጓለ፡ እመሕያው፡

ተሰበሰቡና፡ ቃሉን፡ ይነግራቸ
፫ ው፡ ነበር። አራ ት፡ ሰዎችም፡ የተ
ሸከሙት፡ ሽባ፤ አመጡለት።
፬ ሰሌ፡ ሕዝቡም፡ ወደርሱ፡ ማቅ
ረብ፡ ቢያቅታቸው፡ እርሱ፡ ያለ
በትን፡ የቤቱን፡ ጠፈር፡ አነሡ፡
ነድለውም፡ ሸባው፡ የተኛበትን፡
አልጋ፡ አወረዱ።
፭ ኢየ ሱስም፡ እምነታቸውን፡ አ
ይቶ፡ ሽባውን፡ አንተ፡ ልጅ፡ ኃጢ
አትህ፡ ተሠረየችልህ፡ አለው።
፮ ከጻ ፎችም፡ አንዳንዱ፡ በዚያ፡ ተ
ቀምጠው፡ ነበር፡ በልባቸውም፡
፯ ይህ፡ ሰው፡ ለምን፡ እንደዚህ፡ ይ
ናገራል፡ ይሳደባል፡ ከአንዱ፡ ከ
እግዚአብሔር፡ በቀር፡ ኃጢአ
ት፡ ሊሠርይ፡ ማን፡ ይችላል፡ ብለ
፰ ው፡ አሰቡ። ወዲ ያውም፡ ኢየሱ
ስ፡ በልባቸው፡ እንዲህ፡ እንዳ
ሰቡ፡ በመንፈሱ፡ አውቆ፡ አላቸ
ው፡ በልባችሁ፡ ይህን፡ ለምን፡ ታ
ስባላችሁ።
፱ ሽባ ውን፡ ኃጢአትህ፡ ተሠረየች
ልህ፡ ከማለት፡ ወይስ፡ ተነሣ፡ አ
ልጋህንም፡ ተሸከምና፡ ሒድ፡ ከ
፲ ማለት፡ ማናቸው፡ ይቀላል። ነገ
ር፡ ግን፡ ለሰው፡ ልጅ፡ በምድር፡
ላይ፡ ኃጢአትን፡ ሊሠርይ፡ ሥል

ከመ፡ ይኅድግ፡ ኀጢአተ፡ በዲበ፡
፲፩ ምድር። ወካዕበ፡ ይቤሎ፡ ለውእ
ቱ፡ ድውይ፡ ለከ፡ እብለከ፡ ተንሥ
እ፡ ወንሣእ፡ ዓራተከ፡ ወእቱ፡ ቤ
፲፪ ተከ። ወተንሥአ፡ ሶቤሃ፡ ወነሥአ፡
ዓራቶ፡ ወወፅአ፡ በቅድመ፡ ኵሉ፡
ወደንገፁ፡ ኵሎሙ፡ ወአእኰ
ቱዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወይቤ
ሉ፡ ግሙራ፡ ኢርኢነ፡ ዘከመዝ።
፲፫ ወእምዝ፡ ሖረ፡ ካዕበ፡ መንገለ፡ ባ
ሕር፡ ወሖሩ፡ ኀቤሁ፡ ኵሉ፡ ሕዝ
ብ፡ መመሀሮሙ።

፲፬ ወኀሊፎ፡ እምህየ፡ ርእዮ፡ ለሌ
ዊ፡ ወልደ፡ እልፍዮስ፡ እንዘ፡ ይነ
ብር፡ ኀበ፡ ምጽባሕ፡ ወይቤሎ፡
ትልወኒ፡ ወተንሥአ፡ ወተለዎ።
፲፭ ወእምዝ፡ መሰሐ፡ በቤቱ፡ እግዚ
እ፡ ኢየሱስ፡ ወብዙኃን፡ ኃጥአን፡
ወመጸብሐን፡ ረፈቁ፡ ምስለ፡ እ
ግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወአርዳኢሁ፡
ወብዙኃን፡ እሙንቱ፡ እለ፡ ተለ
፲፮ ውዎ። ወርእዮሙ፡ ጸሐፍት፡ ወ
ፈሪሳውያን፡ ከመ፡ ይበልዕ፡ ም
ስለ፡ ኃጥአን፡ ወመጸብሐን፡ ይቤ
ልዎሙ፡ ለአርዳኢሁ፡ ለምንት፡ ሊ
ቀክሙ፡ ይበልዕ፡ ወይሰቲ፡ ምስለ፡
፲፯ ኃጥአን፡ ወመጸብሐን። ወሰሚዖ፡

ጣን፡ እንዳለው፡ እንድታውቁ፡
፲፩ ዘንድ። ደግ መኛም፡ ድውዩን፡ ተ
ነሣና፡ አልጋህን፡ ተሸክመህ፡ ወደ
ቤትህ፡ ግባ፡ እልሃለሁ፡ አለው።
፲፪ ያዚን፡ ጊዜ፡ ተነሣና፡ አልጋው
ን፡ ተሸክሞ፡ በሰው፡ ሁሉ፡ ፊት፡ ወ
ጣ፡ ሰው፡ ሁሉ፡ እስኪደንቅ፡ ድ
ረስ፡ እግዚአብሔርንም፡ አመስ
ገኑ፡ እንዲህ፡ ያለ፡ ከቶ፡ አላየን
፲፫ ም። ም፡ ፩፡ ፳፯። ደግ ሞም፡ ወደ፡ ባ
ሕር፡ ዳር፡ ወጣ፡ ሰውም፡ ሁሉ፡
ወደ፡ እርሱ፡ ይመጣ፡ ነበር፡ ያስ
ተምራቸውም፡ ነበር።

፲፬ እር ሱም፡ ሲያልፍ፡ የእልፍዮ
ስን፡ ልጅ፡ ሌዊን፡ ተቀምጦ፡ ሲቀ
ርጥ፡ አየው፡ ተከተለኝም፡ አለ
ው፡ እርሱም፡ ተነሥቶ፡ ተከተ
፲፭ ለው። በቤ ቱም፡ ለምሳ፡ ተቀ
ምጦ፡ ሳለ፡ ብዙ፡ ቀራጮችና፡ ኃ
ጢአተኞች፡ ከኢየሱስና፡ ከደቀ፡
መዛሙርቱ፡ ጋራ፡ ተቀምጠው፡
ነበር፡ የተከተሉትም፡ እጅግ፡ ነ
፲፮ በሩ። ሉቃ፡ ፮፡ ፲፯። ጻፎ ችና፡ ፈሪሳው
ያንም፡ ከቀራጮችና፡ ከኃአተኞ
ች፡ ጋራ፡ ለምን፡ ይበላል፡ ይጠጣ
ልም፡ አሉዋቸው።
፲፯ ኢየ ሱስም፡ ሰምቶ፡ ሐሙማን፡
እንጂ፡ ባለጤኖች፡ ባለመድኃኒ

እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ይቤሎሙ፡
ሕሙማን፡ ይፈቅድዎ፡ ለዓቃ
ቤ፡ ሥራይ፡ ወአኮ፡ ጥዑያን፡ ኢ
መጻእኩ፡ እጸውዖ፡ ጻድቃነ፡
፲፰ አላ፡ ኃጥአነ፡ ለንስሓ። ወአርዳ
ኢሁሰ፡ ለዮሐንስ፡ ወእለሂ፡ ፈ
ሪሳውያን፡ ኮኑ፡ ይጸውሙ፡ ወ
መጽኡ፡ ወይቤልዎ፡ በእፎ፡ አ
ርዳኢሁ፡ ለዮሐንስ፡ ወአርዳኢ
ሆሙ፡ ለፈሪሳውያን፡ ይጸውሙ
ወአርዳኢከሰ፡ ኢይጸውሙ።
፲፱ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡
ይክሉኑ፡ ደቂቁ፡ ለመርዓዊ፡ ጾ
ዊመ፡ እምጣነ፡ ሀሎ፡ መርዓዊ፡
፳ ምስሌሆሙ። ወባሕቱ፡ ይበጽሕ፡
መዋዕል፡ አመ፡ ይነሥእዎ፡ ለመ
ርዓዊ፡ እምኔሆሙ፡ ወይእተ፡
፳፩ አሚረ፡ ይጸውሙ። ወአልቦ፡ ዘ
ይጠቀብ፡ ዓምደ፡ ዲርግሐ፡ ው
ስተ፡ ሰጠተ፡ ልብስ፡ ብሉይ፡ ወ
እመ፡ አኮሰ፡ ያነቅዖ፡ ጥቀበቱ፡
ሐዲስ፡ ለብሉይ፡ ወያዐብዮ፡ ለ
፳፪ ሰጠቱ። ወአልቦ፡ ዘይወዲ፡ ወይ
ነ፡ ሐዲሰ፡ ውስተ፡ ዝቅ፡ ብሉይ፡
እስመ፡ ያነቅዖ፡ ወይን፡ ሐዲስ፡
ለዝቅ፡ ብሉይ፡ ወወይኑሂ፡ ይት
ከዑ፡ ወዝቁሂ፡ ይትኀጐል፡
ወለወይንሰ፡ ሐዲስ፡ ውስተ፡ ዝ

ትን፡ አይሹትም፡ ጻድቃንን፡ ያ
ይደለ፡ ኃጥአንን፡ ወደ፡ ንስሐ፡
ልጸራ፡ መጥቻለሁና።
ም፡ ፩፡ ፲፫።
፲፰ የዮሐንስንም፡ ደቀ፡ መዛሙ
ርት፡ የፈሪሳውያንም፡ ወገን፡
ይጾሙ፡ ነበርና፡ መጥተው፡ የ
ዮሐንስና፡ የፈሪሳውያን፡ ደቀ፡
መዛሙርት፡ ለምን፡ ይጾማሉ፡
ደቀ፡ መዛሙርትህ፡ ግን፡ አይ
ጾሙም፡ አሉት።
፲፱ ኢየሱስም፡ አላቸው (ሚዜዎች)
ሙሽራው፡ ከእርሳቸው፡ ጋራ፡
ይጾሙ፡ ዘንድ፡ ይችላሉን።
፳ ነገር፡ ግን፡ ሙሽራው፡ ከእርሳ
ቸው፡ የሚለይበት፡ ዘመን፡ ይ
መጣልና፡ በዚያን፡ ጊዜ፡ ይጾማ
፳፩ ሉ። ማንም፡ ባርጌ፡ ልብስ፡ ላይ፡
አዲስ፡ እራፊ፡ የሚጥፍ፡ (የሚ
ጠቅም) የለም፡ ያለዚያ፡ ግን፡
አዲሱ፡ እራፊ፡ አሮጌውን፡
ይቀዳዋል፡ መቀደዱም፡ ታላቅ፡
፳፪ ይሆናል። አዲስ፡ ጸጅም፡ ባርጌ፡
አቁማዳ፡ (ቀርበታ) የሚያኖር፡
የለም፡ ያለዚያም፡ አዲሱ፡ ጸጅ፡
አሮጌውን፡ አቁማዳ፡ ያፈነዳዋ
ል፡ ጸጁም፡ ይፈሳል፡ አቁማዳ
ውም፡ ይበላሻል። አዲሱ፡ ጸጅ፡ ግ

ቅ፡ ሐዲስ፡ ይወድድዎ፨

፳፫ ወእምዝ፡ ካዕበ፡ ወፈረ፡ እግዚ እ፡ ኢየሱስ፡ በሰንበት፡ እንተ፡ ገ ራውህ፡ ወአርዳኢሁኒ፡ ምስሌ ሁ፡ ወአኀዙ፡ ይምሐዉ፡ ሠዊተ፡ ወይጼሑ፡ ሎቱ፡ ፍኖተ፨

፳፬ ወይቤልዎ፡ ፈሪሳውያን፡ ርኢ፡ ዘይገብሩ፡ አርዳኢክ፡ በሰንበት፡ ዘኢ ይከውን፨

፳፭ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱ ስ፡ ግሙራ፡ ኢያንበብክሙኑ፡ ዘ ገብረ፡ ዳዊት፡ አመ፡ ርኅበ፡ ውእ ቱኒ፡ ወእለ፡ ምስሌሁ፨ ፳፮ ዘከመ፡ ቦአ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፡ እንዘ፡ አብያታር፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ ወበል ዓ፡ ኅብስተ፡ መሥዋዕት፡ ዘኢይ ከውን፡ ለበሊዕ፡ ዘእንበለ፡ ለካ ካህናት፡ ለባሕቲቶሙ፡ ወወ ሀቦሙ፡ ለእለ፡ ምስሌሁ፨

፳፯ ወይቤሎሙ፡ ሰንበትሰ፡ በእንተ፡ ሰብእ፡ ተፈጥረት፡ ወአኮ፡ ሰብእ፡ በእንተ፡ ሰንበት፨
ወእግዚእ፡ ውእቱ፡ ለሰንበት፡ ወ ልደ፡ እጓለ፡ እመሕያው፨ ፨

ምዕራፍ፡ ፫።

ን፡ ባዲሱ፡ አቁማዳ፡ ይገለብጧል፡

፳፫ ከዚህ፡ በኋላ፡ ኢየሱስ፡ በሰንበ ት፡ ቀን፡ በእርሻ፡ መካከል፡ ሲሔ ድ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ በመንገድ፡ ሲያልፉ፡ እሸት፡ ይነቅሉ፡ ነበር፡ መንገዱንም፡ ያቃኑለት፡ ጀመ ር፨ ሉቃ፡ ፮፡ ፩፡ ፭። ማቴ፡ ፲፪፡ ፩፡ ፰፨

፳፬ ፈሪሳው ያንም፡ እነሆ፡ ደቀ፡ መዛሙርት ህ፡ በሰንበት፡ ማድረግ፡ የማይገ ባውን፡ ሲያደርጉ፡ አስተውል፡ አሉት፨

፳፭ እር ሱም፡ አላቸው፡ ዳዊ ት፡ በተራበ፡ ጊዜ፡ ከእርሱም፡ ጋራ፡ ያሉት፡ ያደረገውን፡ አላነበባች ሁምን፨

፳፮ አብ ያታር፡ የካህናት፡ አለቃ፡ በነበረበት፡ ወራት፡ ወደ ቤተ፡ እግዚአብሔር፡ ገብቶ፡ መ ብሉ፡ ለካህናት፡ ብቻ፡ እንጂ፡ ለ እርሱ፡ የማይገባውን፡ የመሥ ዋዕቱን፡ ኅብስት፡ እንደ፡ በላ፡ ደ ግሞ፡ ከእርሱ፡ ጋራ፡ ለነበሩት፡ እንደ፡ ሰጣቸው፨ ፩ሳሙ፡ ፳፩፡ ፮፡ ፳፪፡ ፳። ዘሌዋ፡ ፳፬፡ ፱፨

፳፯ ሰን በት፡ ስለ፡ ሰው፡ ተፈ ጠረች፡ እንጂ፡ ሰው፡ ስለ፡ ሰንበት፡ አልተፈጠረም፡ አላቸው።
የሰ ንበት፡ ጌታዋም፡ የሰው፡ ልጅ፡ ነው፨ ፨ ፨ ፨ ፨

ምዕራፍ፡ ፫።

በመስጊድ፡ እጁ፡ የሰለለችውን፡ እንዳዳነ፨ ብዙ፡ ሰ
ዎችም፡ እንደ፡ ፈወሰ፨ አሥራ፡ ሁለቱን፡ ሐዋርያት፡ እ

፩ ወቦአ፡ ካዕበ፡ ምኵራበ፡ ወሀሎ፡ ህ
የ፡ ብእሲ፡ ዘየብሰት፡ እዴሁ።

፪ ወይትዓቀብዎ፡ ለእመ፡ ይፌውሶ፡
በሰንበት፡ ከመ፡ ያስተዋድይ
፫ ዎ፨ ወይቤሎ፡ ለውእቱ፡ ብእሲ፡
ዘፅውስ፡ እዴሁ፡ ተንሥእ፡ ወቁ
፬ ም፡ ማዕከለ፨ ወይቤሎሙ፡ ይ
ከውንኑ፡ በሰንበት፡ ገቢረ፡ ሠ
ናይ፡ ኦው፡ ገቢረ፡ እኩይ፡ አሕ
ይዎ፡ ነፍስኑ፡ ወሚመ፡ ቀቲል፡
ወአርመሙ፨

፭ ወነጸርሙ፡ እንዘ፡ ይትመዓ
ዕ፡ ወይቴክዝ፡ በእንተ፡ ዑረተ፡
ልቦሙ፡ ወይቤሎ፡ ለውእቱ፡
ብእሲ፡ ስፋሕ፡ እዴከ፡ ወሰፍ
ሐ፡ እዴሁ፡ ወሐይወት፨
፮ ወወፂኦሙ፡ ፈሪሳውያን፡ ም
ስለ፡ ሰብአ፡ ሄሮድስ፡ ተማከ
ሩ፡ ከመ፡ ይቅትልዎ፨
፯ ወተግኅሠ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡
ምስለ፡ አርዳኢሁ፡ መንገለ፡
ባሕር፡ ወተለውዎ፡ ብዙኃን፡
ኖቀ፡ እምገሊላ፡ ወእምይሁ
፰ ዳ፨ ወእምኢየሩሳሌም፡ ወእ
ምኢዶምያስ፡ ወእማዕዶተ፡

ንዴ፡ መረጠ። ከሥጋ፡ ዝምድና፡ መንፈሳዊ፡ ዝምድና፡
እንዲበልጥ፨ ✤ ✤ ✤ ✤ ✤ ✤

፩ ደግሞም፡ ወደ፡ መስጊድ፡ ገባ፡ በ
ዚያም፡ እጁ፡ የሰለለ፡ ሰው፡ ነበረ።

፪ ማቴ፡ ፲፪፡ ፱፡ ፲፯። ሉቃ፡ ፮፡ ፲፯፨ በሰንበት፡
ያድነውም፡ እንደ፡ ሆነ፡ ብለው፡
፫ ሊያሳጡት፡ ይጠብቁት፡ ነበሩ፡ እ
ጁ፡ የሰለለውንም፡ ሰው፡ በመ
፬ ካከል፡ ቁም፡ አለው፨ በሰንበ
ት፡ መልካም፡ ሥራ፡ መሥራት
ይገባልን፡ ወይስ፡ ክፉ፡ ማድ
ረግ፡ ነፍስ፡ ማዳን፡ ነውን፡ ወ
ይስ፡ መግደል፡ አላቸው፡ እር
ሳቸው፡ ግን፡ ዝም፡ አሉ፨
፭ ስለ፡ ልባቸው፡ ድንዛዜ፡ አዝ
ኖ፡ ወደ፡ እርሳቸው፡ ዙሮ፡ በ
ቍጣ፡ ዓይን፡ አየ፡ ያንንም፡ ሰ
ው፡ እጅህን፡ ዘርጋ፡ አለው፤
ዘረጋትም፡ እጁም፡ ደህና፡ ሆነ
፮ ች፨ ዮሐ፡ ፲፩፡ ፶፫፨ በዚያ፡ ጊዜ፡ ፈሪሳ
ውያንም፡ መጥተው፡ ሊገድሉ
ት፡ ከሄሮድስ፡ ሰዎች፡ ጋራ፡ ተ
፯ ማከሩበት፨ ማቴ፡ ፳፪፡ ፲፯፨ ኢየሱ
ስ፡ ግን፡ ከደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ጋ
ራ፡ ወደ፡ ባሕር፡ ሔደ፡ እጅግም፡
ሰዎች፡ ከገሊላና፡ ከይሁዳ፡ ተከ
፰ ተሉት፨ ያደረገውንም፡ ሁሉ፡ በ
ሰሙ፡ ጊዜ፡ ከኢየሩሳሌም፡ ከኢ

ዮርዳኖስ፡ ወእምጢሮስ፡ ወ
እምሲዶና፡ ወብዙኃን፡ ጥቀ፡
መጽኡ፡ ኀቤሁ፡ ሰሚዖሙ፡ ኵ
፱ ሎ፡ ዘገብረ። ወይቤሎሙ፡ ለ
አርዳኢሁ፡ ያጽንሑ፡ ሎቱ፡ ሐ
መረ፡ ከመ፡ ኢይትጋፍዕዎ፡ ሰ
ብእ።
፲ እስመ፡ ለብዙኃን፡ አሕየዎ
ሙ፡ እስከ፡ ይወድቁ፡ ዲቤሁ፡
ወያስተብቍዕዎ፡ ከመ፡ ይግ
ሥሥዎ፡ ኵሎሙ፡ ሕሙማ
፲፩ ን። ወእለሂ፡ እኩያን፡ አጋንን
ት፡ ርኩሳን፡ እምከመ፡ ርእዩ
ዎ፡ ይሰግዱ፡ ሎቱ፡ ወይጸርሑ፡
እንዘ፡ ይብሉ፡ አንተ፡ ውእቱ፡
ወልደ፡ እግዚአብሔር።
፲፪ ወብዙኀ፡ ይጌሥጾሙ፡ ከመ፡
ግሁደ፡ ኢይረስይዎ።
፲፫ ወዐርገ፡ ደብረ፡ ወጸውዐ፡ እለ፡
ፈቀደ፡ ወሐሩ፡ ኀቤሁ።
፲፬ ወረሰየ፡ ዐሠርተ፡ ወክልኤተ፡
ወሰመዮሙ፡ ሐዋርያተ፡ ወ
ረሰዮሙ፡ ከመ፡ የሀልዉ፡ ም
ስሌሁ፡ ወይፈንዎሙ፡ ይስ
ብኩ።
፲፭ ወአብሐሙ፡ ያውጽኦሙ፡ አ
ጋንንተ፡ ወይፈውሱ፡ ድዉያ
፲፮ ነ። ወሰመዮ፡ ለስምዖን፡ ጴጥሮስ፡

ዱምያስም፡ ከዮርዳኖስ፡ ማ
ዶም፡ ከጢሮስና፡ ከሲዶናም፡
አጠገብ፡ እጅግ፡ ሰዎች፡ ወደ፡
፱ እርሱ፡ መጡ። ስለ፡ ሰዎቹም፡
ብዛት፡ እንዳያስጨንቁት፡ ታ
ንኳ፡ እንዲያዘጋጁለት፡ ደቀ፡
መዛሙርቱን፡ አዘዛቸው።
፲ ብዙ፡ ሰዎችን፡ ስለ፡ ፈወሰ፡ ሕመ
ም፡ ያለባቸው፡ ሁሉ፡ እርሱን፡
ለመዳሰስ፡ በላዩ፡ እስከ፡ መ
ጋፋት፡ ደርሰው፡ ነበርና።
፲፩ ርኩሳን፡ አጋንንት፡ ያደረባቸው
ም፡ ባዩት፡ ጊዜ፡ [illegible]፡ ይ
ሰግዱለት፡ ነበር፡ የእግዚአብ
ሔርም፡ ልጅ፡ አንተ፡ ነህ፡ እያሉ፡
ይጮሁ፡ ነበር። ሉቃ፡ ፬ ፵፬።
፲፪ እንዳይገልጡትም፡ እጅግ፡ [illegible]
[illegible]፡ ገሠጻቸው። ም፡ ፩፡ ፴፬
፲፫ ወደ፡ ተራራም፡ ወጥቶ፡ የወደ
ዳቸውን፡ ጠራ፡ ወደ፡ እርሱም፡
፲፬ መጡ። ማቴ፡ ፲፡ ፩፡ ሉቃ፡ ፮፡ ፲፪፡ ፲፪ ሠ
ራ፡ ሁለቱን፡ መርጦ፡ ሐዋርያ
ት፡ አላቸው፡ ሊያስተምሩም፡
ይልካቸው፡ ዘንድ፡ ከእርሱ፡
ጋራ፡ እንዲኖሩ፡ አደረጋቸው።
፲፭ ድውያንንም፡ ለመፈወስ፡ ሰ
ይጣኖትንም፡ ለማውጣት፡ ሥ
፲፮ ልጣን፡ ሰጣቸው። በየ ስማች

፲፯ ወያዕቆብ፡ ወልደ፡ ዘብዴዎስ፡ ወዮሐንስ፡ እኁሁ፡ ለያዕቆብ. ወሰመዮሙ፡ ቦአኔርጌስ፡ ዘ ቲቀ፡ ነጐድጓድ፡ ብሂል።

፲፰ ወእንድርያስ፡ ወፊልጶስ፡ ወበ ርተሎሜዎስ፡ ወማቴዎስ፡ ወ ቶማስ. ወያዕቆብ. ወልደ፡ እ ልፍዮስ፡ ወታዴዎስ፡ ወስም ዖን፡ ቀነናዊ፨

፲፱ ወይሁዳ፡ አስቆርታዊ፡ ዘአግ ብኦ፨

፳ ወበ ዊኦ፡ ቤተ፡ መጽኡ፡ ካዕበ፡ እሕዛብ፡ ብዙኃን፡ እስከ፡ ኢያበውሁ ዎ፡ይብልዕዎ ክ ለ፨

፳፩ ወሰሚዖሙ፡ አዝማዲሁ፡ መ ጽኡ፡ የአኃዝዎ፡ እስመ፡ አኀወ፡ ልቡ፡ ይቤልዎ፨ ወጸሐፍትኒ፡ እ

፳፪ ለ፡ ወረዱ፡ እምኢየሩሳሌም፡ ይቤሉ፡ ብዔል፡ ዜቡል፡ አኃዞ፡ ወበመልአኮሙ፡ ለአጋንንት፡

፳፫ ያወፅኦሙ፡ ለአጋንንት፨ ወጸ ውዖሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወመሰሎ፡ ሎሙ፡ ወይቤሎ ሙ፡ እፎ፡ ይክል፡ ሰይጣን፡ ለሰ

፳፬ ይጣን፡ አውፅኦቶ፨ ወመንግሥ ትኒ፡ ዘበበይናቲሃ፡ ትትናፈቅ፡

ው፡ ጸራቸው፡ ስምዖን፡ ጴጥሮስ፡

፲፯ አለው፨ የዘ ብዴዎስን፡ ልጅ፡ ያ ዕቆብንም፡ የያዕቆብ፡ ወንድ ም፡ ዮሐንስንም፡ ስማቸውን፡ ቦአኔርጌስ፡ አላቸው፡ የነጐድ ጓድ፡ ልጆች፡ ማለት፡ ነው፨ ሉቃ፡፲፱፡

፲፰ ፶፬፨ እን ድርያስንም፡ ፊልጶስን ም፡ በርተሎሜዎስንም፡ ማቴ ዎስንም፡ ቶማስንም፡ የእልፍ ዮስን፡ ልጅ፡ ያዕቆብንም፡ ታዴ ዎስንም፡ የቃናው፡ ስምዖንን

፲፱ ም፨ የአ ስቆሮቱ፡ ይሁዳንም፡ እርሱም፡ አሳልፎ፡ የሰጠው፨

፳ ወደ፡ ቤትም፡ በገባ፡ ጊዜ፡ እንጀ ራ፡ ለመብላት፡ስንኳ፡ እስኪሳ ነው፡ ድረስ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ ተሰ

፳፩ በሰቡ፨ ዘመዶቹም፡ በሰሙ፡ ጊ ዜ፡ ልቡ፡ ዞነጋ፡ ብሰዋሏና፡ ሊያ

፳፪ ዙት፡ መጡ፨ ከኢ ሩሳሌም፡ የ ወረዱ፡ ጻፎችም፡ ብዔል፡ ዜቡ ል፡ አለበት፡ በሰይጣናትም፡ አ ለቃ፡ ሰይጣናትን፡ ያወጣል፡ አሉ፡

፳፫ ማቴ፡፲፪፡፳፭፡፴፪፨ ሉቃ፡፲፩፡፲፭፡፳፪፨ ኢየ ሱ ስም፡ ጸርቶ፡ ሰይጣን፡ ሰይጣንን፡ ያወጣው፡ ዘንድ፡ እንዴት፡ ይ ችላል፡ ብሎ፡ በምሳሌ፡ ነገራቸ

፳፬ ው፨ መን ግሥትም፡ እርስ፡ በርሷ፡ ብ ትለያይ፡ ያች፡ መንግሥት፡ ትጸና፡

፳፭ ኢትቀውም፡ ይእቲ፡ መንግሥት ✤ ወ
ወእመኒ፡ ቤት፡ ተናፈቀት፡ በበ
ይናቲሃ፡ ኢትቀውም፡ ይእቲ፡
፳፮ ቤት ✤ ወሰይጣንሂ፡ ለእመ፡ ተን
ሥአ፡ በበይናቲሁ፡ ወተናፈቀ፡
ኢይቀውም፡ አላ፡ ማኅለቅተ፡
፳፯ ይረክብ ✤ ወአልቦ፡ ዘይክል፡ በዊ
አ፡ ቤተ፡ ኃያል፡ ወበርብሮተ፡
ንዋዩ፡ ለእመ፡ ኢቀደመ፡ አ
ሥሮቶ፡ ለውእቱ፡ ኃያል፡ ወ
እምዝ፡ ይበረብር፡ ቤቶ ✤
፳፰ አማን፡ እብለክሙ፡ ኵሉ፡ ኃ
ጢአት፡ ወፅርፈት፡ ይትኀ
ደግ፡ ለእጓለ፡ እመሕያው ✤
፳፱ ወዘሰ፡ ፀረፈ፡ ዲበ፡ መንፈስ፡
ቅዱስ፡ ኢይትኀደግ፡ ሎቱ፡
ለዓለም፡ ወይትኴነን፡ በደይ
ን፡ ለዝሉፉ ✤
፴ እስመ፡ ይቤሉ፡ ጋኔን፡ ርኩስ፡ አ
፴፩ ኀዘ ✤ ወመጽኡ፡ እሙ፡ ወአኀ
ዊሁ፡ ወቆሙ፡ አፍአ፡ ወለአኩ፡
ኀቤሁ፡ ይጸውዕዎ ✤

፴፪ ወይነብሩ፡ ሰብእ፡ ብዙኃ፡ በዓ
ውዱ፡ ወይቤልዎ፡ ነዮሙ፡ አ
ምከ፡ ወአኃዊከ፡ አፍአ፡
ይቀውሙ፡ ወየኃሥሡከ ✤
፴፫ ወአውሥአ፡ ወይቤሎሙ፡ መ

፳፭ ዘንድ፡ አትችልም ✤ ቤትም፡ እ
ርስ፡ በእርስዋ፡ ብትለያይ፡ ያ
ች፡ ቤት፡ ትጸና፡ ዘንድ፡ አትችል
፳፮ ም ✤ ሰይጣንም፡ እርስ፡ በእር
ርሱ፡ ቢጣላ፡ ቢለያይም፡ በዚሁ፡
ይፈጸማል፡ እንጂ፡ ሊጸና፡ አይ
፳፯ ችልም ✤ ማንም፡ አስቀድሞ፡ ብ
ርተውን፡ ካላሠረ፡ ወደ፡ ብርቱ፡
ቤት፡ ገብቶ፡ እቃውን፡ ይዘርፍ፡
ዘንድ፡ አይችልም፡ ከዚያ፡ ወ
ዲያም፡ በቤቱ፡ ያለውን፡ ይዘር
፳፰ ፍል ✤ በሰው፡ ልጆች፡ የሚሳደ
ቡት፡ ስድብና፡ ኃጢአት፡ ሁሉ፡
እንዲሠረይ፡ እውነት፡ እላች
፳፱ ኋለሁ ✤ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ላይ፡
የሚሳደብ፡ ግን፡ የዘለዓለም፡
ፍርድ፡ ይፈረድበታል፡ እን
ጂ፡ ሥርየት፡ የለውም ✤
፴ ርኩስ፡ መንፈስ፡ አድሮበታል፡
፴፩ ይሉ፡ ነበሩና ✤ ቀ፣ ፳፪ ✤ እናቱ፡ ወ
ንድሞቹም፡ መጥተው፡ በው
ጭ፡ ቆመው፡ ይጠሩሳቸው፡ ዘ
ንድ፡ ላኩ ✤ ማቴ፣ ፲፪፣ ፵፮፣ ሉቃ፣ ፰፣ ፲፱ ✤
፴፪ በዙሪያውም፡ ተቀምጠው፡ የ
ነበሩ፡ ሰዎች፡ እናትህና፡ ወንድ
ሞችህ፡ እነሆ፡ ፡ በውጭ፡
ቆመው፡ ይሹሃል፡ አሉት ✤
፴፫ እርሱም፡ እናቴስ፡ ማናት፡ ወን

ኍ፡ ይእቲ፡ እምየ፡ ወአኃውየ፡
፴፬ ወነጸሮሙ፡ ለእለ፡ ይነብሩ፡ ዐውዱ፡ ወይቤ፡ ነዮሙ፡ እምየኒ፡ ወአኀውየኒ።
፴፭ እስመ፡ ኵሉ፡ ዘይገብር፡ ፈቃዶ፡ ለእግዚአብሔር፡ ውእቱ፡ እኁየኒ፡ ወእኅትየኒ፡ ወእምየኒ።

ምዕራፍ ፬።

በመርከብ፡ ሆኖ፡ ለሕዝቡ፡ ሁሉ፡ በምሳሌ፡ እንዳስተማረ። ዘር፡ ተዘርቶ፡ ሳይታወቅ፡ እንዲያድ

፩ ወአኀዘ፡ ካዕበ፡ ይምሀሮሙ፡ አንተ፡ መንገለ፡ ባሕር፡ ወተጋብኡ፡ ብዙኃን፡ ሰብእ፡ ኀቤሁ፡ እስከ፡ የዐርግ፡ ውስተ፡ ሐመር፡ ወይነብር፡ ውስተ፡ ባሕር፡ ወኵሉ፡ ሰብእ፡ ውስተ፡ ምድሮሙ፡
፪ ይቀውሙ። ወመሀሮሙ፡ ወመሰለ፡ ሎሙ፡ ብዙኀ፡ ወይቤሎሙ፡ እንዘ፡ ይሜህሮሙ።
፫ ስምዑ፡ ወፈረ፡ ይዝራእ፡ ዘይዘርእ።
፬ ወእንዘ፡ ይዘርእ፡ ቦ ዘወድቀ፡ ውስተ፡ ፍኖት፡ ወመጽኡ፡ አዕዋፍ፡ ወበልዕዎ።
፭ ወቦ፡ ዘወድቀ፡ ውስተ፡ ኰኵሕ፡ ኀበ፡ አልቦ፡ መሬት፡ ብዙኀ፡ ወፍጡነ፡ በቊለ፡ እስመ፡ አል

ድሞቼስ፡ እነማናቸው፡ ብሎ፡
፴፬ መለሳቸው። በዙሪያው፡ ተቀምጠው፡ ወደነበሩትም፡ አይቶ፡ እነሆ፡ እናቴም፡ ወንድሞቼም። አለ።
፴፭ የእግዚአብሔርን፡ ፈቃድ፡ የሚያደርግ፡ ሁሉ፡ እርሱ፡ ወንድሜ፡ እኅቴም፡ እናቴም፡ ነውና።

ምዕራፍ ፬።

ጌታ። ስለ፡ ስናፍጭ፡ ምሳሌ። በመርከብ፡ ሳሉ፡ አውሎ፡ ነፋስ፡ እንደተነሣ።

፩ ደግሞም፡ በባሕር፡ ዳር፡ ያስተምር፡ ጀመር፡ ወደ፡ መርከብም፡ ገብቶ፡ በባሕር፡ እስኪቀመጥ፡ ድረስ፡ እጅግ፡ ሰዎች፡ ወደ፡ እርሱ፡ ተሰበሰቡ፤ ሰውም፡ ሁሉ፡ በባሕሩ፡ ዳር፡ በምድር፡ ላይ፡ ነበረ።
፪ ማቴ፡ ፲፫፡ ፩፡ ፴፫። ሉቃ፡ ፰፡ ፬፡ ፲፭። ብዙ፡ ምሳሌም፡ መስሎ፡ ያስተምራቸው፡ ነበረ፤ ሲያስተምራቸውም፡ እንዲህ፡ አላቸው።
፫ ስሙ፡ እነሆ፡ ዘሪ፡ ይዘራ፡ ዘንድ፡ ወጣ።
፬ እርሱም፡ ሲዘራ፡ ከዘሩ፡ አንዳንዱ፡ በመንገድ፡ የወደቀ፡ አለ፡ የሰማይም፡ ወፎች፡ መጥተው፡ በሉት።
፭ እጅግም፡ መሬት፡ በሌለበት፡ በጭንጫ፡ ላይ፡ የወደቀ፡ አለ፡ ፈጥኖም፡ በቀለ፡ ለመሬቱ፡ ጥልቀት

፮ ቦ፡ ዕመቀ፡ ለመሬቱ። ወሠረቀ፡
ፀሐይ፡ አውዐዮ፡ እስመ፡ ኢኮነ፡
ዕሙቀ፡ መሬቱ፡ ወአልቦ፡ ሥር
ው፡ የብሰ።
፯ ወቦ ዘወድቀ፡ ውስ
ተ፡ ሦክ፡ ወሐነቆ፡ ሦክ፡ ወኢፈ
ረየ።
፰ ወቦ፡ ዘወድቀ፡ ውስተ፡ ምድር፡
ሠናይት፡ ወበቊለ፡ ወልህቀ፡ ወ
ፈረየ፡ ወወሀበ፡ ፍሬ፡ ቦ፡ ዘሠላ
ሳ፡ ወቦ፡ ዘስሳ፡ ወቦ፡ ዘምዕት።
፱ ወ
ይቤ፡ ዘቦ፡ እዝን፡ ሰሚዐ፡ ለይስ
ማዕ።
፲ ወሶበ፡ ተባሕተወ፡ ተስእ
ልዎ፡ እለ፡ ኮኑ፡ ምስሌሁ፡ ምስ
ለ፡ ፲ቱ፡ ወ፪ቱ፡ አርዳኢሁ፡ ም
ሳሌሁ።
፲፩ ወይቤሎሙ፡ ለክሙ፡
ተውህበ፡ ታእምሩ፡ ምሥጢራ፡
ለመንግሥተ፡ እግዚአብሔር፡
ወለእለሰ፡ በአፍአ፡ ምሳሌ፡ ይ
ከውኖሙ፡ ኵሉ።
፲፪ ከመ፡ ርእየ፡ ይርአዩ፡ ወኢያእ
ምሩ፡ ወሰሚዐ፡ ይስምዑ፡ ወ
ኢይለብዉ፡ ከመ፡ ኢይነስሑ፡
ወኢይሣሃሎሙ፡ ወኢይትኃ
ደግ፡ ሎሙ፡ ኃጢአቶሙ።
፲፫ ወይቤሎሙ፡ ኢታእምሩኑ፡ ዘ
ንተ፡ ምሳሌ፡ እፎኑመ፡ እንከ፡ ተ
አምሩ፡ ኵሉ፡ አምሳለ።

፮ ነት፡ የለውምና። ፀሐይም፡ በ
ወጣች፡ ጊዜ፡ ተቃጠለ፡ ሥርም፡
ባይኖረው፡ ደረቀ፡ መሬቱ፡ ጥል
ቅ፡ አይደለምና።
፯ በእሾህ፡ ላይ፡
ም፡ የወደቀ፡ አለ፡ እሾህም፡ ወ
ጥቶ፡ አነቀውና፡ አላፈራም።
፰ በመልካም፡ መሬትም፡ የወደቀ፡
አለ፡ በቀለ፡ አደገም፡ አንዱም፡
ሠላሳ፡ ሌላው፡ ስሳ፡ ሌላውም፡
መቶ፡ ፍሬ፡ ሰጠ።
፱ የሚሰማ፡ ጆ
ሮ፡ ያለውም፡ ይስማ፡ አላቸው።
፲ ብቻውንም፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ በዙሪያ
ው፡ የነበሩት፡ ከአሥራ፡ ሁለቱ፡
ጋራ፡ ምሳሌውን፡ ጠየቁት።
፲፩ አላቸውም፡ ለእናንተ ፡ የእግ
ዚአብሔርን፡ መንግሥት፡ ም
ሥጢር፡ ማወቅ፡ ተሰጥዋችኋ
ል፡ በውጭ፡ ላሉት፡ ግን፡ ነገር፡ ሁ
ሉ፡ በምሳሌ፡ ይሆንባቸዋል።
፲፪ ፩፡ቆር፡፫፡፲፪። ማየትን፡ እያዩ፡ እንዳ
ይመለከቱ፡ መስማትንም፡ እየ
ሰሙ፡ እንዳያስተውሉ፡ እንዳ
ይመለሱም፡ ይቅርም፡ እንዳይ
ላቸው፡ ኃጢአታቸውም፡ እን
ዳይሠረይላቸው። ኢሳ፡፮፡፱፡፲።
፲፫ አላ ፡ ፡ ቸውም፡ ይህን፡ ምሳሌ፡
አላወቃችሁምን፡ እንዴትስ፡

፲፬ ወዘራኢሰ፡ ውእቱ፡ ዘይዘርዕ፡
፲፭ ቃለ፡ እግዚአብሔር። ወእሉ፡ እ
ሙንቱ፡ እለ፡ ውስተ፡ ፍኖት፡ ኀ
በ፡ ተዘርአ፡ ቃል፡ ወእምከመ፡
ሰምዑ፡ ቃለ፡ ይመጽእ፡ ሰይጣ
ን፡ ሶቤሃ፡ ወይነሥእ፡ እምአል
፲፮ ባቢሆሙ፡ ቃለ፡ ዘተዘርዓ። ወ
እሉ፡ ካዕበ፡ እሙንቱ፡ ዘውስተ፡
ኰኵሕ፡ ተዘርኡ፡ እለ፡ ይሰም
፲፯ ዑ፡ ቃለ፡ ወይትዌከፍዎ፡ በፍሥሐ
ሶቤሃ። ወአልቦሙ፡ ሥርወ፡ ለ
ጊዜሃ፡ ዲዕሙ፡ እሙንቱ፡ ወእ
ምከመሰ፡ ኮነ፡ ምንዳቤ፡ ወስ
ዴት፡ በእንተዝ፡ ቃል፡ የዓልዉ፡
፲፰ ሶቤሃ። ወእሉ፡ እሙንቱ፡ እለ፡
ውስተ፡ ሦክ፡ ተዘርኡ፡ እለ፡ ይ
፲፱ ሰምዕዎ፡ ለቃል። ወሐሊና፡ ዝን
ቱ፡ ዓለም፡ ወፍትወተ፡ ብዕል፡
ወባዕድኒ፡ ኵሉ፡ ፍትወት፡ ይ
በውእ፡ ወየኀንቅዎ፡ ለቃል፡
፳ ወኢይፈሪ። ወእሉ፡ እሙን
ቱ፡ እለ፡ ውስተ፡ ምድር፡ ሠናይ
ት፡ ተዘርኡ፡ እለ፡ ይሰምዑ፡ ቃ
ለ፡ ወይትዌከፍዎ፡ ወይፈርዩ፡
አሐዱ፡ በሠላሳ፡ ወአሐዱ፡ በስ
ሳ፡ ወአሐዱ፡ በምዕት።
፳፩ ወይቤሎሙ፡ ቦኑ፡ ዘያኅትዉ፡

ምሳሌውን፡ ሁሉ፡ ታውቃ
፲፬ ላችሁ። ዘሪው፡ ቃሉን፡ የሚዘ
፲፭ ራው፡ ነው። ቃልም፡ በተዘራበ
ት፡ በመንገድ፡ ያሉ፡ እነዚህ፡ ና
ቸው፡ ቃሉን፡ ከሰሙ፡ በኋላ፡ ሰ
ይጣን፡ ፈጥኖ፡ ይመጣል፡ በልባ
ቸውም፡ የተዘራውን፡ ቃል፡ ይ
፲፮ ወስዳል። እንዲሁም፡ በጭን
ጫ፡ ላይ፡ የተዘሩት፡ ቃሉን፡ ሰ
ምተው፡ ለጊዜው፡ በደስታ፡ የ
፲፯ ሚቀበሉት፡ ናቸው። ግን ለጊዜ
ው፡ ናቸው፡ እንጂ፡ ሥር፡ የላቸ
ውም፡ ስለዚህም፡ ቃል፡ መከ
ራ፡ ወይም፡ ስደት፡ በሆነ፡ ጊዜ፡ የ
ን፡ ጊዜውን፡ ይሰነካከላሉ።
፲፰ በእሾህም፡ ላይ፡ የተዘሩ፡ እነ
ዚህ፡ ናቸው፡ ቃሉን፡ የሚሰሙ፡
፲፱ የዚህም፡ ዓለም፡ አሳብና፡ የባ
ለጠግነት፡ መታለል፡ ሌላው
ንም፡ ነገር፡ መመኘት፡ ገብተ
ው፡ ቃሉን፡ ይንቁታል፡ ያለ፡ ፍ
ሬም፡ ይቀራል። ም፡ ፲፡ ፳፫።
፳ በመልካም፡ ምድርም፡ የተዘ
ሩ፡ እነዚህ፡ ናቸው፡ ቃሉን፡ የ
ሚሰሙ፡ የሚቀበሉትም፡ ፍሬ
ም፡ ያደርጋሉ፡ አንዱ፡ ሠላሳ፡
ሌላውም፡ ስድሳ፡ ሌላውም፡
፳፩ መቶ። ደሳቸውም፡ ነበር፡ በ

ማኅቶት፡ወያመጽእዋ፡ከመ፡ያንብርዋ፡ታሕተ፡ከፈር፡አው፡ታሕተ፡ዓራት፡አኮኑ፡አላ፡ዮንብርዋ፡ዲበ፡ተቅዋማ።

፳፪ አልቦ፡ኅቡዕ፡ዘይትከበት፡ወአልቦ፡ክዱን፡ዘኢይትከሠት።

፳፫ ወዘቦ፡እዝን፡ሰሚዐ፡ለይስማዕ።

፳፬ ወይቤሎሙ፡ለብዉ፡ዘትሰምዑ፡በዉእቱ፡መሥፈርት፡ዘሰፈርክሙ፡ይሰፍሩ፡ለክሙ፡ወይዌስኩክሙ።

፳፭ እስመ፡ለዘቦ፡ይሁብዎ፡ወይዌስክዎ፡ወለዘሰ፡አልቦ፡እለሂቦ፡የሀይድዎ።

፳፮ ወይቤሎሙ፡ከመዝ፡ይእቲ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡ከመ፡ብእሲ፡ዘዘርአ፡ዘርአ፡ውስተ፡ገራህቱ።

፳፯ ወነዊሞ፡ይትነሣእ፡መዓልተ፡ወሌሊተ፡ወይዋሕዩ፡ወዘርኡ፡ይፈሪ፡ወይልህቅ፡ወውእቱሰ፡ኢየአምር።

፳፰ ወባሕቲታ፡ምድር፡ትሁብ፡ፍሬሃ፡ቀዳሚ፡ሣዕረ፡ወእምዝ፡ሰብለ፡ወእምዝ፡ፍጹመ፡ሥርናየ፡ውስተ፡ሰብሉ።

፳፱ ወእምዝ፡ፈጺመ፡ፈርየ፡ሶቤሃ፡ይፌኑ፡ማዕፀደ፡እስመ፡

ውኑ፡ከዕንቅብ፡ወይም፡ከአልጋ፡በታች፡ለማኖር፡መብራት፡ያበራሉን፡በመቅረዙ፡ላይ፡እንዲያስቀምጧት፡አይደለምን። ማቴ፡፭፡፲፭፡ ሉቃ፡፰፡፲፮፡፲፫።

፳፪ ሳይገለጥ፡ተሠውሮ፡የሚቀር፡የለምና፡ሳይገለጥ፡ተሸፍኖ፡የሚኖር፡የለምና። ማቴ፡፲፡፳፮፡ ሉቃ፡፲፪፡፪።

፳፫ የሚሰማ፡ጆሮም፡ያለው፡ይስማ።

፳፬ አላቸውም፡የምትሰሙትን፡አስተውሉ፡በምትሰፍሩበት፡መስፈሪያ፡ይሰፍሩላችኋል፡ይጨምሩላችኋልም። ማቴ፡፲፫፡፲፪።

፳፭ ላለው፡ይጨምሩለታልና፡የሌለውንግን፡ያንኑ፡ያለውን፡ቀሉ፡ይወስዱበታል። ማቴ፡፲፫፡፲፪።

፳፮ አላቸውም፡የእግዚአብሔር፡መንግሥት፡በምድር፡ላይ፡ዘርን፡እንደ፡ዘራ፡ሰው፡እንዲሁ፡ናት።

፳፯ ሌሊትና፡ቀን፡ይተኛልም፡ይነሣልም፡ዘሩም፡ይበቅላል፡እርሱም፡ሳያውቀው፡ያድጋል። ያዕ፡፭፡፯።

፳፰ ምድርቱም፡ከእርስዋ፡ፍሬ፡ታመጣለች፡በመጀመሪያ፡ቡቃያ፡ኋላም፡ዛላ፡ኋላም፡በዛላው፡ላይ፡ፍጹም፡ስንዴ።

፳፱ ፈጽሞም፡ካፈራ፡በኋላ፡መከር፡ደርሷልና፡ያን፡ጊዜ፡ማጭድ፡ይሰዳል።

፴ በጽሐ፡ ማዕረር። ወይቤ፡ በምን
ቱ፡ እስተማስላ፡ ለመንግሥተ፡
እግዚአብሔር፡ ወምንተ፡ ትመ
፴፩ ስሌ። ከመ፡ ሓጠተ፡ ሰናፔ፡ እንተ፡
ተዘርአት፡ ውስተ፡ ምድር፡ ወ
ትንዕስ፡ እምኵሉ፡ አዝርእት፡
ዘውስተ፡ ምድር።
፴፪ ወእምከመ፡ ዘርእዋ፡ ትበቊል፡
ወተዓቢ፡ እምኵሎን፡ አሕማ
ላት፡ ወትገብር፡ አዕፁቀ፡ ዓበ
ይተ፡ እስከ፡ ይክሉ፡ አዕዋፈ፡ ሰ
ማይ፡ አጽልሎ፡ ውስተ፡ አዕፁ
ቂሃ።
፴፫ ወበ ዘከመዝ፡ አምሳል፡ ተናገ
ሮሙ፡ ቃሎ፡ በአምጣነ፡ ይክሉ፡
ሰሚዐ።
፴፬ ወዘ እንበለ፡ ምሳሌስ፡ ኢተናገ
ሮሙ፡ ወበባሕቲቶሙ፡ ይፌ
ክር፡ ለአርዳኢሁ፡ ኵሎ።
፴፭ ወይእቲ፡ አሚረ፡ መስዩ፡ ይቤ
ሎሙ፡ ለአርዳኢሁ፡ ንዕዱ፡ ማ
፴፮ ዕዶተ። ወኀደጎሙ፡ ለሕዝብ፡ ወ
ነሥእዎ፡ በሐመር፡ ወቦ፡ ካልእ
ትኒ፡ አሕማር፡ ምስሌሆሙ።
፴፯ ወመጽአ፡ ዓውሎ፡ ዓቢይ፡ ነፋ
ስ፡ ወደሠወጥ፡ ማይ፡ እሞገድ፡

፴ እለም፡ የእግዚአብሔር፡ መን
ግሥት፡ ማንን፡ ትመስላለች፡ ወ
ደስ፡ በምን፡ ምሳሌ፡ እንመስላ
፴፩ ታለን። ማቴ፡ ፲፫፡ ፴፩፡ ፴፪። ሉቃ፡ ፲፫፡ ፲፰፡ ፲፱፡ እ
ንደ፡ ሰናፍጭ፡ ቅንጣት፡ ናት። እር
ስዋም፡ በምድር፡ ሳይ፡ በተዘራ
ች፡ ጊዜ፡ በምድር፡ ሳይ፡ ካለ፡ ዘር፡
፴፪ ሁሉ፡ ታንሳለች። በተዘራችም፡
ጊዜ፡ ትበቅላለች፡ ከአትክልት
ም፡ ሁሉ፡ የምትበልጥ፡ ትሆናለች፡
ታላላቅ፡ ጫፎችም፡ ታወጣለች፡
የሰማይ፡ ወፎች፡ በጥላዋ፡ በታች፡
መጠጋት፡ እስኪቻላቸው፡ ድረ
፴፫ ስ። መስማቱንም፡ በሚችሉበት፡
መጠን፡ እንደዚህ፡ በሚመስል፡
በብዙ፡ ምሳሌ፡ ቃሉን፡ ይነግራቸ
፴፬ ው፡ ነበር። ያለ፡ ምሳሌ፡ ግን፡ አል
ነገራቸውም፡ ደቀ፡ መዛሙርቱ
ም፡ ለብቻቸው፡ ሳሉ፡ ነገሩ፡ ሁ
ሉ፡ ይተረጕምላቸው፡ ነበረ።
፴፭ በዚ ያም፡ ቀን፡ በመሸ፡ ጊዜ፡ ወ
ደ፡ ማዶ፡ እንሒድ፡ አላቸው። ማ
፴፮ ቴ፡ ፰፡ ፲፰፡ ፳፫፡ ፳፯። ሉቃ፡ ፰፡ ፳፪፡ ፳፭። ሰውን
ም፡ አሰናብቶ፡ በዚያው፡ በታን
ኳ፡ እንደ፡ ነበረ፡ ወሰዱት፡ ደግ
ሞም፡ ሌላዎች፡ ታንኳዎች፡ ከእ
፴፯ ርሳቸው፡ ጋራ፡ ነበሩ። ታላቅም፡
ዓውሎ፡ ነፋስ፡ መጣ፡ ከማዕበ

ውስተ፡ ሐመር፡ እስከ፡ መልአ፡
ማይ፡ ውስተ፡ ሐመር።

፴፰ ወወእቱሰ፡ መንገለ፡ ከዋላ፡ ሐ
መር፡ ተተርኢሶ፡ ኖመ፡ ወአንቅ
ሕዎ፡ ወይቤልዎ፡ ሊቅ፡ ኢያሐዝነ
ከኑ፡ እንዘ፡ ንመውት። ፴፱ ወተንሥአ፡
ወገሠጾሙ፡ ለነፋሳት፡ ወይቤ
ላ፡ ለባሕር፡ ተፈፀሚ፡ ወአ
ርምሚ፡ ወኀደገ፡ ነፋስ፡ ወኮነ፡
ዛኅነ፡ ዓቢይ።

፵ ወይቤሎሙ፡ ምንትኑ፡ ያፈር
ሃክሙ፡ ኦድኩማን፡ ከመ፡ ዝኑ፡
አልብክሙ፡ ሃይማኖት።

፵፩ ወፈርሁ፡ ዓቢየ፡ ፍርሃተ፡ ወተ
በሀሉ፡ በበይናቲሆሙ፡ መኑ፡ እን
ጋ፡ ውእቱ፡ ዝንቱ፡ ዘይትኤዘዙ፡
ሎቱ፡ ባሕርኒ፡ ወነፋሳትኒ። ።

ምዕራፍ ። ፭ ።

በጌርጌሴኖን፡ ርኩስ፡ መንፈስ፡ ያደረበትን፡ እን
ጸጸነ፨ ስለ፡ ኢያኢሮስን፡ ደም፡ ስለሚፈሳት፡

፩ ወበጽሑ፡ ማዕዶተ፡ ባሕር፡ ኀ
በ፡ ብሔረ፡ ጌርጌሴኖን።

፪ ወወሪዶ፡ እምሐመር፡ ተቀበሎ፡
ሶቤሃ፡ ብእሲ፡ ዘእኩይ፡ ጋኔን፡
ሳዕሌሁ፡ ወፂኦ፡ እመቃብር።

፫ ወይነብር፡ ውስተ፡ መቃብር፡
ወሰእንዎ፡ አጽንዖቶ፡ በመዋቅ

ሉም፡ የተነሣ፡ ውኃ፡ ወደ፡ መር
ከብ፡ ይገለበጥ፡ ነበረ፡ ውኃው፡
በታንኳ፡ እስኪመላ፡ ድረስ።

፴፰ እርሱም፡ በስተኋላ፡ ተንተርሶ፡
ተኝቶ፡ ነበረ፡ እርሳቸውም፡ አን
ቅተው፡ (አስነሥተው፡ መም
ሕር፡ ሆይ፡ ስንጠፋ፡ አያሳዝን
ህምን፡ አሉት። ፴፱ ተነሥቶም፡
ነፋሱን፡ ገሠጸ፡ ባሕሩንም፡ ጸ
ጥ፡ በል፡ አለው። ነፋሱም፡ ዝ
ም፡ አለ፡ ታላቅም፡ ጸጥታ፡ ሆነ።

፵ እናንተ፡ ደካሞች፡ ለምን፡ ትፈ
ራላችሁ፡ እንዴ፡ ህስ፡ እምነት፡
የላችሁምን፡ አላቸው።

፵፩ ታላቅ፡ ፍርሃትም፡ ፈሩ፡ እር
ስ፡ በርሳቸውም፡ ባሕርም፡ ነ
ፋስም፡ የሚታዘዝለት፡ ይህ፡
ማነው፡ ተባባሉ።

ምዕራፍ ። ፭ ።

ሴት፨ የኢያኢሮስን፡ ልጅ፡ እንደ፡ አስነሣ፨

፩ ወደ፡ ባሕር፡ ማዶም፡ ወደ፡ ጌር
ጌሴኖን፡ አገር፡ መጡ። ማቴ፡ ፰፡

፪ ፳፰፡ ፴፬፡ ሉቃ፡ ፰፡ ፳፮፡ ፴፱፡ ከመርከብ
ም፡ በወጣ፡ ጊዜ፡ ርኩስ፡ መንፈስ፡
የያዘው፡ አንድ፡ ሰው፡ ከመቃብር፡

፫ ወጥቶ፡ ፈጥኖ፡ ተገናኘው። መኖ
ሪያውም፡ በመቃብር፡ ነበረ፡ ማ

ሐቱኒ፡ እንዘ፡ ዘሌፈ፡ ይሞቅሕ
ዎ፡ ወአልቦ፡ ዘይክል፡ አድክሞ
፬ ቶ። እስመ፡ መዋቅሕቲኒ፡ ይሰ
ብር፡ ወሰናስሌኒ፡ ይቀጠቅጥ።

፭ ወዘልፈ፡ የዓውድ፡ መዓልተ፡
ወሌሊተ፡ በውስተ፡ መቃብር፡
ወበውስተ፡ አድባር፡ እንዘ፡ የ
ዐወዩ፡ ወይጌምድ፡ ሥጋሁ፡ በ
፮ ዕብን። ወሶበ፡ ርእዮ፡ ለእግዚእ፡
ኢየሱስ፡ እምርሑቅ፡ ሮፀ፡ ወ
፯ ሰገደ፡ ሎቱ። ወጸርሐ፡ በዓቢ
ይ፡ ቃል፡ ወይቤ፡ ምንት፡ ብየ፡
ምስሌከ፡ ኢየሱስ፡ ወልደ፡ እ
ግዚአብሔር፡ ልዑል፡ አምህ
ከ፡ በእግዚአብሔር፡ ከመ፡ ኢ
ትሣቅየኒ።
፰ እስመ፡ ይቤሎ፡ ለውእቱ፡ ጋኔ
ን፡ እኩይ፡ ፃዕ፡ እምላዕሌሁ።
፱ ወተስእሎ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡
ወይቤሎ፡ መኑ፡ ስምከ፡ ወይ
ቤሎ፡ ውእቱ፡ ጋኔን፡ ሌጌዎን፡ ስ
፲ ምየ፡ እስመ፡ ብዙኃን፡ ንሕነ። ወአ
ስተብቍዖ፡ ብዙኃ፡ ከመ፡ ኢይስ
፲፩ ድዶሙ፡ አፍአ፡ እምብሔር። ወ
ቦ፡ ህየ፡ መራዕየ፡ አሓርው፡ ብ
ዙኅ፡ ዘይትረዐይ፡ መንገለ፡ ደብ

ንም፡ በሰንሰለት፡ ያሥረው፡ ዘን
ድ፡ ስንኳ፡ አይችልም፡ ነበር።
፬ ብዙ፡ ጊዜም፡ በእግር፡ ብረት፡ ሲያ
ሥሩት፡ ማፅናቱ፡ ተሳናቸው፡ የ
ሚችለውም፡ አልነበረም፡ ሰን
ሰለቱንም፡ ይበጥስ፡ እግር፡ ብረ
፭ ቱንም፡ ይሰብር፡ ነበርና። ሁሌ፡ ጊ
ዜም፡ ሌሊትና፡ ቀን፡ በመቃብር
ና፡ በተራራ፡ እየጮኸ፡ ይዞር፡ ነ
በር፡ ሰውነቱንም፡ በብልጭት፡
፮ ይተፈትፍ፡ ነበር። ኢየሱስንም፡
ከሩቅ፡ ባየው፡ ጊዜ፡ ሩጦ፡ ሰገ
፯ ደለት። በታላቅ፡ ድምፅም፡ እ
የጮኸ፡ የልዑል፡ የእግዚአብ
ሔር፡ ልጅ፡ ኢየሱስ፡ ሆይ፡ እኔ፡
ከአንተ፡ ጋራ፡ ምን፡ አለኝ፡ እን
ዳትሣቅየኝ፡ በእግዚአብሔር፡
እምልሃለሁ፡ አለው። ማቴ፡ ፰፡ ፳፱።
፰ እንተ፡ ርኩስ፡ መንፈስ፡ ከዚህ፡
ሰው፡ ውጣ፡ ይለው፡ ነበርና።
፱ ኢየሱስም፡ ስምህ፡ ማነው፡ ብ
ሎ፡ ጠየቀው፡ ጋኔኑም፡ መለሶ፡
ብዙ፡ ነንና፡ ስሜ፡ ሌጌዎን፡ ነ
፲ ው፡ አለው። ከሀገርም፡ ወደ፡
ውጭ፡ እንዳይሰደው፡ አጥብ
፲፩ ቆ፡ ለመነው። በዚያም፡ በተራ
ራው፡ ጥግ፡ ብዙ፡ የእሪያ፡ መን
ጋ፡ ይሰማራ፡ ነበር።

፲፪ ር፨ወአስተብቍዕዎ፡ ኵሉ፡ አ
ጋንንት፡ ወይቤልዎ፡ ፈንወነ፡
ውስተ፡ አኅርው፡ ከመ፡ ንባእ፡ ላ
፲፫ ዕሌሆሙ፨ወአብሖሙ፡ እግዚ
እ፡ ኢየሱስ፡ ወወፂኦሙ፡ እሙ
ንቱ፡ አጋንንት፡ ቦኡ፡ ላዕለ፡ አ
ኅርው፡ ወአብደ፡ እሙንቱ፡
መራዕይ፡ ወጸድፉ፡ ውስተ፡
ባሕር፡ ወኮኑ፡ መጠነ፡ እስራ፡
፲፬ ምዕት፡ ወሞቱበውስተ፡ ባሕር፨ወ
ጕዩ፡ ኖሎት፡ ወዜነዉ፡ ለአህ
ጉር፡ ወለአዕፃዳት፡ ወወፅኡ፡
፲፭ ከመ፡ ይርአዩ፡ ዘኮነ፨ወመጽኡ፡
ኀበ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወረከ
ብዎ፡ ለጋኔን፡ እኁዘ፡ እንዘ፡ ይነ
ብር፡ ወልቡሲ፡ ገብአ፡ ወልቡ
፲፮ ሰ፡ ልብሶ፡ ዝኩ፡ ዘአኀዞ፡ ሌጌዎን፨ወዜነ
ውዎሙ፡ ፡ እለ፡ ርእዩ፡ በከ
መ፡ ኮነ፡ ዘጋኔን፡ ወዘበእንተ፡
አኅርው፨
፲፯ ወአኀዙ፡ ያስተብቍዕዎ፡ ከመ፡
ይፃእ፡ እምደወሎሙ።
፲፰ ወዓረገ፡ ሐመረ፡ ወአስተብቍ
ዕዎ፡ ውእቱ፡ ዘጋኔን፡ ይሑር፡
ምስሌሁ፨
፲፱ ወከልኦ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወ
ይቤሎ፡ ሑር፡ ቤተከ፡ ኀበ፡ አ
ሊአከ፡ ወንግር፡ ኵሎ፡ ዘገብ

፲፪ ሰይጣናትም፡ ሁሉ፡ ወደ፡ እሪ
ዎቹ፡ እንገባባቸው ዘንድ፡ ስደዱን፡ ብ
፲፫ ለው፡ ለመኑት፨ በዚያም፡ ጊዜ፡
ኢየሱስ፡ ፈቀደላቸው፡ ርኩሳ
ን፡ መናፍስትም፡ ወጡና፡ ወደ፡
እሪያው፡ ገቡ፡ መንጋውም፡ ሁ
ሉ፡ እየበረገገ፡ ወደ፡ ባሕር፡ ተ
ወረወረ፡ ሁለትም፡ ሺህ፡ ያህሉ፡
ነበር፡ በባሕርም፡ ሰጠሙ፨
፲፬ እረኞቹ፡ ግን፡ ሸሹ፡ በከተማ
ም፡ በሀገርም፡ አወሩ፡ ሕዝቡም፡
የሆነውን፡ ነገር፡ ለማየት፡ ወጡ፡
፲፭ ወደ፡ ኢየሱስም፡ ቀረቡ፡ ጋኔን፡
የያዘው፡ ሌጌዎንም፡ የነበረበ
ቱን፡ ተቀምጦ፡ ልብሱንም፡ ለ
ብሶ፡ አእምሮውም፡ ተመልሶ፡
፲፮ አዩና፡ ፈሩ፨ ጋኔን፡ አድሮበት፡
የነበረው፡ ሰው፡ የሆነውንና፡
በእሪያውም፡ የተደረገውን፡
ያዩ፡ ሰዎች፡ ነገርዋቸው፨
፲፯ ከሀገራቸውም፡ ይሒድ፡ ዘንድ፡
ይለምኑት፡ ጀመሩ፨
፲፰ ወደ፡ ታንኳም፡ በወጣ፡ ጊዜ፡ ጋኔ
ን፡ አድሮበት፡ የነበረው፡ ከእ
ርሱ፡ ጋራ፡ ይሆን፡ ዘንድ፡ ለመነ
፲፱ ው፨ ኢየሱስም፡ አልፈቀደለት
ም፡ ነገር፡ ግን፡ ወደ፡ ቤትህና፡ ወ
ደ፡ ሰዎችህ፡ ዘንድ፡ ሒድህ፡ እ

ሬ፡ ዘገብረ፡ ለከ፡ እግዚአብ
ሔር፡ ወዘከመ፡ ተሣሀለከ።

፳ ወሖረ፡ ወአኀዘ፡ ይስብክ፡ በ
ዐሥሩ፡ አህጉር፡ ኵሉ፡ ዘገብ
ረ፡ ሎቱ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወ
፳፩ አንከሩ፡ ኵሎሙ። ወካዕበ፡ ዐ
ደወ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ በሐ
መር፡ ማዕዶተ፡ ወተጋብኡ፡
ብዙኃ፡ ሰብእ፡ ኀቤሁ፡ በኀበ፡
፳፪ ሐይቀ፡ ባሕር። ወመጽአ፡ ኀቤ
ሁ፡ አሐዱ፡ ብእሲ፡ መጋቤ፡ ም
ኵራብ፡ ዘስሙ፡ ኢያኢሮስ፡
ወረከበ፡ ወሰገደ፡ ሎቱ፡ ታ
ሕተ፡ እገሪሁ።
፳፫ ወብዙኀ፡ አስተብቍዖ፡ ወይ
ቤ፡ ወለትየ፡ አልጸቀት፡ ትሙ
ት፡ ወባሕቱ፡ ነዓ፡ ደይ፡ (እንብ
ር፡) እዴከ፡ ላዕሌሃ፡ ወተሐዩ።

፳፬ ወሖረ፡ ምስሌሁ፡ ወተለውዎ፡
ብዙኃ፡ ሰብእ፡ ወተጋፍዕዎ።
፳፭ ወመጽአት፡ ብእሲት፡ እንተ፡ ደ
ም፡ ይውሕዛ፡ እምዐሠርቱ፡
፳፮ ወክልኤቱ፡ ክረምተ። ወብዙ
ኀ፡ አሕመምዋ፡ ብዙኃን፡ ዐቀ
ብት፡ ሠራይ፡ ወአስተዋፅአ
ት፡ ኵሎ፡ ንዋያ፡ ወአኀለቀት፡

ግዚአብሔር፡ የሠራልህን፡ ሁ
ሉ፡ አንተ ም፡ እንዴ፡ ማረህ፡ን
ገራቸው፡ አለው።
፳ ሒዶም፡ ኢየሱስ፡ ያደረገለት
ን፡ ሁሉ፡ በአሥሩ፡ አህጉር፡ ያ
ስብክ፡ ጀመረ፡ ሁሉም፡ ተደነ
፳፩ ቁ። ም፡ ፯፡ ፴፩። ኢየሱስም፡ ደግሞ፡
በተንኳ፡ ወደማዶ፡ ተሻገረ፡ እ
ሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወይ
ቤሎሙ፡ ሀቡ፡ ዘቄሣር፡ ለቄ
ሣር፡ ወዘእግዚአብሔርኒ፡ ግበሩ፡
ለእግዚአብሔር፡ ወአንከርዎ ✠
፲፰ ወመጽኡ፡ ኀቤሁ፡ ሰዱቃውያን፡
እለ፡ ይብሉ፡ አልቦ፡ ትንሣኤ፡
ምውታን ✠

፲፱ ወተስእልዎ፡ ወይቤልዎ፡ ሊ
ቅ፡ ሙሴ፡ ጸሐፈ፡ ለነ፡ ለእመ
ቦ፡ ዘሞተ፡ እኁሁ፡ ወኀደገ፡ ብ
እሲቶ፡ እንዘ፡ አልቦ፡ ውሉድ፡
እኁሁ፡ ያውስባ፡ ለብእሲቱ፡
ወያቅም፡ ዘርአ፡ ለእኁሁ ✠
፳ ሀለው፡ እንከ፡ ሰብዐቱ፡ አኃ
ው፡ ወአውሰባ፡ ዘይልህቅ፡
ብእሲተ፡ ወሞተ፡ እንዘ፡ አ
ልቦ፡ ውሉድ ✠
፳፩ ወአውሰባ፡ ካልኡ፡ ወሞተ፡
እንዘ፡ አልቦ፡ ውሉድ፡ ወሣል
ሱኒ፡ ከማሁ ✠
፳፪ ወእስከ፡ ሰብአቲሆሙ፡ አው

የው፡ ዘንድ፡ ዲናሩን፡ (ፒሳው
ን)፡ አምጡልኝ፡ አላቸው ።
፲፮ እርሳቸውም፡ አመጡለትና፡
ይህ፡ መልኩ፡ ጽሕፈቱስ፡ የማ
ነው፡ አላቸው፡ እርሳቸውም፡
፲፯ የቄሣር፡ አሉት ✠ ኢየሱስም፡
መልሶ፡ የቄሣርን፡ ለቄሣር፡ የ
እግዚአብሔርንም፡ ለእግዚ
አብሔር፡ ስጡ፡ አላቸው፡ በእ
ርሱም፡ ተደነቁ ✠ ሮሜ፡ ፲፫፡ ፯ ✠
፲፰ ትንሣኤ፡ ሙታንም፡ የለም፡
የሚሉ፡ ሰዱቃውያን፡ ወደ፡ እ
ርሱ፡ መጥተው፡ እንዲህ፡ ብ
ለው፡ ጠየቁት ✠ ማቴ፡ ፳፪፡ ፳፫፡ ፴፫ ✠
፲፱ ሉቃ፡ ፳፡ ፳፯፡ ፴፱ ✠ መምህር፡ ሆይ፡ ሙ
ሴ፡ አንድ፡ ሰው፡ ወንድሙ፡ ል
ጅ፡ ሳይወልድ፡ ሚስቱን፡ ትቶ፡
ቢሞት፡ ወንድሙ፡ ሚስቱን፡
አግብቶ፡ ለወንድሙ፡ ዘር፡ ያቁ
ም፡ (ይተካ)፡ ብሎ፡ ጽፎ፡ ነበር ✠
፳ ዘዳግ፡ ፳፭፡ ፭ ✠ እንግዲህ፡ ሰባት፡
ወንድማማች፡ ነበሩ፡ የመጀ
መሪያውም፡ ሚስት፡ አገባና፡
ዘር፡ ሳያስቀር፡ ሞተ ✠
፳፩ ሁለተኛውም፡ አገባት፡ እርሱ
ም፡ ደግሞ፡ ዘር፡ ሳያስቀር፡ ሞ
ተ፡ ሦስተኛውም፡ እንዲሁ ✠
፳፪ ሰባቱም፡ ሁሉ፡ አግብተዋት፡

ሰብዑ፡ ወኢደጉ፡ ውሉደ፡ ወ
ድኅረ፡ ኵሎሙ፡ ሞተት፡ ይእ
፳፫ ቲ፡ ብእሲት። አመ፡ የሐይዉ፡
እንከ፡ ምውታን፡ ለመኑ፡ እ
ምኔሆሙ፡ ትከውኖ፡ ብእሲ
ተ፡ እስከ፡ ሰብዐቲሆሙ፡ እ
፳፬ ውሰብዋ። ወአውሥአ፡ እግ
ዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወይቤሎሙ፡
እኮኑ፡ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ትስሕ
ቱ፡ በኢያእምሮ፡ መጻሕፍት፡
፳፭ ወኢኃይሎ፡ እግዚአብሔር። አመ
ሰ፡ የሐይዉ፡ ምውታን፡ ኢያወ
ስቡ፡ ወኢይትዋሰቡ፡ አላ፡ ከ
መ፡ መላእክት፡ እግዚአብሔ
፳፮ ር፡ እሙንቱ፡ በሰማያት። ወከ
መሰ፡ የሐይዉ፡ ምውታን፡ ኢ
ያንበብክሙኑ፡ በውስተ፡ መ
ጽሐፈ፡ ሙሴ፡ ዘይቤሎ፡ እ
ግዚአብሔር፡ በኀበ፡ ዕፀ፡ ጳ
ጦስ፡ እንዘ፡ ይብል፡ አነ፡ ውእ
ቱ፡ እግዚአብሔር፡ አምላ
ክከ፡ አምላከ፡ አብርሃም፡ አም
፳፯ ላከ፡ ይስሐቅ፡ ወአምላከ፡ ያዕቆብ። ኢ
ኮነኬ፡ አምላከ፡ ምውታን፡ አላ፡
አምላከ፡ ሕያዋን፡ ውእቱ፡
ወአንትሙሰ፡ ብዙኃ፡ ትጌግ
፳፰ ዩ። ወመጽአ፡ አሐዱ፡ ጸሐፊ፡
ሰሚዖ፡ ከመ፡ ተኃሠሥዎ፡ ወ

ዘር፡ አላስቀሩም፡ ከሁሉም፡
በኋላም፡ ያች፡ ሴት፡ ሞተች።
፳፫ እንግዲህ፡ ሙታን፡ በተነሡ፡
ጊዜ፡ ከእርሳቸው፡ ለማንኛ
ው፡ ሚስት፡ ትሆናለች፡ ሰባቱ
ም፡ አግብተዋታልና።
፳፬ ኢየሱስም፡ መልሶ፡ አላቸው፡
ስለዚህ፡ ነገር፡ መጻሕፍትን፡
የእግዚአብሔርንም፡ ኃይ
ል፡ ባለማወቅ፡ የምትስቱ፡ አ
፳፭ ይደለምን። ሙታንስ፡ በሚነ
ሡበት፡ ጊዜ፡ በሰማይ፡ እንደ
ሉ፡ እንደ፡ መላእክት፡ ናቸ
ው፡ እንጂ፡ አያገቡም፡ አይ
፳፮ ጋቡም። ሙታን፡ እንዲነሡ፡
ግን፡ በሙሴ፡ መጽሐፍ፡ እግ
ዚአብሔር፡ በቍጥቋጦ፡ ውስ
ጥ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክ
ህ፡ እኔ፡ ነኝ፡ የአብርሃም፡ አም
ላክ፡ የይስሐቅም፡ አምላክ፡
የያዕቆብም፡ አምላክ፡ ብሎ፡
የተናገረውን፡ አላነበባችሁ
፳፯ ምን። ዘፀአ፡ ፫፡ ፮። ኢየሱም፡
የሕያዋን፡ አምላክ፡ ነው፡ እ
ንጂ፡ የሙታን፡ አምላክ፡ አ
ይደለም፡ እናንተ፡ ግን፡ እጅ
፳፰ ግ፡ ትስታላችሁ። ከጻፎችም፡
አንዱ፡ ሲከራከሩ፡ መልካም፡

ሶበ፡ርእየ፡ከመ፡ሠናየ፡ተሠ
ጠዎሙ፡ተስእሎ፡ወይቤሎ፨
አይኑ፡ትእዛዝ፡ቀዳሚት፡እ
ምኵሉ፨

፳፱ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየ
ሱስ፡ወይቤሎ፡ዛቲ፡ይእቲ፡
ቀዳሚት፡እምኵሉ፡ትእዛ
ዝ፡ስማዕ፡እስራኤል፡እግ
ዚአብሔር፡አምላክነ፡አሐ
ዱ፡እግዚአብሔር፡ውእቱ።
፴ ወአፍቅሮ፡ለእግዚአብሔ
ር፡አምላክከ፤በኵሉ፡ልብ
ከ፡ወበኵሉ፡ነፍስከ፡ወበ
ኵሉ፡ሕሊናከ፤ወበኵሉ፡ኃ
ይልከ፡ዛቲ፡ይእቲ፡ቀዳሚ
ት፡ትእዛዝ፨
፴፩ ወካልእታሂ፡እንተ፡ትመ
ስላ፡አፍቅር፡ቢጸከ፡ከመ፡
ነፍስከ፡ወዘየዓቢ፡እምእ
ላንቱ፡ትእዛዛት፡አልቦ።

፴፪ ወይቤሎ፡ውእቱ፡ጸሐፊ፡ሠ
ናየ፡ትቤ፡ሊቅ፡አማን፡አሐ
ዱ፡ውእቱ፡እግዚአብሔር፡
ወአልቦ፡ባዕድ፡ዘእንበሌሁ።

፴፫ ወከመ፡ታፍቅሮ፡በኵሉ፡ል

እንዴ፡መለሰላቸው፡አዪቶ፡
ወደ፡እርሱ፡ቀረበና፡ከትእ
ዛቱ፡ሁሉ፡መጀመሪያዩቱ፡
ማናቸዩቱ፡ናት፡ብሎ፡ጠየቀ
ው፨ ማቴ፡፳፪፡፴፬፡፵። ሉቃ፡፲፡፳፭፡፳፰፨

፳፱ ኢየሱስም፡መለሰለት፡አለ
ውም፡ከትእዛዝ፡ሁሉ፡መጀ
መሪያዩቱ፡የምትበልጠው፡
ይህች፡ናት፡እስራኤል፡ሆይ፡
ስማ፡እግዚአብሔር፡አምላ
ካችን፡አንድ፡እግዚአብሔ
፴ ር፡ነው፨ ዘዳግ፡፮፡፫፡፬ ፨ አንተም፡
በልብህ፡ሁሉ፡በነፍስህም፡
ሁሉ፡በሐሳብህም፡ሁሉ፡በ
ኃይልህም፡ሁሉ፡እግዚአብ
ሔር፡አምላክህን፡ውደድ፡
መጀመሪያዩቱ፡ትእዛዝ፡ይ
ህች፡ናት፨ ሁለተኛዩቱም፡
እርስዋን፡የምትመስል፡ይ
ህች፡ናት፡ባልንጀራህን፡እ
ንደ፡ራስህ፡ውደድ፡ከእነዚ
ህ፡የሚበልጥ፡ሌላ፡ትእዛዝ፡
፴፪ የለም፨ ዘሌ፡፲፱፡፲፰፨ ጸሐፊው
ም፡አለው፡መምህር፡ሆይ፡
መልካም፡ተናገርህ፡እግዚ
አብሔር፡በውነት፡አንድ፡ነ
ው፡ከእርሱም፡በቀር፡ሌላ፡
፴፫ የለም፨ በልብህም፡ሁሉ፡በ

ብከ፡ ወበኵሉ፡ ነፍስከ፤ ወበ
ኵሉ፡ ሐሊናከ፤ ወበኵሉ፡ ኃ
ይልከ፡ ወከመ፡ ታፍቅር፡ ቢ
ጸከ፡ ከመ፡ ነፍስከ፡ ወዝንቱ፡
ይኄይስ፡ እምኵሉ፡ መባዕ፡
ወእምኵሉ፡ መሥዋዕት።
፴፬ **ወር**እዮ፡ ከመ፡ ጠቢብ፡ ውእ
ቱ፡ ይቤሎ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡
ኢኮንከ፡ ርኁቀ፡ እመንግሥተ፡
እግዚአብሔር፡ ወአልቦ፡ እ
ንከ፡ ዘተኀበለ፡ ይሰአሎ።
፴፭ **ወይ**ቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱ
ስ፡ እንዘ፡ ይሜህሮሙ፡ በም
ኵራብ፡ እፎ፡ ይብሉ፡ ጸሐፍ
ት፡ ወልደ፡ ዳዊት፡ ውእቱ፡ ክ
ርስቶስ።
፴፮ **ወለ**ሊሁስ፡ ዳዊት፡ ይቤ፡ በመ
ንፈስ፡ ቅዱስ፡ ይቤሎ፡ እግዚ
እ፡ ለእግዚእየ፡ ንበር፡ በየማ
ንየ፡ እስከ፡ አገብኦሙ፡ ለጸላ
እትከ፡ ታሕተ፡ መከየደ፡ እገ
፴፯ ሪከ። **ዘለ**ሊሁ፡ ዳዊት፡ እግዚ
እየ፡ ይቤሎ፡ እፎ፡ እንከ፡ ይ
ከውኖ፡ ወልደ፡ ወኵሉ፡ ሕዝ
ብ፡ ሠናየ፡ ያጸምዕዎ።
፴፰ **ወይ**ቤሎሙ፡ እንዘ፡ ይሜህሮ
ሙ፡ ዑቁ፡ እምጸሐፍት፡ እለ፡

ሐሳብህም፡ ሁሉ፡ በነፍስህም፡
ሁሉ፡ በኃይልም፡ ሁሉ፡ እርሱ
ን፡ ብትወድ፡ ባልንጀራህንም፡
እንደ፡ ራስህ፡ ብትወድ፡ ይህ፡
ከቍርባን፡ ከመሥዋዕትም፡
ሁሉ፡ ይበልጣል። ፩ሳሙ፡ ፲፭፡ ፳፪።
፴፬ **ኢየ**ሱስም፡ በአእምሮ፡ እንደ፡
መለሰለት፡ ባየ፡ ጊዜ፡ አንተ፡
ከእግዚአብሔር፡ መንግሥት፡
የራቅህ፡ አይደለህም፡ አለው፡፡
ማንም፡ ደግሞ፡ ይጠይቀው፡
ዘንድ፡ የደፈረ፡ የለም። የሐዋ፡
፳፯፡ ፳፯፡ ፳፱። ፴፭ **ኢየ**ሱስም፡ በመ
ቅደስ፡ ሲያስተምራቸው፡ አላ
ቸው፡ ጻፎች፡ ክርስቶስን፡ የ
ዳዊት፡ ልጅ፡ ነው፡ እንደ፡ ምን፡
ይላሉ። ማቴ፡ ፳፪፡ ፵፩፡ ፵፭፡ ሉቃ፡ ፳፡ ፵፩።
፴፮ ፵፩ ። **ዳዊ**ት፡ ግን፡ ራሱ፡ በመን
ፈስ፡ ቅዱስ፡ አለ፡ ጌታ፡ ጌታዬ
ን፡ ጸላቶችህን፡ ከእግርህ፡ ሚ
ማ፡ በታች፡ እስካደርግልህ፡ በ
ቀኜ፡ ተቀመጥ፡ ኣለው። መዝ፡ ፻፲፡ ፩።
፴፯ **እር**ሱ፡ ዳዊት፡ ጌታዬ፡ ያለው፡
እንዴት፡ ልጁ፡ ይሆናል፡ ከሕ
ዝቡም፡ እጅግ፡ ሰዎች፡ ደስ፡ ብ
ሏቸው፡ ይሰሙት፡ ነበር።
፴፰ **ሲያ**ስተምራቸውም፡ አላቸው፡
ተሳብሰው፡ መመላለስንና፡ በ

ይፈቅዱ፡ ያንሶስዉ፡ ተሳቢ
ሶሙ፡ ወተአምኆቶሙ፡ በ
ምሥያጣት፨
፴፱ ወነቢረ፡ ፍጽም፡ በውስተ፡ አ
ዕዋዲት፡ ወርእሰ፡ ምርፋቅ
፵ ቅ፡ በውስተ፡ ምሳሐት፨ እለ፡
ይውህጥዎን፡ ለአብያተ፡ መ
በለታት፡ ወይትሜየኑ፡ በ
ነዋህ፡ ጸሎቶሙ፡ እሉ፡ ይ
ረክቡ፡ ዘየዓቢ፡ ኵነኔ፨
፵፩ ወነቢሮ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡
መንጸረ፡ ሙዳየ፡ ምጽዋት፡
ይሬኢ፡ ሰብአ፡ ዘያበውኡ፡
ጸሪቀ፡ ወይወድዩ፡ ውስተ፡
ሙዳየ፡ ምጽዋት፡ ወብዙኃ
ን፡ አብዕልት፡ እለ፡ አብኡ፡ ብዙኃ።
፵፪ ወመጽአት፡ አሓቲ፡ ብእሲት፡
ነዳይት፡ መበለት፡ ወአብ
አት፡ ክልኤ፡ ጸራይቀ፡ ዘይብ
ልዎ፡ ቆድራንጤስ፨
፵፫ ወጸውዖሙ፡ ለአርዳኢሁ፡
ወይቤሎሙ፡ አማን፡ እብ
ለክሙ፡ ከመ፡ ዛቲ፡ ነዳይት፡
መበለት፡ አብዝኃት፡ አብኦ፡
እምኵሎሙ፡ እለ፡ አብኡ፡
፵፬ ውስተ፡ ሙዳየ፡ ምጽዋት፨ እ
ስመ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ አብኡ፡
እምተረፈሙ፡ አብኡ፡ ወይ

ሄገበያው፡ ሰላምታ፡ መስጠ
ትን፡ ከሚወዱ፡ ከጸሮች፡ ተ
ጠበቁ፨ ማቴ፡ ፳፫፡ ፩፡ ፴፱፡፡ ሉቃ፡ ፳፡ ፵፭፡ ፵፯፨
፴፱ በመስጊድም፡ ፊት፡ ለፊት፡ በ
መብልም፡ ጊዜ፡ በላይኛው፡
፵ ማዕድ፡ መቀመጥ፨ ጸሎታቸ
ውንም፡ በማስረዘም፡ ምክ
ንያት፡ የባልቴቶችን፡ ቤቶች፡
ገንዘብ፦ የሚበሉ፡ እነዚህ፡
ትልቅ፡ ኵነኔ፡ ይቀበላሉ፨
፵፩ ኢየሱስም፡ በመዝገብ፡ ሣፅ
ን፡ ፊት፡ ተቀምጦ፡ ሰዎች፡ በ
ሣፅኑ፡ ገንዘብ፡ እንዴት፡ እ
ንዲያገቡ፡ ያይ፡ ነበር፡ ባለጸጎ
ችም፡ የሆኑት፡ እጅግ፡ ያገቡ፡
ነበሩ፨ ፪፡ ነገ፡ ፲፪፡ ፱፡፡ ሉቃ፡ ፳፩፡ ፩፡ ፬፨
፵፪ አንዲትም፡ ድኻ፡ ሴት፡ ባልቴ
ት፡ መጥታ፡ ሁለት፡ ነሐስ፡ አገ
ባች፡ ይኸውም፡ አንድ፡ ድሪም፡
ፒሳ፦ ያህላል፨ ሉቃ፡ ፲፪፡ ፶፱፨
፵፫ ደቀ፡ መዛሙርቱንም፡ ጠርቶ፡
እላቸው፡ በሣፅን፡ ካገቡት፡
ሁሉ፡ ይህች፡ ድኻ፡ ባልቴት፡
አብልጣ፡ እንዳገባች፡ እው
ነት፡ እላችኋለሁ፨
፵፬ ሁሉ፡ ከገንዘባቸው፡ የተረፈ
ውን፡ አግብተዋልና፡ ይህች፡
ግን፡ ከድኅነትዋ፡ ያላትን፡ ን

ኣቲሰ፡ እምተፅናሳ፡ ኵሉ፡ ዘ
ባቲ፡ አብአት፡ ወኵሉ፡ መንበርታ።

ምዕራፍ ። ፲፫ ።

ስለ፡ ኢየሩሳሌም፡ ጥፋት፡ ስለ፡ ሐሳዊ፡ መሲሕ፡
መነሣት፨ ስለ፡ ምጽአት፨ ስለ፡ በለስ፡ ምሳ

፩ ወወፂኦ፡ እምኵራብ፡ ይቤሎ፡
አሐዱ፡ እምአርዳኢሁ፡ ሊቀ፡
ርኢ፡ ምንተ፡ ይመስል፡ ንድ
ቁ፡ ወዕበኒሁ፨

፪ ወአውሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱ
ስ፡ ወይቤሎ፡ ትሬኢኑ፡ ዘንተ፡
ኵሎ፡ ንድቀ፡ ዓቢየ፡ ኢይትኅ
ደግ፡ ዝየ፡ ዕብን፡ ዲበ፡ ዕብን፡ ዘ
ኢይትነሠት፨

፫ ወእንዘ፡ ይነ
ብር፡ ውስተ፡ ደብረ፡ ዘይት፡
አንጻረ፡ ምኵራብ፡ ተስእልዎ፡
በባሕቲቶሙ፡ ጴጥሮስ፡ ወ
ያዕቆብ፡ ወዮሐንስ፡ ወእን
ድርያስ፨

፬ ወይቤልዎ፡ ንግረነ፡
ማዕዜ፡ ይከውን፡ ዝንቱ፡ ግ
ብር፡ ወምንት፡ ትእምርቱ፡
አመ፡ ይከውን፡ ዝንቱ፡ ኵሉ፡

፭ ወ
አውሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡
ወአኀዘ፡ ይበሎሙ፡ ዑቁ፡

፮ ኢያስሕቱክሙ፨ እስመ፡ ብ
ዙኃን፡ ይመጽኡ፡ በስምየ፡
እንዘ፡ ይብሉ፡ አነ፡ ውእቱ፡

ብረትዋን፡ ሁሉ፡ አገባች፨
፬፡ ቆሮ፨ ፰፡ ፲፬፨ ለ(ወ)፨ ፨ ፨

ምዕራፍ ። ፲፫ ።

ሌ፨ ስለ፡ ትጉሆች፡ አገልጋዮች፨ ፨
፨ ፨ ፨ ፨ ፨ ፨ ፨

፩ እርሱም፡ ከመቅደስ፡ ሲወጣ፡
ከደቀ፡ መዛሙርቱ፡ አንዱ፡ መ
ምህር፡ ሆይ፡ እይ፡ ይህ፡ ታላቅ፡
ድንጊያ፡ ሕንፃውስ፡ ምን፡ ይ
መስላል፡ አለው፨ ሉቃ፡ ፳፩፡ ፭፨

፪ ኢየሱስም፡ መልሶ፡ ይህን፡ ታላ
ቅ፡ ሕንፃ፡ ታያለህን፡ ሳይፈ
ርስ፡ ድንጊያ፡ በድንጊያ፡ ላይ፡
አይቀርም፡ አለው፨

፫ እርሱም፡ በመቅደስ፡ ትይዩ፡
በደብረ፡ ዘይት፡ ተቀምጦ፡ ስ
ለ፡ ጴጥሮስና፡ ያዕቆብ፡ ዮሐ
ንስና፡ እንድርያስም፡ ለብ
ቻቸው፡ ጠየቁት፨

፬ ይህ፡ ነገር፡ መቼ፡ ይሆናል፡ ይህ
ስ፡ እንዲፈጸም፡ ምልክቱ፡ ም
ንድር፡ ነው፡ ንገረንም፡ አሉ
ት፨

፭ ኢየሱስም፡ መልሶ፡ ይላቸ
ው፡ ጀመረ፡ ማንም፡ እንዳያ
ስታችሁ፡ ዕወቁ፨

፮ ብዙዎች፡ እኔ፡ ክርስቶስ፡ ነኝ፡
እያሉ፡ በስሜ፡ መጥተው፡ ብ
ዙዎችን፡ ያስታሉና፨

ክርስቶስ፡ ወያስሕቶሙ፡
፯ ለብዙኃን ✢ ወእመ፡ ሰማዕ
ክሙ፡ አፅባዕተ፡ ወድምፀ፡
ፀባኢት፡ ኢትደንግፁ፡ እስ
መ፡ ሀለዎ፡ ይኩን፡ ዝንቱ፡ ወ
ባሕቱ፡ አኮ፡ ሶቤሃ፡ ዘየኃልቅ።
፰ ወይትነሣእ፡ ሕዝብ፡ ዲበ፡ ሕ
ዝብ፡ ወነገሥት፡ ላዕለ፡ ነገሥ
ት፡ ወይመጽእ፡ ድልቅልቅ፡
በበብሔሩ፡ ወይመጽእ፡ ረኃ
ብ፡ ወዝንቱ፡ ቀዳሚሁ፡ ለፃዕር። ወ
፱ አንትሙሰ፡ ዑቁ፡ ርእሰክሙ፡
ወይወስዱክሙ፡ ኀበ፡ አዕዋ
ዳት፡ ወይቀሥፉክሙ፡ በመ
ኳርብት፡ ወይትባጽሑክሙ፡
[illegible] ፡ ኀበ፡ መሳእ
ክት፡ ወነገሥት፡ በእንቲአየ፡
ከመ፡ ይኩን፡ ስምዐ፡ ላዕሌሆ
ሙ ✢
፲ ወለኵሉ፡ አሕዛብ፡ ይቀ
ድሙ፡ ይስብክዎ፡ ለወንጌል።
፲፩ ወሶበ፡ ያበጽሑክሙ፡ ወያ
ሚጥዉክሙ፡ ኢትቅድሙ፡
ሐልዮ፡ ዘትብሉ፡ ወዘትነቡ፡
አላ፡ ዘይትወሀበክሙ፡ በጊ
ዜሃ፡ ንቡ፡ እስመ፡ ኢኮንክሙ፡
አንትሙ፡ ዘትነብቡ፡ ዘእንበ

፯ ሰልፉንና፡ የሰልፉንም፡ ወሬ፡
በሰማችሁ፡ ጊዜ፡ እንዳትደ
ነግጡ፡ ዕወቁ፡ ይህ፡ ይሆን፡
ዘንድ፡ ይገባልና፡ ነገር፡ ግን፡
ፍጻሜው፡ ገና፡ ነው ✢
፰ ሕዝብም፡ በሕዝብ፡ ላይ፡ መ
ንግሥትም፡ በመንግሥት፡ ላ
ይ፡ ይነሣልና፡ በያገሩም፡ መ
ናወጥና፡ ረሀብ፡ ሁከትም፡
፱ ይሆናል ✢ ይህም፡ የፃዕር፡
መጀመሪያ፡ ነው፡ እናንተ፡ ግ
ን፡ ለራሳችሁ፡ ተጠበቁ፡ ወደ፡
ሸንጎም፡ ይወስዷችኋል፡
በጸሎት፡ ቤታቸውም፡ ይገ
ርፉዋችኋል፡ ስለ፡ እኔም፡ ወ
ደ፡ ነገሥታትና፡ ወደ፡ መካን
ንትም፡ ፊት፡ ያደርሱዋችኋ
ል፡ ምስክር፡ ይሆንባችሁ፡
፲ ዘንድ ✢ ማቴ፡ ፲፡ ፲፯፡ ፳፪ ✢ አስቀድ
ሞም፡ ለአሕዛብ፡ ሁሉ፡ ወን
ጌል፡ ይሰብክ፡ ዘንድ፡ ይገባ
፲፩ ል ✢ ም፡ ፲፯፡ ፲፩ ✢ ወስደውም፡ አሳ
ልፈው፡ በሰጧችሁ፡ ጊዜ፡ የ
ምትናገሩትን፡ አስቀድማ
ችሁ፡ አታስቡ፡ በዚያንም፡ ጊ
ዜ፡ የሚሰጣችሁን፡ ተናገሩ፡
መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ነው፡ እንጂ፡

ሉ፡ መንበሉ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፤
፲፪ ወያገብእ፡ እኅው፡ እኅዋሁ፡
ለሞት፡ ወእብእኒ፡ ውሉዶ፡
ወውሉድ፡ ይትነሥኡ፡ ዲበ፡
አዝማዲሆሙ፡ ወይቀትሉ
፲፫ ዎሙ ✢ ወትከውኑ፡ ጽሉአነ፡
በኀበ፡ ኵሉ፡ ሰብእ፡ በእንተ፡
ስምየ፤ ወዘሰ፡ አዘለፈ፡ ትዕ
ግሥቶ፡ ውእቱ፡ ያድኅን ✢
፲፬ ወሶበ፡ ርኢክሙ፡ ኅሣሮ፡ ለ
ሙስና፡ ዘይቤ፡ ዳንኤል፡ ነ
ቢይ፡ ዘይቀውም፡ ውስተ፡ መ
ካን፡ ቅዱስ፡ ኀበ፡ ኢይደሉ፡ ዘ
ያነብብ፡ ለይለቡ፡ ወይእተ፡
አሚረ፡ እለ፡ ውስተ፡ ይሁዳ፡
ይጐየዩ፡ ውስተ፡ አድባር።
፲፭ ወዘኒ፡ ውስተ፡ ናሕስ፡ ሀሎ፡ ኢ
ይረድ፡ ውስተ፡ ቤቱ፡ ወኢይ
ባዕ፡ ይንሣእ፡ ዘኮነ፡ እምቤ
፲፮ ቱ ✢ ወዘኒ፡ ውስተ፡ ገዳም፡ ሀ
ሎ፡ ኢይትመየጥ፡ ድኅሬሁ፡
፲፯ ይንሣእ፡ ልብሶ ✢ ወዓ ሐቱ፡ ለእ
ሎን፡ ለፅኑሳት፡ ወለእለ፡ የሐ
ፅና፡ ይእተ፡ አሚረ፡ በውእቱ፡
፲፰ መዋዕል ✢ ወጸልዩ፡ ከመ፡ ኢ
ይኩን፡ ጐያክሙ፡ በክረምት።
፲፱ እስመ፡ ይከውን፡ ይእቲ፡ አ
ሚረ፡ ዓቢይ፡ ሕማም፡ ዘእም

እናንተ፡ የምትናገሩ፡ አይደላች
፲፪ ሁምና ✢ ወንድም፡ ወንድሙ
ን፡ አባት፡ ልጁን፡ ለሞት፡ አሳል
ፎ፡ ይሰጣል፤ ልጆችም፡ በወላ
ጆቻቸው፡ ላይ፡ ይነሣሉ፡ ያገ
፲፫ ድሉዋቸዋልም ✢ ስለ፡ ስሜም፡
በሁሉ፡ ዘንድ፡ የተጸላችሁ፡
ትሆናላችሁ፡ እስከ፡ ፍጻሜ፡
የሚታገሥ፡ ግን፡ እርሱ፡ ይድ
፲፬ ናል ✢ በነቢዩ፡ በዳንኤል፡ የተ
ባለውንም፡ የመፍረሱን፡ ር
ኩሰት፡ በማይገባው፡ ስ
ፍራ፡ ቆሞ፡ ባያችሁ፡ ጊዜ፡ አ
ንባቢው፡ ያስተውል፤ በዚያ
ም፡ ጊዜ፡ በይሁዳ፡ ያሉ፡ ወደ፡
ተራራ፡ ይሽሹ ✢ ዳን፡ ፱፡ ፳፯፡ ፲፪፡ ፩፡ ፲፩ ✢
፲፭ በሰገነትም፡ ያለ፡ ወደ፡ ምድ
ር፡ ቤት፡ አይውረድ፡ ከቤቱም፡
አንዳች፡ ይወስድ፡ ዘንድ፡ አይ
፲፮ ግባ ✢ በእርሻም፡ ያለ፡ ልብሱ
ን፡ ይወስድ፡ ዘንድ፡ ወደ፡ ኋላ፡
፲፯ አይመለስ ✢ ነገር፡ ግን፡ በዚ
ያ፡ ወራት፡ ለርጉዞችና፡ ለሚ
ያጠቡ፡ ወዮላቸው ✢
፲፰ ሽሽታችሁም፡ በክረምት፡ እ
ንዳይሆን፡ ጸልዩ ✢
፲፱ በዚያ፡ ወራት፡ እግዚአብሔ
ር፡ ዓለሙን፡ ከፈጠረው፡ ጀ

አመ፡ ኮነ፡ ዓለም፡ ኢኮነ፡ ከማ
ሁ፡ ወአምአመ፡ ፈጠረ፡ እግዚ
አብሔር፡ ዓለመ፡ ኢኮነ፡ ወኢይ
፳ ከውንሂ ። ወሶበ፡ አኮ፡ ዘአሕጸ
ሮን፡ እግዚአብሔር፡ ለእማን
ቱ፡ መዋዕል፡ እምኢድኅነ፡ ኵሉ፡
ዘነፍስ፡ ወባሕቱ፡ በእንተ፡ ኅ
ሩያኒሁ፡ እለ፡ ኀረየ፡ እግዚአብ
ሔር፡ የሐጽሮን፡ ለእማንቱ፡ መዋ
፳፩ ዕል ። ወይእቲ፡ አሚረ፡ እመቦ፡
ዘይቤለክሙ፡ ነዋ፡ ዝየ፡ ሀሎ፡
ክርስቶስ፡ ወነዋ፡ ከሐከ፡ ኢ
፳፪ ትእመኑ ። እስመ፡ ይመጽኡ፡
ሐሳውያን፡ መሢሕ፡ ወሐሳ
ውያን፡ ነቢያት፡ ወይገብሩ፡
ተአምረ፡ ወመንክረ፡ ከመ፡
ያስሕቱ፡ ሶበ፡ ይትከሀሎሙ፡
፳፫ ለኅሩያንሂ ። ወአንትሙሰ፡ ዑ
ቁ፡ ናሁ፡ አቅደምኩ፡ ነገሮተ
ከሙ፡ ኵሎ ።
፳፬ ወባሕቱ፡ በውእቱ፡ መዋዕል፡
እምድኅረ፡ ውእቱ፡ ምንዳቤ፡
ፀሐይኒ፡ ይጸልም፡ ወወርኅ
ኒ፡ ኢየሁብ፡ ብርሃኖ ።
፳፭ ወከዋክብትኒ፡ ይወድቁ፡ እ
ምሰማይ፡ ወይትከወስ፡ ኃይ
፳፮ ለ፡ ሰማያት ። ወአሜሃ፡ ይሬእ
ዩዎ፡ ለወልደ፡ እጓለ፡ እመሕ

ምር፡ እስከ፡ ዛሬ፡ እንደ፡ እ
ርሱ፡ ያልሆነ፡ ለእንግዲህም፡
ደግሞ፡ የማይሆን፡ ትልቅ፡
፳ መከራ፡ ይሆናልና ። እግ ዚአብ
ሔርስ፡ ያችን፡ ወራት፡ ባያሳጥ
ራት፡ ሥጋ፡ የለበሰ፡ ሁሉ፡ ባል
ዳነም፤ ነገር፡ ግን፡ እግዚአብ
ሔር፡ ስለመረጣቸው፡ ሰዎች፡
እነዚያ፡ ወራቶች፡ ያጥራሉ ።
፳፩ ደኅ፡ ፲፪፡ ፩ ። በዚያ፡ [illegible] ጊዜም፡
ማንም፡ ክርስቶስ፡ ከዚህ፡ ነ
ው፡ ወይም፡ ከዚያ፡ ነው፡ ቢሏ
፳፪ ችሁ፡ አትመኑ ። እስ ተኞች፡
መሢሖች፡ እስተኞችም፡ ነቢ
ያት፡ ይነሣሉና፡ ቢቻላቸው
ስ፡ የተመረጡትን፡ ስንኳ፡ ለ
ማሳት፡ ተአምራትና፡ ምልክ
፳፫ ትን፡ ያደርጋሉ ። እና ንተ፡ ግ
ን፡ እወቁ፡ እነሆ፡ ነገሩን፡ ሁ
ሉ፡ አስቀድሜ፡ ነገርኋችሁ ።
፳፬ ነገ ር፡ ግን፡ በዚያ፡ ወራት፡ ከዚ
ያ፡ መከራ፡ በኋላ፡ ፀሐይ፡ ትጨ
ልማለች፡ ጨረቃም፡ ብርሃኗ
ን፡ አትሰጥም ።
፳፭ የሰ ማይ፡ ከዋክብትም፡ ይ
ወድቃሉ፡ በሰማይ፡ ያሉ፡ ኃይ
፳፮ ላት፡ ይናወጣሉ ። በዚ ያም፡ ጊ
ዜም፡ የሰውን፡ ልጅ፡ ከብሮ፡

ያው፡ እንዘ፡ ይመጽእ፡ በደመና፡
ምስለ፡ ኀይል፡ ዓቢይ፡ ወብዙ
፳፯ ኅ፡ ስብሐት። ወይእቲ፡ አሚረ፡
ይፌንዎሙ፡ ለመላእክቲሁ፡
ወያስተጋብዕዎሙ፡ ለኅሩያ
ኒሁ፡ እም አርባዕቱ፡ ነፋሳት፡
፳፰ እምአጽናፈ፡ ምድር፡ እስከ፡ አጽናፈ፡ ሰማይ። ወ
እምበለስ፡ አእምሩ፡ አምሳሊ
ሁ፡ እምከመ፡ ለምለመ፡ አዕጹ
ቂሃ፡ ወሠረፀ፡ ቈጽላ፡ ይትዓወ
፳፱ ቅ፡ ከመ፡ አልጸቀ፡ ማዕረር። ከማ
ሁኬ፡ አንትሙኒ፡ እምከመ፡ ር
ኢክሙ፡ ዘንተ፡ ኵሎ፡ ከመ፡ ኮ
ነ፡ አእምሩ፡ ከመ፡ በጽሐ፡ ኀበ፡
፴ ኆኅት። አማን፡ አክሙ፡ ከመ፡
ኢተኀልፍ፡ ዛቲ፡ ትውልድ፡ ዘእ
ንበለ፡ ይኩን፡ ዝንቱ፡ ኵሉ።
፴፩ ሰማይ፡ ወምድር፡ የኀልፍ፡ ወቃ
፴፪ ልየኀልፍ። ወበእንተሰ፡ ይእቲ፡
ዕለት፡ ወይእቲ፡ ሰዓት፡ አልቦ፡
ዘየአምራ፡ ኢመላእክት፡ ሰ
ማይ፡ ወኢወልድ፡ ዘእንበለ፡
፴፫ አብ፡ ባሕቲቱ። ዑቁ፡ ትጉሁ፡ ወ
ጸልዩ፡ እስመ፡ ኢተአምሩ፡ ማ
እዜ፡ መዋዕለ፡ ጊዜሁ።
፴፬ ከመ፡ ብእሲ፡ ዘይነግድ፡ ወየኀ
ድግ፡ ቤቶ፡ ወይሁቦሙ፡ ግብ
ሮሙ፡ ለአግብርቲሁ፡ ለለአ

ኀይልና፡ ከምስጋና፡ ጋራ፡ በዳ
መና፡ ሲመጣ፡ ያዩታል።
፳፯ በዚያም፡ ጊዜ፡ መላእክቱን፡ ይ
ሰዳል፡ የተመረጡትንም፡ ከ
ራቱ፡ ነፋሳት፡ ከምድር፡ ዳር፡
እስከ፡ ሰማይ፡ ዳርቻ፡ ይሰበስ
፳፰ ባሉ። ማቴ፡ ፳፬፡ ፴፩። ምሳሌውንም፡
ከበለስ፡ ዕወቁ፡ ጫፍዋ፡ በለ
መለመ፡ ቅጠሏም፡ ባቈጠቈ
ጠ፡ ጊዜ፡ መከር፡ እደ፡ ደረሰ፡ ደ
፳፱ ታወቃል። ማቴ፡ ፳፬፡ ፴፪። እንደሁ
ም፡ እናንተ፡ ደግሞ፡ ይህ፡ ሁሉ፡
ሲሆን፡ ያያችሁ፡ እንደ፡ ሆነ፡ በ
ደጅ፡ ላይ፡ እንደ፡ ቀረበ፡ ዕወቁ።
፴ ይህም፡ ሁሉ፡ እስኪሆን፡ ድረስ፡
ይህች፡ ትውልድ፡ እንዳታልፍ፡
እውነት፡ እላችኋለሁ።
፴፩ ሰማይና፡ ምድር፡ ያልፋል፡ ቃሌ፡
፴፪ ግን፡ አያልፍም። ስለ፡ ዚያች፡ ቀ
ን፡ ስለ፡ ዚያችም፡ ሰዓት፡ ግን፡
ከአብ፡ በቀር፡ ማንም፡ አያው
ቀትም፡ የሰማይ፡ መላእክት
፴፫ ም፡ ወልድም። የሚሆን ፡ ፡ ፡
በትንም፡ ጊዜ፡ አታውቁምና፡
ተጠንቀቁ፡ ተግታችሁም፡ ጸል
፴፬ ዩ። የሰው፡ ልጅ፡ ቤቱን፡ ትቶ፡
እንደሚሔድ፡ ሰው፡ ነውና።
ለአገልጋዮቹም፡ ለያንዳንዱ

ሐዴ፡ እምኔሆሙ፡ ወይኤዝ
ዞ፡ ለዐጸዊኒ፡ ከመ፡ ይትጋህ፨
፴፭ ትጓሁ፡ እንከ፡ እስመ፡ ኢተአም
ሩ፡ ማዕዜ፡ ይመጽእ፡ በዓለ፡ ቤ
ት፡ እመሂ፡ ሠርከ፡ ወእመሂ፡
መንፈቀ፡ ሌሊት፡ ወእመሂ፡ ጊ
ዜ፡ ይነቁ፡ ዶርሆ፡ ወእመሂ፡ ጸ
፴፮ ቢሐ፨ ኢይምጻእክሙ፡ ግብተ፡
ወኢይርከብክሙ፡ እንዘ፡ ት
፴፯ ነውሙ፨ ወናሁ፡ እብለክሙ፡ ለ
ኵልክሙ፡ ትግሁ፨ ፨ ፨

ምዕራፍ፡ ፲፬ ።

ስለ፡ በዓለ፡ ፋሲካና፡ ዋጋው፡ ውድ፡ የሆነ፡ ሽቱ፡
እንደ፡ ተቀባ፡ ይሁዳ፡ አሳልፎ፡ ሊሰጠው፡ እ
ንደ፡ ተነጋገረ፨ ሥጋውንና፡ ደሙን፡ እንደ፡
ሠጣቸው፨ ሁላችሁም፡ ትክዱኛላችሁ፡ እ

፩ ወእስከ፡ ሠኑይ፡ መዋዕል፡ ፋሲ
ካ፡ ወበዓለ፡ መጸለትት፡ ኀሠሡ፡
ሊቃነ፡ ካህናት፡ ወጸሐፍት፡
ከመ፡ ይትመየንዎ፡ ወየአኀዝ
ዎ፡ ወይቅትልዎ፨
፪ ወይቤሉ፡ አኮኬ፡ በበዓል፡ ከመ፡
ኢይትሀወኩ፡ ሕዝብ፨

፫ ወእንዘ፡ ሀሎ፡ ቤታንያ፡ በቤተ፡
ስምዖን፡ ዘለምጽ፡ እንዘ፡ ይረ
ፍቅ፡ መጽአት፡ ብእሲት፡ ወአ
ምጽአት፡ ዕፍረተ፡ ዘአልባስጥ

ሥራቸውን፤ እንደሠጣቸው፡ በረኛውም፡ እ
ንዲተጋ፡ ያዘዋል፨ ማቴ፡ ፳፭፡ ፲፬ ሉቃ፡
፴፭ ፲፱፡ ፲፪፨ እሁንም፡ ትጉ፡ ባለቤቱ፡
መቼ፡ እንዲመጣ፡ አታውቁ
ምና፡ በማታ፡ ወይስ፡ በኩሌ፡ ሌ
ሌሊት፡ ወይስ፡ ዶሮ፡ ሲጮህ፡
ወይስ፡ በማለዳ፨ ሉቃ፡ ፲፪፡ ፴፰፨
፴፮ ድንገት፡ መጥቶ፡ ተኝታችሁ፡ እ
፴፯ ንዳያገኛችሁ፨ እነሆ፡ ለእናን
ተም፡ የምነግራችሁን፡ ለሁሉ፡
ትጉ፡ እላለሁ፨ ፨ ፨ ፨

ምዕራፍ፡ ፲፬ ።

ንዳላቸው፨ በጊቴሴማኒ፡ እንደ፡ ጸለየና፡ ይ
ሁዳ፡ እንዲስያዘው፨ በካህናት፡ አለቃ፡ ፊ
ት፡ እንደ፡ ቆመና፡ እንደ፡ ተጠየቀ፨ ጴጥሮ
ስ፡ እንደ፡ ካደና፡ ንስሐ፡ እንደ፡ ገባ፨ ፨

፩ በዓለ፡ ፋሲካ፡ በዓለ፡ ናዕትም
ከሁለት፡ ቀን፡ በኋላም፡ ነበር፤
የካህናት፡ አለቆችም፡ ጻፎች
ም፡ በተንኰል፡ ይዘው፡ ይገድ
ሉት፡ ዘንድ፡ ይሹ፡ ነበር፨ ማቴ፡
፪ ፳፮፡ ፩፡ ፭፨ ዮሐ፡ ፲፫፨ ነገር፡ ግን፡ በሕ
ዝብ፡ ሁከት፡ እንዳይሆን፡ በ
በዓል፡ አይሆንም፡ አሉ፨ ማቴ፡
፫ ፳፮፡ ፯፨ ፲፫፨ ዮሐ፡ ፲፪፡ ፩፡ ፫፨ እርሱም፡
በቢታንያ፡ በለምጻሙ፡ ስም
ዖን፡ ቤት፡ ለመብል፡ ተቀምጦ፡
ሳለ፡ ዋጋው፡ የበዛና፡ ውድም፡

ርስ፡ ዘናርዱ፡ ቅድው፡ ዘዕፁ
ብ፡ ሤጡ፡ ወአኰሰቶ፡ ወሠጠ
ት፡ ዲበ፡ ርእሱ።

፬ ወቦ፡ እለ፡ ተምዕዑ፡ ወይቤሉ፡ ለ
ምንት፡ መጠነዝ፡ ኀጕል፡ ዘዝ፡
ዕፍረት።

፭ እምኢተክህለኑ፡ ይሠየጥ፡ ዝ
ንቱ፡ ዕፍረት፡ ፈድፋደ፡ እም
ሠለስቱ፡ ምዕት፡ ዲናር፡ ወየ
ሀብዎ፡ ለነዳያን፡ ወገሠጽዋ።

፮ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱ
ስ፡ ኅድግዋ፡ ለዛቲ፡ ብእሲት፡ ወ
ኢተሥርኅዋ፡ ሠናየ፡ ግብረ፡ ገ
ብረት፡ ላዕሌየ።

፯ ወለነዳያንሰ፡ ዘልፈ፡ ትረክቦ
ሙ፡ በኀቤክሙ፡ ወጊዜ፡ ፈቀ
ድክሙ፡ ታሤንዩ፡ ላዕሌሆ
ሙ፡ ወኪያየሰ፡ አኮ፡ ዘልፈ፡
ዘትረክቡኒ።

፰ ወዛቲኒ፡ ዘባቲ፡ ገብረት፡ ወአ
ቅደመት፡ ወቀብዐተኒ፡ ሥጋ
የ፡ ለቀበርየ።

፱ አማን፡ እብለክሙ፡ ኀበ፡ ሰበክ
ዎ፡ ለዝንቱ፡ ወንጌል፡ ውስተ፡

የሆነ፡ ሽታውም፡ የጣፈጠ፡ ናር
ዶስ፡ የሚባል፡ የሽቱ፡ ጠርሙ
ስ፡ የያዘች፡ ሴት፡ መጣች፡ ጠር
ሙሱንም፡ ሰበረችና፡ በራሱ፡
ላይ፡ አፈሰሰችው።

፬ ከሰዎችም፡
በልባቸው፡ እንዲህ፡ ብለው፡
የተቈጡ፡ አሉ። የዚህ፡ ሽቱ፡
ይህን፡ ያህል፡ ሽቱ፡ ለምንድር፡
ነው።

፭ ይህ፡ ሽቱ፡ ከሶስት፡ መቶ፡
ድረም፡ ለሚበልጥ፡ ተሸጦ፡ ለ
ድሆች፡ ይሰጥ፡ ዘንድ፡ ባልተቻ
ለም፡ ነበርን፡ ተቈጥዋትም።

፮ ኢየሱስ፡ ግን፡ እሳቸው፡ ተውዋ
ት፡ ለምን፡ ታደክምዋታላች
ሁ፡ ለእኔ፡ መልካም፡ ማድረ
ግን፡ አደረገችልኝ።

፯ ድኆችስ፡ ሁል፡ ጊዜ፡ ከእናንተ፡
ጋራ፡ ናቸው፡ በወደዳችሁት
ም፡ ጊዜ፡ መልካም፡ ታደርጉ
ላቸው፡ ዘንድ፡ ትችላላችሁ፡
እኔን፡ ግን፡ ሁል፡ ጊዜ፡ የምታ
ገኙ፡ አይደላችሁም። ዘዳግ፡ ፲፭፡ ፲፩

፰ ይህችም፡ የሚቻላትን፡ ሁሉ፡
ፈጽማ፡ ያደረችውን፡ ሥጋዬ
ንም፡ የቀባችኝን፡ ለመቃብሬ፡
አስቀደመችው።

፱ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ ይህ፡ ወን
ጌል፡ በሚነገርበት፡ ዘንድ፡ በ

ኰሉ፡ ዓለም፡ ይነግሩ፡ ዘገብ
ረት፡ ዛቲ፡ ወይዜክርዋ፨
፲ ወይሁዳ፡ አስቆርታዊ፡ አሐዱ፡
እም ዐሠርቱ፡ ወክልኤቱ፡ ሐ
ረ፡ ኀበ፡ ሊቃነ፡ ካህናት፡ ከመ፡
ያግብኦ፡ ሎሙ፨
፲፩ ወሰሚዖሙ፡ ተፈሥሑ፡ ወተ
ናገርዎ፡ የሀብዎ፡ ሠላሳ፡ ብ
ሩረ፡ ወፈቀደ፡ በጽሚት፡ ያግ
ብኦ፡ ሎሙ፨

፲፪ ወአመ፡ ቀዳሚት፡ ዕለት፡ በዓ
ለ፡ መጸለት፡ ፋሲካ፡ አመ፡ ይ
ጠብሑ፡ ፍሥሐ፡ ይቤልዎ፡ አ
ርዳኢሁ፡ በአይቴ፡ ትፈቅድ፡
ንሑር፡ ወናስተዳሉ፡ ለከ፡ ፍ
ሥሐ፡ ትብላዕ፨
፲፫ ወፈነወ፡ ክልኤተ፡ እምአርዳ
ኢሁ፡ ወይቤሎሙ፡ ሑሩ፡ ሀ
ገረ፡ ወትረክቡ፡ ብእሴ፡ ዘይ
ፀውር፡ ፃሕበ፡ ማይ፡ ወተለ
ውዎ፡ ኀበ፡ ቦአ፨
፲፬ ወ፡ በልዎ፡ ለበዓለ፡ ቤት፡ ይቤ
ለከ፡ ሊቅ፡ አይቴ፡ ጽርሕ፡ ኀ
በ፡ አበልዕ፡ ፍሥሐ፡ ምስለ፡
አርዳእየ፨

፲፭ ወውእቱ፡ ያርእየክሙ፡ ጽርሐ፡

ዓለሙ፡ ሁሉ፡ ይህች፡ ያደረገ
ችውን፡ ይነግሩላታል፡ ያስባ
ታልም፨ ከአሥራ፡ ሁለቱም፡ አ
ንዱ፡ የአስቆሮቱ፡ ይሁዳ፡ አሳ
ልፎ፡ ሊሰጣቸው፡ ወደ፡ ካህና
ት፡ አለቆች፡ ሔደ፨ ማቴ፡ ፳፮፡ ፲፬።
ሮ፫፨ ሉቃ፡ ፳፪፡ ፫፡ ፳፪፨ እርሳቸውም፡
በሰሙ፡ ጊዜ፡ ደስ፡ አላቸው፡
ሠላሳ፡ ብርም፡ ይሰጡት፡ ዘን
ድ፡ ተነጋገሩት፡ አሳልፎም፡ እ
ንዲሰጣቸው፡ ምቹ፡ ጊዜ፡ ይ
ሻ፡ ነበር፨ የፋሲካውንም፡ በ
ግ፡ በሚያርዱበት፡ በመጀመ
ሪያው፡ የቂጣ፡ በዓል፡ ቀን፡ ደ
ቀ፡ መዛሙርቱ፡ ፋሲካን፡ ትበ
ላ፡ ዘንድ፡ ወዴት፡ ሔደን፡ ልና
ሰናዳልህ፡ ትወዳለህ፡ አሉት።
ከደቀ፡ መዛሙርቱም፡
ሁለት፡ ልኮ፡ አላቸው፡ ወደከ
ተማ፡ ሒዳችሁ፡ የውኃ፡ እንስ
ራ፡ የተሸከመ፡ ሰው፡ ታገኙላ
ችሁና፡ ከገባበት፡ ተከተሉት፨
ባለ ቤቱንም፡ መምህር፡ ከደ
ቀ፡ መዛሙርቴ፡ ጋራ፡ ፋሲካ
ን፡ የምበላበት፡ የእንግዶች፡
አዳራሽ፡ ወዴት፡ ነው፡ ይልሃል፡
በሉት፨ ም፡ ፲፭፡ ፫፨
እርሱም፡ የተጻፈውንና፡ የተ

ዓቢየ፡ ወንጹሬ፡ ወርሑየ፡ ወ
ህየ፡ አስተዳልዉ፡ ለነ ፨
፲፮ ወሖሩ፡ አርዳኢሁ፡ ሀገረ፡ ወረ
ከቡ፡ በከመ፡ ይቤሎሙ፡ ወ
አስተዳለዉ፡ በህየ ፨ ፋሲካ።
፲፯ ወመሰዮ፡ ሖረ፡ ምስለ፡ ዐሠ
ርቱ፡ ወክልኤቱ፡ አርዳኢሁ።
፲፰ ወእንዘ፡ ይረፍቁ፡ ወይበልዑ፡
ይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱ
ስ፡ አማን፡ እብለክሙ፡
አሐዱ፡ እምኔክሙ፡ ያገብአኒ፡
፲፱ ወውእቱ፡ ዘይበልዕ ፨ ወአኀዙ፡
ይትከዙ፡ ወይቤልዎ፡ በበአ
፳ ሐዱ፡ አነኑ፡ እንጋ፡ ውእቱ ፨ ወ
አውሥአ፡ ወይቤሎሙ፡ አሐ
ዱ፡ እምዐሠርቱ፡ ወክልኤቱ፡
ዘይጸብሕ፡ ምስሌየ፡ ውስተ፡
፳፩ መጸብሕየ ፨ ወልደ፡ እጓለ፡ እ
መሕያው ሰ፡ የሐውር፡ በከ
መ፡ ጽሑፍ፡ በእንቲአሁ፡ ወ
ባሕቱ፡ አሌ፡ ሎቱ፡ ለውእቱ፡
ብእሲ፡ ዘእምኃዕሌሁ፡ ይት
ሜጠውዎ፡ ለወልደ፡ እጓለ፡ እመ
ሕያው፡ እምኄየሶ፡ ሶበ፡ ኢተወለ
፳፪ ደ፡ ለውእቱ፡ ብእሲ ፨ ወእንዘ፡ ይ
በልዑ፡ ነሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱ
ስ፡ ኅብስተ፡ ወባረከ፡ ወፈተተ፡

ዘጋጁውን፡ ታላቅ፡ የሰገነት፡
አዳራሽ፡ ያሳያችኋል፡ በዚም፡
አሰናዱልን ፨ ፲፮ ደቀ፡ መዛሙርቱ
ም፡ ሒደው፡ ወደ፡ ከተማ፡ መ
ጡ፡ እንዳላቸውም፡ አገኙ፡ ፋሲ
፲፯ ካንም፡ አዘጋጁ ፨ በመሸም፡ ጊ
ዜ፡ ከአሥራ፡ ሁለቱ፡ ደቀ፡ መዛ
ሙርቱ፡ ጋራ፡ መጣ ፨
፲፰ ተቀምጠውም፡ ሲበሉ፡ ኢየ
ሱስ፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ ከ
እናንተ፡ አንዱ፡ ከእኔ፡ ጋራ፡ የሚ
በላው፡ አሳልፎ፡ ይሰጠኛል፡ አ
፲፱ ላቸው ፨ ያዝኑም፡ ጀመር፡ እያ
ንዳንዱም፡ ከቶ፡ እኔ፡ እሆንን፡
፳ አሉ ፨ ዮሐ፡ ፲፫፡ ፳፩፡ ፳፪ ፨ መልሶም፡ አ
ላቸው፡ ከአሥራ፡ ሁለቱ፡ አን
ዱ፡ እጁን፡ ከኔ፡ ጋራ፡ ወደ፡ ወጭ
ት፡ የሚጠልቅ፡ ነው ፨
፳፩ የሰው፡ ልጅም፡ ስለ፡ እርሱ፡ እ
ንደ፡ ተጻፈ፡ ይሔዳል። ነገር፡ ግ
ን፡ የሰው፡ ልጅ፡ በጁ፡ ለሚሰ
ጥ፡ ለዚያ፡ ለሰው፡ ወዮለት፡ ያ
ሰው፡ ባይወለድ፡ በተሻለው፡
፳፪ ነበር ፨ ሲበሉም፡ ኅብስቱን፡ አ
ንሥቶ፡ ያዘ፡ ባረከውም፡ ቈር
ሶም፡ ይህ፡ ሥጋዬ፡ ነው፡ እንኩ፡
ብሉ፡ ብሎ፡ ሰጣቸው ፨ ፩፡ ቆሮ፡ ፲፩፡
፳፫፡ ፳፬ ፨

ወወሀቦሙ፡ ወደቢሎሙ፡ ን
ሥኡ፡ ብልዑ፡ ዝውእቱ፡ ሥጋየ፡
፳፯ ወአሥአ፡ ጽዋዓኒ፡ ወአእኰቶ፡
ወወሀቦሙ፡ ወደቢሎሙ፡ ን
ሥኡ፡ ስትዩ፡ እምኔሁ፡ ኵልክሙ።
፳፰ ወደቢሎሙ፡ ዝውእቱ፡ ደም
የ፡ ዘሐዲስ፡ ሥርዓት፡ ዘይትክ
፳፱ ዐው፡ በእንተ፡ ብዙኃን፨ አማን፡ አ
ብለክሙ፡ ኢይሰቲ፡ እምዝንቱ፡
ፍሬ፡ ወይን፡ እስከ፡ እንታክቲ፡
ዕለት፡ አመ፡ እሰትዮ፡ ሐዲሰ፡
በመንግሥተ፡ እግዚአብሔር።
፴ ወአንቢሮሙ፡ ወሰቢሖሙ፡ ወ
ፅኡ፡ ውስተ፡ ደብረ፡ ዘይት።

፴፩ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡
ኵልክሙ፡ ትክህዱኒ፡ በዛቲ፡
ሌሊት፡ እስመ፡ ጽሑፍ፡ ዘይብ
ል፡ እቀትሎ፡ ለኖላዊ፡ ወይዘ
፴፪ ረዉ፡ አባግዒሁ፨ ወእምድኅረ፡
ተንሣእኩ፡ እቀድመክሙ፡ ገ
፴፫ ሊላ፨ ወይቤሎ፡ ጴጥሮስ፡ ለእ
መኒ፡ ኵሎሙ፡ ክህዱከ፡ አንሰ፡
፴፬ ኢይክህደከ፨ ወይቤሎ፡ እግዚ
እ፡ ኢየሱስ፡ አማን፡ እብለከ፡
አንተ፡ ትክሕደኒ፡ ዮም፡ ሠልሰ፡
በዛቲ፡ ሌሊት፡ ዘእንበለ፡ ይንቁ፡
፴፭ ዶርሆ፡ ፫ተ ፡ ጊዜ፨ ወአፈድፈ

፳፯ ጽዋውንም፡ አንሥቶ፡ ያዘ፡ አመ
ስግኖም፡ ሰጣቸውም፡ ሁሉም፡
ከእርሱ፡ ጠጡ፨
፳፰ አላቸውም፡ ለሐዲስ፡ ኪዳን፡ ስ
ለ፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ የሚፈስ፡ ደሜ፡
፳፱ ይህ፡ ነው፨ በእግዚአብሔር፡
መንግሥት፡ አዲሱን፡ እስከ፡
እምጠጣበት፡ እስከዚያ፡ ቀን፡
ድረስ፡ ከዚህ፡ ከወይን፡ ጭማቂ፡
እንዳልጠጣ፡ እውነት፡ እላችኋ
፴ ለሁ፨ የምስጋናም፡ መዝሙር፡
ከዘመሩ፡ በኋላ፡ ወደ፡ ደብረ፡
ዘይት፡ ወጡ፨ መዝ፡ ፻፲፫ ፡ ፻፲፰፨
፴፩ ኢየሱስም፡ አላቸው፡ በዚች፡ ሌ
ሊት፡ ሁላችሁ፡ ትክዱኛላችሁ፡
ጠባቂውን፡ እገድላለሁ፡ በጎ
ቹም፡ ይበተናሉ፡ የሚል፡ ተጽፏልና፨ ዘካ፡ ፲፫፡ ፯፡
፴፪ ነገር፡ ግን፡ ከተነሣሁ፡ በኋላ፡
ወደ፡ ገሊላ፡ እቀድማችኋለሁ።
፴፫ ምዕ፡ ፲፬፡ ፳፨ ጴጥሮስም፡
ሁሉም፡ ቢክዱህ፡ እኔ፡ አልክ
፴፬ ድህም፡ አለው፨ ኢየሱስም፡
እውነት፡ እልሃለሁ፡ ዛሬ፡ በዚ
ች፡ ሌሊት፡ ዶሮ፡ ሳይጮህ፡ ሶስ
ት፡ ጊዜ፡ ትክዱኛለህ፡ አለው፨
፴፭ ዮሐ፡ ፲፫፡ ፴፰፨ እርሱ፡ ግን፡ ነገሩን፡ አ

ዴ፡ ተኃሊፎተ፡ ጴጥሮስ፡ እን
ዘ፡ ይብል፡ እመውትሂ፡ ምስ
ሌከ፡ ወኢይክሕደከ።
፴፩ ወከማሁ፡ ይቤሉ፡ ኵሎሙ፡
ወሖሩ፡ ዓፀደ፡ ወይን፡ እንተ፡
ስማ፡ ጌቴሴማኒ፡ ወይቤሎ
ሙ፡ ለአርዳኢሁ፡ ንበሩ፡ ዝየ፡
፴፪ እስከ፡ አሐውር፡ እጼሊ። ወነ
ሥኦሙ፡ ለጴጥሮስ፡ ወለያዕ
ቆብ፡ ወለዮሐንስ፡ ምስሌሁ፡
፴፫ ወአኀዘ፡ ይተክዝ፡ ወይኄዝን። ወ
ይቤሎሙ፡ ተከዘት፡ ነፍስየ፡ እስከ፡
፴፬ ለሞት፡ ንበሩ፡ ዝየ፡ ወትግሁ፡ እንከ፡ ወ
እምዝ፡ ተአተተ፡ ሕቀ፡ ወሰገደ፡
ውስተ፡ ምድር፡ ወጸለየ፡ ከመ፡
ትኅለፍ፡ እምኔሁ፡ ይእቲ፡ ሰ
፴፭ ዓት፡ ለእመ፡ ይትከሀል። ወይ
ቤ፡ አአባ፡ ወአቡየ፡ ኵሉ፡ ይት
ከሀለከ፡ አኅልፋ፡ እምኔየ፡ ለ
ዛቲ፡ ጽዋዕ፡ ወባሕቱ፡ ፈቃደ፡
ዚአከ፡ ለይኩን፡ ወአኮ፡ ፈቃ
፴፮ ደ፡ ዚአየ። ወገቢኦ፡ ረከቦሙ፡
እንዘ፡ ይነውሙ፡ ወይቤሎ
ለጴጥሮስ፡ ኦስምዖን፡ ትነው
ምኑ፡ ወኢትክል፡ ተአግሦ፡ አ
ሐተ፡ ሰዓተ።
፴፯ ትጉሁ፡ ወጸልዩ፡ ከመ፡ ኢት
ባኡ፡ ውስተ፡ መንሱት፡ እስ

በርትቶ፡ ካንተ፡ ጋራ፡ የምሞ
ት፡ ስንኳ፡ ብሆን፡ አልክድህም።
አለ፡ ሁሉም፡ ደግሞ፡ እንዲህ፡
፴፩ አሉ። ጌቴሴማኒም፡ ወደ፡ አሚ
ሉት፡ ስፍራ፡ ሔዱ፡ ደቀ፡ መዛ
ሙርቱንም፡ ከዚያ፡ ሒጄ፡ እ
ስክጸልይ፡ ከዚህ፡ ተቀመጡ፡
፴፪ አላቸው። ጴጥሮስንና፡ ያዕቆብ፡
ዮሐንስንም፡ ከእርሱ፡ ጋራ፡ ይ
ዞ፡ ሔደ፡ ያዝንም፡ ይተክዝም፡
፴፫ ጀመረ። ነፍሴ፡ እስክሞት፡ ድ
ረስ፡ አዝናለች፡ ከዚህ፡ ቈዩ፡ ትጉ
፴፬ ም፡ አላቸው። ዮሐ፡ ፲፪፡ ፳፯። ከእነርሱም
ጥቂት፡ ፈቀቅ፡ ብሎ፡ ይቻል፡ እ
ንደ፡ ሆነ፡ ጊዜዪቱ፡ ከእርሱ፡
ታልፍ፡ ዘንድ፡ በምድር፡ ሳደ፡
፴፭ እየሰገደ፡ ጸለየ። አባ፡ አባቴ፡
ሆይ፡ ሁሉ፡ ይቻልሃልና፡ ይህች
ን፡ ጽዋ፡ ከእኔ፡ አሳልፋት፡ ነገ
ር፡ ግን፡ ያንተ፡ ፈቃድ፡ ይሁን፡ እ
ንጂ፡ የኔ፡ ፈቃድ፡ አይደለም።
፴፮ አለ። ም፡ ፲፡ ፴፰። መጥቶም፡ ተኝተ
ው፡ አገኛቸው፡ ጴጥሮስንም፡
አለው፡ ስምዖን፡ ሆይ፡ አንተ
ም፡ ተኝተሃልን፡ አንዲት፡ ሰ
ዓት፡ ስንኳ፡ ትተጋ፡ ዘንድ፡ አል
፴፯ ቻልህምን። ወደ፡ ፈተና፡ እንዳ
ትገቡ፡ ተግታችሁ፡ ጸልዩ፡ ነፍ

መ። መንፈስ፡ ይፈቅድ፡ ወሥ
ጋ፡ ደዱክም፨
፫፱ ወሐረ፡ ካዕበ፡ ወጸለየ፡ ወከ
፵ ማሁ፡ ከመ፡ ይቤ፨ ወገቢኦ፡
ካዕበ፡ ወረከቦሙ፡ እንዘ፡ ይ
ነውሙ፡ እስመ፡ ከበዳ፡ አዕ
ይንቲሆሙ፡ ወኢየአምሩ፡
፵፩ ዘይነብቡ፨ ወመጽአ፡ በሣልስ፡
ወይቤሎሙ፡ ኑሙ፡ እንከ
ሰ፡ ወአዕርፉ፡ ምዕረ፡ እስ
መ፡ ናሁ፡ በጽሐ፡ ጊዜሁ፡ ወና
ሁ፡ ያገብእዎ፡ ለወልደ፡ እጓ
ለ፡ እመሕያው፡ ውስተ፡ እደ፡
፵፪ ኃጥኣን፨ ተንሥኡ፡ ንሑር፡
ናሁ፡ በጽሐ፡ ዘያገብአኒ፨
፵፫ ወእንዘ፡ ይትናገሮሙ፡ በጽሐ፡
ሶቤሃ፡ ይሁዳ፡ አስቆሮታዊ፡
አሐዱ፡ እምዐሠርቱ፡ ወ፪ቱ፡
ወምስሌሁ፡ ብዙኃን፡ ሰብእ፡
ምስለ፡ መጣብሕ፡ ወአብት
ር፡ እምኀበ፡ ሊቃነ፡ ካህናት፡
፵፬ ወጸሐፍት፡ ወረበናት፨ ወወሀ
ቦሙ፡ ትእምርት፡ በዘያገብ
አ፡ ወይቤሎሙ፡ ዘሰዐምክ
ዎ፡ ውእቱ፡ አኃዝዎ፡ ወአጽን
ዕዎ፡ ወድዎ፨
፵፭ ወሶቤሃ፡ መጽአ፡ ኀቤሁ፡ ወ
ይቤሎ፡ ረቢ፡ ወሰዐሞ፨

ስ፡ (መንፈስ፡) የተዘጋጀ፡ ነው፡
ሥጋ፡ ግን፡ የደከመ፡ ነውና።
፫፱ ሁለተኛም፡ ሒዶ፡ እንደፊተኛው፡ ቃ
፵ ሉ፡ ጸለየ፨ ደግሞም፡ በተመለሰ፡
ጊዜ፡ ተኝተው፡ አገኛቸው፡ ዓ
ይኖቻቸው፡ ከብደው፡ ነበሩ
ና፡ የሚመልሱትንም፡ አያው
፵፩ ቁም፡ ነበር፨ ሶስተኛም፡ መጥ
ቶ፡ አላቸው፡ እንግዲህስ፡ ተ
ኙ፡ አንድ፡ ጊዜም፡ ዕረፉ፡ ሰዓ
ቱ፡ … ደርሶዋልና፡ እነሆ፡
የሰው፡ ልጅም፡ በኃጥአን፡ እ
ጅ፡ አልፎ፡ ይሰጣል፨
፵፪ እነሆም፡ አሳልፎ፡ የሚሰጠኝ፡
ቀርበዋልና፡ ተነሡ፡ እንሂድ፨
፵፫ ይህንንም፡ ሲናገር፡ በዚያ፡ ጊ
ዜ፡ ከአሥራ፡ ሁለቱ፡ አንዱ፡ ይ
ሁዳ፡ መጣ፡ ከካናት፡ አለቆች
ና፡ ከጸፎች፡ ከሽማግሌዎችም፡
እጅግ፡ ሰዎች፡ ሰይፍና፡ ጎመ
ድ፡ ይዘው፡ ከእርሱ፡ ጋራ፡ ነበ
፵፬ ሩ፨ ዮሐ፡ ፲፰፡ ፱፡ ፲፫፨ አሳልፎ፡ የሚ
ሰጠውም፡ የምስመው፡ እር
ሱ፡ ነውና፡ አጽንታችሁ፡ ያዙ
ችሁ፡ ውሰዱት፡ ብሎ፡ ምልክት፡ ሰጥ
ቶዋቸው፡ ነበር፨
፵፭ ያን፡ ጊዜም፡ ወደ፡ እርሱ፡ ቀር
ቦ፡ መምህር፡ ብሎ፡ ሳመው፨

፵፮ ወሰፍሑ፡ እዴዊሆሙ፡ ላዕ
፵፯ ሌሁ፡ ወአኀዝዎ። ወመልሐ፡ መ
ጥባሕቶ፡ አሐዱ፡ እምእለ፡
ይቀውሙ፡ ምስሌሁ፡ ወዘበ
ጦ፡ ለገብረ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ ወ
፵፰ መተሮ፡ እዝኖ። ወአውሥአ፡
እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወይቤሎ
ሙ፡ ከመ፡ ዘሠራቂኑ፡ ትድኀ
ኑ፡ ወፃእክሙ፡ ምስለ፡ መጣ
፵፱ ብሕ፡ ወአብትር፡ ተአኀዙኒ፡
ወ ኵሎ፡ አሚረ፡ ሀለውኩ፡ ም
ስሌክሙ፡ እሜህር፡ በምኵ
ራብ፡ ወኢአኀዝክሙኒ፡ ወ
ሐቱ፡ ከመ፡ ይብጻሕ፡ ቃል፡ ዘ
፶ ጽሑፍ፡ ውስተ፡ መጻሕፍት። ወ
ኀደግዎ፡ ኵሎሙ፡ አርዳኢ
፶፩ ሁ፡ ወጐዩ። ወተለ ፡ ዎ፡ አሐ
ዱ፡ ወሬዛ፡ ዘኮነ፡ ይትዐጸፍ፡
ሰንዱነ፡ ዕራቆ።
፶፪ ወአኀዝዎ፡ ወራዛት፡ ወኀደ
ገ፡ ሰንዱኖ፡ ወጐየ፡ ዕራቆ።
፶፫ ወወሰድዎ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱ
ስ፡ ኀበ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ ወተጋ
ብኡ፡ ኀቤሁ፡ ኵሎሙ፡ ሊቃ
ነ፡ ካህናት፡ ወጸሐፍት፡ ወ
ረበናት።
፶፬ ወተለዎ፡ ጴጥሮስ፡ እምርኁ
ቅ፡ እስከ፡ ውሣጤ፡ ዓፀደ፡ ሊ

፵፮ እርሳቸውም፡ እጃቸውን፡ ዘ
፵፯ ርግተው፡ ያዙት። ከእርሱም፡
ጋራ፡ ከቆሙት፡ አንዱ፡ ሰይፍ፡
መዘዘና፡ የካህናትን፡ አለቃ፡
ሎሌ፡ መታው፡ ጆሮውንም፡
፵፰ ቈረጠው። ኢየሱስም፡ መል
ሶ፡ እሳቸው፡ በሌባ፡ ላይ፡ እን
ድትመጡ፡ ሰይፍና፡ ጎመድ፡
ይዛችሁ፡ ልትይዙኝ፡ መጣች
፵፱ ሁን። ሁል፡ ጊዜም፡ በመቅደ
ስ፤ እያስተማርኩ፡ ከእናን
ተ፡ ጋራ፡ ስኖር፡ አልያዛችሁኝ
ም፡ ነገር፡ ግን፡ በመጻሕፍት፡
የተጻፈው፡ ይፈጸም፡ ዘንድ፡
፶ ነው። ደቀ፡ መዛሙርቱም፡ ሁ
ሉ፡ ትተውት፡ ሸሹ።
፶፩ በራቁትነቱ፡ ላይ፡ ነጠላ፡ ልብ
ስ፡ የለበሰ፡ አንድ፡ ጐበዝም፡ ይ
ከተለው፡ ነበር፡ ጐበዛዝትም፡
፶፪ ያዙት። እርሱም፡ ነጠላውን፡
ትቶ፡ ራቁቱን፡ አመለጠ።
፶፫ ኢየሱስንም፡ ይዘው፡ ወደ፡ ካ
ህናት፡ አለቃ፡ ወሰዱት፡ የካ
ህናት፡ አለቆችና፡ ሽማግሌ
ች፡ ጸፎችም፡ ሁሉ፡ ወደ፡ እር
ሱ፡ ዘንድ፡ ተሰበሰቡ።
፶፬ ጴጥሮስም፡ በሩቅ፡ ሁኖ፡ እስከ፡
ካህናት፡ አለቃ፡ ቤት፡ አጥር፡

ቀ፡ ካህናት፡ ወነበረ፡ ምስለ፡
ወዓልያኒሆሙ፡ ይስሐን፡ መ
ንገለ፡ በርህ።
፶፭ ወኅሠሡ፡ ሊቃነ፡ ካህናት፡ ወ
ኵሉ፡ ዓውድ፡ በዘያስተዋድ
ይዎ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ከ
መ፡ ይቅትልዎ፡ ወኃጥኡ።

፶፮ ወብዙኃን፡ እለ፡ አስተዋድይ
ዎ፡ በሐሰት፡ ወኀበረ፡ ቃሎ
፶፯ ሙ። ወቦ፡ እለ፡ ተንሥኡ፡ ሰማ
ዕተ፡ ሐሰት፡ ወነበቡ።

፶፰ ወይቤሉ፡ ንሕነ፡ ሰማዕናሁ፡ እ
ንዘ፡ ይብል፡ አነ፡ እነሥቶ፡ ለዝ
ንቱ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ ዘእዱ፡ ገ
ብር፡ ወሠሉስ፡ ዕለት፡ አሐንጾ፡
፶፱ ካልአ፡ ዘእድ፡ ኢገብሮ። ወምስ
ለ፡ ዝኒ፡ ኢኀበረ፡ ስምዖሙ።
፷ ወተንሥአ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ በማ
ዕከለ፡ ዓውድ፡ ወሐተቶ፡ ለእ
ግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወይቤሎ፡ አ
ልቦኑ፡ ዘትሠጠው፡ እንዘ፡ መ
፷፩ ጠነ፡ ያስተዋድዩከ። ወአ
ርመመ፡ ወኢተሠጥዎ፡ ወኢ
ምንተኒ፡ ወካዕበ፡ ሐተቶ፡
ሊቀ፡ ካህናት፡ ወይቤሎ፡ አ
ንተኑ፡ ውእቱ፡ ክርስቶስ፡ ወ

ግቢ፡ ደከተለው፡ ነበር፡ ከሎ
ሳሌቶቻቸውም፡ ጋራ፡ ተቀም
ጦ፡ በብርሃኑ፡ በኵል፡ እሳት፡
፶፭ ይሞቅ፡ ነበረ። የካህናት፡ አለ
ቆች፡ ግን፡ ሸንጎም፡ ሁሉ፡ ኢየ
ሱስን፡ ይገድሉት፡ ዘንድ፡ ም
ስክር፡ ይፈልጉ፡ ነበሩ፡ ነገር፡
ግን፡ አላገኙም። ዮሐ፡ ፲፰፡ ፲፱፡ ፳፩።
፶፮ ብዙዎችም፡ በሐሰት፡ ይመሰ
ክሩበት፡ ነበሩ፡ ምስክርነታች
ውም፡ አልተስማማም።
፶፯ የሐሰት፡ ምስክሮችም፡ ተነ
ሥተው፡ እንዲህ፡ ብለው፡ ተና
፶፰ ገሩ፡ ይህ፡ እጅ፡ የሠራውን፡
መቅደስ፡ አፍርሼ፡ በሶስተኛ
ው፡ ቀን፡ ሌላ፡ በእጅ፡ ያልተሠ
ራ፡ እሠራለሁ፡ ሲል፡ እኛ፡ ሰ
፶፱ ማነው። ዮሐ፡ ፪፡ ፲፱፡ ፳፩። ከዚህም፡
ጋራ፡ ምስክርነታቸው፡ አልተ
ስማማም። የካህናት፡ አለቃ
ም፡ ቁሞ፡ ይህን፡ ያህል፡ ሲያ
ሳጡህ፡ አንዳች፡ ስንኳን፡ አት
መልስምን፡ ብሎ፡ ኢየሱስ
ን፡ ጠየቀው። እርሱ፡ ግን፡ ዝ
ም፡ አለ፡ አንዳችም፡ አልመለ
ሰም፡ ደግሞም፡ የካህናት፡ አ
ለቃ፡ አንተ፡ የቡሩክ፡ ልጅ፡ ክር
ስቶስ፡ ነህን፡ ብሎ፡ ጠየቀው።

፷፪ ልዱ፡ ለቡሩክ ፨ ወይቤሎ፡ እ
ግዚእ፡ ኢየሱስ፡ እወ፡ አነ፡ ው
እቱ፡ ወትሬእይዎ፡ ለወልደ፡
እጓለ፡ እመሕያው፡ እንዘ፡ ይ
፷፫ ነብር፡ በየማነ፡ ኃይል፡ ወይመጽ
እ፡ በደመና፡ ሰማይ ፨ ወሰጠጠ፡
አልባሲሁ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ ወ
ይቤ፡ ምንቱ፡ እንከ፡ ትፈቅዱ፡
፷፬ ሎቱ፡ ሰማዕት ፨ ናሁ፡ ለሊክ
ሙ፡ ሰማዕክሙ፡ ጽርፈቶ፡
ምንከ፡ ትብሉ፡ ወአግብኡ፡ ፍ
ትሐ፡ ኵሎሙ፡ ወይቤሉ፡ ይ
፷፭ ቅትሎ ፨ ወአኀዙ፡ እምው
ስቴቶሙ፡ ይውርቅዎ፡ ወይ
ጽፍዕዎ፡ ገጾ፡ ወይኰርዕዎ፡
ወይብልዎ፡ ተነበይ፡ ለነ፡ ክር
ስቶስ፡ መኑ፡ ጸፍአከ፡ ወኮኑ፡
፷፮ ወዓልት፡ ይፄፍዕዎ ፨ ወእንዘ፡
ሀሎ፡ ጴጥሮስ፡ ታሕተ፡ ውስ
ተ፡ ዓፀድ፡ መጽአት፡ አሐቲ፡
ወለት፡ እምአዕማተ፡ ሊቀ፡
፷፯ ካህናት ፨ ወርእየቶ፡ ለጴጥ
ሮስ፡ እንዘ፡ ይስኀን፡ ወነጸ
ረቶ፡ ወትቤሎ፡ አንተኒ፡ ም
ስለ፡ ኢየሱስ፡ ናዝራዊ፡ ሀሎ
፷፰ ከ ፨ ወክህደ፡ ወይቤላ፡ ኢየአ
ምር፡ ወኢይጤይቅ፡ ዘት
ብሊ፡ ወወፅአ፡ አፍአ፡ ኀበ፡

፷፪ ም፡ ፲፭፡ ፬፡ ኢሳ፡ ፶፫፡ ፯ ፨ ኢየሱስም፡ እ
ዎን፡ እኔ፡ ነኝ፡ የሰው፡ ልጅን
ም፡ በኃይል፡ ቀኝ፡ ተቀምጦ፡
በሰማይ፡ ደመና፡ ሲመጣ፡ ታዩ
፷፫ ታላችሁ፡ አለው ፨ የካህናት፡
አለቃም፡ ልብሱን፡ ቀደደና፡
አለ፡ ለምን፡ ምስክር፡ ትፈ
ልጉበታላችሁ ፨
፷፬ እነሆ፡ እናንተ፡ ስድቡን፡ ሰ
ማችሁ፡ እንግዲህ፡ ምን፡ ትላ
ላችሁ፡ ሁሉም፡ ሞት፡ ይገባዋ
ል፡ ብለው፡ ፈረዱበት ፨ ዮሐ፡ ፲፱፡ ፯
፷፭ ከእነርሱም፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ ይ
ተፉበት፡ ጀመሩ፡ ፊቱንም፡ ሸ
ፍነው፡ እየጸፉና፡ እየመቱ፡
ክርስቶስ፡ ሆይ፡ ማነው፡ የመ
ታሕ፡ ትንቢት፡ ተናገርልኝ፡ ይ
፷፮ ሉት፡ ነበሩ፡ ሎሌዎችም፡ ይጸፉት፡ ነበሩ ፨ ጴጥሮስም፡ በ
ታችኛው፡ ቤት፡ ሳለ፡ ከካህ
ናት፡ አለቃ፡ ገረዶች፡ አንዲት፡
መጣች ፨ ዮሐ፡ ፲፰፡ ፲፭፡ ፳፯ ፨
፷፯ ጴጥሮስንም፡ ተቀምጦ፡ እሳ
ት፡ ሲሞቅ፡ አይታ፡ አስተዋለ
ችውና፡ አንተም፡ ከናዝሬቱ፡
ኢየሱስ፡ ጋራ፡ ነበርህ፡ አለች
፷፰ ው ፨ እርሱ፡ ግን፡ አንች፡ የም
ትዪውን፡ ፈጽሚ፡ አላውቅ
ም፡ ብሎ፡ ካደ፤ ወደ፡ ውጭም፡

ጸናፌ፡ ዓፀዱ፡ ወነቀወ፡ ዶ
፷፱ ርሆ፨ ወርእየቶ፡ ካዕበ፡ ይእ
ቲ፡ ወለተ፤ ወትቤሎሙ፡ ለ
እለ፡ ይቀውሙ፡ ህየ፡ ዝንቱ
ኒ፡ እምኔሆሙ፡ ውእቱ፡ ወክ
፸ ህደ፡ ካዕበ፨ ወእምድኅረ፡ ሕ
ቀ፡ ካዕበ፡ ይቤልዎ፡ ለጴጥሮ
ስ፡ እለ፡ ይቀውሙ፡ አማን፡
እምኔሆሙ፡ አንተ፤ ወገሊ
ላዊ፡ አንተ፡ ወቃልከ፡ ይመ
ስል፡ ቃሎሙ፨
፸፩ ወአኀዘ፡ ይትረገም፡ ወይም
ሐል፡ ከመ፡ ኢየአምሮ፡ ለው
እቱ፡ ብእሲ፡ ዘትብሉ፤ ወሶ
ቤሃ፡ ካዕበ፡ ነቀወ፡ ዶርሆ፨
፸፪ ወተዘከረ፡ ጴጥሮስ፡ ቃሎ፡ ለ
እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ዘይቤሎ፡
ሥልሰ፡ ትክህደኒ፡ ዘእንበ
ለ፡ ይንቁ፡ ዶርሆ፡ ክልኤ፡ ጊ
ዜ፡ ወበከየ፨ ፨ ፨ ፨

ምዕራፍ ፲፭ ።

ሊነጋ፡ ሊቃነ፡ ካህናት ፡ እንዴ፡ ተማከሩበት
ና፨ በጲላጦስ፡ ፊት፡ እንዴ፡ ቆመ፡ በርባን
ን፡ ተውልን፡ ብለው፡ እንዴ፡ ለመኑ፨ እንደላ

ወሶበ፡ ጸብሐ፡ ተማከሩ፡ ሊቃ
ነ፡ ካህናት፡ ወረበናት፡ ወጸሐ
ፍት፡ ወኵሉ፡ ዓውድ፤ ወሐ
መዱዎ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡

ወዶ፡ ቤቱ፡ ዶጅ፡ ወጣ፡ ዶሮ
፷፱ ም፡ ጮኸ፡ ደግመኛም፡ ገረዲ
ቱ፡ አየችውና፡ ከዚያ፡ ለቆሙ
ት፡ ሰዎች፡ ይህም፡ ከነርሳቸ
ው፡ ወገን፡ ነው፡ አለቻቸው፤
፸ እርሱም፡ ደግሞ፡ ካዴ፡ ከጥ
ቂትም፡ ጊዜ፡ በኋላ፡ በዚያ፡
የቆሙት፡ ጴጥሮስን፡ አንተ፡
በእውነት፡ ከእርሳቸው፡ ወ
ገን፡ ነህ፡ የገሊላም፡ ሰው፡ ነ
ህ፡ አነጋገርህ፡ ያስታውቅብ
፸፩ ሃልና፡ አሉት፨ እርሱም፡ እ
ኒ፡ ይህን፡ የምትሉትን፡ ሰው፡
አላውቀውም፡ አያለ፡ ራሱን፡
ይረግም፡ ይምልም፡ ጀመረ።
፸፪ ደግሞ፡ ሁለተኛ፡ ዶሮ፡ ጮኸ፡
ጴጥሮስም፡ ኢየሱስ፡ ሁለት፡
ጊዜ፡ ዶሮ፡ ሳይጮህ፡ ሶስት፡ ጊ
ዜ፡ ትክደኛለህ፡ ያለውን፡ አ
ስቦ፡ አለቀሰ፨ ቍ፡ ፸፪፨

ምዕራፍ ፲፭ ።

ገጡበት፨ እንዴ፡ ሰቀሉት፨ እንዴ፡ ሞተ፨
እንዴ፡ ተቀበረ፨ ማርያም፡ መግደላዊትና፨
ሊላዉቱ፡ ማርያም፡ መቃብሩን፡ እንዳዩ፨

ሊነጋም፡ የካህናት፡ አለቆ
ችና፡ ሽማግሌዎች፡ ጸፎችና፡
ሸንጎም፡ ሁሉ፡ ተማክረው፡
ኢየሱስን፡ አሥረው፡ ወሰ

ወወሰድዎ፡ ወመጠውዎ።
ለጲላጦስ፨
፪ ወተስእሎ፡ ጲላጦስ፡ ወይቤ
ሎ፡ አንተኑ፡ ንጉሦሙ፡ ለአ
ይሁድ፡ ወአውሥአ፡ እግዚ
እ፡ ኢየሱስ፡ ወይቤሎ፡ አን
፫ ተ፡ ትብል፨ ወአስተዋደይዎ፡
ሊቃነ፡ ካህናት፡ ብዙኀ፡ ወ
ውእቱሰ፡ አልቦ፡ ዘአውሥ
፬ አ፨ ወሐተቶ፡ ካዕበ፡ ጲላጦስ፡
ወይቤሎ፡ አልቦኑ፡ ዘትሠ
ጠው፡ እንዘ፡ መጠነዝ፡ ያ
፭ ስተዋድዩከ፨ ወኢተሠጥዎ፡
እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወኢም
ንተኒ፡ እስከ፡ አንከሮ፡ ጲላ
፮ ጦስ፨ ወለበዓል፡ ያሐዩ፡ ሎ
ሙ፡ አሐደ፡ እምነ፡ ሙቁሐ
፯ ን፡ ዘኢብደሩ፨ ወሀሎ፡ አሐዱ፡
ዘስሙ፡ በርባን፡ ሙቁሕ፡
ምስለ፡ እለ፡ ገብሩ፡ ሀከከ፡
ወምስለ፡ ቀተልተ፡ ነፍስ፨
፰ ወዓርጉ፡ ሕዝብ፡ ወከልሑ፡
ወሰአሉ፡ ይገብር፡ ሎሙ፡ በ
፱ ከመ፡ ያለምድ፨ ወአውሥአ፡
ጲላጦስ፡ ወይቤሎሙ፡ ት
ፈቅዱኑ፡ እደዎ፡ ለክሙ፡
ለንጉሠ፡ አይሁድ፨
፲ እስመ፡ የአምሮሙ፡ ከመ፡

ዷት፡ ለጲላጦስም፡ አሳል
ፈው፡ ሰጡት፨ ማቴ፡፳፯። ሉቃ፡፳፫፨
፪ ዮሐ፡፲፰፨ ጲላጦስም፡ የአይሁ
ድ፡ ንጉሥ፡ አንተ፡ ነህን፡ ብሎ፡
ጠየቀው፡ ኢየሱስም፡ መል
ሶ፡ አንተ፡ ትላለህ፡ አለው፨
፫ የካህናት፡ አለቆችም፡ በብ
ዙ፡ ነገር፡ ከሰሱት፡ እርሱ፡ ግ
ን፡ ምንም፡ አልመለሰም፨
፬ ጲላጦስም፡ ደግሞ፡ ይህን፡ ያ
ህል፡ ሲያሳጡህ፡ ምንም፡ አት
መልስምን፡ ብሎ፡ ጠየቀው።
፭ ኢየሱስ፡ ግን፡ ምንም፡ አልመ
ለሰለትም፡ ጲላጦስ፡ እስኪ
ደነቅ፡ ድረስ፨ ም፡፲፮፡፳፩፨ ኢሳ፡፶፫፡
፮ ፯፨ በየበዓሉም፡ ሕዝቡ፡ የወ
ደዱት፡ አንድ፡ እሥር፡ ይፈታ
፯ ላቸው፡ ነበረ፨ ሁከት፡ ካደረ
ጉና፡ ነፍስ፡ ከገደሉ፡ ሽፍቶ
ችም፡ ጋራ፡ የታሠረ፡ በርባን፡
የሚሉት፡ አንድ፡ ሰው፡ ነበረ፤
፰ ሕዝቡም፡ ወጥተው፡ ጮሁ፡ እ
ንደ፡ ልማዱም፡ ያደርግላቸው፡
፱ ዘንድ፡ ለመኑ፨ ጲላጦስ፡ ግን፡
የአይሁድን፡ ንጉሥ፡ እፈታ
ላችሁ፡ ዘንድ፡ ትወዳላችሁ
ን፡ ብሎ፡ መለሰላቸው፨
፲ የካህናት፡ አለቆች፡ በቅንኣ

በቅንዓቶሙ፡ አግብዕዎ፡ ሊ
ቃነ፡ ካህናት፨
፳፩ ወሊቃነ፡ ካህናትሰ፡ ሆኮሙ፡
ለሕዝብ፡ ከመ፡ በርባንሃ፡ ይ
ስአሉ፡ ያሕዩ፡ ሎሙ።
፳፪ ወካዕበ፡ አውሥአ፡ ጲላጦስ፡
ወይቤሎሙ፡ ምንተ፡ እንከ፡
ትፈቅዱ፡ እረስዮ፡ ለዘተብህ
፳፫ ለ፡ ንጉሠ፡ አይሁድ፨ ወካዕበ፡
ከልሑ፡ ኵሎሙ፡ ወይቤሉ፡
፳፬ ስቅሎ፨ ወይቤሎሙ፡ ጲላጦ
ስ፡ ምንተ፡ እኩየ፡ ገብረ፤ ወ
ፈድፋደ፡ ጸርሑ፡ ወይቤሉ፡
፳፭ ስቅሎ፨ ወመከረ፡ ጲላጦስ፡ ይ
ግበር፡ ፈቃዶሙ፡ ለሕዝብ፡
ወአሕየወ፡ ሎሙ፡ በርባን
ሃ፡ ወቀሠፎ፡ ለእግዚእ፡ ኢየ
ሱስ፡ ወወሀቦሙ፡ ይስቅልዎ፡
፳ ወአብዕዎ፡ ሐራ፡ ውሣጤ፡ ዓ
ፀድ፡ ኀበ፡ ምኵናን፡ ወጸውዑ፡
ኵሎ፡ ሠገራተ፡ ሰጲራ።

፳ ወአልበስዎ፡ ሜላተ፡ ወጸፈሩ፡
አክሊለ፡ ዘሦክ፡ ወአስተቀ
ጸልዎ፡ ላዕለ፡ ርእሱ። ወይሣ
፳፰ ለቅዎ፨ ወይብልዎ፡ በሐ፡ ንጉ
ሥሙ፡ ለአይሁድ፨

ት፡ አሳልፈው፡ እንሰጡት፡
ያውቅ፡ ነበረና፨ ዮሐ፡ ፲፩፡ ፵፰፨
፳፩ የካህናት፡ አለቆችም፡ በርባ
ንን፡ ይፈቱላቸው፡ ዘንድ፡ እ
ንዲለምኑ፡ ሕዝቡን፡ አባበ
፳፪ ሉ፨ ጲላጦስም፡ መልሶ፡ የአ
ይሁድ፡ ንጉሥ፡ የተባለውን፡
ምን፡ ላድርገው፡ ትሻላችሁ፡
፳፫ አላቸው፨ ደግመኛም፡ ስቀለ
ው፡ እያሉ፡ ጮሁ፨
፳፬ ጲላጦስም፡ ምን፡ ክፉ፡ አደረ
ገ፡ አላቸው፡ እርሳቸው፡ ግን፡
ስቀለው፡ እያሉ፡ ጩኸት፡
፳፭ አበዙ፨ ጲላጦስም፡ የሕዝቡ
ን፡ ፈቃድ፡ ያደርግ፡ ዘንድ፡
ወደደ፤ በርባንንም፡ ፈታላ
ቸውና፡ ኢየሱስን፡ ገርፎ፡
ይሰቅሉ፡ ዘንድ፡ አሳልፎ፡ ሰ
፳ ጣቸው፨ ጭፍሮችም፡ ወደ፡ ፍ
ርድ፡ ሰፍራ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ ይ
ዘውት፡ ገቡ፡ ጭፍራንም፡ ሁ
ሉ፡ አከማቹበት፨
፳ ቀይ፡ ሐርም፡ አለበሱት፡ የሾ
ህ፡ አክሊልም፡ ጐነጐኑና፡ በ
ራሱ፡ ላይ፡ ደፍተው፡ ዘበቱ
፳፰ በት፨ እንዲህም፡ ይሉት፡ ነበ
ር፡ የአይሁድ፡ ንጉሥ፡ ሆይ፡
ሰላም፡ ላንተ፡ ይሁን፨

፲፱ ወይኰርእዎ፡ ርእሶ፡ በሕለት፡
ወይዌርቅዎ፡ ውስተ፡ ገጹ፡
ወያስተበርኩ፡ ወይሰግዱ፡
ሎቱ።

፳ ወሶበ፡ ተሣለቁ፡ ላዕሌሁ፡ ሰለ
ብዎ፡ ውእተ፡ ሜላተ፡ ወአል
በስዎ፡ አልባሲሁ፡ ወወሰድ
ዎ፡ ኀበ፡ ይሰቅልዎ። ፳፩ ወዐበጡ፡
አሐደ፡ ኀላፌ፡ ፍኖት፡ ዘስ
ሙ፡ ስምዖን፡ ቀሬናዊ፡ አተ
ወ፡ እምሐቅል፡ ወውእቱ፡
እምአቡሆሙ፡ ለእለ፡ እስክ
ንድሮስ፡ ወለርፎስ፡ ከመ፡ ይ
፳፪ ፁር፡ መስቀሎ። ወወሰድዎ፡ ብ
ሔረ፡ ጎልጎታ፡ ዘበትርጓሜ
ሁ፡ ይብልዎ፡ ቀራንዮ፡ መካን።

፳፫ ወወሀብዎ፡ ይስተይ፡ ወይነ፡
ምስለ፡ ከርቤ፡ ቱሱሕ፡ ወአ
በየ፡ ሰትዮ።

፳፬ ወሶበ፡ ሰቀልዎ፡ ተዓፀው፡ ዱ
በ፡ አልባሲሁ፡ ወተካፈሉ፡
ዘከመ፡ ይነሥኡ።

፳፭ ወሠለስቱ፡ ሰዓት፡ ውእቱ፡ ሶ
፳፮ ቤሃ፡ ገኢ፡ ይሰቅልዎ። ወኮነ፡
ላዕሌሁ፡ መጽሐፈ፡ ጌጋዩ፡ ዘ
ይብል፡ ዝንቱ፡ ውእቱ፡ ንጉሥ
፳፯ ሙ፡ ለአይሁድ። ወሰቀሉ፡ ም
ስሌሁ፡ ክልኤተ፡ ፈያተ፡ አሐ

፲፱ ራሱንም፡ በዘንግ፡ ይመቱት
ና፡ ይተፉበትም፡ ነበሩ፡ በጉ
ልበታቸውም፡ ተንበርክከ
ው፡ ይሰግዱለት፡ ነበሩ።

፳ ከዘበቱበትም፡ በኋላ፡ ቀዩን፡
ልብስ፡ ገፈፉና፡ ልብሱን፡ አ
ልብሰው፡ ሊሰቅሉት፡ አወ
፳፩ ጡት። ስምዖን፡ ቀሬናዊ፡ የተ
ባለም፡ አንድ፡ መንገድ፡ አላ
ፊ፡ እርሱም፡ የእለ፡ እስክን
ድሮስና፡ የሮፎስ፡ አባት፡ ከ
ውጭ፡ ሲመጣ፡ መስቀሉን፡ ይ
ሸከም፡ ዘንድ፡ ገተቱ። ሮሜ፡
፳፪ ፲፮፡ ፲፫። ትርጓሜው፡ የራስ፡ አጽ
ንት፡ ቦታ፡ ወደ፡ ተባለ፡ ወደ፡ ጎ
ልጎታም፡ ወሰዱት።

፳፫ በከርቤ፡ የተደባለቀ፡ ወይን፡
ይጠጣ፡ ዘንድ፡ ሰጡት፡ እርሱ፡
ግን፡ አልጠጣውም። መዝ፡ ፷፱፡

፳፬ ፳፩። በሰቀሉትም፡ ጊዜ፡ በልብ
ሱ፡ ላይ፡ ዕፃ፡ ተጣጣሉና፡ እን
ደረሳቸው፡ ተካፈሉ። መዝ፡ ፳፪

፳፭ ፲፰። የሰቀሉትም፡ ጊዜ፡ ሦስት፡
፳፮ ሰዓት፡ ነበር። የበደሉም፡ ጽ
ሕፈት፡ ደብዳቤ፡ የአይሁድ፡
ንጉሥ፡ የሚል፡ በላዩ፡ ላይ፡ ነ
፳፯ በር። ከእርሱም፡ ጋራ፡ አንዱን፡
በቀኙ፡ አንዱንም፡ በግራው፡

ዲ፡ በየማኑ፡ ወአሐዱ፡ በጸጋ
ሙ። ፳፰ ወተፈጸመ፡ ዘይቤ፡ መ
ጽሐፍ፡ ተኈለቈ፡ ምስለ፡ ገበ
ርተ፡ ዓመፃ። ፳፱ ወኃለፍትኒ፡ ይ
ጸርፉ፡ ላዕሌሁ፡ ወየሐውሱ፡
ርእሶሙ፡ ወይቤልዎ፡ ኦ ዘይ
ነሥቶ፡ ለቤተ፡ መቅደስ፡ ወበ
ሠሉስ፡ ዕለት፡ የሐንፆ።

፴ አድኅን፡ ርእሰከ፡ ወረድ፡ እስ
ኩ፡ እመስቀልከ። ፴፩ ወከማሁ፡
ሊቃነ፡ ካህናትኒ፡ ወጸሐፍት፡
ይሣለቁ፡ ላዕሌሁ፡ ወይብል
ዎ፡ ዘባዕደ፡ ያድኅን፡ ወርእ
ሶ፡ ኢይክል፡ አድኅኖ።

፴፪ ወክርስቶስ፡ ውእቱ፡ ንጉሠ፡
እስራኤል፡ ለይረድ ኪ፡ ይእ
ዜ፡ እምነ፡ መስቀሉ፡ ወንርአ
ይ፡ ወንእመን፡ ቦቱ፡ ወእለሂ፡
ተሰቅሉ፡ ምስሌሁ፡ ይዘነጕ
ጕዎ።
፴፫ ወሶበ፡ ኮነ፡ ጊዜ፡ ቀትር፡ ጸል
መ፡ ጸሐይ፡ ወኵሉ፡ ዓለም፡
ጸልመ፡ እስከ፡ ተሱት፡ ሰዓት።
፴፬ ወጊዜ፡ ተሱዓት፡ ሰዓት፡ ገዐረ፡
እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ በዓቢይ፡
ቃል፡ ወይቤ፡ ኤሎሂ፡ ኤሎሂ፡

አድርገው፡ ሁለት፡ ወንበዴች፡
ሰቀሉ። ፳፰ መጽሐፍ፡ ከበደለኞ
ኞች፡ ጋራ፡ ተቈጠረ፡ ያለውም፡
ተፈጸመ። ኢሳ፡ ፶፫፡ ፲፪። ፳፱ መንገድ፡
አላፎችም፡ ይሰድቡት፡ ነበ
ሩ፡ ራሳቸውንም፡ እየነቀነቁ፡
ይሉ፡ ነበሩ፡ ቤተ፡ መቅደስን፡
የምታፈርሰው፡ በሶስት፡ ቀ
ንም፡ የምትሠራው፡ አወይ።
ም፡ ፲፬፡ ፶፰። ፴ አራስህን፡ አድን፡ ከ
መስቀልም፡ ውረድ። ፴፩ እንዲ
ሁም፡ ደግሞ፡ የካህናት፡ አለ
ቆችና፡ ጸፎችም፡ እርስበር
ሳቸው፡ ያፌዙበት፡ ነበር፡ እ
ንዲህ፡ እያሉ፡ ሌሎችን፡ ያ
ድናል፡ ራሱን፡ ግን፡ ማዳን፡ አ
ይችልም። ፴፪ አንተንም፡ እናም
ን፡ ዘንድ፡ የእስራኤል፡ ንጉ
ሥ፡ ክርስቶስ፡ ዛሬ፡ ከመስቀ
ል፡ ይውረድ፤ ከእርሱም፡ ጋ
ራ፡ የተሰቀሉት፡ ያሸምዋጥ
ጡት፡ ነበሩ። ማቴ፡ ፲፯፡ ፵፡ ፬።
፴፫ ቀትርም፡ ፮ ሰዓት፡ በሆነ፡ ጊ
ዜ፡ ፀሐይ፡ ጨለመች፡ እስከ፡
ዘጠኝ፡ ሰዓትም፡ በምድር፡ ላ
ይ፡ ጨለማ፡ ሆነ። ፴፬ በዘጠነኛው
ም፡ ሰዓት፡ ኢየሱስ፡ ኤሎሄ፡
ኤሎሄ፡ ላማ፡ ሰበቅታኒ፡ ብሎ

ሳማ፡ ሰበቅታኒ፡ ዘበትርጓሜ
ሁ፡ ይብል፡ አምላኪየ፡ አምላ
ኪየ፡ ለምንት፡ ኀደገኒ ፨
፴፭ ወቦ፡ እለ፡ ይቤሉ፡ እምእለ፡ ይ
ቀውሙ፡ ህየ፡ ኤልያስሃ፡ ይጼ
፴፮ ውዕ ፨ ወሮጸ፡ አሐዱ፡ ወመል
ኦ፡ ሰፍነገ፡ ብኂአ፡ ወአሠሩ፡
በሕለት፡ ወአስተዮ፡ ወይቤ፡
ኅድጉ፡ ንርአይ፡ ለእመ፡ ይ
መጽእ፡ ኤልያስ፡ ያውርዶ ፨

፴፯ ወገዐረ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ በ
ዓቢይ፡ ቃል፡ ወመጠወ፡ ነፍ
፴፰ ሶ፡፡ ወተሠጠ፡ መንጦላዕተ፡
ምኵራብ፡ ለክልኤ፡ እምላ
፴፱ ዕሉ፡ እስከ፡ ታሕቱ ፨ ወርእዮ፡ ሐራዊ፡ ለቃ፡
፻፡ ዘይቀውም፡ መንጸሬ፡ ከመ፡
ከመዝ፡ ገዐሮ፡ ሞተ፡ ይቤ፡ አ
ማን፡ ዝንቱ፡ ብእሲ፡ ወልዱ፡ እ
ግዚአብሔር፡ ውእቱ ፨

፵ ወሀለዋ፡ አንስት፡ ይቀውማ፡
ወይኔጽራ፡ እምርሑቅ፡ ወ
ውእቶን፡ ማርያም፡ መግደ
ላዊት፡ ወማርያም፡ እንተ፡
ያዕቆብ፡ ዘይንዕስ፡ ወእሙ፡
ለዮሳ፡ ወሰሎሜ ፨
፵፩ እለ፡ ተለዋሁ፡ እምገሊላ፡ ወ

በታላቅ፡ ቃል፡ ጮኸ፡ ትርጓ
ሜውም፡ አምላኬ፡ አምላኬ፡
ለምን፡ ተውኸኝ፡ ማለት፡ ነው።
፴፭ መዝ፡ ፳፩፡ ፩ ፨ በዚያም፡ ከቆሙት፡
ሰዎች፡ አነሆ፡ ኤልያስን፡ ይጠ
፴፮ ራል፡ አሉ ፨ አንዱም፡ ሩጦ፡ ስ
ፍንጉን፡ መጣጣ፡ መላበትና፡
በዘንግ፡ ዓሥር፡ አጠጣው፡
እንዲህ፡ ሲል፡ ተዉት፡ ኤል
ያስ፡ መጥቶ፡ ያወርደው፡ እ
ንደ፡ ሆነ፡ እንይ ፨
፴፯ ኢየሱስም፡ በታላቅ፡ ቃል፡ ጮ
ኸ፡ ነፍሱንም፡ ሰጠ ፨
፴፰ የቤተ፡ መቅደስም፡ መጋረጃ፡
ከላይ፡ እስከ፡ ታች፡ ከሁለት፡
፴፱ ተቀደደ ፨ በእንጻሩም፡ ቁሞ፡
የነበረው፡ የመቶው፡ አለቃ፡
እንዲህ፡ ጮሆ፡ ነፍሱን፡ እን
ደ፡ ሰጠ፡ ባየ፡ ጊዜ፡ ይህ፡ ሰው፡
በእውነት፡ የእግዚአብሔ
ር፡ ልጅ፡ ነው፡ አለ ፨
፵ ደግሞም፡ በሩቅ፡ የሚያዩ፡
ሴቶች፡ ነበሩ፡ እርሳቸውም፡
መግደላዊት፡ ማርያምም፡
የታናሹ፡ የያዕቆብንና፡ የዮ
ሳ፡ እናት፡ ሰሎሜም፡ ነበሩ ፨
ሉቃ፡ ፳፫፡ ፵፱፡ ፲ ፨
፵፩ እነዚህም፡ በገሊላ፡ ሳለ፡ ይ

ተለዐካሁ፡ ወገዐዳትሂ፡ ብዙ
ኃት፡ እለ፡ ዓርጋ፡ ምስሌሁ፡ ኢ
የሩሳሌም።

፵፪ ወመስዮ፡ ዓርብ፡ እሚሃ፡ በእተ፡
ሰንበት፡ ውእቱ።

፵፫ መጽአ፡ ዮሴፍ፡ እምአርማቴያ
ስ፡ ብእሲ፡ ኄር፡ ወጠቢብ፡ ወ
ውእቱ፡ ይሴፎ፡ መንግሥተ፡
እግዚአብሔር፡ ወተሀበለ፡ ወ
ቦአ፡ ኀበ፡ ጲላጦስ፡ ወሰአለ፡
ሥጋሁ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፨

፵፬ ወአንከረ፡ ጲላጦስ፡ እፎ፡ ሞ
ተ፡ ወጸውዖ፡ ለሐራዊ፡ ወተ
ስእሎ፡ ወይቤሎ፡ ወድአኑ፡
ሞተ፡ ወይቤ፡ እወ፡ ሞተ።

፵፭ ወአእሚሮ፡ በኀበ፡ ሐራዊ፡ ከ
መ፡ ሞተ፡ ሶቤሃ፡ ጸገዎ፡ ለዮ
ሴፍ፡ ሥጋሁ።

፵፮ ወተሣየጠ፡ ሰንዱናተ፡ ወአው
ረዶ፡ ወገነዞ፡ በሰንዱናት፡ ወ
ቀበሮ፡ ውስተ፡ መቃብር፡ ዘአ
ውቀረ፡ ውስተ፡ ኰኵሕ፡ ወአ
ንኰርኰረ፡ እብነ፡ ውስተ፡ እ
ፈ፡ መቃብር።

፵፯ ወማርያም፡ መግደላዊት፡ ወ
ማርያም፡ እመ፡ ዮሳ፡ ርእያ።

ከተሉትና፡ ያገለግሉት፡ የ
ነበሩ፡ ናቸው፡ ሌሎችም፡
ብዙ፡ ከእርሱ፡ ጋራ፡ ወደ፡ ኢ
የሩሳሌም፡ የወጡ፡ ነበሩ።

፵፪ በመሸም፡ ጊዜ፡ ዓርብ፡ ማታ፡
የሰንበት፡ መግቢያ፡ ነበር።

፵፫ ዮሐ፡ ፲፱፡ ፴፰ ። ደግ ሰውና፡ ምክር፡
አዋቂ፡ እርሱም፡ የእግዚአ
ብሔርን፡ መንግሥት፡ ተስፋ፡
ያደርግ፡ የነበረ፡ የአርማት
ያሱ፡ ዮሴፍም፡ መጣ፡ ደፍሮ
ም፡ ወደ፡ ጲላጦስ፡ ገባና፡ የኢ
የሱስን፡ ሥጋ፡ ለመነ።

፵፬ ጲላጦስ
ም፡ እንዴት፡ እንደ፡ ሞተ፡ አደ
ነቀ፡ የመቶ፡ አለቃውንም፡ ጠ
ርቶ፡ ፈጽሞ፡ ሞተን፡ ብሎ፡
ጠየቀው። የመቶ፡ አለቃውም፡

፵፭ አዎን፡ ሞተ፡ አለው። ነገሩንም፡
ከመቶው፡ አለቃ፡ ባወቀ፡ ጊዜ፡
ሥጋውን፡ ለዮሴፍ፡ ሰጠው።

፵፮ እርሱም፡ በፍታ፡ ገዛና፡ አው
ርዶ፡ በበፍታ፡ ገነዘው፡ በአ
ለት፡ ላይ፡ ባሳነፀው፡ መቃብ
ርም፡ ቀበረው፡ የመቃብሩን
ም፡ ደጅ፡ አፍ፡ ደንጊያ፡ አገላ
ብጦ፡ ገጠመው።

፵፯ የመግደላዊቱ፡ ማርያምና፡
የዮሳ፡ እናት፡ ማርያምም፡

ኀበ፡ ቀበርዎ።

፠ ፠ ፠ ፠ ፠ ፠

ምዕራፍ ። ፲፮ ።

እንደ፡ ተነሣ፡ ዕማርያም፡ መግደላዊት
ና፡ ሰሊሎሜም፡ ሐዋርያት፡ እንደተገለጠ።

፩ ወሶበ፡ ኀለፈ፡ ሰንበት፡ ማር
ያም፡ መግደላዊት፡ ወማርያ
ም፡ እሙ፡ ለያዕቆብ፡ ወሰሎ
ሜ፡ ተሣየጣ፡ አፈው፡ ከመ፡
ይምጽአ፡ ወይቅብዋ፡ ሥጋ
፪ ሁ። ወሐራ፡ ወእንግሐ፡ ጥቀ፡
ሐዊረ፡ ኀበ፡ መቃብር፡ በእ
ሑድ፡ ሰንበት፡ ሶበ፡ ሠረቀ፡
ፀሐይ።
፫ ወይቤላ፡ በበይናቲሆን፡ መኑ፡
ይክሥተ፡ ለነ፡ ለዕብን፡ እም
ኆኅተ፡ መቃብር፡ ወዐባይ፡
፬ ይእቲ፡ ጥቀ። ወረዊጾን፡ ርእ
ያሃ፡ ለእብን፡ ኀበ፡ እንኰር
፭ ኵረት። ወበዊኦን፡ ውስተ፡ መ
ቃብር፡ ረከባ፡ አሐደ፡ ወረዛ፡
እንዘ፡ ይነብር፡ መንገለ፡ የ
ማን፡ ወይለብስ፡ አልባሰ፡
ንጹሐ፡ ወደንገፃ።
፮ ወይቤሎን፡ ኢትደንግፃ፡ ኢ
የሱስሃ፡ ናዝራዊ፡ ዘተሰቅ
ለ፡ ተኅሥሣ፡ ተንሥአ፡ ወኢሀ

የተቀበረበትን፡ ያዩ፡ ነበሩ።

፠ ፠ ፠ ፠ ፠ ፠

ምዕራፍ ። ፲፮ ።

የጥምቀቱን፡ ሥርዓት፡ እንዳስተማረ፡ ወ
ደ፡ ሰማይ፡ እንደ፡ ዓረገና፡ በእግዚአብሔ
ር፡ ቀኝ፡ እንደ፡ ተቀመጠ። ፠ ፠

፩ ሰንበትም፡ ባለፈ፡ ጊዜ፡ የመግ
ደላዊቱ፡ ማርያምና፡ ማርያም
ም፡ የያዕቆብ፡ እናት፡ ሰሎሚ
ም፡ መጥተው፡ ሥጋውን፡ ሊ
ቀቡት፡ ሽቱ፡ ገዙ። ማቴ፡ ፳፰ ፡ ሉቃ፡
፪ ፳፬ ፡ ዮሐ፡ ፳ ፡ ፩፡ ቆሮ፡ ፲፭። ከሳምን
ቱም፡ በመጀመሪያ፡ ቀን፡ እጅ
ግ፡ ማልደው፡ ገና፡ ፀሐይ፡ ሲ
ወጣ፡ ወደ፡ መቃብር፡ ሔዱ።
፫ እርስ፡ በርሳቸውም፡ ድንጊ
ያውን፡ ከመቃብሩ፡ ደጅ፡ አፍ፡
ማን፡ ያነሣልናል፡ አሉ፡ እጅ
፬ ግም፡ ትልቅ፡ ነበርና። ሲመለ
ከቱም፡ ድንጊያው፡ ተገልብጦ፡
፭ አዩ። ወደ፡ መቃብርም፡ በገቡ፡
ጊዜ፡ አንድ፡ ጕልማሳ፡ በስተ
ቀኝ፡ ፡ ተቀምጦ፡ ነጭ
መጐናጸፊያ፡ ለብሶም፡
፡ አዩና፡ ደነገጡ።
፮ እርሱም፡ አላቸው፡ አትደንግ
ጡ፡ የተሰቀለውንም፡ የና
ዝሬቱ፡ ኢየሱስን፡ ትሻላችሁ፡

ሎ፡ ዝየስ፡ ወናሁ፡ መካኑ፡
ኀበ፡ ተቀብረ።

፯ ወባሕቱ፡ ሑሩ፡ ወንግራሆ
ሙ፡ ለአርዳኢሁ፡ ወለጴጥ
ሮስ፡ ከመ፡ ይቅድሞሙ፡ ገ
ሊላ፡ ወበህየ፡ ይሬእዩዎ፡
በከመ፡ ይቤሎሙ።

፰ ወወፅአ፡ እምነ፡ መቃብር፡
ወጕየ፡ እስመ፡ አኀዞን፡ ረአ
ድ፡ ወድንጋፄ፡ ወኢነገራ፡ ወ
ኢለመኑሂ፡ እስመ፡ ፈርሃ።

፱ ወተንሢኦ፡ በጽባሕ፡ ፡ በ
እሑድ፡ ሰንበት፡ አስተርአ
ያ፡ ቅድመ፡ ለማርያም፡ መ
ግደላዊት፡ እንተ፡ እምኔሃ፡
አውፅአ፡ ስብዐተ፡ አጋንን
ተ።

፲ ወይእቲ፡ ሐዊራ፡ ዜነቶሙ፡
ለእለ፡ ምስሌሁ፡ ሀለዉ፡ ይ
ላሕዉ፡ ወይበክዩ።

፲፩ ወእሙንቱሂ፡ ሶበ፡ ሰምዑ፡
ከመ፡ አስተርአያ፡ ወሕያ
ው፡ ውእቱ፡ ፡ ኢአመንዋ።

እርሱ፡ ግን፡ ተነሥተዋል፡
ከዚህ፡ የለም፡ የተቀበረበ
ትም፡ ቦታው፡ እነሆ።

፯ ነገር፡ ግን፡ ሒዱ፡ ለደቀ፡
መዛሙርቱና፡ ለጴጥሮስ፡
ወደ፡ ገሊላ፡ ይቀድማችኋል፡
እንደ፡ ነገራችሁም፡ በዚያ፡ ት
ዩታላችሁ፡ ብላችሁ፡ ንገሩ
ዋቸው። ምዕ፡ ፲፬፡ ፳፰።

፰ ከመቃብርም፡ ሸሽተው፡ ወ
ጡ፡ መንቀጥቀጥና፡ መደነቅ
ም፡ ይዘዋቸው፡ ነበርና፡ ስለ
ፈሩ፡ ለማንም፡ አንዳች፡ አል
ተናገሩም።

፱ ከሳምንቱም፡ በመጀመሪ
ያው፡ ቀን፡ ማለዳ፡ ተነሥቶ፡
ሰባት፡ አጋንንት፡ ላወጣላት፡
ለመግደላዊቱ፡ ማርያም፡
አስቀድሞ፡ ተገለጠላት። ሉ
ቃ፡ ፰፡ ፪።

፲ እርስዋም፡ ሒዳ፡ ከእርሱ፡
ጋራ፡ ለኖሩትና፡ ሲያዝኑና፡
ሲያለቅሱም፡ ለነበሩት፡ ነ
ገረቻቸው።

፲፩ እርሳቸውም፡ ሕያው፡ እንደ
ሆነ፡ ለእርስዋም፡ እንደ፡ ተ
ገለጠላት፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ አ
ላመኑዋትም።

፲፪ ወእምዝ፡ አስተርአዮሙ፡ ለክልኤቱ፡ እምኔሆሙ፡ በካልእ፡ ራእይ፡ እንዘ፡ የሐውሩ፡ ሐቅለ።

፲፫ ወሖሩ፡ እሙንቱሂ፡ ወዜነው፡ ለቢጾሙ፡ ወሎሙኒ፡ ኢአምንዎሙ።

፲፬ ወእምድኅረዝ፡ ካዕበ፡ እንዘ፡ ይረፍቁ፡ ዐሠርቱ፡ ወአሐዱ፡ አስተርአዮሙ፡ ወገሠፃሙ፡ በእንተ፡ ሕፀፀ፡ አሚኖቶሙ፡ ወግዕዘ፡ ፅንዐ፡ ልቦሙ፡ እስመ፡ ለእለ፡ ርእዩዎ፡ ከመ፡ ተንሥአ፡ ኢአምንዎሙ።

፲፭ ወይቤሎሙ፡ ሑሩ፡ ውስተ፡ ኵሉ፡ ዓለም፡ ወስብኩ፡ ወንጌለ፡ ለኵሉ፡ ፍጥረት።

፲፮ ዘአምነ፡ ወዘተጠምቀ፡ ይድኅን፡ ወዘሰ፡ ኢአምነ፡ ይደየን።

፲፯ ወተአምር፡ ባሕቱ፡ ለእለ፡ አምኑ፡ በዝንቱ፡ ይተሉዎሙ፡ በስመ፡ ዚአየ፡ አጋንንተ፡ ያወፅኡ፡ ወይትናገሩ፡ በልሳናት፡ ሐዲሳት።

፲፰ ወአራዊተ፡ ምድር፡ ይእኂ

፲፪ ከዚያ፡ በኋላ፡ ከእነርሳቸው፡ ለሁለቱ፡ ወደ፡ አገር፡ ሲሔዱ፡ በመንገድ፡ በሌላ፡ መልክ፡ ተገለጠ። ሉቃ፡ ፳፬፡ ፲፫።

፲፫ እርሳቸውም፡ ሒደው፡ ለባልንጀሮቻቸው፡ ነገሯቸው፡ እነዚያንም፡ ደግሞ፡ አላመኗቸውም።

፲፬ በኋላም፡ ለአሥራ፡ አንዱ፡ ተቀምጠው፡ ሲበሉ፡ ተገለጠ፡ ስለ፡ ሃይማኖታቸው፡ መጕደልና፡ ስለ፡ ልባቸውም፡ ጽናት፡ ገሠፃቸው፡ እነዚያን፡ ተነሥቶ፡ ያዩትን፡ አላመናቸውምና።

፲፭ አላቸውም፡ ወደ፡ ዓለም፡ ሁሉ፡ ሒዱችሁ፡ ለፍጥረቱ፡ ሁሉ፡ ወንጌልን፡ ስበኩ። ማቴ፡ ፳፰፡ ፲፱። ፲፱።

፲፮ ያመነም፡ የተጠመቀም፡ ይድናል፡ ያላመነ፡ ግን፡ ይፈረድበታል። የሐዋ፡ ፪። ፴፰።

፲፯ ያመኑትን፡ ግን፡ ይህች፡ ተአምራት፡ ትከተላቸዋለች፡ በስሜም፡ ሰይጣናትን፡ ያወጣሉ፡ በሌላም፡ አዲስ፡ ቋንቋ፡ ይናገራሉ። የሐዋ፡ ፪፡ ፬፡ ፲፩፡ ፲፡ ፵፮። ፲፱፡ ፲፯።

፲፰ እባቦችንም፡ የያዛሉ፡ የሚ

ዙ፡ ወዘኒ፡ ይቀትል፡ ለአመ፡ ሰትዩ፡ አልቦ፡ ዘይነክዮሙ፡ ወዲበ፡ ድውያን፡ እደዊሆሙ፡ ያነብሩ፡ ወይሚጥኑ።

ግድሉም፡ ነገር (መርዝ፡) ቢጠጡ፡ አይጐዳቸውም፡ እጃቸውንም፡ በድውያን፡ ላይ፡ ይጭናሉ፡ እነርሳቸው፡ ይድናሉ። ሉቃ፡ ፲፡ ፲፱። የሐዋ፡ ፳፰፡ ፫፡ ያዕ፡ ፭፡ ፲፬። ፲፭።

፲፱ ወእግዚእነሰ፡ ኢየሱስ፡ እምድኅረ፡ ተናገሮሙ፡ ዓርገ፡ ውስተ፡ ሰማይ፡ ወነበረ፡ በየማነ፡ እግዚአብሔር፡ አቡሁ።

፲፱ ጌታችንም፡ ከተናገራቸው፡ በኋላ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ዓረገ፤ በአባቱም፡ በእግዚአብሔር፡ ርም፡ቀኝ፡ ተቀመጠ። የሐዋ፡ ፩፡ ፩፡ ፲፪።

፳ ወወፂኦሙ፡ እሙንቱ፡ ሰበኩ፡ በኵለሄ፡ እንዘ፡ እግዚእ፡ ይረድእ፡ ወቃሎ፡ ያፀንዕ፡ በተአምር፡ ዘይተሉ፡ አሜን።

፳ እነርሳቸውም፡ ወጥተው፡ በስፍራው፡ ሁሉ፡ ሰበኩ፡ ጌታም፡ ይረዳቸው፡ ነበረ፡ ቃሉንም፡ በምትከተል፡ ተአምራት፡ ያጸና፡ ነበረ። አሜን። ዕብ፡ ፪፡ ፬።

ተፈጸመ፡ ወንጌለ፡ ማርቆስ።

የማርቆስ፡ ወንጌል፡ ተፈጸመ።

ኀበስራተ፡ ሉቃስ፡ ወንጌላዊ፡ አሐዱ፡ እምሰብአ፡ ወክልኤቱ፡ አርድእት። ጸሎቱ፡ ወበረከቱ፡ የሃሉ፡ ምስለ፡ ንጉሥነ፡ ኀይለ፡ ሥላሴ፡ ወምስለ፡ ንግሥትነ፡ ወለተ፡ ጊዮርጊስ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን።

ምዕራፍ፡ ፩ ።

ምዕራፍ፡ ፩ ።

ስለ፡ መጥምቁ፡ ዮሐንስ፡ ልደት። ስለ፡ ገብርኤል፡ ብስራት። እመቤታችን፡ ወደ፡ ኤልሳቤጥ፡ እንደ፡ ሔደች። ስለ፡ ዮሐንስ፡ ስምና፡ ስለ፡ ዘካርያስ፡ መናገር።

፩ እስመ፡ ብዙኃን፡ እለ፡ አኀዙ፡ ደንገሩ፡ ወደምሀሩ፡ በእንተ፡ ግብር፡ ዘአምኑ፡ በላዕሌነ።

፪ በከመ፡ መጠውኑ፡ እለ፡ ቀዲሙ፡ ርእዮቶ፡ ወተልእክዎ፡ ለቃሉ።

በእኛ፡ ዘንድ፡ ፈጽሞ፡ የታመነውን፡ የሥራውን፡ ነገር፡ በሥርዓት፡ ሊጽፉና፡ ሊያስተምሩ፡ የጀመሩ፡ ብዙ፡ ናቸውና። ከእኛ፡ አስቀድሞ፡ በዓይን፡ ያዩትና፡ የቃሉ፡ አገልጋዮች፡ የነበሩ፡ እንደ፡ ነገሩን።

፫ ወረትዐኒ፡ ሊተኒ፡ እትልዎ፡ እምጥንቱ፡ ወጥዩቀ፡ ኵሉ፡ በበመትልው፡ እጽሐፍ፡ ለከ፡ ኦ አዚዝ፡ ቴዎፍሎስ።

፫ ዮሐ፡ ፩፡ ፲፬ ። ፩ ጴጥ፡ ፩፡ ፲፮። የከበርክ፡ ቴዎፍሎስ፡ ሆይ፡ እኔም፡ ደግሞ፡ ከጥንት፡ ጀምሬ፡ በእውነት፡ ተከትዬዋለሁና፡ የተረዳሁትን፡ ሁሉ፡ በየተራው፡ እጽፍልህ፡ ዘንድ፡ ወደድሁ።

፬ ከመ፡ ታእምር፡ ጥዩቀ፡ ድድቀ፡ ኃይለ፡ ነገር፡ ዘተመሐርከ።

፬ የሐዋ፡ ፩፡ ፩። የተማርከውን፡ እውነተኛ፡ ትምህርት፡ ጠንቅቀህ፡ ታውቅ፡ ዘንድ። ፩፡ ጢሞ፡ ፫፡ ፲፭።

፭ ወኮነ፡ በመዋዕለ፡ ሄሮድስ፡ ንጉሠ፡ ይሁዳ፡ ሀሎ፡ አሐዱ፡ ካህን፡ ዘስሙ፡ ዘካርያስ፡ በመዋዕለ፡ አብያ፡ ወብእሲቱኒ፡ እምአዋልደ፡

፭ በይሁዳ፡ ንጉሥ፡ በሄሮድስ፡ ዘመን፡ ከአብያ፡ ወገን፡ (ክፍል)፡ ዘካርያስ፡ የሚባል፡ አንድ፡ ካህን፡ ነበረ፡ ሚስቱም፡ ከአሮን፡ ልጆች፡

አሮን፡ ወስማ፡ ኤልሳቤጥ።

፮ ወክልኤሆሙ፡ ጻድቃን፡ እሙንቱ፡ በቅድመ፡ እግዚአብሔር፡ ወየሐውሩ፡ በኵሉ፡ ትእዛዙ፡ ወሥርዓቱ፡ ለእግዚአብሔር፡ ዘእንበለ፡ ነውር፡ ወንጹሓን፡ እሙንቱ።

፯ ወአልቦሙ፡ ውሉድ፡ እስመ፡ መካን፡ ይእቲ፡ ኤልሳቤጥ፡ ወ፪ኤሆሙ፡ ልሂቃን፡ እሙንቱ፡ ወኀለፈ፡ መዋዕሊሆሙ። ፰ ወእምዝ፡ እመ፡ ይገብር፡ ግብረ፡ ክህነት፡ በዐብረቱ፡ ቅድመ፡ እግዚአብሔር።

፱ በከመ፡ ይገብሩ፡ ካህናት፡ በጽሐ፡ ጊዜ፡ የዐጥን፡ ወቦአ፡ ቤተ፡ መቅደሱ፡ ለእግዚአብሔር።

፲ ወኵሉ፡ ሕዝብ፡ ሀለው፡ በምልዓሙ፡ ይጼልዩ፡ በአፍአ፡ በጊዜ፡ ሰዓተ፡ ዕጣን።

፲፩ ወአስተርአዮ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ መንገለ፡ የማነ፡ ምሥዋዐ፡ ዘዕጣን። ፲፪ ወሶበ፡ ርእዮ፡ ደንገፀ፡ ዘካርያስ፡ ወፍርሃት፡ ወረዓድ፡ ላዕሌሁ።

፲፫ ወይቤሎ፡ መልአክ፡ ኢትፍራህ፡ ዘካርያስ፡ እስመ፡ ተሰምዐ፡ ጸሎትከ፡ ወብእሲትከኒ፡ ኤልሳቤጥ፡ ትወልድ፡ ለከ፡ ወልደ፡ ወትሰምዮ፡ ስሞ፡ ዮሐንስ።

ወገን፡ ናት፡ ስምዋም፡ ኤልሳቤጥ፡ ነበር። ፩፡ ዜና፡ ፳፬፡ ፲። ፮ ሁለቱም፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ጻድቃን፡ ነበሩ፡ በእግዚአብሔርም፡ ትእዛዝና፡ ሥርዓት፡ ያለነውር፡ የሚሔዱ፡ ንጹሓን፡ ነበሩ። ዘፍ፡ ፲፯፡ ፩። የሐዋ፡ ፳፫፡ ፩።

፯ ኤልሳቤጥም፡ መካን፡ ነበረችና፡ ልጅ፡ አልነበራቸውም፡ ሁለቱም፡ አርጅተው፡ ዘመናቸው፡ አልፎ፡ ነበር። ዘፍ፡ ፲፰፡ ፲፩። ፰ ከዚህም፡ በኋላ፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ በክህነት፡ ሥራ፡ ለማገልገል፡ ተራው፡ በሆነ፡ ጊዜ፡

፱ እንደ፡ ካህናት፡ ልማድ፡ የሚያጥንበት፡ ጊዜ፡ ሲደርስ፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ መቅደስ፡ ገባ። ዘፀአ፡ ፴፡ ፩፡ ፰። ፲ በዕጣንም፡ ጊዜ፡ ሕዝቡም፡ ሁሉ፡ በውጭ፡ ይጸልዩ፡ ነበር። ዘሌዋ፡ ፲፮፡ ፲፯። ፲፯። የሐዋ፡ ፲፡ ፭፡ ፲።

፲፩ የእግዚአብሔርም፡ መልአክ፡ በዕጣን፡ መሠዊያው፡ በስተቀኝ፡ ቁሞ፡ ታየው። ዘፀአ፡ ፴፡ ፩። ፲፪ ዘካርያስም፡ ባየው፡ ጊዜ፡ ደነገጠ፡ እጅግ፡ ፍርሃትም፡ ወደቀበት። መሳ፡ ፲፫፡ ፳፪፡ ፳፪።

፲፫ መልአኩም፡ አለው፡ ዘካርያስ፡ ሆይ፡ አትፍራ፡ ጸሎትህ፡ ተሰምቷልና፡ ሚስትህ፡ ኤልሳቤጥም፡ ልጅ፡ ትወልድልሃለች፡ ስሙንም፡ ዮሐንስ፡ ትለዋለህ። ፩፡ ዮሐ፡ ፳፡ ፲፬።

፲፬ ወይከውነከ፡ ትፍሥሕተ፡ ወሐ
ሤተ፡ ወብዙኃን፡ ይትፌሥሑ፡ በ
፲፭ ልደቱ፨ እስመ፡ ዓቢየ፡ ይከውን፡
ውእቱ፡ በቅድመ፡ እግዚአብሔ
ር፡ ወኢይሰቲ፡ ወይነ፡ ወሜሰ፡ ወ
ይመልዕ፡ ሳዕሌሁ፡ መንፈስ፡ ቅ
ዱስ፡ እምከርሠ፡ እሙ፨

፲፮ ወለብዙኃን፡ እምደቂቀ፡ እስ
ራኤል፡ ይመይጦሙ፡ ኀበ፡ እግ
ዚአብሔር፡ አምላኮሙ፨
፲፯ ወውእቱ፡ የሐውር፡ ቅድሜሁ፡
በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ወበኃይለ፡
ኤልያስ፡ ከመ፡ ይሚጥ፡ ልበ፡ አበ
ው፡ ኀበ፡ ውሉድ፡ ወለከሐድያን፡
ውስተ፡ ሕሊና፡ ጻድቃን፡ ከመ፡ ያ
ሥራዕ፡ ሕዝበ፡ ዘድልው፡ ለእግ
ዚአብሔር፨
፲፰ ወይቤሎ፡ ዘካርያስ፡ ለመልአ
ክ፡ እግዚአብሔር፡ በምንት፡ አ
አምር፡ ከመ፡ ይከውን፡ ዝንቱ፡
ናሁ፡ አነሂ፡ ልሂቅ፡ ወለብእሲት
፲፱ የኒ፡ ኀለፈ፡ መዋዕሊሃ፨ ወተሠጥ
ዎ፡ መልአክ፡ ወይቤሎ፡ አነ፡ ው
እቱ፡ ገብርኤል፡ ዘእቀውም፡
ቅድመ፡ እግዚአብሔር፡ ዘተፈ
ነውኩ፡ ኀቤከ፡ እንግርከ፡ ወእ
፳ ዜኑከ፡ ዘንተ፨ ወናሁ፡ ትከውን፡ በሃ

፲፬ ደስታም፡ አሌሌታም፡ ይሆንል፡
በመወለዱም፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ ደ
፲፭ ስ፡ ይላቸዋል፨ ቍ፡ ፳፫፡ ፫፨ በእግዚ
አብሔር፡ ፊት፡ ታላቅ፡ ይሆናል
ና፡ የወይንና፡ የማር፡ ጠጅም፡
አይጠጣም፡ ከእናቱም፡ ማኅፀ
ን፡ ጀምሮ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ያድ
ርበታል፨ መሳ፡ ፲፫፡ ፬፡ ፭፨ ማቴ፡ ፲፩፡ ፱፡ ፲፨
፲፮ ከእስራኤልም፡ ልጆች፡ ብዙዎ
ችን፡ ወደ፡ አምላካቸው፡ ወደ፡ እ
ግዚአብሔር፡ ይመልሳቸዋል።
፲፯ እርሱም፡ ያባቶችን፡ ልብ፡ ወደ፡
ልጆች፡ የማይታዘዙትን፡ ወደ፡ ጻ
ድቃን፡ ጥበብ፡ ይመልስ፡ ዘንድ፡ የ
ቀና፡ ሕዝብንም፡ ለእግዚአብሔ
ር፡ የተዘጋጀ፡ ያደርግ፡ ዘንድ፡ በ
ኤልያስ፡ መንፈስና፡ በኃይሉም፡
በፊቱ፡ ይሄዳል፨ ማቴ፡ ፲፯፡ ፲፩። ሚልክ፡
፲፰ ፫፡ ፩፡ ፬፡ ፯፨ ዘካርያስም፡ መልአኩን፡
እኔሆ፡ እኔ፡ ሽማግሌ፡ ነኝ፡ ሚስቴ
ም፡ ዘመንዋ፡ አልፎልና፡ ይህ፡ እ
ንደሆን፡ በምን፡ አውቃለሁ፡ አለ
፲፱ ው፨ መልአኩም፡ መልሶ፡ አለው፡
እኔ፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ የም
ቆመው፡ ገብርኤል፡ ነኝ፡ ይኽን
ንም፡ የምስራች፡ እነግርህ፡ ዘን
ድ፡ ተልኬ፡ መጣሁ፨ ዳን፡ ፰፡ ፲፮፨ ዕብ፡
፳ ፩፡ ፲፬፨ እነሆም፡ በጊዜው፡ የሚፈ

መ፡ ወኢትክል፡ ነቢበ፡ እስከ፡
አመ፡ ይከውን፡ ዝንቱ፡ እስመ፡
ኢአመንከኒ፡ ነገርየ፡ ዘይከው
ን፡ ወይትፌጸም፡ በዕድሜሁ።
፳፩ ወሀለወ፡ ሕዝብ፡ ይጸንሕዎ፡ ለ
ዘካርያስ፡ ወአንከርዎ፡ እስመ፡
ጐንደየ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡
፳፪ ወወፂኦ፡ ኀቢሆሙ፡ አፍአ፡ ስእ
ነ፡ ተናግሮቶሙ፡ ወአእመርዎ፡
ከመ፡ ቦ፡ ዘአስተርአዮ፡ በቤተ፡
መቅደስ፡ ወነበረ፡ ከማሁ፡ አን
ዘ፡ በሃም፡ ውእቱ፡ ወይኤምር
ሙ፡ በእዴሁ። ፳፫ ወእምዝ፡ ፈጺሞ፡
መዋዕለ፡ ግብረቱ፡ አተወ፡ ቤ
ቶ። ፳፬ ወእምድኅረ፡ እማንቱ፡ መ
ዋዕል፡ ፀንሰት፡ ኤልሳቤጥ፡ ብ
እሲቱ፡ ወከበተት፡ ርእሳ፡ ፭ተ፡
አውራኀ፡ እንዘ፡ ትብል።
፳፭ ከ፡ መዝ፡ ረሰየኒ፡ ሊተ፡ እግዚ
አብሔር፡ አመ፡ ሐወጸኒ፡ በዝ
ንቱ፡ መዋዕል፡ ያእትት፡ ዝንጓ
ጊየ፡ እምሰብእ። ፳፮ ወበሳድስ፡ ወ
ርኅ፡ ተፈነወ፡ ገብርኤል፡ መልአ
ክ፡ እምኀበ፡ እግዚአብሔር፡ ኀ
በ፡ አሐቲ፡ ሀገር፡ ዘገሊላ፡ እንተ፡
ስማ፡ ናዝሬት።
፳፯ ኀበ፡ ድንግል፡ እንተ፡ ተፍኅረት፡
ለብእሲ፡ ዘስሙ፡ ዮሴፍ፡ ዘእ

ጸመውን፡ ይህን፡ ቃሌን፡ አሳመ
ንህምና፡ ይህ፡ እስኪሆን፡ ድረስ፡
ድዳ፡ ትሆናለህ፡ መናገርም፡ አ
ትችልም። ቁ፡ ፵፭።
፳፩ ሕዝቡ፡ ግን፡ ዘካርያስን፡ ይጠብ
ቁት፡ ነበሩ፡ በቤተ፡ መቅደስም፡
ውስጥ፡ ስለ፡ ዘገየ፡ እጅግ፡ ተደ
ንቀው፡ ነበር። ፳፪ በወጣ፡ ጊዜ፡ ሊ
ናገራቸው፡ ዘንድ፡ አልቻለም፡
በቤተ፡ መቅደስም፡ ራእይ፡ እን
ዳየ፡ አወቁ፡ እርሱም፡ እንዲሁ፡
ድዳ፡ ሆኖ፡ ኖረ፡ በእጁም፡ ይጠ
ቅሳቸው፡ ነበረ። ፳፫ የማገልገሉ
ንም፡ ወራት፡ በፈጸመ፡ ጊዜ፡ ወ
ደ፡ ቤቱ፡ ሔደ። ፳፬ ከዚያም፡ ቀን፡
በኋላ፡ ሚስቱ፡ ኤልሳቤጥ፡ ፀነ
ሰች፡ ሰውነትዋንም፡ አምስት፡
ወር፡ ሠወረች፡ እንዲህ፡ ስትል።
፳፭ እግዚአብሔር፡ በዚህ፡ እኔን፡
በጐበኘኝ፡ ወራት፡ ስድቤን፡ ከሰ
ው፡ ያርቅልኝ፡ ዘንድ፡ እንዲህ፡
ሠራልኝ። ዘፀአ፡ ፴፡ ፳፫። ፳፮ በስድስተ
ኛውም፡ ወር፡ መልአኩ፡ ገብርኤ
ል፡ ከገሊላ፡ ክፍል፡ ናዝሬት፡ ወ
ደ፡ እምትባል፡ ወደ፡ አንዲት፡ አ
ገር፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡
ተላከ። ዮሐ፡ ፩፡ ፵፯። ፳፯ ከዳዊት፡ ወገ
ን፡ የሚሆን፡ ስሙን፡ ዮሴፍ፡ ለ

ምቤተ፡ዳዊት፡ወስማ፡ለይእ
ቲ፡ድንግል፡ማርያም።

፳፰ ወቦአ፡መልአክ፡ኀቤሃ፡ወይ
ቤላ፡ተፈሥሒ፡ፍሥሕት፡እ
ምልዕተ፡ጸጋ፡እግዚአብሔር፡
ምስሌኪ፡ወቡርክት፡አንቲ፡
እምአንስት፨

፳፱ ወርእያ፡ደንገፀት፡እምቃሉ፡
ወሀለየት፡ወትቤ፡እፎኑ፡ዘ
ከመዝ፡አምኃ፡ይትአምኁ፨

፴ ወይቤላ፡መልአክ፡ኢትፍርሂ፡
ማርያም፡እስመ፡ረከብኪ፡ሞ
ገሰ፡በኀበ፡እግዚአብሔር፨

፴፩ ወናሁ፡ትፀንሲ፡ወትወልዲ፡
ወልደ፡ወትሰምዪዮ፡ስሞ፡
ኢየሱስ።

፴፪ ውእቱ፡ዓቢይ፡ወይሰመይ፡
ወልደ፡እግዚአብሔር፡ልዑ
ል፡ወይሁቦ፡እግዚአብሔር፡
አምላክ፡መንበረ፡ዳዊት፡አቡ
ሁ፨

፴፫ ወይነግሥ፡ለቤተ፡ያዕቆብ፡
ለዓለም፡ወአልቦ፡ማኅለቅት፡
ለመንግሥቱ፨

፴፬ ወትቤሎ፡ማርያም፡ለመልአክ፡
እፎኑ፡ይከውነኒ፡ዝንቱ፡እን

ሚሉት፡ለአንድ፡ሰው፡ወደ፡
ታጨች፡ወደ፡አንዲት፡ድንግ
ል፤የድንግሊቱም፡ስም፡ማርያ
ም፡ነበር፨ መዝ፡፹፫፡፲፰። ማቴ፡፩፡፲፰፡፲፰፨

፳፰ መልአኩም፡ወደ፡እርስዋ፡ገብ
ቶ፡ጸጋን፡የተመላሽ፡ሆይ፡ደስ፡
ይበልሽ፡እግዚአብሔር፡ካንች፡
ጋራ፡ነው፡ከሴቶችም፡ይልቅ፡
የተባረክሽ፡ነሽ፡አላት፨ ዮሐ፡፩፡፲፯፨

፳፱ እርስዋም፡ባየችው፡ጊዜ፡ከነገ
ሩ፡የተነሣ፡ደነገጠች፡እንዲህ፡
ያለ፡ሰላምታ፡ምንድር፡ነው፡እያ
ለችም፡አሰበች፨

፴ መልአኩም፡አ
ላት፡ማርያም፡ሆይ፡ከእግዚአብ
ሔር፡ዘንድ፡ጸጋን፡አግኝተሻልና፡
አትፍሪ፨ የሐዋ፡፯፡፵፯፨

፴፩ እነሆም፡ት
ፀንሻለሽ፡ወንድ፡ልጅም፡ትወ
ልጃለሽ፡ስሙንም፡ኢየሱስ፡ት
ይዋለሽ፨ ኢሳ፡፯፡፲፬። ማቴ፡፩፡፳፩፡፳፫፨

፴፪ ይህ፡ታላቅ፡ይሆናል፡የልዑል፡ል
ጅም፡ይባላል፡እግዚአብሔር፡
አምላክም፡የአባቱ፡የዳዊትን፡
ዙፋን፡ይሰጠዋል፨ ፪፡ሳሙ፡፯፡፲፪፨

፴፫ በያዕቆብ፡ቤት፡ለዘለዓለም፡ይ
ነግሣል፡ለመንግሥቱም፡ፍጻ
ሜ፡የለውም፨ ዳን፡፯፡፲፬። ሚክ፡፬፡፯፨

፴፬ ማርያምም፡መልአኩን፡ወንድ፡
ሳላውቅ፡ይህ፡እንዴት፡ይሆና

፴፭ ዘ፡ ኢየአምር፡ ብእሴ፨ ወአው
ሥአ፡ መልአክ፡ ወይቤላ፡ መን
ፈስ፡ እግዚአብሔር፡ ቅዱስ፡ ይ
መጽእ፡ ላዕሌኪ፡ ወኃይለ፡ ል
ዑል፡ ይጼልለኪ፡ ወዘኒ፡ ይት
ወለድ፡ እምኔኪ፡ ቅዱስ፡ ውእ
ቱ፡ ወይሰመይ፡ ወልደ፡ እግዚ
፴፮ አብሔር፡ ልዑል፨ ወናሁ፡ ኤል
ሳቤጥኒ፡ እንተ፡ እምአዝማድ
ኪ፡ ይእቲኒ፡ ፀንሰት፡ ወረከበ
ት፡ ወልደ፡ በልሂቃቲሃ፡ ወናሁ፡ሳ
፴፯ ድስ፡ ዝንቱ፡ ወርኃ፡ ለእንተ፡ ይብልዋ፡
መካን፨ እስመ፡ አልቦ፡ ነገር፡ ዘይ
፴፰ ስአኖ፡ ለእግዚአብሔር፨ ወትቤ
ሎ፡ ማርያም፡ ነየ፡ አመቱ፡ እግዚ
አብሔር፡ ይኩነኒ፡ በከመ፡ ትቤ
ለኒ፡ ወሖረ፡ ወኃለፈ፡ እምኀ
፴፱ ቤሃ፡ መልአክ፨ ወተንሥአት፡
ማርያም፡ ፍጡነ፡ በውእቱ፡ መ
ዋዕል፡ ወሖረት፡ ደወለ፡ ዓይነ፡
፵ ከርም፡ ወበጽሐት፡ ሀገረ፡ ይሁዳ፡ ወ
ቦአት፡ ቤተ፡ ዘካርያስ፡ ወአም
፵፩ ኃተ፡ ለኤልሳቤጥ፨ ወሶበ፡ ሰምዓ
ት፡ ኤልሳቤጥ፡ ቃላ፡ ለማርያም፡ እ
ንዘ፡ ፡ ትትአምኃ፡ አንፈር
ዓፀ፡ እጓል፡ በውስተ፡ ከርሣ፡ ወ
፵፪ መልዓ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ላዕለ፡
ኤልሳቤጥ፨ ወከልሐት፡ በዓቢ

፴፭ ሌ፡ አለችው፨ መልአኩም፡ መሌ
ሶ፡ አላት፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡
ወዱ፡ አንቺ፡ ይመጣል፡ የልዑል፡
ኃይልም፡ ይጸልልሻል፡ ስለዚ
ህም፡ ዱግሞ፡ ከአንቺ፡ የሚወለ
ደው፡ ቅዱስ፡ ነው፡ የእግዚአብ
ሔርም ልጅ፡ ይባላል፨ ማቴ፡ ፩፡ ፲፰፡ ፳፡፡
፴፮ ዳን፡ ፱፡ ፳፬፨ እነ ሆም፡ ዘመድሽ፡ ኢ
ልሳቤጥ፡ በእርጅናዋ፡ ልጅ፡ ፀነ
ሰች፡ ለዚያች፡ መካን፡ ለምትባ
ለው፡ ስንኳ፡ ይህ፡ ወር፡ ስድስተ
፴፯ ኛ፡ ነው፨ ለእግዚአብሔር፡ የሚ
ሳነው፡ ነገር፡ የለምና፨ ኤር፡ ፴፪፡ ፲፯ ፳፯
፴፰ ዘካ፡ ፰፡ ፮ ፡፡ ሮሜ፡ ፬፡ ፳፩፨ ማርያምም፡ እነ
ሆዪ፡ የእግዚአብሔር፡ አገልጋይ፡
እንደ፡ ነገርህ፡ ይሁንልኝ፡ አለች
ው፡ መልአኩም፡ ከእርስዋ፡ ተ
፴፱ ለይቶ፡ ሔደ፨ በዚያም፡ ወራት፡
ማርያም፡ ፈጥና፡ ተነሣች፡ በተራ
ራውም፡ በኩል፡ ወደ፡ ይሁዳ፡ ከ
፵ ተማ፡ ደረሰች፨ ወደ፡ ዘካርያስም፡
ቤት፡ ገብታ፡ ለኤልሳቤጥ፡ ሰላ
፵፩ ምታ፡ ሰጠች፨ ኤልሳቤጥም፡ የ
ማርያምን፡ ሰላምታ፡ በሰማች፡
ጊዜ፡ ፅንሱ፡ በማኅፀኗ፡ ዘለለ፡
በኤልሳቤጥም፡ መንፈስ፡ ቅዱ
፵፪ ስ፡ መላበት፨ ቁ፡ ፲፩ ፨ በታላቅ፡ ቃል
ም፡ ጮኸች፡ አለችም፡ አንቺ፡ ከሴ

ደ፡ ቃለ፡ ወትቤ፡ ቡርክት፡ አን
ቴ፡ እምአንስት፡ ወቡሩክ፡ ፍ
፵፫ ሬ፡ ከርሥኪ። ወምንትኑ፡ አነ፡ ከ
መ፡ ትምጽኢ፡ ኀቤየ፡ እሙ፡ ለ
እግዚእየ።
፵፬ እስመ፡ ናሁ፡ ሶበ፡ ሰማዕኩ፡ ቃ
ለኪ፡ እንዘ፡ ትትአምኅኒ፡ አን
ፈርዓፀ፡ እጓል፡ በውስተ፡ ከር
፵፭ ሥየ፡ በፍሥሐ፡ ወበሐሤት። ወ
ብፅዕት፡ አንቲ፡ እንተ፡ አምነ
ከመ፡ ይከውን፡ ቃል፡ ዘነገሩኪ፡
እምኀበ፡ እግዚአብሔር።
፵፮ ወትቤ፡ ማርያም፡ ተዓብዮ፡ ነፍስ
የ፡ ለእግዚአብሔር።
፵፯ ወትትሐሠይ፡ መንፈስየ፡ በአ
ምላኪየ፡ ወመድኃንየ።
፵፰ እስ መ፡ ርእየ፡ ሕማማ፡ ለአመ
ቱ፡ ወናሁ፡ እምይእዜሰ፡ ያስ
ተ፡ በፅዑኒ፡ ኵሉ፡ ትውልድ።
፵፱ እስመ፡ ገብረ፡ ሊተ፡ ኀይለ፡ ዐ
ቢያተ፡ ወቅዱስ፡ ስሙ።
፶ ወሣህሉኒ፡ ለትውልደ፡ ትውል
ድ፡ ለእለ፡ ይፈርህዎ።
፶፩ ወገብረ፡ ኃይለ፡ በመዝራዕቱ፡
ወዘረዎሙ፡ ለእለ፡ ያበብዩ፡

ቶች፡ ይልቅ፡ የተባረክሽ፡ ነሽ።
የሆድሽም፡ ፍሬ፡ የተባረከ፡ ነ
፵፫ ው። ቍ፡ ፳፰ የጌ ታዬስ፡ እናት፡
ወደ፡ እኔ፡ ትመጣ፡ ዘንድ፡ ለእ
ኔ፡ እንዴት፡ ይገባኛል።
፵፬ እነ ሆም፡ የሰላምታሽን፡ ድም
ፅ፡ በሰማሁ፡ ጊዜ፡ ከደስታ፡ የተ
ነሣ፡ ፅንሱ፡ በማኅፀኔ፡ ውስጥ፡
፵፭ ዘለለ። ከእ ግዚአብሔር፡ ዘን
ድ፡ ስለ፡ አንቺ፡ የተናገረው፡ ቃ
ል፡ እንዲፈጸም፡ ለምታምኚ፡
ለአንቺም፡ ምስጋና፡ ይገባሻ
፵፮ ል። ም፡ ፲፩፡ ፳፰ ማርያምም፡ አለች፡
ሰውነቴ፡ እግዚአብሔርን፡ ታ
፵፯ ከብረዋለች። ፩፡ ሳሙ፡ ፪፡ ፩፡ ፲ ነፍ
ሴም፡ በመድኃኒቴ፡ በእግዚአ
ብሔር፡ ደስ፡ ይላታል። ዕንባ፡ ፫፡ ፲፰
፵፰ የእ ገልጋዩቱን፡ መዋረድ፡ አ
ይቶዋልና፡ እነሆም፡ ከዛሬ፡ ጀ
ምሮ፡ ትውልድ፡ ሁሉ፡ ያመሰግ
ኑኛል። መዝ፡ ፻፲፫፡ ፯፡ ፯ ዘፍጥ፡ ፴፡ ፲፫፡ ም፡ ፲፩፡
፵፱ ፳፯ እር ሱም፡ ብርቱ፡ የሚሆ
ን፡ ታላቅ፡ ሥራን፡ አድርጎል
ኛልና፡ ስሙ፡ ቅዱስ፡ ነው። መዝ፡
፶ ፻፳፯፡ ፫፡ ኢሳ፡ ፯፡ ፫ ደፋ ርታውም፡ በ
ሚፈሩት፡ በልጅ፡ ልጅ፡ ይኖራ
፶፩ ል። መዝ፡ ፻፫፡ ፲፫፡ ፲፯ ኃይ ልን፡ በክን
ዱ፡ አደረገ፡ ትዕቢተኞችንም፡

ሐሊና፡ ልቦሙ።
፶፪ ወነ ሠቶሙ፡ ለኃያላን፡ እመና
ብርቲሆሙ፡ ወአዕበዮሙ፡
ለትሑታን።
፶፫ ወአ ጽገቦሙ፡ እምበረከቱ፡
ለርኁባን፡ ወፈነዎሙ፡ ዕራቆ
ሙ፡ ለብዑላን።
፶፬ ወተ ወክፎ፡ ለእስራኤል፡ ቍል
ዒሁ፡ ወተዘከረ፡ ሣህሎ።
፶፭ ዘይ ቤሎሙ፡ ለአበዊነ፡ ለአብ
ርሃም፡ ወለዘርኡ፡ እስከ፡ ለ
ዓለም።
፶፮ ወነ በረት፡ ማርያም፡ ኀቤሃ፡ መጠ
ነ፡ ሠለስቱ፡ አውራኀ፡ ወእም
ድኅረሁ፡ አተወት፡ ቤታ።

፶፯ ወበ ጽሐ፡ ወርኃ፡ ለኤልሳቤጥ፡
ከመ፡ ትለድ፡ ወወለደት፡ ወል
ደ። ፶፰ ወሰ ምዑ፡ አዝማዲሃ፡ ወ
ዕዓዋሪሃ፡ ከመ፡ አዕበየ፡ እግ
ዚአብሔር፡ ሣህሎ፡ ላዕሌ
ሃ፡ ወተፈሥሑ፡ ላቲ።
፶፱ ወእ ምዝ፡ እመ፡ ሰሙን፡ ዕለ
ት፡ ወሰድዎ፡ ለሕፃን፡ ከመ፡
ይግዝርዎ፡ ወሰመይዎ፡ በስ
፷ መ፡ አቡሁ፡ ዘካርያስ። ወአ ው
ሥአት፡ እሙ፡ ወትቤ፡ አልቦ፡
፷፩ አላ፡ ዮሐንስ፡ ይሰመይ። ወይ ቤል

በልባቸው፡ አሳብ፡ በተነ። ፳፪፡ ሳሙ፡
፶፪ ፳፪፡ ፳፫። ኃያ ላኑን፡ ከዙፋናቸው፡
አዋረደ፡ የተዋረዱትንም፡ ከፍ፡
ከፍ፡ አደረጋቸው። መዝ፡ ፬፴፯፡ ፲።
፶፫ የተ ራቡትንም፡ በበጎ፡ ነገር፡ አ
ጸገባቸው፡ ባለጠጎችንም፡ ባ
ዶ፡ እጃቸውን፡ ሰደዳቸው። መዝ፡
፶፬ ፹፫፡ ፲፩፡ ፱፯፡ ፱። ዮሐ፡ ፩፡ ፲፩፡ ምሕረቱንም፡
አስቦ፡ አገልጋዩን፡ እስራኤልን፡
፶፭ ተቀበለ። ዘዳግ፡ ፯፡ ፯፡ ፰። ለአ ባቶቻች
ን፡ እንደ፡ ተናገረ፡ ለአብርሃም፡
ለዘሩም፡ እስከ፡ ዘለዓለም፡ ድረስ።
፶፮ ዘፍ፡ ፲፯፡ ፯፡ ፲፰፡ ፲፰። ማርያምም፡ ሦስት፡
ወር፡ የሚያህል፡ በእርስዋ፡ ዘን
ድ፡ ተቀምጣ፡ ከዚያ፡ በኋላ፡ ወ
ደ፡ ቤትዋ፡ ተመለሰች።
፶፯ ኤል ሳቤጥም፡ ትወልድ፡ ዘንድ፡
ወራትዋ፡ ደረሰ፡ ወንድ፡ ልጅ
፶፰ ም፡ ወለደች። ቍ፡ ፲፫። ጐረ ቤቶቿ
ና፡ ዘመዶቿም፡ እግዚአብሔር፡
ምሕረቱን፡ እንዳበዛላት፡ ሰ
ምተው፡ ከእርስዋ፡ ጋራ፡ ደስ፡
፶፱ አላቸው። በስ ምንተኛውም፡
ቀን፡ ሕፃኑን፡ ሊገዝሩት፡ መጡ፡
በአባቱም፡ ስም፡ ዘካርያስ፡ አ
፷ ሉት። ዘፍ፡ ፲፯፡ ፲፪። እና ቱ፡ ግን፡ መል
ሳ፡ ዮሐንስ፡ ይባል፡ እንጂ፡ አይሆ
፷፩ ንም፡ አለች። ቍ፡ ፲፫። እነ ርሱም፡

ዋ፡ አልቦ፡ እምአዝማድኪ፡ ዘ
ከማሁ፡ ስሙ።

፷፪ ወቀጸብዎ፡ ለአቡሁ፡ ወይቤል
ዎ፡ ምንተ፡ ትፈቅድ፡ ይሰምይ

፷፫ ዎ። ወሰአለ፡ ለውሐ፡ ወጸሐፈ፡
ዐንዘ፡ ይብል፡ ዮሐንስ፡ ስሙ፡ ወ

፷፬ አንከሩ፡ ኵሎሙ። ወተከሥተ፡
አፉሁ፡ ወልሳኑ፡ ሶቤሃ፡ ወነበ
በ፡ ወባረኮ፡ ለእግዚ አብሔር።

፷፭ ወኮነ፡ ፍርሃት፡ ላዕለ፡ ኵሉ፡ ሰ
ብእ፡ ዘውእቱ፡ ብሔር፡ ወላዕ
ለ፡ ኵሉ፡ ደወለ፡ ይሁዳ፡ ወተና
ገርዎ፡ ለዝንቱ፡ ነገር፡ በኵሉ፡

፷፮ ብሔረ፡ ይሁዳ። ወዐቀብዎ፡ በል
ቦሙ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ሰምዕ
ዎ፡ ወይቤሉ፡ ምንትኑ፡ እንጋ፡
ውእቱ፡ ዝንቱ፡ ሕፃን፡ እስመ፡
እዴ፡ እግዚ አብሔር፡ ላዕሌሁ።

፷፯ ወመልአ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ላዕ
ሌ፡ ዘካርያስ፡ አቡሁ፡ ወተነበ
የ፡ ወይቤ።

፷፰ ይትባረክ፡ እግዚ አብሔር፡ አ
ምላክ፡ እስራኤል፡ ዘተሣሃለ
ነ፡ ወገብረ፡ መድኀኒተ፡ ለሕ
ዝበ፡ ዚአሁ።

፷፱ ወአንሥአ፡ ለነ፡ ቀርነ፡ መድኀ
ኒትነ፡ እምቤተ፡ ዳዊት፡ ገብ
ሩ።

ከወገንሽ፡ ማንም፡ በዚህ፡ ስ
ም፡ የሚጠራ፡ የለም፡ አሏት።

፷፪ አባ ቱም፡ ማን፡ ሊባል፡ እንዲወ

፷፫ ድ፡ ጠቀሱት። እር ሱም፡ ትንሽ፡
ብራና፡ ለምኖ፡ ስሙ፡ ዮሐንስ፡
ነው፡ ብሎ፡ ጻፈ፡ ሁሉም፡ አድ

፷፬ ነቁ። ያን፡ ጊዜውንም፡ አፉ፡ ተ
ከፈተ፡ መላሱም፡ ተፈታ፡ እግ
ዚ አብሔርንም፡ አያመሰገነ፡

፷፭ ተናገረ። መዝ፡ ፸፲፯፡ ፲። በጐ ረቤቶ
ቻቸውምላይ፡ ፍርሃት፡ ሆነ፡ ደ
ደህም፡ ነገር፡ በመላ፡ በይሁዳ፡
ተራሮች፡ ሁሉ፡ ተወራ። መዝ፡ ፴፩፡ ፫፡ ፬።

፷፮ የሰ ሙትም፡ ሁሉ፡ ነገሩን፡ በል
ባቸው፡ አኖሩት፡ እንዲህ፡ ሲሉ፡
እንጃ፡ ይህ፡ ሕፃን፡ ምን፡ ይሆን፡
የእግዚ አብሔር፡ እጅ፡ ከእር
ሱ፡ ጋራ፡ ነበረችና። ዕዝ፡ ፯፡ ፯፡ ሉቃ፡

፷፯ ፫፡ ፲፭። በአ ባቱ፡ በዘካርያስም፡
መንፈስ፡ ቅዱስ፡ መልቶበት፡
ነበር፡ እንዲህም፡ ብሎ፡ ትንቢ

፷፰ ት፡ ተናገረ። ይቀ ር፡ ያለን፡ ለወ
ገኖቹ፡ መዳንን፡ ያደረገ፡ የእስ
ራኤል፡ አምላክ፡ እግዚ አብ
ሔር፡ ይባረክ። መዝ፡ ፸፪፡ ፲፩፡ ኢሳ፡ ፶፫፡

፷፱ ፩። ሉቃ፡ ፯፡ ፲፯። ከእ ገልጋዩም፡ ከ
ዳዊት፡ ቤት፡ የመድኀኒትን፡ ቀ
ንድ፡ አስነሣልን። መዝ፡ ፻፴፩፡ ፲፯። የሐዋ፡

፸ በከመ፡ ነበበ፡ በአፈ፡ ነቢያቲሁ፡ ቅዱሳን፡ እለ፡ እምዓለም።

፸፩ ከመ፡ ያድኅነነ፡ እምእደ፡ ፀርነ፡ ወእምእደ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ይጸልኡነ። ፸፪ ከመ፡ ይግበር፡ ሣህሎ፡ ምስለ፡ አበዊነ፡ ወከመ፡ ይዘክር፡ ኪዳኖ፡ ቅዱሰ።

፸፫ መሐላሁ፡ ዘመሐለ፡ ለአብርሃም፡ አቡነ፡ ከመ፡ የሀበነ። በዘ ኢንፈርህ፡ እምእደ፡ ፀርነ፡ ያድኅነነ፡ ወናምልኮ።

፸፬ በጽድቅ፡ ወበርትዕ፡ በቅድሜሁ፡ ወበኵሉ፡ መዋዕሊነ። ፸፭ ወአንተኒ፡ ሕፃን፡ ነቢየ፡ ልዑል፡ ትሰመይ፡ እስመ፡ ተሐውር፡ ቅድመ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ፡ ትጺሕ፡ ፍኖቶ። ፸፮ ከመ፡ ተሀቦሙ፡ ለአሕዛብ፡ ያእምሩ፡ መድኃኒቶሙ፡ በዘ ይትኃደግ፡ ሎሙ፡ ኃጢአቶሙ። ፸፯ በሣህሉ፡ ወበምሕረቱ፡ ለአምላክነ፡ ለዘ ሐወጸነ፡ እምአርያም፡ ወሠረቀ፡ ከመ፡ ያርእዮሙ፡ ብርሃኖ። ፸፰ ለእለ፡ ይነብ

፸ ፩፡ ፲፪ ✤ ከጥንት፡ ጀምሮ፡ በነበሩት፡ በቅዱሳን፡ በነቢያት፡ አፍ፡ እንደ፡ ተናገረ ✤ ኤር፡ ፴፫፡ ፯ ✤ የሐዋ፡ ፫፡ ፳፩፡ ፳፬ ✤

፸፩ ከጸላቶቻችን፡ ከሚጸሉንም፡ ሁሉ፡ እጅ፡ ያድነን፡ ዘንድ ✤ መዝ፡ ፻፮፡ ፲፡ ✤ ዘሌዋ፡ ፳፮፡ ፵፪ ✤ ፸፪ ምሕረቱንም፡ ከአባቶቻችን፡ ጋራ፡ ያደርግ፡ ዘንድ፡ የተቀደሰውን፡ ኪዳኑን፡ ያስብ፡ ዘንድ ✤ ዘፍ፡ ፳፪፡ ፲፯ ። ሚክ፡ ፯፡ ፳ ✤

፸፫ ለአባታችን፡ ለአብርሃም፡ የማለለትን፡ መሐላውን፡ ይሰጠን፡ ዘንድ ✤ ከጸላቶቻችን፡ እጅ፡ ስለአዳነን፡ ያለ፡ ፍርሃት፡ እናመልከው፡ ዘንድ ✤ ቲቶ፡ ፪፡ ፲፪፡ ፲፬ ✤

፸፬ በቅድስና፡ በጽድቅም፡ በፊቱ፡ በሕይወታችን፡ ዘመን፡ ሁሉ ✤ ፸፭ ገላ፡ ፪፡ ፳፡ ቆላ፡ ፩፡ ፳፩ ✤ አንተም፡ ሕፃን፡ የልዑል፡ ነቢይ፡ ትባላለህ፡ መንገዱን፡ ልትጸርግ፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ትሔዳለህና ✤ ማቴ፡ ፮ ፫፡ ፫ ። ሚልክ፡ ፬፡ ፭ ✤ ኃጢአታቸው፡ የሚሠረይበትን፡ መድኃኒታቸውን፡ እንዲያውቁ፡ ለሕዝቡ፡ ትሰጥ፡ ዘንድ ✤ ኢሳ፡ ፵፫፡ ፲፩ ። ኤር፡ ፴፩፡ ፴፬ ✤ ፸፯ በአምላካችን፡ ይቅርታና፡ በምሕረቱ፡ ከላይ፡ የወጣ፡ ብርሃን፡ እኛን፡ ይጐበኘን፡ ዘንድ ✤ ዘኍል፡ ፸፰ ፳፬፡ ፲፯ ። ኢሳ፡ ፲፡ ፩፡ ፪ ✤ በጨለማና፡ በ

ኑ፡ ውስተ፡ ጽልመት፡ ወጽላ
ሎተ፡ ሞት፡ ከመ፡ ያርትዕ፡ እገ
ሪነ፡ ውስተ፡ ፍኖተ፡ ሰላም።
፹ ወልህቀ፡ ሕፃን፡ ወጸንዐ፡ በመ
ንፈስ፡ ቅዱስ፡ ወነበረ፡ ሐቅ
ለ፡ እስከ፡ አመ፡ ደገደስዎ፡ ኀ
በ፡ እስራኤል ፨ ፨ ፨ ፨

ምዕራፍ ፪ ።

ስለ፡ ጌታችን፡ መወለድ፡ ስለ፡ እረኞችና፡ ስለ፡ መ
ላእክት ፨ ስለ፡ ግዝረትና፡ ስለ፡ ስሙ ፨ በአርብዓ፡
ቀን፡ ወደ፡ መቅደስ፡ እንደገቡት ፨ ስምዖን፡ እን

፩ ወኮነ፡ በውእቱ፡ መዋዕል፡ ወፅ
አ፡ ትእዛዝ፡ እምኀበ፡ አውግስ
ጦስ፡ ቄሣር፡ ከመ፡ ይጽሐፍ፡
፪ ኵሉ፡ ዓለም ፨ ወውእቱ፡ ጸሐ
ፍ፡ ቀዳሚ፡ ውእቱ፡ አመ፡ ቄሬኔዎ
ስ፡ መስፍን፡ ለሶርያ ፨
፫ ወሖሩ፡ ኵሉ፡ ሰብእ፡ ይጽሐፍ፡
፬ በበሀገሩ ፨ ወዓርገ፡ ዮሴፍኒ፡
እምገሊላ፡ እምሀገረ፡ ናዝሬ
ት፡ መንገለ፡ ይሁዳ፡ ኀበ፡ ሀገረ፡
ዳዊት፡ እንተ፡ ስማ፡ ቤተ፡ ልሔ
ም፡ እስመ፡ እምሀገረ፡ ዳዊት፡
ወእምአዝማደ፡ ቤቱ፡ ውእቱ ፨
፭ ወሖረ፡ ይጽሐፍ፡ ምስለ፡ ማርያ
ም፡ እንተ፡ ፈኀኑ፡ ሎቱ፡ ብእሲ
፮ ተ፡ እንዘ፡ ፅንስት፡ ይእቲ ፨ ወ
እምዝ፡ እንከ፡ እንዘ፡ ሀለው፡

ሞት፡ ጽላ፡ ለተቀመጡት፡ ያ
በራ፡ ዘንድ፡ እግሮቻችንንም፡
በሰላም፡መንገድ፡ያቀና፡ ዘንድ ፨ ኢሳ፡ ፱፡ ፪፡ ፷፡
፹ ፩ሮሜ፡ ፲፫፡ ፲፪ ፨ ሕፃኑም፡ አደገ፡ በመ
ንፈስም፡ ጸና፡ ለእስራኤልም፡
እስከ፡ ታየበት፡ ቀን፡ ድረስ፡ በ
በረሃ፡ ኖረ ፨ ምዕ፡ ፪፡ ፵፡ ፶፪። ማቴ፡ ፫፡ ፩።

ምዕራፍ ፪ ።

ዴ፡ ታቀፈውና፡ ትንቢት፡ እንደ፡ ተናገረ ፨ በልጅነ
ቱ፡ በቤተ፡ መቅደስ፡ ከአይሁድ፡ ሊቃውንት፡ ጋ
ራ፡ እንደ፡ ተከራከረ ፨ ፨ ፨ ፨ ፨

፩ በዚያም፡ ወራት፡ አገሩ፡ ሁሉ፡ ይ
ጻፍ፡ ዘንድ፡ ከአውግስጦስ፡ ቄሣ
ር፡ ትእዛዝ፡ ወጣ ፨
፪ ይህም፡ ጽሕፈት፡ መጀመሪያ፡
ቄሬኔዎስ፡ በሶርያ፡ አገር፡ በተ
ሾመ፡ ጊዜ፡ ነበረ ፨ የሐዋ፡ ፭፡ ፴፯ ፨
፫ ሁሉም፡ እያንዳንዱ፡ በያገሩ፡
፬ ይጻፍ፡ ዘንድ፡ ሔደ ፨ ዮሴፍም፡
ከዳዊት፡ አገር፡ ከዘመዶቹም፡
ወገን፡ ስለ፡ ነበረ፡ ከናዝሬት፡
አገር፡ ከገሊላ፡ ወደ፡ ይሁዳ፡ ቤ
ተ፡ ልሔም፡ ወደ፡ እምትባል፡ ወ
ደ፡ ዳዊት፡ ከተማ፡ ወጣ ፨
፭ ም፡ ፭፡ ፳፯ ፨ ሚክ፡ ፭፡ ፩ ፨ ከእጮኛው፡
ከማርያም፡ ጋራ፡ ፀንሳ፡ ሳለች፡ ይ
፮ ጻፍ፡ ዘንድ ፨ ም፡ ፩፡ ፳፯ ፨ በዚያው
ም፡ ሳሉ፡ የምትወልድበት፡ ቀ

ህየ፡ በጽሐ፡ ዕለተ፡ ወሊዶታ፨
፯ ወወለደት፡ ወልደ፡ ዘበኵራ።
ወአሠረቶ፡ መንኮብያቲሁ፡
ወጠብለለቶ፡ በአጽርቅት፡
ወአስከበቶ፡ ውስተ፡ ጎል፡ እ
ስመ፡ አልቦሙ፡ መካን፡ ው
ስተ፡ ማኅደሮሙ፨
፰ ወሀለዉ፡ ኖሎት፡ ውስተ፡ ውእ
ቱ፡ ብሔር፡ ወይተግሁ፡ ወይሔ
ልዉ፡ ወየዐቅቡ፡ መራዕዪሆ
ሙ፡ ሌሊተ፨ ወናሁ፡ ቆመ፡ መ
፱ ልአክ፡ እግዚአብሔር፡ ኀቤሆ
ሙ፡ ወስብሐተ፡ እግዚአብሔ
ር፡ በረቀ፡ ላዕሌሆሙ፡ ወፈር
ሁ፡ ዓቢየ፡ ፍርሃተ፨
፲ ወይቤሎሙ፡ መልአክ፡ ኢት
ፍርሁ፡ እስመ፡ ናሁ፡ እዜንወ
ክሙ፡ ዓቢየ፡ ዜና፡ ዘይከውን፡
ፍሥሐ፡ ለኵሉ፡ ሕዝብ፨
፲፩ እስመ፡ ናሁ፡ ተወልደ፡ ለክሙ፡
ዮም፡ መድኅን፡ ዘውእቱ፡ ክ
ርስቶስ፡ እግዚእ፡ ቡሩክ፡ በ
፲፪ ሀገረ፡ ዳዊት፨ ወከመዝ፡ ትእ
ምርቱ፡ ለክሙ፡ ትረክቡ፡ ሕ
ፃነ፡ ዕሡረ፡ መንኵብያቲሁ።
ወስኩበ፡ ውስተ፡ ጎል፡ ወጥብ
ሉለ፡ በአጽርቅት፨
፲፫ ወግብተ፡ መጽኡ፡ ምስለ፡ ው

ን፡ ደረሰ፨
፯ የበኵር፡ ልጅዋንም፡ ወለደች፡
አውራ፡ ጣቱንም፡ አሠረችው፡
በመጠቅለያም፡ ጠቀለለች
ው፡ በበረትም፡ አስተኛችው፡
በእንግዶች፡ ማረፊያ፡ ስፍራ፡
አልነበራቸውምና፨ ማቴ፡ ፩፡ ፳፭፨
፰ በዚያችም፡ አገር፡ ሌሊት፡ አ
የተጉ፡ መንጋቸውን፡ የሚጠ
ብቁ፡ እረኞች፡ ነበሩ፨
፱ እነሆ፡ የእግዚአብሔር፡ መ
ልአክ፡ በእነርሳቸው፡ ሳይ፡
ቆመ፡ የእግዚአብሔርም፡ ክብ
ር፡ በዙሪያቸው፡ አበራ፡ ታላቅ፡
ፍርሃትም፡ ፈሩ፨ ኢሳ፡ ፷፡ ፩፡ ፲፱፨
፲ መልአኩም፡ አላቸው፡ እነሆ፡ እኔ፡ ለ
ሕዝብ፡ ሁሉ፡ ታላቅ፡ ደስታ፡ የ
ሚሆን፡ የምስራች፡ እነግራ
ችኋለሁ፡ አትፍሩ፨ ኢሳ፡ ፶፪፡ ፩፡ ፲፱፨
፲፩ እነሆ፡ ዛሬ፡ በዳዊት፡ አገር፡ መ
ድኅን፡ እርሱም፡ ክርስቶስ፡ የ
ተባረከ፡ ጌታ፡ ተወልዶላችኋ
፲፪ ልና፨ ዮሐ፡ ፩፡ ፳፭፨ ይህም፡ ምል
ክት፡ ይሁንላችሁ፡ ሕፃኑን፡ አ
ውራ፡ ጣቶቹን፡ ታሥሮ፡ በመ
ጠቅለያ፡ ተጠቅልሎ፡ በበረት፡
ተጠቅልሎ፡ ታገኙታላችሁ፡
፲፫ ድንገትም፡ ብዙ፡ የሰማይ፡ ሠ

ኦቱ፡ መልአክ፡ ብዙኃን፡ ሐራ፡
ሰማይ፡ እንዘ፡ ይሴብሕዎ፡ ለእ
ግዚአብሔር፡ ወይብሉ፡፡

፲፬ ስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ በ
ሰማያት፡ ወሰላም፡ በምድር፡
ለእጓለ፡ እመሕያው፡ ሥም
ረቱ፡፡

፲፭ ወእምዝ፡ ዓረጉ፡ መላእ
ክት፡ እምኀቤሆሙ፡ ውስተ፡
ሰማይ፡ ይቤሉ፡ እሙንቱ፡ ሰ
ብእ፡ ኖሎት፡ በበይናቲሆሙ፡
ንሑር፡ ወንንሶሱ፡ እስከ፡ ቤተ፡
ልሔም፡ ወንእምር፡ ዘንተ፡ ነ
ገረ፡ ዘአርአየነ፡ እግዚአብሔ
ር፡፡

፲፮ ወሐሩ፡ ፍጡነ፡ ወረከብ
ዎሙ፡ ለማርያም፡ ወለዮሴፍ፡
ወለሕፃን፡ ይሰክብ፡ ውስተ፡
ጎል፡፡

፲፯ ወርእዮሙ፡ አእመሩ፡ በ
እንተ፡ ሕፃን፡ ዘነገርዎሙ፡፡

፲፰ ወኵሎሙ፡ እለ፡ ሰምዑ፡ አን
ከሩ፡ ዘነገርዎሙ፡ ኖሎት፡፡

፲፱ ወማርያምሰ፡ ተዐቅብ፡ ዘንተ፡
ኵሎ፡ ነገረ፡ ወትወድዮ፡ ውስ
ተ፡ ልባ፡፡

፳ ወተመይጡ፡ ኖሎት፡ እንዘ፡
ይሴብሕዎ፡ ወያአኵትዎ፡ ለ
እግዚአብሔር፡ በእንተ፡ ኵሉ፡

ራዊት፡ ከመልአኩ፡ ጋራ፡ መ
ጥተው፡ እግዚአብሔርን፡ ያ
መሰግኑ፡ ነበር፡ እንዲህ፡ እያ
ሉ፡፡ ዳን፡ ፯፡ ፲፡፡ ራእ፡ ፭፡ ፲፩፡፡

፲፬ በሰማይ፡ ለ
እግዚአብሔር፡ ምስጋና፡ ይሁ
ን፡ በምድርም፡ ሰላም፡ በ
ሰውም፡ እርሱ፡ በሚፈቅደው፡፡
ኢሳ፡ ፶፯፡ ፲፱፡፡ ሮሜ፡ ፭፡ ፩፡፡ ኤፌ፡ ፪፡ ፲፬፡ ፲፯፡፡

፲፭ መ
ላእክትም፡ ከነእርሳቸው፡ ወ
ደ፡ ሰማይ፡ በወጡ፡ ጊዜ፡ እረኞ
ቹ፡ እርስ፡ በርሳቸው፡ ይህን፡ እ
ግዚአብሔር፡ የገለጸልንን፡
ነገር፡ እናይ፡ ዘንድ፡ ወደ፡ ቤተ፡
ልሔም፡ እንሒድ፡ ተባባሉ፡፡

፲፮ ፈጥነውም፡ ሒደው፡ ማርያም
ንና፡ ዮሴፍን፡ ሕፃኑንም፡ በበረ
ት፡ ተኝቶ፡ አገኙ፡፡ ማቴ፡ ፪፡ ፲፩፡፡

፲፯ ባዩም፡ ጊዜ፡ የነገርዋቸውን፡ ስለ
ዚህ፡ ሕፃን፡ እንዴ፡ ሆነ፡ አውቀ
ው፡ አወሩ፡፡ ቍ፡ ፲፡ ፲፪፡

፲፰ የሰ
ሙት
ም፡ ሁሉ፡ እረኞች፡ የነገርዋቸ
ውን፡ ነገር፡ አደነቁ፡፡

፲፱ ማርያም፡
ግን፡ ይህንን፡ ሁሉ፡ ነገር፡ ትጠ
ብቀውና፡ በልብዋም፡ ታኖረ
ው፡ ነበረች፡፡ ም፡ ፩፡ ፳፱፡፡ ፵፰፡ ፵፱፡፡

፳ እረኞችም፡ እንደተባለላቸ
ው፡ ባሰሙትና፡ ባዩት፡ ሁሉ፡
እግዚአብሔርን፡ እያመሰገ

ዘርአዩ፡ ወሰምዑ፡ ዘከመ፡ ይ
፳፩ ቢልዎሙ፨ ወአመ፡ ተፈጸመ፡
[illegible]፡ ሰሙን፡ ዕለት፡ ወሰድዎ፡
ለሕፃን፡ ከመ፡ ይግዝርዎ፡ ወ
ሰመይዎ፡ ስሞ፡ ኢየሱስ፡ በከ
መ፡ ሰመዮ፡ መልአክ፡ እምቅ
ድመ፡ ትፅንሶ፡ በከርሣ፨
፳፪ ወአመ፡ ተፈጸመ፡ መዋዕለ፡ን
ጽሒሙ፡ በከመ፡ ሕገ፡ ሙሴ፡
ወሰድዎ፡ ኢየሩሳሌም፡ ያቅ
ምዎ፡ ቅድመ፡ እግዚአብሔር።

፳፫ በከ መ፡ ጽሑፍ፡ ውስተ፡ ሕገ፡
እግዚአብሔር፡ ኵሉ፡ ተባዕት፡
ዘይፈትሕ፡ ማኅፀነ፡ እሙ፡ ቅ
ዱስ፡ ይሰመይ፡ ለእግዚአብ
ሔር፨
፳፬ ወከ መ፡ ያብኡ፡ መሥዋዕተ፡
በከመ፡ ተብህለ፡ ውስተ፡ ሕገ፡
እግዚአብሔር፡ ዘውገ፡ ማዕ
ነቀ፡ ወእመ፡ አኮ፡ ክልኤቱ፡ እ
፳፭ ጐለ፡ ርግብ፨ ወሀ ሎ፡ ብእሲ፡
በኢየሩሳሌም፡ ዘስሙ፡ ስም
ዖን፡ ወውእቱ፡ ጻድቅ፡ ወየዋ
ህ፡ ወይሴፎ፡ ፍሥሐሆሙ፡ ለ
እስራኤል፡ ወመንፈስ፡ ቅዱ
ስ፡ ላዕሌሁ፨

ኑና፡ እያከበሩ፡ ተመለሱ።። መዝ፣
፳፩ ፲፩፡፯፡ ፩፨ ስም ንት፡ ቀንም፡ በተፈ
ጸመ፡ ጊዜ፡ ሕፃኑን፡ ሊገዝሩ
ት፡ ወሰዱት፡ ስሙንም፡ ገና፡ በ
ማኅፀን፡ ሳይፀነስ፡ አስቀድ
ሞ፡ መልአኩ፡ እንደ፡ ሰየመ
ው፡ ኢየሱስ፡ አሉት፨ ም፡፩፡ ፴፩፨
፳፪ ፶፬፨ የመ ንጻታቸውም፡ ወራት፡
በደረሰ፡ ጊዜ፡ እንደ፡ ሙሴ፡
ሕግ፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡
ያቆሙት፡ ዘንድ፡ ወደ፡ ኢየሩ
ሳሌም፡ ይዘውት፡ ወጡ፨ ዘሌዋ፡
፳፫ ፲፪፡ ፮፨ በእ ግዚአብሔር፡ ሕግ፡
እንደ፡ ተጻፈ፡ የእናቱን፡ ማኅ
ፀን፡ የሚከፍት፡ (በኵር) ወን
ድ፡ ሁሉ፡ ለእግዚአብሔር፡ የ
ተቀደሰ፡ ይባላል፨ ዘጸአ፡ ፲፫፡ ፪፨
፳፬ በእ ግዚአብሔርም፡ ሕግ፡ እ
ንደ፡ ተባለ፡ ሁለት፡ ዋልያ፡ ወይ
ም፡ ሁለት፡ የርግብ፡ ግልገሎ
ች፡ መሥዋዕት፡ ያቀርቡ፡ ዘን
፳፭ ድ፨ ዘሌዋ፡ ፲፪፡ ፰፨ እነ ሆ፡ በኢየሩሳ
ሌም፡ ስሙን፡ ስምዖን፡ የሚሉ
ሩ፡ይጸልእ፡ብርሃነ፡ወኢይመ
ጽእ፡ኀበ፡ብርሃን፡ከመ፡ኢይት
ከሠቶ፡ምግባሩ፡እስመ፡እኩ
፳፩ ይ፡ውእቱ። ወሰ፡ይገብር፡ጽድ
ቀ፡ይመጽእ፡ኀበ፡ብርሃን፡ከ
መ፡ያስተርኢ፡ምግባሩ፡እስ
መ፡በእንተ፡እግዚአብሔር፡
፳፪ ይገብር። ወእምዝ፡ሖረ፡እግ
ዚእ፡ኢየሱስ፡ወአርድእቲሁ፡
ውስተ፡ምድረ፡ይሁዳ፡ወህየ፡
ነበረ፡ምስሌሆሙ፡እንዘ፡ያጠ
፳፫ ምቅ። ወሀሎ፡ዮሐንስኒ፡ያጠ
ምቅ፡በሄኖን፡በቅሩበ፡ሳሌ
ም፡እስመ፡ህየ፡ብዙኅ፡ማ
ያት፡ወይመጽኡ፡ኀቤሁ፡ብ
ዙኃን፡ወያጠምቆሙ።

፳፬ እስመ፡ዓዲሁ፡ኢተወድየ፡ዮ
ሐንስ፡ውስተ፡ቤተ፡ሞቅሕ።
፳፭ ወእምዝ፡ኮነ፡ተኃሥሦ፡ማ
እከለ፡አርድኢሁ፡ለዮሐንስ፡
ምስለ፡አይሁድ፡በእንተ፡አጥ
፳፮ ሕሮ። ወሖሩ፡ኀበ፡ዮሐንስ፡ወ
ይቤልዎ፡ረቢ፡ዝኩ፡ዘምስሌከ፡
ሀሎ፡በማዕዶተ፡ዮርዳኖስ፡ዘአ

ሥራቸው፡ክፉ፡ነውና። ም፡፭፡፳፡፱።
፳ ሮሜ፡፲፫፡፲፪።
ክፉም፡የሚያደርግ፡ሁሉ፡ብ
ርሃንን፡ይጸላልና፡ሥራው፡እ
ንዳይገለጥበት፡ወደ፡ብርሃን፡
አይመጣም፡ሥራው፡ክፉ፡ስለ፡
፳፩ ሆነ። ኤፌ፡፭፡፲፫። እውነት፡የሚያደ
ርግ፡ግን፡ሥራው፡ይገለጥ፡ዘን
ድ፡ወደ፡ብርሃን፡ይመጣል፡በእ
ግዚአብሔር፡ይሠራልና። ኤፌ፡
፳፪ ፭፡፲፱። ከዚህም፡በኋላ፡ኢየሱስ፡
ከደቀ፡መዛሙርቱ፡ጋራ፡ወደ፡
ይሁዳ፡ምድር፡ሔደ፡በዚያም፡
ከእነርሳቸው፡ጋራ፡ሲያጠም
፳፫ ቅ፡ኖረ። ም፡፬፡፩፡፪። ዮሐንስም፡ደ
ግሞ፡በሳሌም፡አቅራቢያ፡በ
ሄኖን፡ያጠምቅ፡ነበር፡በዚያ
ም፡እጅግ፡ውኃ፡ነበረና፡ብዙ፡
ሰዎች፡ወደ፡እርሱ፡እየመጡ፡
ይጠመቁ፡ነበሩ። ም፡፩፡፲፫።
፳፬ ዮሐንስ፡ገና፡ወደ፡ግዞት፡ቤት፡
አልገባም፡ነበርና። ማቴ፡፲፬፡፫።
፳፭ በዮሐንስ፡ደቀ፡መዛሙርትና፡በ
አይሁድም፡መካከል፡ስለ፡ማንጻ
ት፤ማጥመቅ፡ክርክር፡ነበረ። ዘ
፳፮ ኍል፡፴፩፡፳፫። ወደ፡ዮሐንስም፡መጥ
ተው፡መምህር፡ሆይ፡በዮርዳኖስ፡
ማዶ፡ከአንተ፡ጋራ፡የነበረው፡እ

ንተ፡ ሰማዕተ፡ ኮንከ፡ በእንቲ
አሁ፡ ናሁ፡ ሀሎ፡ ውእቱሂ፡ ያጠ
ምቅ፡ ወኵሉ፡ የሐውር፡ ኀቤሁ፨
፳፯ ወአውሥአ፡ ዮሐንስ፡ ወይቤ፡
ኢይክል፡ ሰብእ፡ ነሢአ፡ ጸጋ፡ ለ
ሊሁ፡ ወኢምንተኒ፡ እመ፡ ኢተ
ውህበ፡ ሎቱ፡ እምሰማይ፨
፳፰ አንትሙ፡ ለሊክሙ፡ ሰማዕትየ፡
ከመ፡ እቤለክሙ፡ አነሰ፡ ኢኮን
ኩ፡ ክርስቶስሃ፡ ዳዕሙ፡ ተፈነ
ውኩ፡ ቅድሜሁ፡ እሰብክ፡ ሎቱ።
፳፱ ዘቦቱ፡ መርዓት፡ መርዓዊ፡ ውእ
ቱ፡ ወአርኩሰ፡ ለመርዓዊ፡ ዘይቀ
ውም፡ ወይሰምዖ፡ ፍሥሐ፡ ይት
ፌሣሕ፡ በእንተ፡ ቃለ፡ መርዓዊ፡
ወፍሥሓ፡ ዚአየሰ፡ ናሁ፡ ተፈጸ
፴ መት፡፡ ወእንቲአሁ፡ ትበዝኅ፡
ወእንቲአየሰ፡ ትሰልጠት፨
፴፩ እስመ፡ ዘእምላዕሉ፡ መጽአ፡ መ
ልዕልተ፡ ኵሉ፡ ውእቱ፡ ወዘእም
ድርሰ፡ ምድራዊ፡ ውእቱ፡ ወዘበ
ምድር፡ ይነግር፡ ወዘሰ፡ እምሰ
ማይ፡ መልዕልተ፡ ኵሉ፡ ውእቱ።
፴፪ በዘርእየ፡ ወበዘሰምዐ፡ ሰማዕ
ተ፡ ይከውን፡ ወስምዖሰ፡ አልቦ፡
ዘይትዌክፎ፨
ወዘሰ፡ ተወክፈ፡ ስምዖ፡ ዐተበ፡
ከመ፡ እግዚአብሔር፡ ጻድቅ፡

ኛትም፡ የመሰክርህለት፡ እነሆ፡
እርሱ፡ ያጠምቃል፡ ሁሉም፡ ወ
ደ፡ እርሱ፡ ይመጣሉ፡ አሉት፤ ም፡ ፩
፳፯ ፳፯፡-፴፩ ፨ ዮሐንስም፡ መልሶ፡ አለ፡
ሰው፡ ከሰማይ፡ ካልተሰጠው፡ እ
ንዳች፡ ያገኝ፡ ዘንድ፡ አይችልም፤
ም፡ ፲፱፡ ፲፩፡፡ ዕብ፡ ፭፡ ፬ ፨
፳፰ እኔም፡ እመሰክር፡ ዘንድ፡ በፊቱ፡
ተላኪ፡ አለሁ፡ እንጂ፡ ክርስቶስ፡
አይደለሁ፡ እንዳ፡ አልሁ፡ እናንተ፡
ራሳችሁ፡ ምስክሮቼ፡ ናችሁ፨
፳፱ ም፡ ፩፡ ፩፡ ፳ ፨ ሙሽራ፡ ያለችው፡ እር
ሱ፡ ሙሽራ፡ ነው፡ እርሱን፡ ቆሞ፡
የሚሰማው፡ የሙሽራው፡ ሚ
ዜ፡ ግን፡ ስለ፡ ሙሽራው፡ ድምፅ፡
ደስ፡ ይለዋል፡ ደስታዬም፡ እነሆ፡
፴ ተፈጸመች፨ ማቴ፡ ፳፪፡ ፪ ፨ የርሱ
ም፡ ትበዛለች፡ የእኔ፡ ግን፡ ታንስ፡
፴፩ ዘንድ፡ ይገ ል፨ ከላይ፡ የመጣ፡ እ
ርሱ፡ ከሁሉ፡ በላይ፡ ነውና፡ ከም
ድር፡ የሆነ፡ ግን፡ እርሱ፡ ምድራ
ዊ፡ ነው፡ የምድሩንም፡ ይናገራ
ል፡ ከሰማይም፡ የመጣ፡ እርሱ፡
፴፪ ከሁሉ፡ በላይ፡ ነው፨ ም፡ ፲፡ ፳፫ ፨ ያየ
ውም፡ በሰማውም፡ ይመሰክራል፡
ምስክርነቱንም፡ ማንም፡ አይቀ
፴፫ በለውም፨ ቀ፡ ፲፩ ም፡ ፫፡ ፲፱፡ ፴፩ ፨ ምስክር
ቱን፡ የተቀበለ፡ ግን፡ እግዚአብ

ውእቱ፨

፴፬ ወዘ እግዚአብሔር፡ፈነዎ፡ ቃለ፡እግዚአብሔር፡ይነግር፡ እስመ፡አኮ፡በመስፈርት፡ዘይ ሁብ፡እግዚአብሔር፡መንፈሶ፡

፴፭ አብሰ፡ያፈቅር፡ወልዶ፡ወኵሎ አወፈዮ፡ውስተ፡እዴሁ፨

፴፮ ዘየአምን፡በወልድ፡ቦ፡ሕይወ ት፡ዘለዓለም፡ወዘሰ፡ኢየአም ን፡በወልድ፡ኢይሬእያ፡ለሕይ ወት፡አላ፡መቅሠፍቱ፡መዓቱ፡ ለእግዚአብሔር፡ይነብር፡ላዕ ሌሁ፨

ምዕራፍ፡፬።

ከዮሐንስ፡ይልቅ፡የኢየሱስ፡ደቀ፡መዛሙርት፡እ ንዲበዙ፡፡ ስለ፡ሰማርያ፡ሴት፡፡ ስለ፡ሰጋዲት፡

፩ ወአእሚሮ፡እግዚእ፡ከመ፡ ሰምዑ፡ፈሪሳውያን፡ከመ፡ብ ዝኀ፡አርድኢሁ፡ለእግዚእ፡ኢ የሱስ፡ወአብዝኀ፡አጥምቆ፡ እምዮሐንስ፨

፪ ወባሕቱ፡ለሊሁ፡ እግዚእ፡ኢየሱስ፡ኢያጠምቅ፡ ዳዕሙ፡አርድኢሁ፨

፫ ወኀደጋ፡ለምድረ፡ይሁዳ፡ወ ሖረ፡ካዕበ፡ገሊላ፨

፬ ወእንዘ፡ሀለዎ፡ይኅልፍ፡እንተ፡ ሰማርያ፨

ሔር፡እውነተኛ፡እንዲሆነ፡አ

፴፬ ተመ{አሰረደ} ሮሜ፡፫፡፬፨ እግዚአብሔርም፡የላከው፡የእግዚአብሔርን፡ነገር፡ይናገራል፡እ ግዚአብሔር፡መንፈሱን፡ሰፍ

፴፭ ሮ፡አይሰጥምና፤ ም፡፩፡፴፫፡፴፩፨ አብ ም፡ልጁን፡ይወዳልና፡ሁሉንም፡ በእጁ፡ሰጠው፤ ማቴ፡፲፩፡፳፯፡፳፰፡፲፰፨

፴፮ በወልድ፡ያመነ፡የዘለዓለም፡ ሕይወት፡አለው፡በወልድ፡የማ ያምን፡ግን፡የእግዚአብሔር፡ ቁጣ፡በላዩ፡ይኖርበታል፡እንጂ፡ ሕይወትን፡አያይም፨ ቁ፡፲፯፡፲፰፡ኢሳ፡ ፱፡፫፡ራእ፡፲፬፡፲፡፲፩፨

አራት፡ምዕራፍ።

ነገር፡በቅፍርናሆም፡የአንዱን፡ሹም፡ልጅ፡ እንደ፡አዳነ፡፡

ኢየሱስም፡ከዮሐንስ፡አብል ጦ፡እንዲ፡አጠመቀና፡ብዙ፡ደቀ፡ መዛሙርት፡እንዲ፡አደረገ፡ፈ ሪሳውያን፡መስማታቸውን፡አ

፪ ውቆ፨ ም፡፫፡፳፪፡፳፮፨ ቢሆንም፡ደ ቀ፡መዛሙርቱ፡እንጂ፡ራሱ፡ኢ የሱስ፡አላጠመቀም፡ነበር፨

፫ ይሁዳንም፡አገር፡ትቶ፡ሁለ ተኛ፡ወደ፡ገሊላ፡ሔደ፨

፬ በሰማርያም፡በኵል፡ያልፍ፡ዘ ንድ፡የሚያስፈልገው፡ስለ፡ነ

፭ ወበጽሐ፡ ሀገረ፡ ሰምር፡ እንተ፡ ስማ፡ ሲካር፡ ቅሩበ፡ ዓፀደ፡ ወይን፡ ዘወሀበ፡ ያዕቆብ፡ ለዮሴፍ፡ ወልዱ።

፮ ወሀሎ፡ ህየ፡ ዓዘቅት፡ ማይ፡ ዘያዕቆብ፡ ወደኪሞ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ በሐዊረ፡ ፍኖት፡ ነበረ፡ ህየ፡ ኀበ፡ ዓዘቅት፡ ወቀትር፡ ሶቤሃ፡ ጊዜ፡ ስሱ፡ ሰዓት።

፯ ወመጽአት፡ ብእሲት፡ እምሰማርያ፡ ከመ፡ ትቅዳሕ፡ ማየ፡ ወይቤላ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ አስትይኒ፡ ማየ። ፰ እስመ፡ አርዳኢሁሰ፡ ሖሩ፡ ሀገረ፡ ከመ፡ ይሣየጡ፡ ሲሳዮሙ።

፱ ወትቤሎ፡ ይእቲ፡ ብእሲት፡ ሳምራዊት፡ እፎኑ፡ እንዘ፡ አይሁድ፡ አንተ፡ ትስእል፡ እምኀቤየ፡ ትስተይ፡ ማየ፡ እንዘ፡ ሳምራዊት፡ አነ፡ እስመ፡ ኢየኀብሩ፡ ኅርመት፡ አይሁድ፡ ምስለ፡ ሳምራውያን።

፲ ወአውሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ ወይቤላ፡ ሶበሰ፡ ታአምሪ፡ ጸጋሁ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወመኑ፡ ውእቱ፡ ዘይስእለኪ፡ ወይቤለኪ፡ አስትይኒ፡ ማየ፡ አንቲ፡ ዓዲ፡ አ

፭ በረ። ያዕቆብ፡ ለልጁ፡ ለዮሴፍ፡ ወደ፡ ሰጠው፡ ሲካር፡ ወደሚልዋት፡ መንደር፡ አጠገብ፡ ወደ፡ እለችው፡ ወደ፡ ሰማርያ፡ ደረሰ።

፮ ዘፍጥ፡ ፵፰፡ ፳፪። በዚያም፡ የያዕቆብ፡ ውኃ፡ ምንጭ፡ ነበረ፡ ኢየሱስም፡ መንገድ፡ በመሔድ፡ በደከመ፡ ጊዜ፡ ከዚያው፡ ከምንጩ፡ ዘንድ፡ ተቀመጠ፡ ጊዜውም፡ ስድስት፡ ሰዓት፡ ያህል፡ ነበረ።

፯ እነሆም፡ ሴት፡ ውኃ፡ ልትቀዳ፡ ከሰማርያ፡ መጣች፡ ኢየሱስም፡ ውኃ፡ አጠጪኝ፡ አላት። ቁ፡ ፱።

፰ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ምግባቸውን፡ ሊገዙ፡ ወደ፡ መንደር፡ ገብተው፡ ነበሩና።

፱ የሰማርያይቱም፡ ሴት፡ አለችው፡ እኔ፡ የሰማርያ፡ ሴት፡ ስሆን፡ አንተ፡ የአይሁድ፡ ወገን፡ ሁነህ፡ እንዴት፡ ውኃ፡ ትጠጣ፡ ዘንድ፡ ከእኔ፡ ትለምናለህ፡ አይሁድ፡ ከሰማርያ፡ ሰዎች፡ ጋራ፡ በሥርዓት፡ አይገናኙም፡ ነበረና። ማቴ፡ ፲፡ ፭።

፲ ኢየሱስም፡ መለሰ፡ የእግዚአብሔርን፡ ስጦታና፡ ውሀ፡ አጠጪኝ፡ የሚልሽ፡ ማን፡ እንደ፡ ሆነ፡ አውቀሽስ፡ ቢሆን፡ አንቺም፡ በለመንሽውና፡ እርሱም፡ የሕይወ

ምስአልኪዮ፡ወወእቱኒ፡እም
ወሀበኪ፡ማየ፡ሕይወት።
፲፩ ወትቤሎ፡ይእቲ፡ብእሲት፡እግ
ዚኦ፡ማሣየብኒ፡አልብከ፡ወ
ዓዘቅቱኒ፡ዕሙቅ፡ውእቱ፡እ
ምአይቴ፡እንከ፡ለከ፡ማየ፡ሕይ
ወት። ፲፪ አንተኑ፡ተዐቢ፡እምያዕ
ቆብ፡አቡነ፡ዘወሀበነ፡ዘንተ፡
ዓዘቅተ፡ውእቱኒ፡ሰተየ፡እም
ኔሃ፡ወደቂቁኒ፡ወእንስሳሁኒ፨
፲፫ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡
ወይቤላ፡ኵሉ፡ዘይሰቲ፡እም
ዝ፡ማይ፡ይጸምእ፡ዳግመ።
፲፬ ወዘሰ፡ይሰቲ፡እማይ፡ዘእሁቦ፡
አነ፡ኢይጸምእ፡ለዓለም፡አላ፡
ውእቱ፡ማይ፡ዘእሁቦ፡አነ፡ይ
ከውን፡ውስቴቱ፡ነቅዐ፡ማይ፡
ዘይፈለፍል፡ለሕይወት፡ዘለ
ዓለም።
፲፭ ወትቤሎ፡ይእቲ፡ብእሲት፡እ
ግዚኦ፡ሀበኒዮ፡እምውእቱ፡
ማይ፡ከመ፡ኢይጸማእ፡ወኢይ
ምጻእ፡ዝየ፡ዳግመ፡እቅዳሕ።
፲፮ ወይቤላ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ሑ
ሪኪ፡ጸውዒ፡ምተኪ፡ወንዒ፡ዝ
የ። ፲፯ ወአውሥአት፡ይእቲ፡ብእ
ሲት፡ወትቤሎ፡አልብየ፡ምተ፨
ወይቤላ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ሠ

ትን፡ውኃ፡በሰጠሽ፡ነበር፡አላት፨
ም፡፯፡፳፫፡፳፱።
፲፩ ሴቲቱም፡አለችው፡አቤቱ፡መ
ቅጃ፡የለህም፡ምንጩም፡ጥል
ቅ፡ነው፡የሕይወት፡ውኃ፡ከወ
ዴት፡ታገኛለህ።
፲፪ አንተስ፡ይህን፡ምንጭ፡ከሰጠን፡
ከአባታችን፡ከያዕቆብ፡ትበል
ጣለህን፡እርሱም፡ከዚህ፡ጠጣ፡
ልጆቹም፡እንስሶቹም።
፲፫ ኢየሱስም፡መልሶ፡አላት፡ከዚ
ህ፡ውኃ፡የሚጠጣው፡ሁሉ፡ሁለ
ተኛ፡ይጠማል። ም፡፯፡፴፰፨
፲፬ እኔ፡ከምሰጠው፡ውኃ፡የሚጠ
ጣ፡ግን፡ለዘለዓለም፡አይጠማ
ም፡ነገር፡ግን፡እኔ፡የምሰጠው
ውኃ፡በእርሱ፡ውስጥ፡ለዘለ
ዓለም፡የሚፈልቅ፡የሕይወት፡
ውኃ፡ምንጭ፡ይሆንለታል። ም፯፡፴፰፨
፲፭ ሴቲቱም፡አቤቱ፡እንዳልጠማ
ና፡ለመቅዳትም፡ሁለተኛ፡ወደ
ዚህ፡እንዳልመጣ፡ከዚያው፡ው
ኃ፡ስጠኝ፡አለችው። ም፡፯፡፴፬።
፲፮ ኢየሱስም፡ሒደሽ፡ባልሽን፡ጥ
ሪና፡ወደዚህ፡ነዪ፡አላት።
፲፯ ሴቲቱም፡መልሳ፡ባልም፡የለኝ፡
አለችው፡ኢየሱስም፡አላት፡
ባል፡የለኝም፡በማለትሽ፡መል

ናየ፡ ትቤሊ፡ አልብየ፡ ምት።
፲፰ እስኩ፡ ኃምስቱ፡ ዕደው፡ ነበሩ
ምስሌኪ፡ ወይእዜሰ፡ ዘሀሎ
ምስሌኪ፡ ኢኮነ፡ ምትኪ፡ ወዘ
ንተሰ፡ አማነ፡ ትቤሊ።
፲፱ ወትቤሎ፡ ይእቲ፡ ብእሲት፡ እ
ግዚእየ፡ እሬእየከ፡ ከመ፡ ነቢ
ይ፡ አንተ።
፳ አበዊነሰ፡ በዝንቱ፡ ደብር፡ ሰ
ገዱ፡ ወአንትሙሰ፡ ትብሉ፡ ከ
መ፡ በኢየሩሳሌም፡ መካን፡ ው
እቱ፡ ኀበ፡ ይሰግዱ።
፳፩ ወይቤላ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ እ
መኒ፡ ብእሲቶ፡ ከመ፡ ትመጽ
እ፡ ሰዓት፡ ወይበጽሕ፡ ጊዜ፡ ኢ
በዝንቱ፡ ደብር፡ ወኢበኢየሩ
ሳሌም፡ መካን፡ እመ፡ ኢየሰግ
፳፪ ዱ፡ ለአብ። አንትሙሰ፡ ትሰግ
ዱ፡ ለዘኢተአምሩ፡ ወንሕነሰ፡
ንሰግድ፡ ለዘነአምር፡ እስመ፡
መድኃኒት፡ እምነ፡ አይሁድ፡ ው
እቱ።
፳፫ ወባሕቱ፡ ትመጽእ፡ ሰዓት፡ ወይ
እዜ፡ ይእቲ፡ አመ፡ እለ፡ በርቱ
ዕ፡ በአማን፡ ሰጋድያን፡ ይሰግ
ዱ፡ ለአብ፡ በመንፈስ፡ ወበጽድ
ቅ፡ እስመ፡ አብኒ፡ ዘከመዝ፡ የኃ
ሥሥ፡ ዘይሰግዱ፡ ሎቱ።

ካም፡ ትናገርሽ።
፲፰ አስቀድሞ፡ አምስት፡ ባሎች፡
ነበሩሽ፡ ዛሬ፡ ከአንቺ፡ ጋራ፡ ያ
ለው፡ ግን፡ ባልሽ፡ አይደለም
ና፡ ይህንም፡ እውነት፡ አልሽ።
፲፱ ሴቲቱም፡ አለችው፡ አቤቱ፡
አንተ፡ ነቢይ፡ እንደሆንህ፡ አ
ይሃለሁ። ቀ፡ ፳፱፡ ም፡ ፯፡ ፲፬።
፳ አባቶቻችን፡ በዚህ፡ ተራራ፡ ሰ
ገዱ፡ እናንተ፡ ግን፡ ይሰግድበ
ት፡ ዘንድ፡ የሚገባ፡ ስፍራ፡ በኢ
የሩሳሌም፡ ነው፡ ትላላችሁ።
፳፩ ዘጸዓ፡ ፲፪፡ ፫፡ መዝ፡ ፻፳፪። ኢየሱስም፡ አ
ላት፡ አንቺ፡ ሴት፡ በዚህም፡ ተራ
ራ፡ በኢየሩሳሌምም፡ ቢሆን፡
ለአብ፡ የማይሰግዱበት፡ ጊዜ፡
እንዲመጣ፡ እመኚኝ። ሚል፡ ፩፡ ፲፩
፳፪ ሉቃ፡ ፲፯፡ ፳፡ ፳፫። እናንተ፡ ለማታው
ቁት፡ ትሰግዳላችሁ፡ እኛ፡ ግን፡
ለምናውቀው፡ እንሰግዳለን፡
መድኃኒት፡ ከአይሁድ፡ ነውና።
፪ ነገ፡ ፲፯፡ ፳፱፡ ዘፍ፡ ፵፱፡ ፲፡ ሚክ፡ ፭፡ ፪።
፳፫ ነገር፡ ግን፡ በእውነት፡ የሚሰግ
ዱ፡ በመንፈስም፡ በእውነትም፡
ለአብ፡ የሚሰግዱበት፡ ጊዜ፡ ት
መጣለች፡ እርሱዋም፡ አሁን፡ ና
ት፡ አብ፡ እንዲህ፡ የሚሰግዱ
ለትን፡ ይሻልና።

፳፬ እስመ፡ እግዚአብሔር፡ መንፈስ፡ ውእቱ፡ ወእለሂ፡ ይሰግዱ፡ ሎቱ፡ በመንፈስ፡ ወበጽድቅ፡ ሀለዎሙ፡ ይስግዱ፡ ሎቱ።

፳፭ ወትቤሎ፡ ይእቲ፡ ብእሲት፡ ነአምር፡ ከመ፡ ይመጽእ፡ መሲሕ፡ ዘይብልዎ፡ ክርስቶስ፡ ወአመ፡ መጽአ፡ ውእቱ፡ ይነግረነ፡ ኵሎ።

፳፮ ወይቤላ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ አነ፡ ውእቱ፡ ዘእትናገረኪ።

፳፯ ወእምዝ፡ መጽኡ፡ አርዳኢሁ፡ ወአንከርዎ፡ እስመ፡ ምስለ፡ ብእሲት፡ ይትናገር፡ ወባሕቱ፡ አልቦ፡ ዘይቤሎ፡ ምንተ፡ ተኃሥሥ፡ ወምንተ፡ ትትናገር፡ ምስሌሃ።

፳፰ ወኃደገት፡ ቀሡታ፡ ይእቲ፡ ብእሲት፡ ወአተወት፡ ሀገረ፡ ወነገረቶ፡ ለሰብእ፡ ወትቤ።

፳፱ ንዑ፡ ትርአዩ፡ ብእሴ፡ ዘነገረኒ፡ ኵሎ፡ ዘገበርኩ፡ እንዳዒ፡ ለእመ፡ ውእቱ፡ ክርስቶስ።

፴ ወወፅኡ፡ እምሀገር፡ ወሖሩ፡ ኀቤሁ።

፴፩ ወበይእቲ፡ ሰዓት፡ ሰአልዎ፡ አርዳኢሁ፡ ወይቤልዎ፡ ረቢ፡ ብላዕ።

፴፪ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ አንሰ፡ ብየ፡ መብልዕ፡

፳፬ እግዚአብሔርም፡ መንፈስ፡ ስለሆነ፡ የሚሰግዱለትም፡ በመንፈስ፡ በእውነትም፡ ይሰግዱለት፡ ዘንድ፡ ይገባል። ፪ቆሮ፫፡፲፯፡ መዝ፡ ፶፡ ፲፡ ፲፰።

፳፭ ሴቲቱም፡ ክርስቶስ፡ የሚሉት፡ መሲሕ፡ እንዲመጣ፡ እናውቃለን፡ እርሱም፡ በመጣ፡ ጊዜ፡ ሁሉን፡ ይገልጽልናል፡ አለችው። ም፡፩፡፵፩፡ ዳን፡፱፡፳፭።

፳፮ ኢየሱስም፡ የምናገርሽ፡ እኔ፡ እርሱ፡ ነኝ፡ አላት። ም፡፱፡፴፯፡ ኢሳ፡ ፶፪፡፯፡፲፭፡፩።

፳፯ በዚያም፡ ጊዜ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ መጡና፡ ከሴት፡ ጋራ፡ በመናገሩ፡ አደነቁ፡ ነገር፡ ግን፡ ምን፡ ትሻለህ፡ ለምንስ፡ ከእርስዋ፡ ጋራ፡ ትናገራለህ፡ ያለው፡ የለም። ቁ፱።

፳፰ ሴቲቱም፡ እንስራዋን፡ ትታ፡ ወደ፡ ከተማ፡ ሒዳ፡ ለሰዎች፡ ነገረች፡ አለችም።

፳፱ ያደረግሁትን፡ ሁሉ፡ የነገረኝን፡ ሰው፡ ኑ፡ መጥታችሁ፡ እዩ፡ ይህ፡ ክርስቶስ፡ እንደሆነ፡ እንጃ።

፴ ቍ፲፯፡፳፯። ከከተማም፡ ወጥተው፡ ወደ፡ እርሱ፡ መጡ።

፴፩ በዚህም፡ ጊዜ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ መምህር፡ ሆይ፡ ብላ፡ ብለው፡ ለመኑት።

፴፪ ኢየሱስም፡ እናንተ፡ የማታውቁት፡ እኔ፡ የምበላው፡

ዘኢተአምርዎ፡ አንትሙ።
፴፫ ወተበሀሉ፡ አርዳኢሁ፡ በበይ
ናቲሆሙ፡ ቦኑ፡ እንጋ፡ ሰብእ፡
ዘአምጽአ፡ ሎቱ፡ ዘይበልዕ።
፴፬ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየ
ሱስ፡ ሊተሰ፡ መብልዕየ፡ ውእ
ቱ፡ ከመ፡ እግበር፡ ፈቃደ፡ ለአቡ
የ፡ ዘፈነወኒ፡ ወከመ፡ እፈጽም፡
ግብሮ።
፴፭ አኮኑ፡ አንትሙ፡ እለ፡ ትብሉ፡ እ
ስከ፡ ራብዕ፡ ወርኅ፡ ይከውን፡ ለ
ማዕረር። ናሁ፡ እብለክሙ፡ አ
ንሥኡ፡ አዕይንቲክሙ፡ ወነ
ጽሩ፡ ኅበ፡ በሓውርት፡ ከመ፡ ፀ
ዐደወ፡ ወበጽሐ፡ ለማዕረር።
፴፮ እስመ፡ ዘየዐፅድ፡ ይነሥእ፡
ዓስበ፡ ወያስተጋብእ፡ ፍሬ፡ ለ
ሕይወት፡ ዘለዓለም፡ ከመ፡ ዓቡ
ረ፡ ይትፌሥሑ፡ ዘሂ፡ ይዘርእ፡
ወዘሂ፡ የዐርር።
፴፯ ወዝንቱ፡ ነገር፡ ቃለ፡ ጽድቅ፡ እ
ሙን፡ ውእቱ፡ ከመ፡ ካልእ፡ ዘይ
ዘርእ፡ ወካልእ፡ ዘየዐርር።
፴፰ ወአንሰ፡ ፈነውኩክሙ፡ ትዕ
ርሩ፡ በዘ ኢፃመውክሙ፡ በዘ
ባዕድ፡ ፃመወ፡ ወአንትሙ፡ ት
በውኡ፡ ውስተ፡ ፃማሆሙ፡ ለ
አልክቱ።
፴፱ ወብዙኃን፡ እምይ

መብል፡ አለኝ፡ አላቸው።
፴፫ ደቀ፡ መዛሙርቱም፡ እርስ፡ በ
እርሳቸው፡ ምናልባት፡ ሰው፡
የሚበላውን፡ አምጥቶለት፡ ይ
ሆን፡ ተባባሉ።
፴፬ ኢየሱስም፡
አላቸው፡ የእኔስ፡ መብል፡ የላ
ከኝን፡ ፈቃድ፡ አደርግ፡ ዘንድ
ና፡ ሥራውንም፡ እፈጽም፡ ዘን
ድ፡ ነው። ዮም፡ ፯፡ ፴፰፡ ፵፡ መዝ፡ ፵፡ ፱።
፴፭ እናንተስ፡ እስከ፡ አራት፡ ወር፡ መ
ከር፡ ይደርሳል፡ የምትሉ፡ አይ
ደላችሁምን፡ እነሆ፡ እላችኋ
ለሁ፡ ዓይኖቻችሁን፡ አንሡ፡፡
መከሩም፡ ሊደርስ፡ እንደ፡ ገረጣ፡
ምድሩን፡ ተመልከቱት። ማቴ፡ ፱፡ ፴፯
፴፮ የሚያጭድም፡ ዋጋውን፡ ይቀበ
ላል፡ የሚያጭድና፡ የሚዘራም፡
በአንድ፡ ደስ፡ ይላቸው፡ ዘንድ፡
ለዘለዓለም፡ ሕይወት፡ ፍሬን፡
ይሰበስባል።
፴፯ አንዱ፡ እንዲዘራ፡ ሌላውም፡
እንዲያጭድ፡ ይህ፡ ነገር፡ በእ
ውነት፡ የታመነ፡ ነውና።
፴፰ እኔም፡ ያልደከማችሁበትን፡ ታ
ጭዱ፡ ዘንድ፡ እናንተን፡ ላክኋ
ችሁ፡ ሌሎችም፡ በደከሙበት፡
እናንተ፡ በድካማቸው፡ ገባችሁ።
፴፱ ከዚያችም፡ ከሰማርያ፡ ከተ

አቲ፡ ሀገረ፡ ሰምር፡ አምኑ፡ በ
ቱ፡ በእንተ፡ ዘትቤሎሙ፡ ይእ
ቲ፡ ብእሲት፡ ዘሰምዐ፡ ከነቶ፡
እንዘ፡ ትብል፡ ነገረኒ፡ ኵሎ፡
፵ ዘገበርኩ። ወበጽሑ፡ ኀቤ
ሁ፡ ሳምራውያን፡ አስተብቍ
ዕዎ፡ ከመ፡ ይንበር፡ ኀቤሆሙ፡
ወነበረ፡ ህየ፡ ሰኑየ፡ መዋዕለ።
፵፩ ወብዙኃን፡ ጥቀ፡ እምኔሆሙ፡
አለ፡ አምኑ፡ በቱ፡ በእንተ፡ ቃሉ።
፵፪ ወይቤልዋ፡ ለይእቲ፡ ብእሲት፡
አኮ፡ እንከ፡ በነገረ፡ ዚአኪ፡ ዘአ
መነ፡ ቦቱ፡ አላ፡ ለሊነ፡ ሰማዕነ፡
ወጠየቅነ፡ ከመ፡ ዝንቱ፡ ውእቱ፡
ክርስቶስ፡ በአማን፡ መድኅኒ
፵፫ ዓለም። ወእምድኅረ፡ ሰኑይ፡ ር
መዋዕል፡ ወፅአ፡ እግዚእ፡ ኢየ
ሱስ፡ እምህየ፡ ወሖረ፡ ገሊላ።
፵፬ ወለሊሁ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ሰ
ማዕተ፡ ኮነ፡ ከመ፡ ኢይከብር፡
ነቢይ፡ በሀገሩ።
፵፭ ወበዊኦ፡ ገሊላ፡ ተቀበልዎ፡ ኵ
ሎሙ፡ ገሊላውያን፡ እስመ፡
ርእዩ፡ ተአምረ፡ ዘገብረ፡ በ
ኢየሩሳሌም፡ አመ፡ በዓል፡ እ
ስመ፡ እሙንቱኒ፡ ሖሩ፡ ለበዓ
ል።
፵፮ ወሖረ፡ ካዕበ፡ እግዚእ፡ ኢየሱ

ማ፡ ያች፡ ሴት፡ የሠራሁትን፡
ሁሉ፡ ነገረኝ፡ ብላ፡ ስለ፡ መሰ
ከረችው፡ ነገር፡ ብዙ፡ ሰዎች፡
አመኑበት።
፵ የሰማርያም፡ ሰዎች፡ ወደ፡ እር
ሱ፡ መጥተው፡ ከእነርሳቸው፡
ጋራ፡ ይቀመጥ፡ ዘንድ፡ ለመኑ
ት፡ በዚያም፡ ሁለት፡ ቀን፡ ተቀ
፵፩ መጠ። እጅግ፡ የሚበዙትም፡
ስለ፡ ቃሉ፡ አመኑበት።
፵፪ ሴቲቱንም፡ እኛ፡ ይህ፡ በእውነ
ት፡ የዓለም፡ መድኃኒት፡ ክርስ
ቶስ፡ እንዲሆን፡ ሰምተነዋል፡ ተ
ረድተናል፡ ነው፡ እንጂ፡ በአንቺ፡
ቃል፡ ያመንበት፡ አይደለም፡ አ
፵፫ ሉዋት። ከሁለት፡ ቀንም፡ በኋ
ላ፡ ከዚያ፡ ወጥቶ፡ ወደ፡ ገሊላ፡
ሔደ። ማቴ፡ ፬፡ ፲፪፡ ፲፫።
፵፬ ነቢይም፡ በሀገሩ፡ እንደይከብ
ር፡ ኢየሱስ፡ ራሱ፡ ምስክር፡ ሆ
ነ። ማቴ፡ ፲፫፡ ፶፯።
፵፭ ወደ፡ ገሊላም፡ በመጣ፡ ጊዜ፡ የ
ገሊላ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ በበዓል፡ ቀ
ን፡ በኢየሩሳሌም፡ ያደረገው
ን፡ ተአምራት፡ ስለ፡ አዩ፡ ተቀ
በሉት፡ እነርሳቸውም፡ ለበ
ዓል፡ መጥተው፡ ነበሩና።
፵፮ ኢየሱስም፡ ደግሞ፡ ውሀው

ስ፡ ውስተ፡ ቃና፡ ዘገሊላ፡ ኀበ፡
ረሰዮ፡ ማየ፡ ወይነ። ወሀሎ፡ ህ
የ፡ አሐዱ፡ ገብረ፡ ንጉሥ፡ ሰብ
እ፡ እኅበያታዊ፡ ወይደዊ፡ ወል
ዱ፡ በቅፍርናሆም፨

፵፯ ወሰሚዖ፡ ከመ፡ መጽአ፡ እግዚእ
ኢየሱስ፡ እምይሁዳ፡ ውስተ፡
ገሊላ፡ ሖረ፡ ኀቤሁ፡ ወሰአሎ፡ ከ
መ፡ ይረድ፡ ወያሕዩ፡ ሎቱ፡ ወ
ልዶ፡ እስመ፡ አልጸቀ፡ ይሙት፤

፵፰ ወይቤሎ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ አ
መ፡ ተአምረ፡ ወመንክረ፡ ኢርኢ
ክሙ፡ ኢተአመኑ፨

፵፱ ወይቤሎ፡ ውእቱ፡ ገብረ፡ ንጉሥ
ሰኅብእ፡ እኅብያታዊ፡ እግዚኦ፡ ረ
ድ፡ ፍጡነ፡ ዘእንበለ፡ ይሙት፡
ወልድየ፨

፶ ወይቤሎ፡ እግዚእ፡
ኢየሱስ፡ ሑር፡ ወልድከሰ፡ ሐ
ይወ፡ ወአምነ፡ ውእቱ፡ ብእሲ፡
በቃል፡ ዘይቤሎ፡ እግዚእ፡ ኢ
የሱስ፡ ወሖረ፨

፶፩ ወእንዘ፡ ይወ
ርድ፡ ተቀበልዎ፡ አግብርቲሁ፡
ወዜነውዎ፡ ወይቤልዎ፡ ወልድ
ከሰ፡ ሐይወ፨

፶፪ ወተስእሎሙ፡ ሰ
ዓተ፡ እንተ፡ ባቲ፡ ሐይወ፡ ወይቤ
ልዎ፡ ትማልም፡ ጊዜ፡ ሰብዑ፡ ሰ
ዓቱ፡ ኀደጎ፡ ፈፀንቱ፨

፶፫ ወአእመረ፡
አቡሁ፡ ከመ፡ ጊዜ፡ ይእቲ፡ ሰዓት፡

ን፡ ጠጅ፡ ወዱ፡ አደረገበት፡ ወደ፡
ቃና፡ ዘገሊላ፡ መጣ፡ በቅፍርና
ሆምም፡ ልጁ፡ የታመመበት፡
የንጉሥ፡ ወገን፡ የሚሆን፡ አን
ድ፡ ሹም፡ ነበረ፨ ም፡ ፬፡ ፩፡ ፱፨

፵፯ እርሱም፡ ኢየሱስ፡ ከይሁዳ፡
ወደ፡ ገሊላ፡ እንደ፡ መጣ፡ በሰማ፡
ጊዜ፡ ልጁ፡ ለሞት፡ ቀርቦ፡ ነበርና፡
ያድንለት፡ ዘንድ፡ እንዲወርድ፡
ወደ፡ እርሱ፡ ሒዶ፡ ለመነው፨

፵፰ ኢር፡ ፲፯፡ ፲፩፨ ኢየሱስም፡ ምልክት፡
ና፡ ተአምራት፡ ካላያችሁ፡ አታ
ምኑም፡ አለው፨ ም፡ ፬፡ ፲፫፡ ፩ቆሮ፡ ፩፡ ፳፪፨

፵፱ ያም፡ ሹም፡ ጌታ፡ ሆይ፡ ልጁ፡ ሳይ
ሞት፡ ፈጥነህ፡ ውረድ፡ አለው።

፶ ኢየሱስም፡ ልጅህ፡ ድኖልሃል
ና፡ ሒድ፡ አለው፡ ያም፡ ሰው፡ ኢ
የሱስ፡ በነገረው፡ ቃል፡ አምኖ፡
ሒዶ፨ ም፡ ፲፩፡ ፲፱፨

፶፩ ሲወርድም፡ አገልጋዮቹ፡ ተቀ
በሉት፡ ልጅህም፡ ድኗል፡ አሉ
ት፨

፶፪ እርሱም፡ የዳነባትን፡ ሰዓት፡ ጠየቃቸ
ው፡ ትናንትና፡ በሰባት፡ ሰዓት፡
ንዳዱ፡ ተወው፡ አሉት፨

፶፫ አባቱም፡ ኢየሱስ፡ ልጅህ፡ ድኖ
ልሃል፡ ባለው፡ ሰዓት፡ እንደ፡ ሆነ

እንተ፡ ይቤሎ፡ እግዚእ፡ ኢየ
ሱስ፡ ወልድከ፡ ሐይወ፡ ወአ
ምነ፡ ውእቱ፡ ወኵሉ፡ ሰብአ፡
ቤቱ ። ፶፬ ወዝንቱ፡ ካዕበ፡ ዳግሙ፡
ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ዘገብረ፡
ተአምረ፡ መጺኦ፡ እምይሁዳ፡
ውስተ፡ ገሊላ ።

ምዕራፍ፡ ፭ ።

መፃጕዕን፡ እንዴ፡ አዳነ፡፡ አይሁድ፡ በመፃጕዕ
መሬወሰ፡ እንዴ፡ ተቈጡ፡ ና፡ ጌታም፡ ብዙ፡ ኗ

፩ ወእምድኅረዝ፡ ኮነ፡ በበዓሉ
ሙ፡ ለአይሁድ፡ ዓርገ፡ እግዚ
እ፡ ኢየሱስ፡ ኢየሩሳሌም ።
፪ ወበ፡ ውስተ፡ ኢየሩሳሌም፡ ም
ጥማቃት፡ ዘጽሩ ጸዋቄ፡ ዘውእ
ቱ፡ ቀላየ፡ አባግዕ፡ ብሂል፡ ወይ
ብልዋ፡ ሰማ፡ በዕብራይስጥ፡ ቤ
ቴ፡ ሳይዳ፡ ወባቲ፡ ኃምስቱ፡ ሐ
ዋራት ። ፫ ወህየ፡ ይሰክቡ፡ ብዙኃ
ን፡ ድውያን፡ ዕውራን፡ ወሐንካ
ሳን፡ ወይቡሳን፡ ወይጸንሑ፡ ሁ
ከተ፡ ማይ ።
፬ እስመ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፡
በጊዜ፡ ይወርድ፡ ውስተ፡ ምጥ
ማቃት፡ ወየሀውክ፡ ለማይ፡ ዘ
ይወርድ፡ ቀዲሙ፡ እምድኅረ፡
ሁከተ፡ ማይ፡ ወይትኀፀብ፡ የሐ
ዩ፡ እምኵሉ፡ ደዌ፡ ዘቦ ።

ቸ፡ አወቀ፡ እርሱና፡ ቤቱ፡ ሰዎ
ቹ፡ ሁሉ፡ አመኑ ። ዘፍጥ፡ ፲፫፡ ፲፱ ።
፶፬ ኢየሱስም፡ ከይሁዳ፡ ወደ፡ ገሊ
ላ፡ መጥቶ፡ ያደረገው፡ ሁለተኛ፡
ተአምራት፡ ይህ፡ ነው ። ም፡ ፪፡ ፲፩፡ ፳፫፡

አምስት፡ ምዕራፍ ።

ያሉ፡ ቃል፡ እንደ፡ መለሰላቸው ።

፩ ከዚህም፡ በኋላ፡ የአይሁድ፡ በ
ዓል፡ ሆነ፡ ኢየሱስም፡ ወደ፡ ኢየ
ሩሳሌም፡ ወጣ ። ዘሌዋ፡ ፳፫ ፳፬ ።
፪ በኢየሩሳሌምም፡ በበጎ፡ ገበያ፡
አጠገብ፡ በዕብራይስጥ፡ ቤተ፡ ሳ
ይዳ፡ የሚልዋት፡ መጠመቂያ፡ ነ
በረች፡ አምስት፡ መድረክም፡ ነበ
ራት ። ነህም፡ ፫፡ ፩ ።
፫ በዚያም፡ ብዙ፡ በሽተኞች፡ ዕው
ሮችና፡ አንካሶች፡ ጎባጦችም፡ ተ
ኝተው፡ የውሀውን፡ መናወጥ፡ ይ
ጠብቁ፡ ነበሩ ።
፬ የእግዚአብሔር፡ መልአክ፡ ወ
ዱ፡ መጠመቂያው፡ ወርዶ፡ ውሀ
ውን፡ ባናወጠው፡ ጊዜ፡ ውሀው፡
ሲንቀሳቀስ፡ አስቀድሞ፡ ወርዶ፡
የሚጠመቅ፡ ካለበት፡ ደዌ፡ ሁሉ፡
ይፈወስ፡ ነበርና ።

፭ ወሀሎ፡ ህየ፡ አሐዱ፡ ብእሲ፡ ዘ
ሠላሳ፡ ወሰመንቱ፡ ዓመቱ፡ እ
ምዘ ደወየ።

፮ ወኪያሁ፡ ርእዮ፡ እግዚእ፡ ኢ
የሱስ፡ እንዘ፡ ይሰክብ፡ ውስተ፡
ዓራቱ፡ አእመረ፡ ከመ፡ ጕንደ
የ፡ ውስተ፡ ደዌሁ፡ ወይቤሎ፡
ትፈቅድኑ፡ ትሕየው።

፯ ወአውሥአ፡ ውእቱ፡ ድውይ፡
ወይቤሎ፡ እወ፡ እግዚኦ፡ አላ፡ ሰ
ብእ፡ አልብየ፡ ከመ፡ ሰበ፡ ይትሀ
ወክ፡ ማይ፡ ያወርደኒ፡ ውስተ፡ ም
ጥምቃት፡ ወሶበ፡ እመጽእ፡ አነ፡
ባዕድ፡ ይቀድመኒ፡ ወረደ።

፰ ወይቤሎ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ተ
ንሥእ፡ ወንሣእ፡ ዓራተከ፡ ወሑ
ር። ፱ ወሐይወ፡ ሶቤሃ፡ ውእቱ፡ ብእ
ሲ፡ ወነሥአ፡ ዓራቶ፡ ወሖረ። ወሰ
ንበት፡ አሚሃ፡ ይእቲ፡ ዕለት።

፲ ወይቤልዎ፡ አይሁድ፡ ለዘሐይወ፡
ሰንበት፡ ውእቱ፡ ዮም፡ ወኢይከ
ውነከ፡ ከመ፡ ትፁር፡ ዓራተከ።

፲፩ ወአውሥአ፡ ወይቤሎሙ፡ ዘአሐ
የወኒ፡ ውእቱ፡ ይቤለኒ፡ ፁር፡ ዓ
ራተከ፡ ወሑር።

፲፪ ወተስእልዎ፡ ወይቤልዎ፡ መኑ፡
ውእቱ፡ ብእሲሁ፡ ዘይቤለከ፡ ፁ
ር፡ ዓራተከ፡ ወሑር።

፭ ከታመመም፡ ሠላሳ፡ ስምንት፡
ዓመት፡ የሆነው፡ አንድ፡ ሰው፡
በዚያ፡ ነበር።

፮ ኢየሱስም፡ እርሱን፡ ከአልጋ፡
ተኝቶ፡ ባየው፡ ጊዜ፡ ብዙ፡ ዘመን፡
እንደ፡ ታመመ፡ አውቆ፡ ልትፈወ
ስ፡ ትወዳለህን፡ አለው።

፯ ድውዩም፡ መልሶ፡ አዎን፡ ጌታዬ፡
ሆይ፡ ነገር፡ ግን፡ ውሀው፡ በተናወ
ጠ፡ ጊዜ፡ ወደ፡ መጠመቂያው፡ የ
ሚያወርደኝ፡ ሰው፡ የለኝም፡ እ
ኔም፡ እስክመጣ፡ ድረስ፡ ሌላው፡
ቀድሞኝ፡ ይወርዳል፡ አለው።

፰ ኢየሱስም፡ ተነሣና፡ አልጋህን፡
ተሸክመህ፡ ሒድ፡ አለው።

፱ ያም፡ ሰው፡ ያን፡ ጊዜውን፡ ዳነና፡ እ
ልጋውን፡ ተሸክሞ፡ ሔደ፡ ያችም፡
ቀን፡ ሰንበት፡ ነበረች። ም፡ ፱፡ ፲፬።

፲ አይሁድም፡ የዳነውን፡ ሰው፡ ዛ
ሬ፡ ሰንበት፡ ነው፡ አልጋህንም፡ ተ
ሸክም፡ ዘንድ፡ አይገባህም፡ አሉት። ፲

፲፩ ዘፀአ፡ ፳፡ ፲። ኤር፡ ፲፯፡ ፳፩። እርሱም፡ መል
ሶ፡ ያዳነኝ፡ እርሱ፡ አልጋህን፡ ተሸ
ክምና፡ ሒድ፡ ብሎኛል፡ አላቸው።

፲፪ እነርሱም፡ አልጋህን፡ ተሸክምና፡
ሒድ፡ ያለህ፡ ሰው፡ ማነው፡ ብለ
ው፡ ጠየቁት።

፲፫ ወውእቱሰ፡ ዘሐይወ፡ ኢያእመረ፡ መኑ፡ ውእቱ፡ ዘአሕየዎ፡ እስመ፡ ተሠወረ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ማዕከለ፡ ብዙኃን፡ ሰብእ፡ እለ፡ ሀለዉ፡ በውእቱ፡ መካን።

፲፬ ወእምዝ፡ ረከቦ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ለውእቱ፡ ዘሐይወ፡ በምኵራብ፡ ወይቤሎ፡ ናሁ፡ ሐየውከ፡ ዑቅ፡ ኢተአብስ፡ ዳግመ፡ ከመ፡ ዘየአኪ፡ እምዝ፡ ኢይርከብከ።

፲፭ ወሖረ፡ ውእቱ፡ ብእሲ፡ ወነገሮሙ፡ ለአይሁድ፡ ከመ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ውእቱ፡ ዘአሕየዎ።

፲፮ ወበእንተ፡ ዝንቱ፡ ይሰድድዎ፡ አይሁድ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወየኃሥሡ፡ ይቅትልዎ፡ እስመ፡ ከመዝ፡ ይገብር፡ በሰንበት።

፲፯ ወአውሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወይቤሎሙ፡ አቡየ፡ እስከ፡ ይእዜ፡ ይገብር፡ ወአነሂ፡ እገብር።

፲፰ ወበእንተ፡ ዝንቱ፡ ፈድፋደ፡ የኃሥሡ፡ አይሁድ፡ ይቅትልዎ፡ እስመ፡ አኮ፡ ክመ፡ ሰንበተ፡ ባሕቲቶ፡ ዘይሠዐር፡ ዳዕሙ፡ ዓዲ፡ አባሁ፡ ይሬስዮ፡ ለእግዚአብሔር፡ ወያዔሪ፡ ርእሶ፡ ምስለ፡ እግዚአብሔር።

፲፫ የተፈወሰው፡ ግን፡ ያዳነው፡ ማን፡ እንደሆነ፡ አላወቀም፡ ኢየሱስ፡ ከዚያ፡ ቦታ፡ በነበሩት፡ ሰዎች፡ መካከል፡ ተሠውሮ፡ ነበረና፤

፲፬ ከዚህም፡ በኋላ፡ ኢየሱስ፡ በመቅደስ፡ አገኘውና፡ እነሆ፡ ተፈወስህ፡ ከዚህም፡ የባሰ፡ እንዳያገኝህ፡ ሁለተኛ፡ አትበድል፡ አለው። ምሳ፡ ፲፬፡ ፴፬፡፡ ሕዝ፡ ፲፰፡ ፩ ፳ መዝ፡ ፴፰

፲፭ ፬፡ ፫። ያም፡ ሰውም፡ ሔዶ፡ ያዳነው፡ ኢየሱስ፡ እንደሆነ፡ ለአይሁድ፡ ነገረ።

፲፮ በሰንበትም፡ እንደዚህ፡ ያደርግ፡ ስለ፡ ነበረ፡ አይሁድ፡ ኢየሱስን፡ ያሳድዱትና፡ ሊገድሉትም፡ ይፈልጉ፡ ነበሩ። ሉቃ፡ ፲፬፡ ፫፡ ፭።

፲፯ ኢየሱስ፡ ግን፡ አባቴ፡ እስከ፡ ዛሬ፡ ያደርጋል፡ እኔም፡ ደግሞ፡ አደርጋለሁ፡ ብሎ፡ መለሰላቸው።

፲፰ ም፡ ፱፡ ፬፡ ፲፬፡ ፲። ስለዚህም፡ ደግሞ፡ አይሁድ፡ ይገድሉት፡ ዘንድ፡ ጠንክረው፡ ይፈልጉት፡ ነበሩ፡ ዳግመኛ፡ እግዚአብሔርን፡ አባቴ፡ ያደርግና፡ ራሱንም፡ ከእግዚአብሔር፡ ጋራ፡ ያስተካክል፡ ነበር፡ እንጂ፡ ሰንበትን፡ ብቻ፡ የሻረ፡ አይደለምና። ሮሜ፡ ፲፡ ፴፩፡ ፊል፡ ፪፡ ፮።

፲፱ ወእምዝ፡ አውሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወይቤሎሙ፡ አማን፡ አማን፡ እብለክሙ፡ ኢይክል፡ ወልድ፡ ገቢረ፡ ዘእምኀቤሁ፡ ወኢምንተኒ፡ ዘእንበለ፡ ዘርእዮ፡ ለአብ፡ እንዘ፡ ይገብር፡ እስመ፡ ግብረ፡ ዘይገብር፡ አብ፡ ወልድኒ፡ ኪያሁ፡ ይገብር፡ በአምሳሉ።

፳ እስመ፡ አብ፡ ያፈቅር፡ ወልዶ፡ ወኵሎ፡ ያርእዮ፡ ዘውእቱ፡ ይገብር፡ ወዘየዐቢ፡ እምዝ፡ ግብረ፡ ያርእዮ፡ ከመ፡ አንትሙ፡ ታንክሩ።

፳፩ ወበከመ፡ አብ፡ ያነሥአሙ፡ ለምውታን፡ ወያሐይዎሙ፡ ከማሁ፡ ወልድኒ፡ ዘፈቀደ፡ ያሐዩ።

፳፪ እስመ፡ አብሰ፡ ኢይኴንን፡ ወኢመነሂ፡ አላ፡ ኵሎ፡ ኵነኔሁ፡ አወፈዮ፡ ለወልዱ።

፳፫ ከመ፡ ኵሉ፡ ሰብእ፡ ያክብርዎ፡ ለወልድ፡ በከመ፡ ያከብርዎ፡ ለአብ፡ ወዘሰ፡ ኢያከብር፡ ለወልድ፡ ኢያከብሮ፡ ለአብ፡ ዘፈነዎ።

፳፬ አማን፡ አማን፡ እብለክሙ፡ ዘይሰምዕ፡ ቃልየ፡ ወ የአምን፡ በዘፈነወኒ፡ ይረክብ፡ ሕይወተ፡ ዘለዓለም፡ ወኢየሐውር፡ ውስተ፡ ዱ

፲፱ ኢየሱስም፡ መለሰ፡ አላቸው፡ እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ ወልድ፡ ከራሱ፡ አንዳች፡ ያደርግ፡ ዘንድ፡ አይቻልም፡ አብ፡ ሲያደርግ፡ ያየውን፡ እንጂ፡ አብም፡ የሚሠራውን፡ ሥራ፡ ወልድ፡ ደግሞ፡ እንደሁ፡ ያደርጋል። ም፡ ፫፡ ፲፩፡ ፴፪፡ ፲፡ ፳፯፡ — ፳፲።

፳ አብ፡ ልጁን፡ ይወዳልና፡ እርሱም፡ የሚያደርገውን፡ ሁሉ፡ ያሳየዋል፡ እናንተም፡ ታደንቁ፡ ዘንድ፡ ከዚህ፡ የሚበልጥ፡ ሥራ፡ ያሳየዋል። ማቴ፡ ፫፡ ፲፯፡ ም፡ ፩፡ ፱።

፳፩ አብም፡ ሙታንን፡ እንደ ያስነሣቸውና፡ ሕያዋንም፡ እንደ ያደርጋቸው፡ እንዲሁም፡ ወልድ፡ የፈቀደው፡ ሕያው፡ ያደርጋል። ዘዳግ፡ ፴፪፡ ፴፱፡ ሆሴ፡ ፮፡ ፪።

፳፪ አብም፡ በማንም፡ አይፈርድም፡ ፍርዱን፡ ሁሉ፡ ለወልድ፡ ሰጥቶታል፡ እንጂ። ዳን፡ ፯፡ ፲፫፡ ፲፬፡ የሐዋ፡ ፲፯፡ ፴፩።

፳፫ ሰዎች፡ ሁሉ፡ አብን፡ እንደ፡ ያከብሩ፡ ወልድን፡ ያከብሩ፡ ዘንድ፡ ወልድንም፡ የማያከብር፡ የላከውን፡ አብን፡ አያከብርም። ፊል፡ ፪፡ ፲፡ ፲፩፡ ፩ዮሐ፡ ፪፡ ፳፫።

፳፬ እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ ቃሌን፡ የሚሰማ፡ በላከኝም፡ የሚያምን፡ የዘለዓለም፡ ሕይወት፡ አለው፡ ወደ፡ ፍርድም፡ አይ

ይን፡ አላ፡ ዐደወ፡ እሞት፡ ውስ
ተ፡ ሕይወት።

፳፭ አማን፡ አማን፡ እብለክሙ፡ ከመ፡
ይበጽሕ፡ ጊዜሁ፡ ወይእዜ፡ ውእ
ቱ፡ አመ፡ ምውታን፡ ይሰምዕዎ፡
ቃሎ፡ ለወልደ፡ እግዚአብሔር፡
ወእለሰ፡ ሰምዕዎ፡ የሐይዉ።

፳፮ ወበከመ፡ ለአብ፡ ቦቱ፡ ሕይወት፡
ኀቤሁ፡ ከማሁ፡ ለወልድኒ፡ ወሀ
በ፡ ከመ፡ ይኩን፡ ሕይወት፡ ኀቤሁ።

፳፯ ወወሀቦ፡ ሥልጣነ፡ ከመ፡ ይግበር፡
ኰነኔ፡ እስመ፡ ወልደ፡ እግዚአብ
ሔር፡ ወልደ፡ እጓለ፡ እመሕያው፡
ውእቱ።

፳፰ ወበእንተ፡ ዝንቱ፡ ኢታ
ንክሩ፡ እስመ፡ ትመጽእ፡ ሰዓ
ት፡ በዘይሰምዕዎ፡ ቃሎ፡ ኵሎ
ሙ፡ እለ፡ ውስተ፡ መቃብር።

፳፱ ወይወፅኡ፡ እለ፡ ሠናየ፡ ገብሩ፡
ውስተ፡ ትንሣኤ፡ ዘለሕይወት፡
ወእለሰ፡ እኩየ፡ ገብሩ፡ ውስተ፡
ትንሣኤ፡ ዘለደይን።

፴ ኢይክል፡ አንሰ፡ ገቢረ፡ ለልየ፡
ዘእምኀቤየ፡ ወኢምንትኒ፡ አ
ላ፡ በከመ፡ ሰማዕኩ፡ እኴንን፡ ወ
ኰነኔየኒ፡ ጽድቅ፡ ውእቱ፡ እስ
መ፡ ኢየኀሥሥ፡ ፈቃደ፡ ዚአየ፡

ሔድም፡ ከሞት፡ ወደ፡ ሕይወት፡ ተ
ሻገረ፡ እንጂ። ም፡ ፲፫፡ ፴፯ ። መዝ፡ ፴፪፡ ፩፡ ፪፡

፳፭ ሮሜ፡ ፲፡ ፩፡ ፩ዮሐ፡ ፫፡ ፲፬። እውነት፡ እውነት፡
እላችኋለሁ፡ ሙታን፡ የእግዚአብሔር
ን፡ ልጅ፡ ድምፅ፡ የሚሰሙ
ባት፡ ጊዜ፡ እንድትመጣ፡ እርሷ
ም፡ ዛሬ፡ ናት፡ የሚሰሙትም፡ ሕ
ያዋን፡ ይሆናሉ። ኤፌ፡ ፪፡ ፭፡ ፮።

፳፮ ለአብ፡ በእርሱ፡ ዘንድ፡ ሕይወት፡
እንዳለው፡ እንደሁም፡ ደግ
ሞ፡ ለወልድ፡ ሕይወት፡ በእርሱ፡ ተ
ሆን፡ ዘንድ፡ ሰጠው። ምሬ፡ ፩፡ ፩፡ ፬፡ ፩ዮሐ፡ ፭፡ ፲፩

፳፯ ፩። ደግሞም፡ የእግዚአብሔር፡ ል
ጅ፡ የሰው፡ ልጅ፡ ስለ፡ ሆነ፡ ይፈር
ድ፡ ዘንድ፡ ሥልጣን፡ ሰጠው። ዳን፡ ፯

፳፰ ፲፫፡ ፲፬። በመቃብርም፡ ውስጥ፡ ያ
ሉት፡ ሁሉ፡ ድምፁን፡ የሚሰ
ሙባት፡ ጊዜ፡ ትመጣለችና፡ በዚ
ህ፡ አታድንቁ። ፩ተሰ፡ ፬፡ ፲፮።

፳፱ መልካምም፡ የሠሩ፡ ወደ፡ ሕይ
ወት፡ ትንሣኤ፡ ክፉም፡ የሠሩ፡
ወደ፡ ፍርድ፡ ትንሣኤ፡ ይወጣ
ሉ። ም፡ ፳፡ ፵፮ ። ዳን፡ ፲፪፡ ፪።

፴ እኔም፡ ከራሴ፡ አንዳች፡ አደርግ፡
ዘንድ፡ አልችልም፡ እንደ፡ ሰማ
ሁ፡ እፈርዳለሁ፡ እንጂ፡ ፍርዴ
ም፡ እውነት፡ ነው፡ የላከኝን፡ ፈቃ
ድ፡ እንጂ፡ የራሴን፡ ፈቃድ፡ አል

ዘእንበለ፡ ፈቃዱ፡ ለዘፈነወ
ኒ። ፴፩ ወእመሰ፡ ለሊየ፡ ሰማዕ፡ኮ
ንኩ፡ ለርእስየ፡ ኢኮነ፡ እሙነ፡
ስምዕየ።
፴፪ ካልእ፡ ውእቱ፡ ሰማዕትየ፡ ወአ
አምር፡ ከመ፡ ጽድቅ፡ ውእቱ፡
ስምዑ፡ ዘሰምዐ፡ በእንቲአየ።

፴፫ አንትሙ፡ ለአክሙ፡ ኀበ
ዮሐንስ፡ ወነገረክሙ፡ ሰም
ዓ፡ በጽድቅ።
፴፬ ወአንሰ፡ እኮ፡ ሰምዐ፡ ሰብእ፡
ዘአፈቅድ፡ ወባሕቱ፡ ዘንተ፡
እብል፡ ከመ፡ አንትሙ፡ ትድኀ
ኑ።
፴፭ ዝንቱ፡ ውእቱ፡ ማኅቶት፡ ዘየ
ኀቱ፡ ወያበርህ፡ ወአንትሙ፡
ፈቀድክሙ፡ ትትፈሥሑ፡ በ
ብርሃኑ፡ እሐተ፡ ሰዓተ።
፴፮ ወአንሰ፡ ብየ፡ ሰማዕት፡ ዘየዓ
ቢ፡ እምስምዐ፡ ዮሐንስ፡ እስ
መ፡ ግብር፡ ዘወሀበኒ፡ አቡየ፡
ከመ፡ እግበር፡ ወእፈጽም፡ው
እቱ፡ ግብር፡ ዘእገብር፡ ሰማ
ዕትየ፡ ከመ፡ አብ፡ ፈነወኒ።

፴፯ ወአቡየ፡ ዘፈነወኒ፡ ውእቱ፡
ሰማዕትየ፡ ወእምአመ፡ ኮን

ሸምና። ቍ፲፱፡ ም፡፯፡ ፴፫።
፴፩ እኔም፡ ለራሴ፡ ብመሰክር፡ ም
ስክርነቴ፡ እውነት፡ አይደለ
ም። ም፳፫፡፲፫፡፲፬፡፶፬።
ለእኔ፡ የሚመሰክረው፡ ሌላ፡
ነው፡ ስለ፡ እኔም፡ የሚመሰክ
ራት፡ ምስክርነት፡ እውነት፡ እ
ንደሆነች፡ አውቃለሁ። ቍ፷፯።
፴፫ ማቴ፡፫፡፲፯። እናንተ፡ ወደ፡ ዮሐ
ንስ፡ ላካችሁ፡ እርሱም፡ እው
ነት፡ መሰከሮ፡ ነገራችሁ። ም፡፩
፴፬ ፲፱። እኔም፡ የሰው፡ ምስክርነ
ት፡ የምቀበል፡ አይደለሁም፡
ነገር፡ ግን፡ እናንተ፡ ትድኑ፡ ዘ
ንድ፡ ይህን፡ እላለሁ።
፴፭ የሚቃጠልና፡ የሚያበራም፡
መብራት፡ እርሱ፡ ነበረ፡ እናን
ተም፡ ጥቂት፡ ጊዜ፡ በብርሃኑ፡
ደስ፡ ይላችሁ፡ ዘንድ፡ ወደዳች
ሁ። ፴፮ እኔ፡ ግን፡ ከዮሐንስ፡ም ስ
ክርነት፡ የሚበልጥ፡ ምስክር፡
አለኝ፡ እፈጽመውና፡ እሠራው፡
ዘንድ፡ አባቴ፡ የሰጠኝ፡ ሥራ፡ ይ
ህ፡ የምሠራው፡ ሥራ፡ አብ፡ እ
ንደ፡ ላከኝ፡ እርሱ፡ ስለ፡ እኔ፡ ይ
መሰክራልኛልና። ፩ዮሐ፡፭፡፱ ም፲፡፲፮
፴፯ የላከኝ፡ አብም፡ እርሱ፡ ስለ፡ እ
ኔ፡ መሰከረ፡ ከሆነም፡ ጀምሮ፡

ክሙ፡ ቃሎ፡ ኢሰማዕክሙ፡ ወራእዮሂ፡ ኢርኢክሙ።

፴፰ ወቃሉሂ፡ አልብክሙ፡ ወኢይነብር፡ ኀቤክሙ፡ እስመ፡ ዘወእቶ፡ ፈነወ፡ ኪያሁ፡ ኢአመንክሙ።

፴፱ ኃሥሡ፡ ውስተ፡ መጻሕፍት፡ እስመ፡ ቦቱ፡ ይመስለክሙ፡ ዘትረክቡ፡ ሕይወተ፡ ዘለዓለም፡ ወእማንቱ፡ ሰማዕትየ።

፵ ወኢትፈቅዱ፡ ትምጽኡ፡ ኀቤየ፡ ከመ፡ ትርከቡ፡ ሕይወተ።

፵፩ አኮ፡ ኢይፈቅድ፡ ያድሉ፡ ሊቱ፡ ሰብእ።

፵፪ ወባሕቱ፡ አመርኩክሙ፡ ከመ አልብክሙ፡ ፍቅረ፡ እግዚአብሔር፡ ላዕሌክሙ።

፵፫ አነ፡ መጻእኩ፡ በስመ፡ አቡየ፡ ወኢትወክፉኒ፡ ወእመ፡ መጽአ፡ ካልእ፡ በስመ፡ ነፍሱ፡ ኪያሁ፡ ትትዌከፉ።

፵፬ እፎ፡ ትክሉ፡ አሚነ፡ አንትሙ፡ ዘትትበደሩ፡ ክብረ፡ እምቢጽክሙ፡ ወኢትኃሥሡ፡ ክብረ፡ እምእግዚአብሔር፡ ዋሕድ።

፵፭ ኢይምሰልክሙ፡ ዘአነ፡ አሰቱ

ድምፁን፡ ከቶ፡ አልሰማችሁም፡ መልኩንም፡ አላያችሁም። ማቴ፡ ፫፡ ፲፯፡ ዘፀአ፡ ፴፫፡ ፳።

፴፰ ቃሉም፡ በእናንተ፡ ዘንድ፡ አይኖርም፡ እርሱ፡ በላከው፡ አላመናችሁምና።

፴፱ መጻሕፍትን፡ መርምሩ፡ በእነርሳቸው፡ የዘለዓለም፡ ሕይወትን፡ የምታገኙ፡ ይመስላችኋልና፡ እነርሳቸው፡ ግን፡ ስለ፡ እኔ፡ ይመሰክራሉ።

፵ ኢሳ፡ ፴፬፡ ፲፮፡፡ ዘዳግ፡ ፲፰፡ ፲፭-፲፰። የዘለዓለም፡ ሕይወትንም፡ ታገኙ፡ ዘንድ፡ ወደ፡ እኔ፡ መምጣት፡ አትወዱም።

፵፩ ማቴ፡ ፳፬፡ ፭። እኔም፡ ከሰው፡ ክብርን፡ እቀበል፡ ዘንድ፡ አልሻም።

፵፪ ቁ. ፴፬፡ ፵፩። ነገር፡ ግን፡ የእግዚአብሔር፡ ፍቅር፡ እንዴ፡ ሌለባችሁ፡ አወቅኋችሁ።

፵፫ እኔ፡ በአባቴ፡ ስም፡ መጥቼ፡ አልተቀበላችሁኝም፡ ሌላው፡ ግን፡ በራሱ፡ ስም፡ ቢመጣ፡ እርሱን፡ ትቀበሉታላችሁ። ማቴ፡ ፮፬፡ ፳፫።

፵፬ እናንተ፡ እርስ፡ በርሳችሁም፡ መከባበርን፡ የምትወዱ፡ ከአንዱ፡ ከእግዚአብሔር፡ ያለውንም፡ ክብር፡ የማትሹ፡ ታምኑ፡ ዘንድ፡ እንዴት፡ ትችላላችሁ። ም. ፲፪፡ ፵፪ ፵፫።

፵፭ እኔም፡ ከአብ፡ ዘንድ፡ የማጣ

ቀዱየክሙ፡ኀበ፡አብ፡አሉ፡ሀ
ሎ፡ዘያስተዋዱየክሙ፡ወው
እቱ፡ሙሴ፡ዘአንትሙ፡ትሴ
ፈውዎ፨

፵፮ ሶበሰ፡ አመንክምዎ፡ ለሙሴ
ኪያየኒ፡እምአመንክሙኒ፡
እስመ፡በእንቲአየ፡ጸሐፈ፡ር
ውእቱ፨

፵፯ ወእመሰ፡ዘጸሐፈ፡ሙሴ፡ኢ
ተአምኑ፡እፎ፡ቃልየ፡ት አ
ምኑ፨

ምዕራፍ፤ ፮ ።

አምስት፡እንጀራና፡ሁለት፡ዓሣ፡አበርክቶ፡አም
ስት፡ሺ፡ሰዎች፡እንደ፡አጸገበ፨ሊያነግሡት፡እ

፩ ወእምድኅረ፡ዝንቱ፡ሖረ፡እ
ግዚእ፡ኢየሱስ፡ማዕዶተ፡ባሕ
ረ፡ገሊላ፡ዘጥብርያዶስ፨

፪ ወተለውዎ፡ብዙኃን፡አሕዛብ፡
እስመ፡ርእዩ፡ተአምረ፡ዘገብ
ረ፡በላዕለ፡ድውያን፨

፫ ወዐርገ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ው
ስተ፡ደብር፡ወነበረ፡ም
ስለ፡አርዳኢሁ፨

፬ ወአልጸቀ፡በዓለ፡ፋሲካሆሙ፡
ለአይሁድ፨

፭ ወአንሥአ፡አዕይንቲሁ፡እግ
ዚእ፡ኢየሱስ፡ወርእየ፡ብዙ
ኃነ፡ሰብአ፡እንዘ፡ይመጽኡ፡

ላችሁ፡አይመስላችሁ፡የሚ
ያጣላችሁስ፡አለ፡እርሱም፡
እናንተ፡ተስፋ፡የምታደርጉ
ት፡ሙሴ፡ነው፨ዘጸዓ፡፴፩፡፲፯፨

፵፮ በሙሴም፡ብታምኑ፡እኔን፡ባ
መናችሁ፡ነበር፡እርሱ፡
ስለ፡እኔ፡ጽፎአልና፨ዘፍጥ፡፫፡፲፭
፵፱፡፲፨ዘዳግ፡፲፰፡፲፭፨

፵፯ ሙሴ፡የጻፈውንስ፡ካላመናች
ሁ፡በእኔ፡ቃል፡እንዴት፡ታም
ናላችሁ፨

ስድስት፡ምዕራፍ።

እንደ፡ፈለጉ፡በታንኳ፡ሳይሆን፡በእግሩ፡በባሕር፡ሳይ
እንደሔደ፨የሕይወት፡እንጀራ፡እኔ፡ነኝ፡እንደ፡አለ፨

፩ ከዚህ፡በኋላ፡ኢየሱስ፡የጥብ
ርያዶስ፡አውራጃ፡አውራጃ፡ወ
ደሚሆን፡ወደ፡ገሊላ፡ባሕር፡ር
ማዶ፡ሔደ፨

፪ አጅግም፡ሰዎች፡
ተከተሉት፡በድውያን፡የሚ
ያደርገውን፡ተአምራት፡አይ
ተዋልና፨

፫ ኢየሱስ፡ግን፡ወደ፡
ተራራ፡ወጥቶ፡ከደቀ፡መዛ
ሙርቱ፡ጋራ፡ከዚያ፡ተቀመ
ጠ፨

፬ የአይሁድም፡የፋሲካ፡በ
ዓል፡ቀርቦ፡ነበረ፨ም፡፪፡፲፫፡፲፩፡፶፭፨

፭ ኢየሱስም፡ዓይኖቹን፡አቅንቶ፡
ብዙ፡ሰዎች፡ወደ፡እርሱ፡ ሲ
መጡ፡አየና፡ፊልጶስን፡እነዚ

ኀቤሁ፡ ወይቤሎ፡ ለፊልጶስ፡
እምአይቴ፡ ንሣየጥ፡ ኅብስተ፡
ዘናበልዖሙ፡ ለእሉ፨
፮ ወዘንተ፡ ይቤ፡ እንዘ፡ ያሜክ
ሮ፡ ወውእቱሰ፡ የአምር፡ ዘሀ
ለዎ፡ ይግበር፨
፯ ወአውሥአ፡ ፊልጶስ፡ ወይቤ
ሎ፡ ዘክልኤ፡ ፻ቱ፡ ዲናር፡ ኅብስት፡
ኢየአክሎሙ፡ ከመ፡ ይንሥ
ኡ፡ በበሕቅ፡ ለለ፡ አሐዱ፡ እም
ኔሆሙ፨
፰ ወይቤሎ፡ አሐዱ፡ እምአርዳ
ኢሁ፡ ዘውእቱ፡ እንድርያስ፡
እኁሁ፡ ለስምዖን፡ ጴጥሮስ፤
፱ ሀሎ፡ ዝየ፡ ወልድ፡ ዘቦ፡ ኀምስ
ኅብስተ፡ ሰገም፡ ወክልኤተ፡
ዓሣተ፡ ወባሕቱ፡ ምንተ፡ ይበ
ቍዓ፡ እማንቱ፡ ለዘመጠንዝ፡
፲ ሰብእ፨ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡
ኢየሱስ፡ ግበሩ፡ ምርፋቃተ፡ ለ
ሰብእ፡ ወብዙኅ፡ ሣዕሩ፡ ለውእ
ቱ፡ መካን፡ ወረፈቁ፡ አደዊሆ
ሙ፡ ወየአክሉ፡ ኍልቆሙ፡ መ
ጠነ፡ ኀምሳ፡ ምዕት፡ ብእሲ፨
፲፩ ወነሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ው
እተ፡ ኅብስተ፡ ወአእኰቶ፡ ፈተ
ተ፡ ወወሀቦሙ፡ ለእለ፡ ይረፍ
ቁ፡ ወእምዓሣሁኒ፡ ከማሁ፡ ር

ህን፡ እናበላቸው፡ ዘንድ፡ እን
ጀራ፡ ከወዴት፡ እንግዛለን፡ አለ
ው፨ ማቴ፡ ፲፬፡ ፲፫፡ ፳፩፤ ማር፡ ፮፡ ፴፪፡ ፵፬፡ ሉቃ፡ ፱፡ ፲፪፡
፮ ፲፯ ይህንም፡ ማለቱ፡ ሊፈትነ
ው፡ ነው፡ እርሱ፡ ግን፡ የሚያደ
ርገውን፡ ያውቅ፡ ነበር፨
፯ ፊልጶስም፡ መልሶ፡ ከእነርሳ
ቸው፡ እያንዳንዱ፡ ስንኳ፡ ትን
ንሽ፡ ቍራሽ፡ ይወስዱ፡ ዘንድ፡
የሁለት፡ መቶ፡ ዲናር፡ እንጀ
ራ፡ አይበቃቸውም፡ አለው፨
፰ ከደቀ፡ መዛሙርቱም፡ አንዱ፡
የስምዖን፡ ጴጥሮስ፡ ወንድም፡
እርሱም፡ እንድርያስ፡ አለው፤
፱ ከዚህ፡ አምስት፡ የገብስ፡ እን
ጀራና፡ ሁለት፡ ዓሣ፡ የያዘ፡ አን
ድ፡ ልጅ፡ አለ፡ ነገር፡ ግን፡ እነዚ
ህ፡ ይህን፡ ለሚያህል፡ ሰው፡ ም
፲ ን፡ ይበቃሉ፨ ኢየሱስም፡ ሰዎቹ፡
እንዲቀመጡ፡ አድርጉ፡ አላቸ
ው፡ በዚያም፡ ስፍራ፡ እጅግ፡ ሣ
ር፡ ያለበት፡ መስክ፡ ነበር፡ ሰዎ
ቹም፡ ተቀመጡ፡ ቍጥራቸው
ም፡ አምስት፡ ሺህ፡ ያህሉ፡ ነበሩ፨
፲፩ ኢየሱስም፡ እንጀራውን፡ አን
ሥቶ፡ ይዞ፡ አመስግኖ፡ ቈርሶም፡
ለደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ሰጣቸው፡ ደ
ቀ፡ መዛሙርቱም፡ ለተቀመጡት።

መጠነ፡ ፈቀዱ።

ወእምድኅረ፡ ጸግቡ፡ ይቤሎ
ሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ለአርዳ
ኢሁ፡ አስተጋብኡ፡ ዘተርፈ፡
ፍተታተ፡ ከመ፡ አልቦ፡ ዘይት
ገደፍ፡ ወኢምንትኒ፡ እምኔሆ
ን። ወአስተጋብኡ፡ ወመልአ፡
ዓሠርተ፡ ወክልኤተ፡ መሣየ
ምተ፡ እምኃምስቱ፡ ኅብስተ፡
ሰገም፡ ዘተርፈ፡ ፍተታተ፡ እም
ዘበልዑ፡ ወጸግቡ። ወርእዮ
ሙ፡ ሕዝብ፡ ዘገብረ፡ ተአምረ፡
እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ይቤሉ፡ አ
ማን፡ ነቢይ፡ ውእቱ፡ ዝንቱ፡ ዘ
ይመጽእ፡ ውስተ፡ ዓለም።
ወአእመሮሙ፡ እግዚእ፡ ኢየ
ሱስ፡ ከመ፡ ይፈቅዱ፡ ይመጽ
ኡ፡ ይምሥጥዎ፡ ወያንግሥ
ዎ፡ ወተግኅሠ፡ ውስተ፡ ደብ
ር፡ ባሕቲቶ። ወመስዮ፡ ወረዱ
አርዳኢሁ፡ ውስተ፡ ባሕር።
ወዓርጉ፡ ሐመረ፡ ወሖሩ፡ ማዕ
ዶተ፡ ባሕር፡ ኀበ፡ ቅፍርናሆም፡
ወናሁ፡ ወድአ፡ ኮነ፡ ጽልመት፡
ወዓዲሁ፡ ኢመጽአ፡ እግዚእ፡
ኢየሱስ፡ ኀቤሆሙ።

ሰዎች፡ ሰጡ፡ ከዓሣውም፡ እን
ዲሁ፡ የሚያስፈልጋቸውን፡ ያ
ህል። ከጠገቡም፡ በኋላ፡ ደቀ፡
መዛሙርቱን፡ ከእነርሱ፡ አንዳ
ች፡ እንዳይወድቅ፡ የተረፈው
ን፡ ፍርፋሪ፡ አከማቹ፡ አላቸው።

በልተው፡ ከጠገቡትም፡ የተረ
ፈው፡ ከአምስቱ፡ የገብስ፡ እን
ጀራ፡ ፍርፋሪ፡ አሥራ፡ ሁለት፡
መሶብ፡ ሙሉ፡ ሰበሰቡ።
ሕዝቡም፡ ኢየሱስ፡ ያደረገው
ን፡ ተአምራት፡ ባዩ፡ ጊዜ፡ ይህ፡
በእውነት፡ ወደ፡ ዓለም፡ የሚ
መጣው፡ ነቢይ፡ ነው፡ አሉ። ዘዳግ፣
፲፰፡ ፲፭፡ – ፲፰።
ኢየሱስም፡ መጥተው፡ በግድ፡
ያነግሡት፡ ዘንድ፡ እንዲሹ፡
አውቆ፡ ብቻውን፡ ወደ፡ ተራራ፡
ወጣ። ም፡ ፲፬፡ ፳፫።
፲፮ በመሸም፡ ጊዜ፡ ደቀ፡ መዛሙ
ርቱ፡ ወደ፡ ባሕር፡ ወረዱ። ማቴ፡
፲፯ ፲፬፡ ፳፪፡ ፴፫። ማር፡ ፮፡ ፵፯ – ፶፩፡ በታንኳም፡
ገብተው፡ ወደ፡ ባሕር፡ ማዶ፡ ወ
ደ፡ ቅፍርናሆም፡ ተሻገሩ፡ እነ
ሆሙ፡ ፈጽሞ፡ ጨልሞ፡ ነበር፡
ኢየሱስም፡ ገና፡ ወደ፡ እነርሰ
ቸው፡ አልመጣም፡ ነበር።

፲፰ ወባሕርሰ፡ ይትሀወክ፡ እስመ ዓቢይ፡ ነፋስ፡ ይነፍሕ።

፲፱ ወኀሊፎሙ፡ መጠነ፡ ዕሥራ፡ ወኀምስቱ፡ ምዕራፍ፡ አው፡ ሠላሳ፡ ርእይዎ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ እንዘ፡ የሐውር፡ ዲበ፡ ባሕር፡ ወቀርበ፡ ኀበ፡ ሐመር፡ ወፈርሁ።

፳ ወይቤሎሙ፡ ኢትፍርሁ፡ አነ፡ ውእቱ።

፳፩ ወእንዘ፡ ይፈቅዱ፡ ያዕርግዎ፡ ውስተ፡ ሐመር፡ በጽሐት፡ ሐመር፡ ሶቤሃ፡ ውስተ፡ ምድር፡ ኀበ፡ ይፈቅዱ፡ ሐዊረ።

፳፪ ወበሳኒታ፡ ርእዩ፡ ሰብእ፡ እለ፡ ይቀውሙ፡ ማዕዶተ፡ ባሕር፡ ከመ፡ አልቦ፡ ካልእ፡ ሐመር፡ ህየ፡ ዘእንበለ፡ አሐቲ፡ ወከመ ሂ፡ ኢዓርገ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ውስተ፡ ሐመር፡ ምስለ፡ አርዳኢሁ፡ አላ፡ አርዳኢሁ፡ ባሕቲቶሙ፡ ሖሩ።

፳፫ ወመጽአ፡ ካልእት ኒ፡ አሕማር፡ እምጥብርያዶስ፡ ቅሩበ፡ ብሔር፡ ኀበ፡ በልዑ፡ ኅብስተ፡ ዘባረከ፡ እግዚእነ፡

፳፬ ወሶበ፡ ርእዩ፡ እሙንቱ፡ ሰብእ፡ ከመ፡ ኢሀሎ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ህየ፡ ወኢ አርዳኢሁ፡ ዓ

፲፰ ባሕሩ፡ ግን፡ እጅግ፡ ተናወጠ፡ ጽኑ፡ ነፋስ፡ ይነፍስ፡ ነበረና።

፲፱ ሀያ፡ አምስት፡ ወይም፡ ሠላሳ፡ ምዕራፍ፡ ያህል፡ እንደ፡ ሔዱም፡ ኢየሱስን፡ በባሕር፡ ላይ፡ እየሔደ፡ ወደ፡ ታንኳው፡ ሲቀርብ፡ ባዩት፡ ጊዜ፡ ፈሩ።

፳ እርሱም፡ እኔ፡ ነኝ፡ አትፍሩ፡ አላቸው። ኢሳ፡ ፵፫፡ ፩-፫።

፳፩ ወደ፡ ታንኳም፡ ያወጡት፡ ዘንድ፡ ሲፈልጉ፡ ያን፡ ጊዜ፡ ታንኳ ቱ፡ ፈጥና፡ ለመሔድ፡ ወደ፡ ወደ ዱት፡ ምድር፡ ደረሰች።

፳፪ በነገውም፡ በባሕር፡ ዳር፡ ቈመው፡ የነበሩት፡ ሰዎች፡ ከአን ዲት፡ በቀር፡ በዚያ፡ ሌላ፡ ታን ኳ፡ እንዳልነበረ፡ ደቀ፡ መዘሙ ርቱም፡ ለብቻ ቸው፡ ሔዱ፡ እ ንጂ፡ ኢየሱስ፡ ከደቀ፡ መዘሙ ርቱ፡ ጋራ፡ ወደ፡ ታንኳ፡ እንዳል ገባ፡ ባዩ፡ ጊዜ።

፳፫ ደግሞም፡ ጌታችን፡ የባረከው ን፡ እንጀራ፡ ሰበሉበት፡ በታ፡ አቅራቢያ፡ ከሚሆን፡ ከጥብ ርያዶስ፡ ሌሎች፡ ታንኮች፡ መ ጡ። ቍ፡ ፲፩።

፳፬ ሕዝቡም፡ እርሱ፡ ኢ የሱስና፡ ደቀ፡ መዘሙርቱም፡ በዚያ፡ እንደሌሉ፡ ባዩ፡ ጊዜ፡ ወ

ርጉ፡ ውእቶን፡ አሕማር፡ ወበ
ጽሑ፡ ቅፍርናሆም፡ ይኅሥ
ሥዎ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ።
፳፭ ወሶበ፡ ረከብዎ፡ በማዕዶተ፡
ባሕር፡ ይቤልዎ፡ ረቢ፡ ማእ
ዜ፡ መጻእከ፡ ወበጻሕከ፡ ዝየ፧
፳፮ ወአውሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱ
ስ፡ ወይቤሎሙ፡ አማን፡ አማ
ን፡ እብለክሙ፡ ከመ፡ አኮ፡ እን
ቱሙ፡ ዘተኃሥሡኒ፡ በእንተ፡
ዘርኢክሙ፡ ተአምራተ፡ አ
ላ፡ በእንተ፡ ዘበላዕክሙ፡ ኅ
ብስተ፡ ወጸገብክሙ። ፳፯ ተገበ
ሩ፡ እንከ፡ ለመብልዕ፡ ዘይነብ
ር፡ ለሕይወት፡ ዘለዓለም፡ ዘይ
ሁበክሙ፡ ወልዱ፡ እጓለ፡ እመ
ሕያው፡ ወአኮ፡ ለመብልዕ፡ ኃላ
ፊ፡ እስመ፡ ለዝሰ፡ እግዚአብሔ
ር፡ አብ፡ ኃተሞ።
፳፰ ወይቤልዎ፡ ምንተ፡ ንረሲ፡ ከ
መ፡ ንግበር፡ ግብረ፡ እግዚአ
ብሔር። ፳፱ ወአውሥአ፡ እግዚእ፡
ኢየሱስ፡ ወይቤሎሙ፡ ዝን
ቱ፡ ውእቱ፡ ግብረ፡ እግዚአብ
ሔር፡ ከመ፡ ትእመኑ፡ በዘው
እቱ፡ ፈነወ። ፴ ወይቤልዎ፡ ምን
ተ፡ ተአምረ፡ ትገብር፡ ከመ፡
ንርአይ፡ ወንእመንከ፡ በ

ዱ፡ እነዚያው፡ ታንኳች፡ ገብተ
ው፡ ኢየሱስን፡ ሊፈልጉ፡ ወደ፡
ቅፍርናሆም፡ መጡ።
፳፭ በባሕርም ማዶ፡ ባገኙት፡ ጊ
ዜ፡ መምህር፡ ሆይ፡ ወደ፡ ዚህ፡
መቼ፡ መጣህ፡ አሉት።
፳፮ ኢየሱስም፡ መለሰ፡ አላቸው፡
እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለ
ሁ፡ እናንተ፡ የምትሹኝ፡ እንጀ
ራ፡ ስለ፡ በላችሁና፡ ስለ፡ ጸገባ
ችሁም፡ ነው፡ እንጂ፡ ተአምራ
ት፡ ስለ፡ አያችሁ፡ አይደለም።
፳፯ እንግዲህ፡ የሰው፡ ልጅ፡ ለሚ
ሰጣችሁ፡ ለዘለዓለም፡ ሕይወ
ት፡ ለሚኖር፡ መብል፡ ፃሩ (ድ
ከሙ) እንጂ፡ ለሚጠፋው፡ መ
ብል፡ አይደለም፡ ይህንስ፡ እግ
ዚአብሔር፡ አብ፡ አትሞታል
ና። ም፡ ፲፡ ፲፯፡ ፱፡ ፲፱
፳፰ የእግዚአብሔርንም፡ ሥራ፡
እንሠራ፡ ዘንድ፡ ምን፡ እናድር
ግ፡ አሉት። ኢየሱስም መለሰ፡
፳፱ የእግዚአብሔር፡ ሥራ፡ እር
ሱ፡ በላከው፡ ታምኑ፡ ዘንድ፡ ነ
ው፡ አላቸው። ፩ ዮሐ፡ ፫፡ ፳፫፡ ፫
፴ አሉትም፡ አይተን፡ እናምን
ብህ፡ ዘንድ፡ ምን፡ ተአምራት፡
ታደርጋለህ፡ ምንስ፡ ትሠራ

፴፩ ዘገብርኩ፨ አበዊነሰ፡ መና፡ በ
ልዑ፡ በገዳም፡ በከመ፡ ጽሑፍ፡
ኅብስተ፡ እምሰማይ፡ ወሀበ
ሙ፡ ይብልዑ፨
፴፪ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱ
ስ፡ አማን፡ አማን፡ እብለክሙ፡
አኮ፡ ሙሴ፡ ዘወሀበክሙ፡ ው
እቱ፡ ኅብስተ፡ እምሰማይ፡ አ
ላ፡ አቡየ፡ ይሁበክሙ፡ ኅብ
ስተ፡ ጽድቀ፡ እምሰማይ፨
፴፫ እስመ፡ ኅብስቱ፡ ለእግዚአ
ብሔር፡ ውእቱ፡ ዘወረደ፡ እ
ምሰማይ፡ ወይሁብ፡ ሕይወ
ተ፡ ዘለዓለም፨
፴፬ ወይቤልዎ፡ እግዚእ፡ ሀበነ፡
በኵሉ፡ ጊዜ፡ እምውእቱ፡ ኅ
፴፭ ብስት፨ ወይቤሎሙ፡ እግዚ
እ፡ ኢየሱስ፡ አነ፡ ውእቱ፡ ኅ
ብስተ፡ ሕይወት፡ ወዘይመጽ
እ፡ ኀቤየ፡ ኢይርኅብ፡ ወዘዪ፡
የአምኒ፡ ኅብየ፡ ኢይጸምእ፡ ለ
፴፮ ዝሉፉ፨ ወባሕቱ፡ እብለክሙ
ሂ፡ ከመ፡ ርኢክሙኒ፡ ወኢአ
፴፯ መንክሙኒ፨ ኵሉ፡ ዘወሀበ
ኒ፡ አቡየ፡ ይመጽእ፡ ኀቤየ፡
ወለዘሂ፡ መጽአ፡ ኀቤየ፡ ኢያ
ሰድዶ፡ ወኢወፅአ፡ አፍአ፨
፴፰ እስመ፡ አኮ፡ ዘወረድኩ፡ እም

፴፩ ለህ፨ ማቴ፡ ፲፯፡ ፩፨ አባቶቻችን፡ በ
ምድረ፡ በዳ፡ መና፡ በሉ፡ ይበሉ፡
ዘንድ፡ ከሰማይ፡ እንጀራ፡ ሰጣ
ቸው፡ ተብሎ፡ እንዳ፡ ተጻፈ፨
፴፪ ዘፀአ፡ ፲፮፡ ፲፫፡ ፲፬፨ መዝ፡ ፸፯፡ ፳፬፨ ኢየሱስም
አላቸው፡ እውነት፡ እውነት፡
እላችኋለሁ፡ ያን፡ እንጀራ፡
ሙሴ፡ ከሰማይ፡ የሰጣቸው፡ አ
ይደለም፡ እውነተኛ፡ እንጀራ፡ አባቴ፡ ከሰ
ማይ፡ ይሰጣችኋል፡ እንጂ፤ ቊ
፴፫ ፴፫፡ ፶፩፨ ከሰማይም፡ የወረደ፡
ው፡ ለዓለም፡ ሕይወት፡ የሚሰ
ጥ፡ የእግዚአብሔር፡ እንጀራ፡
ነውና፨ ዘጸአ፡ ፲፮፡ ፲፫፨
፴፬ ጌታ፡ ሆይ፡ ከዚያ፡ እንጀራ፡ ሁል፡
ጊዜ፡ ስጠን፡ አሉት፨
፴፭ ኢየሱስም፡ አላቸው፡ የሕይ
ወት፡ እንጀራ፡ እኔ፡ ነኝ፡ ወደ፡
እኔም፡ የሚመጣ፡ አይራብም፡
የሚያምነኝም፡ ለዘለዓለ
ም፡ አይጠማም፤ ም፡ ፬፡ ፲፬፡ ኢሳ፡ ፶፭፡ ፩
፴፮ ነገር፡ ግን፡ አይታችሁኝ፡ እንዳ
ላመናችሁብኝ፡ እላችኋለሁ፤
፴፯ አባቴ፡ የሰጠኝ፡ ሁሉ፡ ወደ፡ እኔ፡
ይመጣል፡ ወደ፡ እኔም፡ የመጣው
ን፡ ወደ፡ ውጭ፡ አልሰደውም፤ ማ
ቴ፡ ፲፩፡ ፳፰፨ ም፡ ፲፯፡ ፯፡ ፱፨
፴፰ ከሰማይ፡ የወረድሁ፡ የላከኝን፡

ሰማይ፡ከመ፡እግበር፡ፈቃድ
የ፡ዘእንበለ፡ፈቃዶ፡ለዘፈነወ
ኒ። ፴፱ ወዝንቱ፡ውእቱ፡ፈቃዱ፡ለ
ዘፈነወኒ፡አብ፡ከመ፡ኵሉ፡ዘ
ወሀበኒ፡ኢይትሐጐል፡እም
ኔሆሙ፡ወኢአሐዱሂ፡አላ፡አ
ነ፡አነሥኦ፡በደኃሪት፡ዕለት፤
፵ ወዝንቱ፡ውእቱ፡ፈቃዱ፡ለአ
ቡየ፡ከመ፡ኵሉ፡ዘርእዮ፡ለ
ወልድ፡ወአምነ፡ቦቱ፡ይርከብ፡
ሕይወተ፡ዘለዓለም፡ወአነ፡አ
ነሥኦ፡በደኃሪት፡ዕለት።

፵፩ ወአንጐርጐሩ፡አይሁድ፡በ
እንቲአሁ፡እስመ፡ይቤሎሙ፡
አነ፡ውእቱ፡ኅብስተ፡ሕይወት
፵፪ ዘወረደ፡እምሰማይ። ወይቤ
ሉ፡አኮኑ፡ዝንቱ፡ውእቱ፡ኢየ
ሱስ፡ወልደ፡ዮሴፍ፡ዘለሊነ፡
ነአምር፡አባሁ፡ወእሞ፡ወእ
ፎ፡እንከ፡ይብለነ፡እምሰማ
፵፫ ይ፡ወረድኩ። ወአውሥአ፡እ
ግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎሙ፡
ኢታንጐርጕሩ፡በበይናቲክ
፵፬ ሙ። አልቦ፡ዘይክል፡መጺአ፡
ኀቤየ፡እመ፡ኢሰሐቦ፡አብ፡ዘ
ፈነወኒ፡ወአነ፡አነሥኦ፡በደ
ኃሪት፡ዕለት።

ፈቃድ፡ነው፡እንጂ፡ፈቃዴን፡
፡ለማድረግ፡አይደለም፡
፴፱ ና። ም፡፬፡፴፬፡ መዝ፡፴፱። የላከኝም፡
የአብ፡ፈቃድ፡ይህች፡ናት፡የ
ሰጠኝን፡ሁሉ፡በኋለኛው፡ቀ
ን፡እስነሣዋለሁ፡እንጂ፡አን
ድ፡ስንኳ፡እንዳይጠፋ። ም፡፲፡፳፰
፵ ፳፱። የላከኝ፡የአባቴም፡ፈቃ
ድ፡ይህ፡ነው፡ወልድን፡አይቶ፡
የሚያምንበት፡ሁሉ፡የዘለዓለ
ም፡ሕይወት፡ያገኝ፡ዘንድ፡
እኔም፡በኋለኛው፡ቀን፡እስ
ነሣዋለሁ። ዘኍ፡፳፩፡፰፡፱ ም፡፫፡፲፬።
፵፩ አይሁድም፡ከሰማይ፡የወረደ
ው፡እንጀራ፡እኔ፡ነኝ፡ስላለ፡አ
ላቸው፡አጕረመረሙበት።
፵፪ አባቱንና፡እናቱንም፡እኛ፡የም
ናውቃቸው፡ይህ፡ኢየሱስ፡የ
ዮሴፍ፡ልጅ፡አይደለምን፡እን
ዴት፡ከሰማይ፡ወረድሁ፡ይላ
ናል፡ይሉ፡ነበር። ማቴ፡፲፫፡፶፭።
፵፫ ኢየሱስም፡መለሰ፡አላቸው፡
እርስ፡በእርሳችሁ፡አታጕረ
ምርሙ።
፵፬ የላከኝ፡አብ፡የሳበው፡ካልሆ
ነ፡በቀር፡ማንም፡ወደ፡እኔ፡ር
መምጣት፡አይችልም፡እኔም፡
በኋለኛው፡ቀን፡እስነሣዋ

፵፭ ወሀሎ፡ጽሑፍ፡ውስተ፡መጽሐፈ፡ነቢያት፡ይከውኑ፡ኵሎሙ፡ምሁራነ፡እምኀበ፡እግዚአብሔር፡፡ወኵሉ፡እንከ፡ዘሰምዐ፡በኀበ፡አቡየ፡ተምሂሮ፡ይመጽእ፡ኀቤየ ✚

፵፮ ወአልቦ፡ዘርእዮ፡ለአብ፡ዘእንበለ፡ዘእምኀቤሁ፡ለእግዚኤብሔር፡ውእቱ፡ኬ፡ዘርእዮ፡ለአብ ✚

፵፯ አማን፡አማን፡እብለክሙ፡ዘየአምን፡ብየ፡ቦ፡ሕይወት፡ዘለዓለም ✚

፵፰ አነ፡ውእቱ፡ኅብስተ፡ሕይወት ✚

፵፱ አበዊክሙሰ፡መና፡በልዑ፡በገዳም፡ወሞቱ ✚

፶ ዝንቱ፡ውእቱ፡ኅብስት፡ዘእምሰማይ፡ወረደ፡ከመ፡ኵሉ፡ዘበልዐ፡እምኔሁ፡ኢይመውት ✚

፶፩ አነ፡ውእቱ፡ኅብስተ፡ሕይወት፡ዘወረደ፡እምሰማይ፡ወዘበልዐ፡እምዝንቱ፡ኅብስት፡የሐዩ፡ለዓለም፡ወዝኒ፡ኅብስት፡ዘአነ፡እሁብ፡ሥጋየ፡ውእቱ፡በእንተ፡ሕይወት፡ዘለዓለም ✚

፶፪ ወተጋዐዙ፡አይሁዙ፡አይሁድ፡በበይናቲሆሙ፡እንዘ፡ይብሉ፡

፵፭ ሉሁ ✚ ቍ፡፲፫ ✚ በነቢያትም፡ሁሉ፡ከእግዚአብሐር፡ዘንድ፡የተማሩ፡ይሆናሉ፡የሚል፡ጽሑፍ፡አለ፡ከአባቴም፡ዘንድ፡ሰምቶ፡የተማረ፡ሁሉ፡ወደ፡እኔ፡ይመጣል ✚ ኢሳ፡፶፬፡፲፫፡ኤር፡፴፩፡፴፫፡፴፬፡

፵፮ ከእግዚአብሐርም፡ዘንድ፡ከሆነው፡በቀር፡አብን፡ያየው፡የለም፡አብንስ፡ያየው፡እርሱ፡ነው ✚ ፩ ጢሞ፡፮፡፲፮ ✚

፵፯ እውነት፡እውነት፡እላችኋለሁ፡በኔ፡የሚያምን፡የዘለዓለም፡ሕይወት፡አለው ✚ ም፡፫፡፲፮ ✚

፵፰ የሕይወትም፡እንጀራ፡እኔ፡ነኝ፡

፵፱ ቍ፡፴፫ ✚ አባቶቻችሁስ፡በምድረ፡በዳ፡መና፡በሉ፡ሞቱም ✚ ቍ፡

፶ ፵፩፡፴፱ ✚ ፩፡ቆሮ፡፲፡፫፡፫ ✚ ይህም፡ከእርሱ፡የሚበላ፡ሁሉ፡እንደይሞት፡ከሰማይ፡የወረደው፡እንጀራ፡ነው ✚

፶፩ ከሰማይም፡የወረደው፡የሕይወት፡እንጀራ፡እኔ፡ነኝ፡ማንም፡ከዚህ፡እንጀራ፡የበላ፡ለዘለዓለም፡ይኖራል፡ይህም፡እንጀራ፡እኔ፡ስለ፡ዓለም፡ሕይወት፡የምሰጠው፡ሥጋዬ፡ነው ✚ ም፡፲፩፡፩፪፡፡ገላ፡፪፡፳፡ዕብ፡፲፡፲ ✚

፶፪ አይሁድም፡ይህ፡እንበላ፡ዘንድ፡ሥጋውን፡ሊሰጠን፡እንዴት፡ይ

እፎ፡ ይክል፡ ዝንቱ፡ የሀበነ፡ ሥጋሁ፡ ንብላዕ።

፶፫ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ አማን፡ አማን፡ እብለክሙ፡ እመ፡ ኢበላዕክሙ፡ ሥጋሁ፡ ለወልደ፡ እጓለ፡ እመሕያው፡ ወኢሰተይክሙ፡ ደሞ፡ አልብክሙ፡ ሕይወት፡ ላዕሌክሙ።

፶፬ ዘበልዐ፡ ሥጋየ፡ ወሰተየ፡ ደምየ፡ ቦሕይወት፡ ዘለዓለም፡ ወአነ፡ አነሥኦ፡ በደኃሪት፡ ዕለት።

፶፭ እስመ፡ ሥጋዬኒ፡ መብልዕ፡ ጽድቅ፡ ዘበአማን፡ ውእቱ፡ ወደምየኒ፡ ሰቴ፡ ሕይወት፡ ዘበአማን፡ ውእቱ።

፶፮ ዘበልዐ፡ ሥጋየ፡ ወሰተየ፡ ደምየ፡ ይሄሉ፡ ምስሌየ፡ ወአነሂ፡ እሄሉ፡ ምስሌሁ።

፶፯ ወበከመ፡ ፈነወኒ፡ አብ፡ ሕያው፡ ወአነሂ፡ ሕያው፡ በእንተ፡ አብ፡ ወዘበልዐ፡ ሥጋየ፡ የሐዩ፡ በእንቲአየ።

፶፰ ዝኬ፡ ውእቱ፡ ኅብስት፡ ዘእምሰማይ፡ ወረደ፡፡ ወአኮ፡ በከመ፡ በልዑ፡ አበዊክሙ፡ መና፡ ወሞቱ፡ ወዘበልዖሰ፡ ለዝንቱ፡ ኅብስት፡ የሐዩ፡ ለዓለም።

፶፱ ወከመዝ፡ ይቤሎሙ፡ በምኵ

ችላል፡ እያሉ፡ እርስ፡ በእርሳቸው፡ ተከራከሩ።

፶፫ ኢየሱስም፡ አላቸው፡ እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ የሰውን፡ ልጅ፡ ሥጋ፡ ካልበላችሁ፡ ደሙንም፡ ካልጠጣችሁ፡ ሕይወት፡ የላችሁም።

፶፬ ሥጋዬን፡ የበላ፡ ደሜንም፡ የጠጣ፡ የዘላለም፡ ሕይወት፡ አለው፡ እኔም፡ በኋለኛዪቱ፡ ቀን፡ አስነሣዋለሁ።

፶፭ ሥጋዬ፡ የእውነት፡ መብል፡ ደሜም፡ የእውነት፡ መጠጥ፡ ነውና።

፶፮ ሥጋዬን፡ የበላ፡ ደሜንም፡ የጠጣ፡ በእኔ፡ ይኖራል፡ እኔም፡ በእርሱ፡ እኖራለሁ። ም፡፲፭፡፬፡፭ ዮሐ፡፫፡፳፬

፶፯ ሕያው፡ አብ፡ እንደ፡ ላከኝ፡ እኔም፡ ስለ፡ አብ፡ ሕያው፡ እንደ፡ ነኝ፡ ሥጋዬንም፡ የሚበላ፡ እርሱ፡ ደግሞ፡ ስለ፡ እኔ፡ ሕያው፡ ሁኖ፡ ይኖራል።

፶፰ ከሰማይ፡ የወረደ፡ እንጀራ፡ ይህ፡ ነው፡ አባቶቻችሁም፡ በልተውት፡ እንደ፡ ሞቱ፡ መና፡ ያለ፡ አይደለም፡ ይህንን፡ እንጀራ፡ የበላ፡ ግን፡ ለዘላለም፡ ይኖራል።

፶፱ በቅፍርናሆም፡

ራብ፡ ዘቅፍርናሆም፡ እንዘ፡ ይሜህሮሙ።

፷ ወብዙኃን፡ እምአርዳኢሁ፡ እለ፡ ሰምዑ፡ ወይቤሉ፡ ዕፁብ፡ ዝንቱ፡ ነገር፡ ወመኑ፡ ይክል፡ ሰሚዖቶ።

፷፩ ወአእመሮሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ በመንፈሱ፡ ከመ፡ እንጐርጕሩ፡ አርዳኢሁ፡ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ወይቤሎሙ፡ ዝኑ፡ ያዐቅፈቅክሙ።

፷፪ ወእፎ፡ እንከ፡ እመ፡ ርኢክምዎ፡ ለወልደ፡ እጓለ፡ እመሕያው፡ እንዘ፡ የዐርግ፡ ኀበ፡ ሀሎ፡ ቀዲሙ።

፷፫ መንፈስ፡ ውእቱ፡ ዘያሐዩ፡ ወሥጋሰ፡ አልቦ፡ ዘይበቍዕ፡ ወኢምንተኒ፡ ወዝኒ፡ ቃል፡ ዘአነ፡ ነገርኩክሙ፡ መንፈስ፡ ውእቱ፡ ወሕይወት፡ ውእቱ።

፷፬ ወባሕቱ፡ ሀለዉ፡ እምውስቴትክሙ፡ እለ፡ ኢየአምኑ፤ እስመ፡ የአምር፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ እምትካት፡ መኑ፡ እሙንቱ፡ እለ፡ ኢየአምኑ፡ በቱ፡ ወመኑ፡ ውእቱ፡ ዘያገብአ።

፷፭ ወይቤሎሙ፡ በእንተ፡ ዝንቱ፡ እብለክሙ፡ አልቦ፡ ዘይክል፡ ረመጺአ፡ ኀቤየ፡ ለእመ፡ ኢተው-

ም፡ በመሰጊድ፡ ሲያስተምራቸው፡ ይህን፡ ተናገራቸው።

፷ ከደቀ፡ መዛሙርቱም፡ ብዙዎች፡ ይህነን፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ ይህ፡ ነገር፡ ጭንቅ፡ ነው፡ ማን፡ ሊሰማው፡ ይቻላል፡ አሉ።

፷፩ ኢየሱስም፡ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ በዚህ፡ እንደ፡ አጕረመረሙ፡ በልቡ፡ አውቆ፡ አላቸው፡ ይህ፡ ያሰናክላችኋልን።

፷፪ የሰው፡ ልጅ፡ ቀድሞ፡ ወደ፡ ነበረበት፡ ሲያርግ፡ ብታዩት፡ እንዴት፡ ነው።

፷፫ ሕይወት፡ የሚሰጥ፡ መንፈስ፡ ነው፡ ሥጋ፡ ግን፡ እንዳች፡ አይጠቅምም፡ ይህም፡ እኔ፡ የምነግራችሁ፡ ቃል፡ መንፈስ፡ ነው፡ ሕይወትም፡ ነው። ፪ቆሮ፡ ፫፡ ፮።

፷፬ ነገር፡ ግን፡ ከእናንተ፡ የማያምኑ፡ አሉ፡ ኢየሱስ፡ የማያምኑት፡ እነማን፡ እንደ፡ ሆኑ፡ አሳልፎ፡ የሚሰጠውም፡ ማን፡ እንደ፡ ሆነ፡ ከጥንት፡ ጀምሮ፡ ያውቅ፡ ነበርና። ም፡ ፲፫፡ ፲፩።

፷፭ ስለዚህም፡ ከአባቴ፡ የተሰጠው፡ ካልሆነ፡ ወደ፡ እኔ፡ መምጣት፡ የሚቻል፡ የለም፡ እላችኋለ

ህበ፡ ሎቱ፡ እምኀበ፡ አብ።

፷፮ ወበእንቲአ፡ ዝንቱ፡ ብዙኃን፡ እምአርዳኢሁ፡ አለ፡ ገብኡ፡ ድኅሬሆሙ፡ ወኢሖሩ፡ እንከ፡ ምስሌሁ።

፷፯ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ለዓሠርቱ፡ ወክልኤቱ፡ አንትሙኒ፡ ትፈቅዱኑ፡ ተሐሩ።

፷፰ ወአውሥአ፡ ስምዖን፡ ጴጥሮስ፡ ወይቤሎ፡ እግዚኦ፡ ኀበ፡ መኑ፡ ነሐውር፡ እንዘ፡ ቃለ፡ ሕይወት፡ ዘለዓለም፡ ኀቤከ።

፷፱ ወንሕነሰ፡ አመነ፡ ወአእመርነ፡ ከመ፡ አንተ፡ ውእቱ፡ ክርስቶስ፡ ወልዱ፡ ለእግዚአብሔር፡ ሕያው።

፸ ወአውሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወይቤሎሙ፡ አኮኑ፡ አነ፡ ኀረይኩክሙ፡ ለዓሠርቱ፡ ወክልኤቱ፡ ወአሐዱ፡ እምኔክሙ፡ ሰይጣን፡ ውእቱ።

፸፩ ወዘንቱሰ፡ ይቤ፡ እንበይነ፡ ይሁዳ፡ ወልደ፡ ስምዖን፡ አስቆሮታዊ፡ እስመ፡ ውእቱ፡ ዘሀለዎ፡ ያግብኦ፡ ወውእቱ፡ አሐዱ፡ እምዓሠርቱ፡ ወክልኤቱ።

ምዕራፍ፡ ፯።

በበዓል፡ ፊደሉት፡ እንዳ፡ ፈለጉት። በምኵራብ፡ እን

ሁ፡ አላቸው። ቍ ፵፬

፷፮ ስለዚህም፡ ከደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ብዙዎቹ፡ ወደ፡ ኋላ፡ አፈገፈጉ፡ ከዚያም፡ ወዲያ፡ ከርሱ፡ ጋራ፡ አልሔዱም።

፷፯ ኢየሱስም፡ አሥራ፡ ሁለቱን፡ እናንተም፡ ልትሔዱ፡ ትፈቅዳላችሁን፡ አላቸው።

፷፰ ስምዖን፡ ጴጥሮስም፡ መለሰ፡ አለው፡ ጌታ፡ ሆይ፡ የዘላለም፡ የሕይወት፡ ቃል፡ ሳለህ፡ ወደ፡ ማን፡ እንሔዳለን። ቍ ፷፫

፷፱ እኛስ፡ አንተ፡ ያሕያው፡ እግዚአብሔር፡ ልጅ፡ ክርስቶስ፡ እንደ፡ ሆንህ፡ አውቀን፡ አምነናል። ም፡ ፩፡ ቍ፲፱፡ ፲፮፡ ፩፪። ማቴ፡ ፲፮ ፲፮

፸ ኢየሱስም፡ መልሶ፡ አሥራ፡ ሁለታችሁን፡ እኔ፡ መርጫችሁ፡ የለምን፡ ከእናንተም፡ አንዱ፡ ሰይጣን፡ ነው፡ አላቸው። ሉቃ፡ ፮

፸፩ ፲፫ ይህንንም፡ ስለ፡ ስምዖን፡ ልጅ፡ ስለ፡ አስቆሮታዊው፡ ይሁዳ፡ አለ፡ አሳልፎ፡ ይሰጠው፡ ዘንድ፡ ያለው፡ እርሱ፡ ነበርና፡ እርሱም፡ ከአሥራ፡ ሁለቱ፡ አንዱ፡ ነበር።

ሰባት፡ ምዕራፍ።

ደ፡ አስተማረቸው፡ ና፡ ትምህርቱን፡ እንደ፡ እደነቁ፡

ዮሐይወት፡ ውሀ፡ እኔ፡ ነኝ፡ እንጸ፡ አለ፡፡ ክርስ
ቶስ፡ ነው፡ አይጸፅም፡ ባማለት፡ እርስ፡ በር

፩ ወእምድኅረ፡ዝንቱ፡ ሖረ፡ እግ
ዚእ፡ ኢየሱስ፡ ውስተ፡ ገሊላ፡
ወኢፈቀደ፡ ይሑር፡ ምድ
ረ፡ ይሁዳ፡ እስመ፡ የኃሥ
ሥዎ፡ አይሁድ፡ ይቅትልዎ ፨

፪ ወቀርበ፡ በዓለ፡ መጸለቶሙ
ለአይሁድ ፨

፫ ወይቤልዎ፡ አኃዊሁ፡ ለእግ
ዚእ፡ ኢየሱስ፡ ፋልስ፡ እምዝ
የ፡ ወሑር፡ ኀበ፡ ብሔረ፡ ይሁዳ፡ ከ
መ፡ እርድኢክኒ፡ ይርአዩ፡ ግ
ብረክ፡ ዘትገብር ፨

፬ እስመ፡ አልቦ፡ ዘይገብር፡ ም
ንተኒ፡ ጽሚተ፡ ወይፈቅድ፡
ክሡተ፡ ይኩን፡ ወእመሰ፡ ዘን
ተ፡ ምግባረ፡ ትገብር፡ አርኢ፡
ርእሰክ፡ ለዓለም ፨

፭ እስመ፡ አኃዊሁኒ፡ ኢአምኑ፡
ቦቱ ፨

፮ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየ
ሱስ፡ ጊዜየሰ፡ ዓዲ፡ እስከ፡ ይ
እዜ፡ ኢበጽሐ፡ ወጊዜ፡ ዚአክ
ሙሰ፡ ዘልፈ፡ ድልው፡ ውእቱ፡፡

፯ ለክሙሰ፡ ኢይክል፡ ዓለም፡ ጸ
ሊአተክሙ፡ ወሊተሰ፡ ይጸል
አኒ፡ እስመ፡ አነ፡ ሰማዕ፡ ላዕሌ

ሳትው፡ እንጸ፡ ተጣሉ፡፡

፩ ከዚህም፡ በኋላ፡ ኢየሱስ፡ በ
ገሊላ፡ ይመላለስ፡ ነበር፡ ወደ፡
ይሁዳ፡ ምድርም፡ ይሔድ፡ ዘ
ንድ፡ አልወደደም፡ አይሁድ፡
ይገድሉት፡ ዘንድ፡ ይሹ፡ ነበ
ርና ፨

፪ ዳስም፡ የሚተክሉበት፡
የአይሁድ፡ በዓል፡ ቀርቦ፡ ነበ
ረ ፨ ዘሌዋ፡ ፳፫፡ ፴፬ ፨

፫ ወንድሞቹም፡
አሉት፡ ደቀ፡ መዛሙርትህ፡ የ
ምትሠራውን፡ ሥራ፡ ያዩ፡ ዘን
ድ፡ ከዚህ፡ ወጥተህ፡ ወደ፡ ይሁዳ፡
ምድር፡ ሒድ ፨ ማቴ፡ ፲፪፡ ፵፮፡ የሐዋ፡ ፩፡ ፲፬፡

፬ ሊገለጽ፡ ወዶ፡ ሳለ፡ በሥውር፡
አንዳች፡ ነገር፡ የሚያደርግ፡
ማንም፡ የለምና፡ ይህንም፡ የ
ምታደርግ፡ ከሆነ፡ ራስህን፡
ለዓለም፡ ግለጽ ፨

፭ ወንድሞቹም፡ ደግሞ፡ አላ
መኑበትም፡ ነበሩና ፨ መዝ፡ ፷፰፡ ፰ ፨

፮ ኢየሱስም፡ አላቸው፡ ጊዜዬ፡
ገና፡ አልደረሰም፡ የእናንተ፡
ጊዜ፡ ግን፡ ሁል፡ ጊዜ፡ የተዘጋ
ጀ፡ ነው ፨ ም፡ ፪፡ ፬ ፨

፯ እናንተን፡ ዓለም፡ ይጸላችሁ፡
ዘንድ፡ አይቻልም፡ እኔን፡ ግን፡
ይጸላኛል፡ ሥራው፡ ክፉ፡ እን

ሁ፡ወእዘለፎ፡በከመ፡እከዩ፡
፰ ምግባሩ፨ አንትሙሰ፡ዕርጉ፡
ውስተ፡ዝንቱ፡በዓል፡ወአንሰ፡ኢየ
ዐርግ፡ውስተ፡ዝንቱ፡በዓል፡
እስመ፡ዓዲ፡ኢበጽሐ፡ጊዜየ።
፱ ወከመዝ፡ይቤሎሙ፡ወነበረ
ውስተ፡ገሊላ፨
፲ ወዐረጎሙ፡አኃዊሁ፡ለበዓል፡
ውእቱ፡አሚረ፡ዐርገ፡ውእቱ
ኒ፡ጽሚተ፡ወአኮ፡ገሃደ፨
፲፩ ወአኃዙ፡አይሁድ፡ይኅሥሥ
ዎ፡በበዓል፡ወይቤሉ፡አይቴ፡
ውእቱ፡ዝክቱ፨
፲፪ ወብዙኃ፡አንጐርጓሩ፡ሕዝ
ብ፡በእንቲአሁ፡ወቦ፡እለ፡ይ
ቤሉ፡ኄር፡ውእቱ፡ወካልኣን፡
ይቤሉ፡አልቦ፡አላ፡ያስሕቶ
ሙ፡ለሕዝብ፨
፲፫ ወባሕቱ፡ክሡተሰ፡አልቦ፡ዘ
ተናገረ፡በእንቲአሁ፡በእን
ተ፡ፍርሀቶሙ፡ለአይሁድ፨
፲፬ ወበመንፈቀ፡መዋዕለ፡በዓ
ል፡ዓርገ፡እግዚእ፡ኢየሱስ
ምኵራበ፡ወአኃዘ፡ይምሀር።
፲፭ ወአንከሩ፡አይሁድ፡ምህሮ
ቶ፡እንዘ፡ይብሉ፡እፎ፡የአ
ምር፡ዝንቱ፡መጽሐፈ፡ዘኢ
ተምህረ፨

ዒ፡ሆነ፡እመሰክርባታለሁና፡
፰ ም፡፫፡፲፱፡፩፨ እናንተም፡ወደዚህ፡
በዓል፡ውጡ፡እኔ፡ግን፡ጊዜዬ
ገና፡አልደረሰምና፡ወደዚህ፡
በዓል፡አልወጣም፨ ም፡፯፡፩፨
፱ ይህንም፡ብሎዋቸው፡በገሊ
ላ፡ቀረ፨
፲ ወንድሞቹም፡ለበዓል፡ከወ
ጡ፡በኋላ፡እርሱም፡በዚያን፡
ጊዜ፡በግልጽ፡ሳይሆን፡ተሠው
ሮ፡ወጣ፨ ፲፩ አይሁድም፡በበዓሉ፡
ውሥጥ፡ያ፡ወዴት፡ነው፡እያ
ሉ፡ይፈልጉት፡ጀመር፨
፲፪ ሕዝቡም፡በእርሱ፡ምክንያ
ት፡እጅግ፡ታወኩ፡ከእነርሳቸ
ውም፡ደግ፡ሰው፡ነው፡የሚ
ሉ፡ነበሩ፡ሌሎቹም፡አይደለ
ም፡ሕዝቡን፡ያስታል፡እንጂ፡
፲፫ ይሉ፡ነበር፨ ም፡፱፡፳፪፨ ነገር፡ግን፡
አይሁድን፡በመፍራት፡ሰለ፡
እርሱ፡ማንም፡በግልጥ፡የተ
፲፬ ናገረ፡የለም፨ ም፡፲፱፡፴፰፨ ኢየሱ
ስም፡በበዓሉ፡እኩሌታ፡ወደ፡
መቅደስ፡ወጥቶ፡ያስተምር
፲፭ ነበር፨ አይሁድም፡ይህ፡ሳይ
ማር፡እንዴት፡መጻሕፍትን፡
ያውቃል፡እያሉ፡ያደንቁ፡ነበ
ር፨ ማቴ፡፲፫፡፶፬፨

፲፮ ወአውሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወይቤሎሙ፡ ትምህርትየሰ፡ ኢኮነት፡ እንቲአየ፡ አላ፡ እንቲአሁ፡ ለዘፈነወኒ፨

፲፯ ወዘሰ፡ ይፈቅድ፡ ይግበር፡ ሥምረቶ፡ ውእቱ፡ የአምር፡ ከመ፡ እምኀበ፡ እግዚአብሔር፡ ውእቱ፡ ትምህርትየ፡ ወአኮ፡ ዘእምኀቤየ፡ ዘእነግር፨

፲፰ ወዘሰ፡ ለርእሱ፡ ይነግር፡ ተድላ፡ ርእሱ፡ የኀሥሥ፡ ወዘሰ፡ ይፈቅድ፡ ያድሉ፡ ለዘፈነዎ፡ ጻድቅ፡ ውእቱ፡ ወአልቦ፡ ዓመፃ፡ በኀቤሁ፨

፲፱ አኮኑ፡ ሙሴ፡ ወሀበክሙ፡ ኦሪተ፡ ወአልቦ፡ አሐዱ፡ ኢእምኔክሙ፡ ዘይገብራ፡ ለኦሪት፡ ለምንት፡ እንከ፡ ተኀሥሡ፡ ትቅትሉኒ፨

፳ ወአውሥኡ፡ ሕዝቡ፡ ወይቤልዎ፡ ጋኔን፡ ኀብከ፡ መኑ፡ የኀሥሥ፡ ይቅትልከ፨

፳፩ ወአውሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወይቤሎሙ፡ አሐደ፡ ግብረ፡ ገበርኩ፡ ወኵልክሙ፡ አንከርክሙ፨

፲፮ ኢየሱስም፡ መለሰ፡ አላቸው፡ ትምህርቴ፡ የእኔ፡ አይደለችም፡ የላከኝ፡ ናት፡ እንጂ፨ ም፡ ፲፡ ፲፯፡ ፲፲፨

፲፯ ፈቃዱንም፡ ያደርጋ፡ ዘንድ፡ የሚወድ፡ ቢኖር፡ ይህ፡ ትምህርቴ፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ እንደ ሆነ፡ ወይም፡ እኔ፡ ከራሴ፡ የምናገር፡ እንደ፡ ሆነ፡ እርሱ፡ ያውቃል፨ ም፡ ፫፡ ፲፩፡ ፲፡ ፴፩፡ ፴፱፡ ፵፯።

፲፰ ከራሱ፡ የሚናገር፡ የራሱን፡ ክብር፡ ይፈልጋል፡ የላከውን፡ ያከብር፡ ዘንድ፡ የሚፈልጋ፡ ግን፡ እርሱ፡ እውነተኛ፡ ነው፡ በእርሱም፡ ሐሰት፡ የለበትም፨ ም፡ ፰፡ ፵፩፡ ፵፬፨

፲፱ ሙሴ፡ ኦሪትን፡ የሰጣችሁ፡ አይደለምን፡ ከእናንተም፡ አንድ፡ ሰንኳ፡ ኦሪትን፡ የሚሠራት፡ የለም፡ እንጋዲህ፡ ለምን፡ ትገድሉኝ፡ ዘንድ፡ ትፈልጋላችሁ፨ ዘፀአ፡ ፳፡ ፩፡ ፳፬ ፲፱፡ ም፡ ፰፡ ፲፯፡ ፲፰፨

፳ ሕዝቡም፡ መለሰው፡ ጋኔን፡ አለብህን፡ ማን፡ ሊገድልህ፡ ይፈልጋል፡ አሉት፨ ም፡ ፲፡ ፳፡ ፴፱

፳፩ ኢየሱስም፡ መለሰ፡ አላቸው፡ አንድ፡ ሥራ፡ አደረግሁ፡ ሁላችሁም፡ አደነቃችሁ፨ ም፡ ፭፡ ፲፡ ፲፮፨

፳፪ በእንተ፡ዝንቱ፡ወሀበክሙ፡ሙ
ሴ፡ግዝረተ፡ወኢኮነት፡እም
ኀበ፡ሙሴ፡አላ፡እምአበው፡
ይእቲ፡ወበሰንበት፡ትገዝር
ዎ፡ለሰብእ፨

፳፫ ወእመሰ፡በሰንበት፡ግዝረተ፡
ይነሥእ፡ሰብእ፡ከመ፡ኢይ
ሠዐር፡ሕጉ፡ለሙሴ፡ለምን
ት፡እንከ፡ትትመዐዑኒ፡ሊተ፡
ለእመ፡አሕየውክዎ፡ለብእሴ
ኵለንታሁ፡በሰንበት፨

፳፬ ኢትፍትሑ፡በአድልዎ፡ለገጽ፡
ሰብእ፡አላ፡ፍትሑ፡ፍትሐ፡
ጽድቀ፨

፳፭ ወቦ፡እለ፡ይቤሉ፡እ
ምሰብአ፡ኢየሩሳሌም፡አኮኑ፡
ዝንቱ፡ውእቱ፡ዘየኀሥሡ፡እ
ይሁድ፡ይቅትልዎ፨

፳፮ ወናሁ፡ገሃደ፡ይትናገሮሙ፡
ወአልቦ፡ዘይቤልዎ፡አእመሩ
ኑ፡እንጋ፡ሊቃውንት፡ከመ፡በ
አማን፡ዝንቱ፡ውእቱ፡ክርስ
ቶስ።

፳፯ ወባሕቱ፡ለዝንቱሰ፡ነአምሮ፡
እምአይቴ፡ውእቱ፡ወለክር
ስቶስሰ፡አመ፡ይመጽእ፡አልቦ፡
ዘየአምሮ፡እምኀበ፡ይመጽእ፨

፳፰ ወአልዐለ፡ቃሎ፡እግዚእ፡ኢ

፳፪ ስለዚህም፡ሙሴ፡ግዝረትን፡
ሰጣችሁ፡ከሙሴም፡አይደለ
ችም፡ከአባቶች፡ናት፡እንጂ፡
ሰውንም፡በሰንበት፡ትገዝሩ
ታላችሁ፨ ዘፍ፡፲፯፡፲፨

፳፫ የሙሴ፡ሕግም፡እንዳይፈርስ፡
ሰው፡በሰንበት፡የሚገዘር፡ከ
ሆነ፡በሰንበት፡ሰውን፡ሁለንተ
ናውን፡ብፈውሰው፡እኔን፡ለ
ምን፡ትነቀፉኛላችሁ፨

፳፬ እውነት፡ፍርድን፡ፍረዱ፡እ
ንጂ፡ለሰው፡ፊት፡አድልታች
ሁ፡አትፍረዱ፨

፳፭ ከኢየሩሳሌ
ምም፡ሰዎች፡የሚሉ፡ነበሩ፡
አይሁድ፡ይገድሉት፡ዘንድ፡
የሚሹ፡ይህ፡አይደለምን፨

፳፮ ቍ፡፲፱፡ እርሱ፡እነሆ፡ፊት፡ለፊ
ት፡ይናገራቸዋል፡እነርሳቸ
ውም፡ምንም፡አላሉትም፡አ
ለቆቹ፡ከዋ፡ይህ፡በእውነት፡
ክርስቶስ፡እንደሆነ፡አውቀ
ው፡ይሆንን፨

፳፯ ይህንም፡ከወ
ዴት፡እንደ፡ሆነ፡እናውቀዋ
ልን፡ክርስቶስ፡ግን፡በመጣ፡
ጊዜ፡ከወዴት፡እንደ፡ሆነ፡ማ
ንም፡የሚያውቅ፡የለም፨ ቍ

፳፰ ቍ፲፩ ኢየሱስም፡በመቅደስ፡ሲ

የሱስ፡ በምኵራብ፡ እንዘ፡ ይ
ሜህር፡ ወይቤ፡ ኪያየ፡ ተአም
ሩ፡ ወተአምሩኒ፡ እምአይቴ፡
አነ፡ ወለልየኒ፡ ኢመጻእኩ፡ አ
ላ፡ ሀሎ፡ ጻድቅ፡ ዘፈነወኒ፡ ዘ
ኢተአምርዎ፡ አንትሙ። ✣

፳፱ ወአንሰ፡ አአምሮ፡ እስመ፡ እ
ምኀቤሁ፡ አነ፡ ወውእቱ፡ ፈ
ነወኒ። ✣

፴ ወፈቀዱ፡ የአኀዝዎ፡ ወባሕ
ቱ፡ አልቦ፡ ዘአንሥአ፡ እዴሁ፡
ላዕሌሁ፡ እስመ፡ ዓዲ፡ ኢበጽ
ሐ፡ ጊዜሁ። ✣

፴፩ ወእምውእቶሙ፡ ሰብእ፡ ብዙ
ኃን፡ አለ፡ አምኑ፡ በቱ፡ ወይቤ
ሉ፡ አመ፡ ይመጽእ፡ ክርስቶስ
ቦኑ፡ ፈድፋደ፡ ተአምረ፡ ይገ
ብር፡ እምዘገብረ፡ ዝንቱ። ✣

፴፪ ወሰምዑ፡ ፈሪሳውያን፡ ከመ፡
እንጐርጐሩ፡ ሕዝብ፡ በእንቲ
አሁ፡ ወፈነዉ፡ ሊቃነ፡ ካህና
ት፡ ወፈሪሳውያን፡ ወዓልያነ
ሆሙ፡ ከመ፡ የአኀዝዎ። ✣

፴፫ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየ
ሱስ፡ ዓዲ፡ ኅዳጠ፡ መዋዕለ፡ ሀ
ሎኩ፡ ምስሌክሙ፡ ወእምዝ፡
አሐውር፡ ኀበ፡ ዘፈነወኒ። ✣

ያስተምር፡ ቃሉን፡ ከፍ፡ አድ
ርጎ፡ እንዲህ፡ አለ፡ እኔን፡ ታው
ቁኛ፡ አላችሁ፡ ከወዴትም፡ እ
ንደ፡ ሆንሁ፡ ታውቃላችሁ፡ እ
ኔም፡ በራሴ፡ የመጣሁ፡ አይደ
ለሁም፡ እኔን፡ የላከኝ፡ እናንተ፡
የማታውቁት፡ እውነተኛ፡ አለ፡

፳፱ እንጂ። ✣ እኔ፡ ግን፡ አውቀዋለ
ሁ፡ ከእርሱ፡ ነኝና፡ እርሱም፡
ልኮኛል። ✣ ማቴ፡ ፲፩፡ ፳፯ ✣

፴ ስለዚህም፡ ሊይዙት፡ ፈለጉ፡
ነገር፡ ግን፡ ጊዜው፡ [illegible]፡ ገና፡ እ
ልደረሰምና፡ ማንም፡ እጁን፡
አልዘረጋበትም ✣ ም፡፲፡፩፡ሉቃ፡፲፱፡፵፫፡

፴፩ ከሕዝቡም፡ ብዙ፡ አመኑበት
ና፡ በውኑ፡ ክርስቶስ፡ በመጣ፡
ጊዜ፡ ይህ፡ ካደረገው፡ ተአም
ራት፡ የሚበልጥ፡ ያደርጋልን፡
አሉ። ✣ ም፡፫፡፴ ✣

፴፪ ፈሪሳውያንም፡ ሕዝቡ፡ በእ
ርሱ፡ የተነጋ፡ እንደ፡ አጕረመ
ረሙ፡ ሰምተው፡ ፈሪሳውያን
ና፡ የካህናትም፡ አለቆች፡ ይይ
ዙት፡ ዘንድ፡ ሎሌዎቻቸውን፡

፴፫ ላኩ። ✣ ኢየሱስም፡ አላቸው፡ እ
ኔ፡ ገና፡ ጥቂት፡ ቀን፡ ከእናንተ፡
ጋራ፡ ነኝ፡ ወደ፡ ላከኝም፡ እሔ
ዳለሁ ✣ ም፡፲፫፡፴፫ ✣

፴፬ ወተኀሥሡኒ፡ ወኢትረክቡኒ፡ ወኀበ፡ አነ፡ አሐውር፡ አንትሙ፡ ኢትክሉ፡ መጺአ ✤

፴፭ ወይቤሉ፡ አይሁድ፡ በበይናቲሆሙ፡ አይቴኑ፡ ሀለዎ፡ ለዝንቱ፡ ይሑር፡ ዘኢንክል፡ ረኪቦቶ፡ ኢሑነ፡ የሐውርኑ፡ እንጋ፡ ኀበ፡ እለ፡ ተዘርዉ፡ ኀበሐረ፡ ፅርዕ፡ ወይሜህሮሙ፡ ለሰብአ፡ ፅርዕ ✤

፴፮ ምንትኑ፡ ዝንቱ፡ ነገር፡ ዘይብለነ፡ ተኀሥሡኒ፡ ወኢትረክቡኒ፡ ወኀበ፡ አነ፡ አሐውር፡ አንትሙ፡ ኢትክሉ፡ መጺአ ✤

፴፯ ወበደኀሪት፡ ዕለት፡ ዘበዓል፡ ዓባይ፡ ቆመ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወከልሐ፡ ወይቤ፡ ዘፀምአ፡ ይምጻእ፡ ኀቤየ፡ ወይስተይ ✤

፴፰ ወዘሂ፡ የአምን፡ ብየ፡ በከመ፡ ይቤ፡ መጽሐፍ፡ አፍላገ፡ ማየ፡ ሕይወት፡ ይውኅዝ፡ እምከርሡ ።

፴፱ ወዘንተ፡ ይቤ፡ በእንተ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ዘሀለዎሙ፡ ይንሥኡ፡ እለ፡ የአምኑ፡ ቦቱ፡ እስመ፡ ዓዲ፡ ኢመጽአ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ በእንተ፡ ዘኢተሰብሐ፡ እግዚ

፴፬ ትሹኛላችሁ፡ አታገኙኝም፡ እኔም፡ ወደምሔድበት፡ እናንተ፡ ትመጡ፡ ዘንድ፡ አትችሉም ✤ ም፡፲፬፡፮ ✤

፴፭ አይሁድም፡ እርስ፡ በርሳቸው፡ አሉ፡ ይህ፡ እኛ፡ ልናገኘው፡ የማንችል፡ ወዴት፡ ይሔድ፡ ይሆን፡ ወይስ፡ የግሪክን፡ ሰዎች፡ ለማስተማር፡ በግሪክ፡ አገር፡ ወደ፡ ተበተኑት፡ ይሔዳልን ✤ የሐዋ፡፲፩፡፩ ✤

፴፮ ትፈልጉኛላችሁ፡ አታገኙኝም፡ እኔም፡ ወደምሔድበት፡ እናንተ፡ መምጣት፡ አትችሉም፡ የሚለን፡ ይህ፡ ነገር፡ ምንድን፡ ነው ✤

፴፯ በኋለኛዪቱም፡ በታላቅዋ፡ በዓል፡ ቀን፡ ኢየሱስ፡ ቁሞ፡ በታላቅ፡ ቃል፡ እንዲህ፡ አለ፡ ማንም፡ የተጸማ፡ ቢኖር፡ ወደ፡ እኔ፡ መጥቶ፡ ይጠጣ ✤ ዘሌዋ፡፳፫፡፴፮፡ ራእ፡፳፪፡፲፯ ✤

፴፰ በእኔም፡ የሚያምን፡ መጽሐፍ፡ እንዳ፡ አለ፡ የሕይወት፡ ውሀ፡ ምንጭ፡ ከሆዱ፡ ይፈልቃል ✤ መዝ፡፹፯፡፯፡፲፯፡፡ ኢሳ፡፲፪፡፫፡፵፬፡፫ ✤

፴፱ ይህንም፡ በእርሱ፡ ያመኑት፡ ይቀበሉት፡ ዘንድ፡ ስለ፡ አላቸው፡ ስለ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ተናገረ፡ ኢየሱስ፡ ስለ፡ አልተመሰገነ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ገና፡ አልመ

አ፡ ኢየሱስ፨

፵ ወብዙኃን፡ እምሕዝብ፡ ሰሚዖሙ፡ ዘንተ፡ ነገረ፡ ይቤሉ፡ አማን፡ ነቢይ፡ ውእቱ፡ ዝንቱ፨

፵፩ ወቦ፡ እለ፡ ይቤሉ፡ ክርስቶስ፡ ውእቱ፡ ወመንፈቆሙ፡ ይቤሉ፡ ቦኑ፡ እምገሊላ፡ ይመጽእ፡ ክርስቶስ፨

፵፪ አኮኑ፡ ይብል፡ መጽሐፍ፡ ከመ እምነ፡ ዘርአ፡ ዳዊት፡ ወእምነ፡ ቤተ፡ ልሔም፡ ሀገሩ፡ ለዳዊት፡ ይመጽእ፡ ክርስቶስ፨

፵፫ ወተናፈቁ፡ ሕዝብ፡ በበይናቲሆሙ፡ በእንቲአሁ፨

፵፬ ወቦ፡ እለ፡ ፈቀዱ፡ የአኀዝዎ፡ ወባሕቱ፡ አልቦ፡ ዘአንሥአ፡ እዴሁ፡ ላዕሌሁ፨

፵፭ ወተሰውጡ፡ ወዓልያኒሆሙ፡ ኀበ፡ ሊቃነ፡ ካህናት፡ ወፈሪሳውያን፡ ወይቤልዎሙ፡ እሙንቱ፡ እፎኑመ፡ ዘኢያምጻእክምዎ፨

፵፮ ወአውሥኡ፡ ወዓልያኒሆሙ፡ ወይቤሉ፡ ግሙራ፡ ኢተናገረ፡ ሰብእ፡ ከማሁ፡ ለውእቱ፡ ብእሲ፨

፵፯ ወአውሥኡ፡ ፈሪሳውያን፡ ወይቤልዎሙ፡ ትጌጋዩኑ፡ አንትሙኒ፨

ጣም፡ ነበርና፨ ኢዩ፡ ፫፡ ፩፨

፵ ከሕዝቡም፡ ብዙ፡ ሰዎች፡ ይህን፡ ሰምተው፡ ይህ፡ በእውነት፡ ነቢይ፡ ነው፡ አሉ፨ ዘዳ፡ ፲፰፡ ፲፭፨

፵፩ ሌሎቹም፡ ይህ፡ ክርስቶስ፡ ነው፡ አሉ፡ እኰሌቶቹ፡ ግን፡ ይሉ፡ ነበሩ፡ በውኑ፡ ክርስቶስ፡ ከገሊላ፡ ይመጣልን፨ ምሳ፡ ፩፡ ፵፮፡

፵፪ ክርስቶስ፡ ከዳዊት፡ ዘር፡ ከዳዊትም፡ አገር፡ ከቤተ፡ ልሔም፡ እንዲመጣ፡ መጽሐፍ፡ ይል፡ የለምን፨ መዝ፡ ፸፩፡ ፲፩፡ ሚክ፡ ፭፡ ፩፡ ማቴ፡ ፪፡ ፭፡ ፮፡

፵፫ ስለ፡ እርሱም፡ በሕዝቡ፡ መከከል፡ መለያየት፡ ሆነ፨ ምሳ፡ ፱፡ ፲፮፨

፵፬ ከእነርሳቸውም፡ ሊይዙት፡ የወደዱ፡ ሰዎች፡ ነበሩ፡ ነገር፡ ግን፡ ማንም፡ እጁን፡ አላነሣበትም፨ ቍ፡ ፴፨

፵፭ ሎሌዎችም፡ ወደ፡ ካህናት፡ አለቆችና፡ ወደ፡ ፈሪሳውያን፡ ተመለሱ፡ እነርሱም፡ ስለምን፡ ያላመጣችሁት፡ አልዋቸው፨

፵፮ ሎሌዎችም፡ መልሰው፡ ከቶ፡ እንደዚያ፡ ሰው፡ ማንም፡ ሰው፡ አልተናገረም፡ አልዋቸው፨ ማቴ፡ ፯፡ ፳፱፨

፵፯ ፈሪሳውያንም፡ መልሰው፡ አልዋቸው፡ እናንተም፡ ደግሞ፡ ተሰታችሁን፨

፵፰ ቦኑ፡ እመላእክት፡ ወእምፈሪሳውያን፡ እለ፡ አምኑ፡ ቦቱ፨

፵፱ ዘእንበለ፡ እሉ፡ ጊጉያን፡ ሕዝብ፡ እለ፡ ኢየአምሩ፡ ኦሪተ፡ ወእሙንቱ፡ ርጉማን፨

፶ ወይቤሎሙ፡ ኒቆዲሞስ፡ ዘሖረ፡ ኀቤሁ፡ ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ቀዲሙ፡ ሌሊተ፡ ወአሐዱ፡ እምኔሆሙ፨

፶፩ አረትኑ፡ ትኴንኖ፡ ለሰብእ፡ ዘእንበለ፡ ይሕትትዎ፡ ቀዲመ፡ ወያእምሩ፡ ዘገብረ፨

፶፪ ወአውሥእዎ፡ ወይቤልዎ፡ አንትኑሂ፡ እምገሊላኑ፡ አንተ፡ ኀሥሥ፡ ወትርአይ፡ ከመ፡ እምገሊላ፡ ኢይትነሣእ፡ ነቢይ፨

፶፫ ወገብኡ፡ ኵሉ፡ ለለአሐዱ፡ ውስተ፡ ቤቶሙ።

ምዕራፍ፡ ፰፡

በምንዝርነት፡ የተያዘች፡ ሴት፡ እንዴ፡ አመጡ። የዓለም፡ ብርሃን፡ እኔ፡ ነኝ፡ እንዴ፡ አለ፡ ሌላም፡ ብዙ፡

፩ ወእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ሖረ፡ ውስተ፡ ደብረ፡ ዘይት።

፪ ወእንግሀ፡ በጽባሕ፡ ወበአ፡ ካዕበ፡ ምኵራበ፡ ወተጋብኡ፡ ኵሉ፡ ሕዝብ፡ ኀቤሁ፡ ወነበረ፡ እንዘ፡ ይሜህሮሙ፨

፫ ወአምጽኡ፡ ኀቤሁ፡ ጸሐፍት፡ ወፈሪሳውያን፡ ብእሲተ፡ እ

፵፰ ወይስ፡ ከአለቆችና፡ ከፈሪሳውያን፡ አንዱ፡ ያመነበት፡ አለን፨

፵፱ ኦሪቱን፡ ከማያውቁ፡ እነዚያ፡ በደለኞች፡ በቀር፡ እነርሳቸውም፡ የተረገሙ፡ ናቸው፨

፶ አስቀድሞም፡ በሌሊት፡ ወደ፡ ኢየሱስ፡ የሔደው፡ ከእነርሱ፡ አንዱ፡ ኒቆዲሞስ፡ አላቸው፨ ም

፶፩ ፫፡፩፰ ኦሪታችን፡ አስቀድሞ፡ ሰይሰማ፡ ያደረገውም፡ ሳይታወቅ፡ በሰው፡ ይፈርዳልን፨ ዘዳግ፡ ፩፣

፶፪ ፲፯፨ እነርሱም፡ መልሰው፡ አንተም፡ ደግሞ፡ ከገሊላ፡ ነህን፡ ነቢይ፡ ከገሊላ፡ እንደይነሣ፡ መርምረህ፡ እይ፡ አሉት፨ ቍ፡ ፵፩፨

፶፫ ሁሉም፡ እያንዳንዱ፡ ወደ፡ ቤታቸው፡ ሔዱ፨

ስምንት፡ ምዕራፍ።

ነገር፡ እንዴ፡ እስተማራቸውና፡ እንዴ፡ ተከራከሩት።

፩ ኢየሱስም፡ ወደ፡ ደብረ፡ ዘይት፡ ሔደ።

፪ ደግሞም፡ ማልዶ፡ ወደ፡ መቅደስ፡ ገባ፡ ሕዝብም፡ ሁሉ፡ ወደ፡ እርሱ፡ መጡ፡ ተቀምጦም፡ ያስተምራቸው፡ ነበር፨

፫ ጻፎችና፡ ፈሪሳውያንም፡ በምንዝርነት፡ የተያዘች፡ ሴት፡

ንተ፡ ተረክበት፡ በዝሙት፡
ወአቀምዋ፡ ውስጠ፨

፬ ወይቤልዎ፡ አመምህር፡ ረከ
ብናሃ፡ ለዛቲ፡ ብእሲት፡ እንዘ፡
ትኤብስ፡ በዝሙት፨

፭ ወበሕግነሰ፡ ሠርዐ፡ ሙሴ፡ ከ
መ፡ ትትወገር፡ በዕብን፡ ወአ
ንተ፡ እንከ፡ ምንተ፡ ትብል፡ በ
እንቲአሃ፨

፮ ወዘንተ፡ ይቤሉ፡ እንዘ፡ ያሜ
ክርዎ፡ ከመ፡ ይርከቡ፡ ምክን
ያተ፡ ላዕሌሁ፡ በዘያስተዋድ
ይዎ፡ ወአትሐተ፡ እግዚእ፡ ኢ
የሱስ፡ አዕይንቲሁ፡ ውስተ፡ ም
ድር፡ እንዘ፡ ይጽሕፍ፡ በአፃ
ባዕቲሁ፨ ፯ ወሶበ፡ ቆሙ፡ ብዙኃ፡
ወአኀንዱዎ፡ ተሰእሎቶ፡ አን
ሥአ፡ አዕይንቲሁ፡ ወይቤሎ
ሙ፡ ዘአልቦ፡ ኃጢአት፡ እምኔ
ክሙ፡ ቀዲሙ፡ ለይግራ፡ በዕ
ብን፨ ፰ ወካዕበ፡ ደነነ፡ ወጸሐፈ፡
ላዕለ፡ ምድር፨

፱ ወሰሚዖሙ፡ እምኔሁ፡ ዘንተ፡
ዘለፋ፡ በልብዎ፡ እንዘ፡ ይሔሩ፡
በበአሐዱ፡ እስከ፡ ወፅኡ፡ ሊቃ
ውንቲሆሙ፡ እምቀዳሚ፡ እስ
ከ፡ ደኃሪ፡ ወተርፈ፡ እግዚእ፡ ኢ
የሱስ፡ ባሕቲቶ፡ ወብእሲትኒ፡

ወዲ፡ እርሱ፡ አምጥተው፡ በ
መካከል፡ አቆምዋት፨ ዘፀአ፡ ፳፡ ፲፬፨

፬ አሉትም፡ መምህር፡ ሆይ፡ ይህ
ች፡ ሴት፡ ስትመነዝር፡ አገኘና
ት፨

፭ እንዲዚችም፡ ያሉትን፡ በድን
ጊያ፡ ትወገር፡ ዘንድ፡ ሙሴ፡ በኦ
ሪት፡ አዘዘን፡ እንጃዲህ፡ አንተስ
ስለ፡ እርሷ፡ ምን፡ ትላለህ፨ ዘዳግ፡
፳፪፡ ፳፪፡ ሕዝ፡ ፲፮፡ ፴፰፡ ፵፡ ዘሌዊ፡ ፳፡ ፲፨

፮ ይህን
ንም፡ ማለታቸው፡ የሚያጣሉ
በትን፡ ምክንያት፡ ያገኙ፡ ዘንድ፡
ሊፈትኑት፡ ነው፡ ኢየሱስም፡
ዓይኖቹን፡ ወደ፡ ታች፡ ዝቅ፡ አ
ድርጎ፡ በምድር፡ ላይ፡ በጣቱ፡
ጻፈ፨ ፯ መላልሰውም፡ በጠየ
ቁት፡ ጊዜ፡ ቀና፡ ብሎ፡ ከእናን
ተ፡ ኃጢአት፡ የሌለበት፡ አስቀ
ድሞ፡ በድንጊያ፡ ይውገራት፡
አላቸው፨ ሮሜ፡ ፪፡ ፩፨

፰ ደግሞ፡ ወደ፡ ምድር፡ አጐንብ
ሶ፡ ጻፈ፨

፱ እርሳቸውም፡ ይህን፡ በሰሙ፡
ጊዜ፡ በሕሊናቸው፡ ተፈርደው፡
ከፊተኞች፡ ሽማግሌዎች፡ ጀም
ረው፡ እስከ፡ ኋለኞች፡ አንድ፡ አ
ንዱ፡ ወጡ፡ ኢየሱስም፡ ብቻው
ን፡ ቀረ፡ ሴቲቱም፡ በመካከል፡ ቁ

ትቀውም፡ ማዕከለ።

፲ ወአንሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ አዕይንቲሁ፡ ወነጸረ፡ ኀቤሃ፡ ወይቤላ፡ እብእሲቶ፡ አይቴ፡ ሀለው፡ እለ፡ ይኬንኑኪ።

፲፩ ወአውሥአት፡ ወትቤሎ፡ አልቦ፡ ዘአሬኢ፡ እግዚእየ፡ ወይቤላ፡ እግዚእየ፡ ኢየሱስ፡ አነሂ፡ አልቦ፡ ዘእኬንነኪ፡ ሑሪ፡ አትዊ፡ ወእምዝ፡ ዲጋመ፡ ኢትአብሲ።

፲፪ ወካዕበ፡ ነበቦሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወይቤ፡ አነ፡ ውእቱ፡ ብርሃኑ፡ ለዓለም፡ ዘተለወኒ፡ ኢየሐውር፡ ውስተ፡ ጽልመት፡ አላ፡ ይረክብ፡ ብርሃነ፡ ሕይወት።

፲፫ ወይቤልዎ፡ ፈሪሳውያን፡ ለሊከ፡ ትንእድ፡ ርእሰከ፡ ኢኮነ፡ ጽድቀ፡ ስምዕከ፡

፲፬ ወአውሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወይቤሎሙ፡ እመኒ፡ ለልየ፡ ሰምዐ፡ ኮንኩ፡ ለርእየ፡ ጽድቅ፡ ውእቱ፡ ስምዕየ፡ እስመ፡ አአምር፡ እምኀበ፡ መጻእኩ፡ ወኀበሂ፡ አሐውር፡ አንትሙሰ፡ ኢታአምሩ፡ እምኀበ፡ መጻእኩ፡ ወኀበሂ፡ አሐውር።

፲፭ አንትሙሰ፡ ሕገ፡ ዘሥጋ፡ ትኬንኑ፡ ወአንሰ፡ ኢይኬንን፡ ወኢ

ማ፡ ነበረች። ሮሜ፡ ፪፡ ፲፪።

፲ ኢየሱስም፡ ዓይኑን፡ አቅንቶ፡ አይቶና፡ አንቺ፡ ሴት፡ የሚያሳጡሽ፡ ወዴት፡ አሉ፡ አላት።

፲፩ እርሷም፡ አቤቱ፡ አንድ፡ ስንኳ፡ አላቸው፡ ኢየሱስም፡ እኔም፡ አልፈርድብሽም፡ ሒጂ፡ ከእንግዲህም፡ ወዲህ፡ ኃጢአት፡ አትሥሪ፡ አላት። ሉቃ፡ ፱፡ ፶፮፡ ምዕ፡ ፫፡ ፲፯።

፲፪ ዳግመኛም፡ ኢየሱስ፡ የዓለም፡ ብርሃን፡ እኔ፡ ነኝ፡ የሚከተለኝም፡ የሕይወት፡ ብርሃንን፡ ያገኛል፡ እንጂ፡ በጨለማ፡ አይመላለስም፡ ብሎ፡ ተናገራቸው። ኢሳ፡ ፵፱፡ ፮፡ ምዕ፡ ፩፡ ፫፡ ፱።

፲፫ ፈሪሳውያንም፡ አንተ፡ ስለ፡ ራስህ፡ ትመሰክራለህ፡ ምስክርነትህም፡ እውነት፡ አይደለም፡ አሉት።

፲፬ ኢየሱስም፡ መልሶ፡ አላቸው፡ እኔ፡ ምንም፡ ስለ፡ ራሴ፡ ብመሰክር፡ ምስክርነቴ፡ እውነት፡ ነው፡ ከወዴት፡ እንደ፡ መጣሁ፡ ወዴትም፡ እንድሔድ፡ አውቃለሁና፡ እናንተ፡ ግን፡ ከወዴት፡ እንደመጣሁ፡ ወዴትም፡ እንድሔድ፡ አታውቁም። ምዕ፡ ፭፡ ፴፩፡

፲፭ እናንተም፡ ሥጋዊ፡ ፍርድን፡ ትፈርዳላችሁ፡ እኔ፡ ግን፡

መነኒ።

፲፮ ወእመሂ፡ ኰነንኩ፡ አነ፡ ጽድቅ፡ ውእቱ፡ ኵነኔየ፡ እስመ፡ ኢኮንኩ፡ አነ፡ ባሕቲትየ፡ አላ፡ አነ፡ ወአብ፡ ዘፈነወኒ።

፲፯ ውስተ፡ ኦሪትክሙኒ፡ ጽሑፍ፡ ከመ፡ ስምዐ፡ ክልኤቱ፡ ሰብእ፡ እሙን፡ ውእቱ።

፲፰ ወአነሂ፡ ሰማዕት፡ ለርእስየ፡ ወአብኒ፡ ዘፈነወኒ፡ ሰማዕትየ።

፲፱ ወይቤልዎ፡ አይቴ፡ ውእቱ፡ አቡከ፡ ወአውሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ወይቤሎሙ፡ ኢኪያየ፡ ታእምሩ፡ ወኢአቡየ፡ ሶበሰ፡ ኪያየ፡ አእመርክሙኒ፡ እም፡ አእመርክምዎ፡ ለአቡየኒ።

፳ ወዘንተ፡ ነገረ፡ ተናገሮሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ በኀበ፡ ሙዳየ፡ ምጽዋት፡ እንዘ፡ ይሜህሮሙ፡ በምኵራብ፡ ወኢአኀዝዎ፡ እስመ፡ ዓዲ፡ ኢበጽሐ፡ ጊዜሁ።

፳፩ ወካዕበ፡ ይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ አንሰ፡ አሐውር፡ ወተኀሥሡኒ፡ ወኢትረክቡኒ፡ ወትመውቱ፡ በኃጢአትክሙ፡ ወኀበ፡ አነ፡ አሐውር፡ አንትሙሰ፡ ኢትክሉ፡ መጺአ።

፳፪ ወይቤሉ፡ አይሁድ፡ ይቀትሎኑ

በማኝም፡ እፈርድም።

፲፮ እኔም፡ ብፈርድ፡ ፍርዴ፡ እውነት፡ ነው፡ እኔና፡ የላከኝ፡ አብ፡ ነን፡ እንጂ፡ ብቻዬን፡ አይደለሁምና። ቁ፡ ፲፱።

፲፯ የሁለት፡ ሰዎችም፡ ምስክርነት፡ እውነት፡ እንደ፡ ሆነ፡ በኦሪታችሁ፡ ተጽፎዋል። ዘዳ፡ ፲፯፡ ፯፡ ም፡ ፲፱፡ ፲፭።

፲፰ እኔ፡ ስለ፡ ራሴ፡ ምስክር፡ ነኝ፡ የላከኝ፡ አብም፡ ይመሰክርልኛል።

፲፱ እነርሱም፡ አባትህ፡ ወዴት፡ ነው፡ አሉት፡ ኢየሱስም፡ መልሶ፡ እኔንም፡ አባቴንም፡ አታውቁም፡ እኔንስ፡ ብታውቁኝ፡ አባቴንም፡ ደግሞ፡ ባወቃችሁት፡ ነበር፡ አላቸው። ም፡ ፲፬፡ ፯።

፳ እርሱ፡ በመቅደስ፡ በምጽዋት፡ ማኖሪያ (ማዕኝ) አጠገብ፡ ሲያስተምራቸው፡ ይህን፡ ተናገረ፡ የያዘውም፡ የለም፡ ጊዜው፡ ገና፡ አልደረሰም፡ ነበርና። ም፡ ፯፡ ፴፡ ሉቃ፡ ፳፪፡ ፶፫።

፳፩ ደግሞም፡ ኢየሱስ፡ እኔ፡ እሔዳለሁ፡ ትሹኛላችሁ፡ አታገኙኝም፡ በኃጢአታችሁም፡ ትሞታላችሁ፡ እኔም፡ ወደምሔድበት፡ እናንተ፡ ትመጡ፡ ዘንድ፡ አትችሉም፡ አላቸው። ፯፡ ም፡ ፯፡ ፴፬፡ ም፡ ፲፫፡ ፴፫።

፳፪ አይሁድም፡ እኔ፡ ወደምሔድበ

እንጋ፡ርእሰ፡ለሊሁ፡ዘይብለ
ኒ፡ኀበ፡አነ፡አሐውር፡አንትሙ፡
ኢትክሉ፡መጺአ፨

፳፫ ወይቤሎሙ፡አንትሙሰ፡እም
ታሕቱ፡አንትሙ፡ወአንሰ፡እም
ላዕሉ፡አነ፡አንትሙሰ፡እምዝ
ንቱ፡ዓለም፡አንትሙ፡ወአንሰ፡
ኢኮንኩ፡እምዝንቱ፡ዓለም፨

፳፬ ወበእንተዝ፡እቤለክሙ፡ከመ
ትመውቱ፡በኀጢአትክሙ፡
ለእመ፡ኢአመንክሙ፡ከመ፡አ
ነ፡ውእቱ፡እሰመ፡ርትመውቱ፡
በኀጢአትክሙ፨

፳፭ ወይቤልዎ፡
አንተ፡መኑ፡አንተ፡ወይቤሎ
ሙ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ቀዳሚ
ኒ፡ነገርኩክሙ፨

፳፮ ወብዙኅ፡ብየ፡ዘእብል፡በእ
ንቲአክሙ፡ወእኴንን፡በቱ፡ወ
ባሕቱ፡ዘፈነወኒ፡ጻድቅ፡ውእ
ቱ፡ወአንሰ፡ዘሰማዕኩ፡በኀ
ቤሁ፡እነግር፡ለዓለም፡

፳፯ ወኢያእመሩ፡ከመ፡በእንተ፡
አብ፡ይቤሎሙ፡

፳፰ ወይቤሎሙ፡እግዚእ፡ኢየ
ሱስ፡አመ፡አልዓልክምዎ፡ለ
ወልደ፡እጓለ፡እመሕያው፡ይ
እቲ፡አሚረ፡ተአምሩ፡ከመ፡አ
ነ፡ውእቱ፡ወአኮ፡ዘእምኀቤየ፡

ቱ፡እናንተ፡ትመጡ፡ዘንድ፡አ
ትችሉም፡ማለቱ፡እርሱ፡ራሱ
ን፡ይገድላልን፡አሉ፨ ም፡፯፡፴፭፨

፳፫ አላቸውም፡እናንተ፡ከታች፡
ናችሁ፡እኔ፡ግን፡ከላይ፡ነኝ፡እና
ንተም፡ከዚህ፡ዓለም፡ናችሁ፡
እኔ፡ግን፡ከዚህ፡ዓለም፡አይደ
ለሁም፨

፳፬ ስለዚህም፡በኃጢአታችሁ፡ት
ሞታላችሁ፡አልኋችሁ፡እኔ፡
እንደ ሆንሁ፡ካላመናችሁ፡በ
ኃጢአታችሁ፡ትሞታላችሁ፡
ና፨

፳፭ እነርሱም፡አንተ፡ማነህ፡
አሉት፡ኢየሱስም፡አላቸው፡
ከጥንት፡ጀምሬ፡ስነግራች
ሁ፡የነበርሁ፡እኔ፡ነኝ፨

፳፮ ስለ፡እናንተም፡የምናገረው
ና፡የምፈርደው፡እጅግ፡ነገር፡
አለኝ፡ነገር፡ግን፡የላከኝ፡እው
ነተኛ፡ነው፡እኔም፡ከእርሱ፡የ
ሰማሁትን፡ለዓለም፡እናገራ
ለሁ፨

፳፯ እርሱም፡ስለ፡አብ፡እን
ደ፡አላቸው፡አላወቁም፨

፳፰ ኢየሱስም፡ደግሞ፡አላቸው፡
የሰውን፡ልጅ፡ከፍ፡ከፍ፡ባደ
ረጋችሁት፡ጊዜ፡እኔ፡እንደሆ
ንሁ፡ያን፡ጊዜ፡ታውቃላችሁ፡
ከራሴም፡አንዳች፡የምሠራ፡

ዘእገብር፡ አላ፡ በከመ፡ መሀ
ረኒ፡ አቡየ፡ ከማሁ፡ እነግር።

፳፱ ወዘፈነወኒ፡ ሀሎ፡ ምስሌየ፡
ወኢየኀድገኒ፡ ባሕቲትየ፡ እ
ስመ፡ አነ፡ እገብር፡ ሥምረቶ፡
ዘልፈ።

፴ ወዘንተ፡ ብሂሎ፡ ብዙኃን፡ እ
ሉ፡ አምኑ፡ ቦቱ።

፴፩ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱ
ስ፡ ለእለ፡ አምኑ፡ ቦቱ፡ አይሁድ፡
አንትሙሂ፡ ለእመ፡ ነበርክሙ፡
በቃልየ፡ አርዳእየ፡ አንትሙ።

፴፪ ወተአምርዋ፡ ለጽድቅ፡ ወጽ
ድቅኒ፡ ታግዕዘክሙ።

፴፫ ወአውሥኡ፡ ወይቤልዎ፡ ዘ
ርአ፡ አብርሃም፡ ንሕነ፡ ወእም
እመ፡ ኮነ፡ ኢተቀነይነ፡ ግሙ
ራ፡ ወኢለመኑሂ፡ እፎ፡ እንከ፡
ትብለነ፡ ግዑዛነ፡ ትከውኑ።

፴፬ ወአውሥአ፡ እግዚእ፡ ኢየሱ
ስ፡ ወይቤሎሙ፡ አማን፡ አማ
ን፡ እብለክሙ፡ ኵሉ፡ ዘይገብ
ራ፡ ለኃጢአት፡ ገብራ፡ ውእቱ፡
ለኃጢአት።

፴፭ ወገብርኒ፡ ኢይነብር፡ ውስተ፡
ቤት፡ ለዝሉፉ፡ ወወልድሰ፡ ይ
ነብር፡ ለዓለም።

አይደለሁም፡ አባቴ፡ እንዳ፡
አስተማረኝ፡ እንዲሁ፡ እናገ
ራለሁ፡ እንጂ። ም፡፫፡፲፬። ም፡፲፪፡፴፪።

፳፱ የላከኝም፡ አብ፡ እርሱ፡ ከእኔ፡
ጋራ፡ ነው፡ ብቻዬንም፡ አይተ
ወኝም፡ ደስ፡ የሚያሰኘውን፡ ነ
ገር፡ ሁል፡ጊዜ፡ አደርጋለሁና።

፴ ቍ፡፲፯። እርሱም፡ ይህን፡ ነገር፡ ሲ
ናገር፡ ብዙዎቹ፡ በእርሱ፡ አመ
ኑበት።

፴፩ ም፡፯፡፴፩። ኢየሱስም፡ ያመ
ኑበትን፡ አይሁድ፡ አላቸው፡ እ
ናንተ፡ በቃሌ፡ ብትጸኑ፡ በእው
ነት፡ ደቀ፡መዛሙርቴ፡ ናችሁ።

፴፪ ም፡፲፫፡፲። እውነትንም፡ ታውቋታ
ላችሁ፡ እውነትም፡ ነፃ፡ ታደር
ጋችኋለች።

፴፫ እነርሱም፡ መል
ሰው፡ እኛ፡ የአብርሃም፡ ዘር፡ ነ
ን፡ ከሆነም፡ ጀምሮ፡ ከቶ፡ ለማ
ንም፡ አልተገዛንም፡ አንተ፡ እን
ዴት፡ ነፃ፡ ትወጣላችሁ፡ ትለና
ለህ፡ አሉት።

፴፬ ማቴ፡፫፡፱። ኢየሱስም፡
መለሰ፡ አላቸው፡ እውነት፡ እ
ውነት፡ እላችኋለሁ፡ ኃጢአት፡
የሚያደርግ፡ ሁሉ፡ እርሱ፡ የ
ኃጢአት፡ ባርያ፡ ነው። ሮ፡፯፡፲፯፡፩፡

፴፭ ፩፡ዮሐ፡፫፡፰። ባርያም፡ ለዘለዓለም፡
በቤት፡ አይኖርም፡ ልጅ፡ ግን፡
ዘለዓለም፡ ይኖራል።

፴፮ ወእምከመሰ፡ ወልድ፡ አግዐ
ዘክሙ፡ አማን፡ ግዑዛን፡ አንት
ሙ። ፴፯ ወአእምር፡ ከመ፡ ዘርአ፡
አብርሃም፡ አንትሙ፡ ወባሕቱ፡
ተኀሥሡ፡ ትቅትሉኒ፡ እስመ፡
ኢይነብር፡ ቃልየ፡ ኀቤክሙ።

፴፰ ወአንሰ፡ ዘርኢኩ፡ በኀበ፡ አቡ
የ፡ እነግር፡ ወአንትሙሂ፡ ዘር
ኢክሙ፡ በኀበ፡ አቡክሙ፡ ትግ
ብሩ። ፴፱ ወአውሥኡ፡ ወይቤልዎ፡
ለነሰ፡ አብርሃም፡ አቡነ፡ ወይ
ቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየሱስ፡ ሰ
በሰ፡ ውሉዱ፡ አብርሃም፡ አንት
ሙ፡ ግብረ፡ አብርሃም፡ እምገ
ብርክሙ። ፵ ወይእዜሰ፡ ተኀሥ
ሡ፡ ትቅትሉኒ፡ ብእሴ፡ ጻድቀ፡
ዘጽድቀ፡ እነግረክሙ፡ ዘሰማ
ዕኩ፡ በኀበ፡ እግዚአብሔር፡ ወ
አብርሃምሰ፡ ኢገብረ፡ ከመዝ።
፵፩ አንትሙሰ፡ ትገብሩ፡ ግብረ፡ አ
ቡክሙ፡ ወይቤልዎ፡ ንሕነሰ፡
ኢተወለድነ፡ እምዝሙት፡ አ
ሉ፡ አሐዱ፡ አብ፡ ብነ፡ ወውእቱ፡
እግዚአብሔር።

፵፪ ወይቤሎሙ፡ እግዚእ፡ ኢየ
ሱስ፡ ሶበሰ፡ እግዚአብሔር፡

፴፮ ልጅም፡ ነፃ፡ ቢያወጣችሁ፡ በ
እውነት፡ ነፃ፡ ወጣችሁ። ሮሜ፮
፴፯ ፲፫፡ ፩፪። እናንተስ፡ የአብርሃም፡
ዘር፡ እንደ፡ ሆናችሁ፡ ፈጽሜ፡
አውቃለሁ፡ ነገር፡ ግን፡ ትገድ
ሉኝ፡ ዘንድ፡ ትሻላችሁ፡ ቃሌ፡
በእናንተ፡ አይኖርምና።
፴፰ እኔ፡ ከአባቴ፡ ዘንድ፡ ያየሁትን፡
እናገራለሁ፡ እናንተም፡ ከአባታ
ችሁ፡ ዘንድ፡ ያያችሁን፡ ታደር
ጋላችሁ። ፴፱ እርሱም፡ መልሰው፡
አባታችን፡ አብርሃም፡ ነው፡
አሉ፡ ኢየሱስም፡ አላቸው፡ የአ
ብርሃም፡ ልጆች፡ ብትሆኑ፡
የአብርሃምን፡ ሥራ፡ በሠራች
ሁ፡ ነበር። ፵ አሁን፡ ግን፡ ከእግዚ
አብሔር፡ የሰማሁትን፡ እው
ነት፡ የምነግራችሁን፡ ሰውል
ትገድሉኝ፡ ትሻላችሁ፡ አብርሃ
ምስ፡ እንዲህ፡ አላደረገም። ም፲፪
፵፩ ፲፪። እናንተ፡ ግን፡ የአባታችሁ
ን፡ ሥራ፡ ትሠራላችሁ፡ እነር
ሱም፡ እኛስ፡ አንድ፡ አባት፡ አለ
ን፡ እንጂ፡ ከዝሙት፡ አልተወ
ለድንም፡ እርሱም፡ እግዚአ
ብሔር፡ ነው፡ አሉት። ኢር፡ ፫፡ ፬።
፵፪ ኢየሱስም፡ አላቸው፡ እግዚአ
ብሔርስ፡ አባታችሁ፡ ቢሆን፡

አቡክሙ፡ እምአፍቀርክ
ሙኒ፡ ኪያየ፡ እስመ፡ አነ፡ እ
ምኀበ፡ እግዚአብሔር፡ ወፃ
እኩ፡ ወመጻእኩ፡ ወአኮ፡ ለሊ
የ፡ ዘመጻእኩ፡ አላ፡ ውእቱ፡
፵፫ ፈነወኒ። እፎ፡ እንከ፡ ኢተአ
ምኑ፡ ቃልየ፡ እስመ፡ ኢትክሉ፡
ሰሚዐ፡ ነገረ፡ ዚአየ።
፵፬ አንትሙሰ፡ እምአቡክሙ፡
ሰይጣን፡ አንትሙ፡ ወፍትወ
ቶ፡ ለአቡክሙ፡ ትፈቅዱ፡ ት
ግበሩ፡ ወውእቱ፡ ቀታሊ፡ ነ
ፍሰ፡ ሰብእ፡ ውእቱ፡ እምት
ካት፡ ወኢይቀውም፡ በጽድቅ፡
እስመ፡ አልቦ፡ ጽድቅ፡ በኀቤ
ሁ። ወሰበ፡ ይነብብ፡ ሐሰተ፡
እምዚአሁ፡ ይነብብ፡ እስመ፡
ሐሳዊ፡ ውእቱ፡ ወአቡሃ፡ ለሐ
፵፭ ቱ። ወአንሰ፡ እስመ፡ ጽድቀ፡
እነግር፡ ኢተአምኑኒ።
፵፮ መኑ፡ እምኔክሙ፡ ዘይዛለፈ
ኒ፡ በእንተ፡ ኀጢአት፡ ወእመ
ሰ፡ አነ፡ ጽድቀ፡ እነግር፡ ለም
ንት፡ እንከ፡ ኢተአምኑኒ።
፵፯ ዘሰ፡ እምእግዚአብሔር፡ ው
እቱ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ይ
ሰምዕ፡ ወበእንተ፡ ዝንቱ፡ ኢት
ሰምዑኒ፡ እስመ፡ ኢኮንክሙ

እኔን፡ በወደዳችሁኝ፡ ነበር፡
እኔ፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡
ወጥቼ፡ መጥቻለሁና፡ እኔም፡
በራሴ፡ የመጣሁ፡ አይደለሁ
ም፡ እርሱ፡ ላከኝ፡ እንጂ።
፵፫ ምነው፡ ነገሬን፡ አታስተውሉ፡
ቃሌን፡ መስማት፡ አኮ፡ ሰለ፡ አ
ልቻላችሁ፡ ነው።
፵፬ እናንተስ፡ ከአባታችሁ፡ ከሰ
ይጣን፡ ናችሁ፡ የአባታችሁንም፡
ምኞት፡ ልታደርጉት፡ ትፈቅዳ
ላችሁ፡ እርሱም፡ ከጥንት፡ ጀ
ምሮ፡ ነፍሰ፡ ገዳይ፡ ነው፡ በእው
ነትም፡ አይጸናም፡ በእርሱ፡ ዘ
ንድ፡ እውነት፡ የለምና፡ ሐሰት
ም፡ በተናገረ፡ ጊዜ፡ ከራሱ፡ ይ
ናገራል፡ ሐሰተኛ፡ የሐሰትም፡
